# የህብረተሰብ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ
## 8ኛ ክፍል

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ


ISBN ቁጥር -
ዋጋ ብር -

የህብረተሰብ ትምህርት የተማሪ መጽሐፍ 8ኛ ክፍል

# የህብረተሰብ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ
## 8ኛ ክፍል



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

## የጥንቃቄ መልዕክት

**ተማሪዎች!**

**ይህን የተማሪ መጽሐፍ በጥንቃቄ ያዙ!**

ይህ መማሪያ መጽሐፍ በቀጣይ ዓመት የናንተ ወንድሞችና እህቶች የሚማሩበት የትምህርትቤታችሁ ንብረት ነው! መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ፤

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክና በአሮጌ ጋዜጣ ወይም በካኪ ወረቀት ሸፍኑ፤
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ ደረቅና ንጹህ በሆነ ቦታ አስቀምጡት፤
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ እርጥበት የሌለውና ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ፤
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ፤
5. መጽሐፉን እያነበባችሁ እያላችሁ ንባባችሁን አቋርጣችሁ እንደገና ለማንበብ ስትፈልጉ ምልክት ማድረጊያ ብጣሽ ወረቀት ወይም ካርድ ተጠቀሙ፤
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ስእሎችን ወይም ገጾችን አትቅደዱ፤
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ ጠግኑት፤
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ፤
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ። ደህንነቱን አረጋግጣችሁ ተቀበሉ።
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትቀበሉ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጣጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)።

ማሳሰቢያ፤ እነዚህ መመሪያዎች ሳይተገበሩ ቀርተው በመጽሐፉ ላይ አንዳች ጉዳት ከደረሰ በወጣው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ያደርጋል።

# የህብረተሰብ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 8ኛ ክፍል


አዘጋጆች:

በላይ ፀጋ (ኤምኤ)

ዓለማየሁ እርቅይሁን (ዶ/ር)

አርታኢዎች:

ሽመልስ አየለ (ኤምኤ)

አበበ ጠየቀ (ኤምኤ)

የቡድን መሪ

ሙሉጌታ ነቅዓ (ረዳት ፕሮፌሰር)

ሰዓሊ

ከበደ አለሙ እና ቀለመወርቅ ተገኘ

ዲዛይነር

አትርሳው ጥግይሁን



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተመደበ በጀት በአብክመ ትምህርት ቢሮና በምሁራን መማክርት ጉባዔ ትብብር ነው፡፡

የመጽሐፉ ሕጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም. አብክመ ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

ምሁራን መማክርት ጉባዔ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

## ማውጫ


መግቢያ ........ vii

ምዕራፍ- 1

አህጉራት፣ የመሬት ቀራጺ ሀይሎች፣ ከባቢ አየር እና የካርታ ንባብ

1.1. አህጉራት እና ውሃማ አካላት ........ 2

1.1.1 አህጉራት ........ 2

1.1.2. ዋና ዋና ውሃማ አካላት ........ 5

1.2. የመሬት ገፅ ቀራፂ ኃይሎች ........ 9

1.3 የመሬት ከባቢ አየር........ 22

1.3.1. የመሬት ከባቢ አየር ንጣፎች ........ 22

1.3.2. የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት ምንነት እና ይዘቶች........ 24

1.3.3 የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች ........ 25

1.3.4 እለታዊ እና ወቅታዊ የአየር ጠባይ መለዋወጥ ........ 26

1.4. የካርታ መስፈርት፣ ርቀትና ስፋትን ማስላት ........ 27

1.4.1. የካርታ መስፈርት አገላለጽ አይነቶች ........ 27

1.4.2. የካርታ መስፈርቶችን መለወጥ ........ 30

1.4.3. በካርታ ላይ ርቀትን እና ስፋትን ማስላት ........ 31

1.4.4. ዓለማቀፋዊ መገኛ ስርዓት (Global Positioning System )........ 36

ምዕራፍ- 2

ስነ ሕዝብ እና የማህበረ- ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

2.1. የባህል ምንነት እና ብዝሀነት ........ 45

2.1.1. የባህል ምንነት እና ዋና ዋና ይዘቶች........ 45

2.1.2. ዓለም አቀፋዊነት፣ የማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶች ተከታታይ ለውጦች52

2.2. ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ........ 54

2.2.1. የመጀመሪያ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ........ 55

2.2.2. ሁለተኛ ደረጃ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች ........ 60

2.2.3. ሶስተኛ ደረጃ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች ........ 64

2.3. ንግድ እና ገበያ ........ 66

2.3.1. የንግድ ምንነት እና ፅንሰ ሀሳብ ........ 66

2.3.2. የንግድ አይነቶች እና ጠቀሜታዎች........ 67

2.3.3 የግብይት አቅርቦትና ፍላጎት፣ የግብይት ዋና ተዋናዮች እና የሸማቾች መብት ጥሰት ........ 68

2.4. የመንግስት ገቢ እና ግብር ........................................................................ 69
2.4.1 የመንግስት ገቢ እና ግብር የሚያስገኛቸው ጥቅሞች በኢትዮጵያ ........... 69

ምዕራፍ-3

የተፈጥሮ ሀብቶች እና የማህበረ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት

3.1 የአካበቢ እንክብካቤ እና አጠቃቀም ለዘላቂ አድገት ....................................... 78
3.1.1. የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀምና ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅሞች .................... 78
3.1.2. ከጊዜ ጋር የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም መለዋወጥ ............................... 85
3.1.3. የተፈጥሮ ሃብቶች እንክብካቤ እና ዘላቂ አጠቃቀም ............................. 86
3.2 እንክብካቤ የጎደለው የሀብት አጠቃቀም እና የሚያስከትላቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች ..........................................................................................................87
3.3. የተፈጥሮ ሀብቶች ተደራሽነት እና የግጭቶች አፈታት ............................. 92

ምዕራፍ-4

ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ

4.1. የዘመናዊ ኢትዮጵያ ምስረታ .............................................................. 103
4.1.1 የዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ዘመን (1855-1868) ................................... 103
4.1.2. የአፄ ዮሐንስ 4ኛ ዘመን (1872-1889)............................................ 107
4.2. የ19ኛው ክፍለ ዘመን የሲራራ ንግድ .................................................. 109
4.3. ኢትዮጵያውያን ለሀገር አንድነትና ሉዓላዊነትን ለማስጠበቅ ያደረጉት ትግል . 111
4.3.1. የግብፅ መስፋፋት እና የኢትዮጵያ ምላሽ............................................ 111
4.3.2. ከሐዊወት ውል በኋላ የተከሰቱ ሁኔታዎች ......................................... 113
4.3.3. የደርቡሽ እና የኢትዮጵያ ግንኙነት ................................................... 115
4.3.4. የኢትዮጵያ እና የጣሊያን ግንኙነት.................................................. 116
4.3.4.1. የአድዋ ጦርነት ............................................................................ 119
4.3.4.2 የአድዋ ድልና ፋይዳው................................................................... 121
4.4. ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ........................................................ 123
4.5. የፋሽስት ጣሊያን ወረራ (1936-1941) ................................................ 125
4.6. የአርበኞች ተጋድሎና የኢትዮጵያ የነጻነት መመለስ ................................. 130
4.7. የሶማሊያ ወረራ ............................................................................. 136

## ምዕራፍ-5

## አፍሪካ ከ1500 በኋላ

5.1 ባርነትና የባሪያ ንግድ በአፍሪካ ........ 142
5.2 የአውሮፓዊያን ቅኝ ግዛት በአፍሪካ ........ 145
5.2.1. የአውሮፓውያን የቅኝ አገዛዝ ምስረታ ሂደት ........ 145
5.2.2. ቅኝ አገዛዝ በአፍሪካዊያን ላይ ያስከተለው ተፅዕኖ ........ 149
5.2.3. የአፍሪካዊያን ፀረ ቅኝ ግዛት ተጋድሎ........ 149
5.3. ነጻ የሆኑ የአፍሪካ ሃገሮች ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ውህደት ለማምጣት የተደረጉ እንቅስቃሴዎች........ 152
5.3.1. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አ.አ.ድ) ........ 152

## ምዕራፍ-6

## ቅድመ-ዘመናዊ እና ዘመናዊ የዓለም ታሪክ

6.1 ታላቁ የጅኦግራፊያዊ አሰሳ ዘመን ........ 158
6.2 ዘመነ-ህዳሴ፣ የፕሮቴስታንት ዕምነት ንቅናቄ እና የካቶሊካዊያን ምላሽ........ 162
6.2.1. ዘመነ-ህዳሴ ........ 162
6.2.2 የፕሮቴስታንት ዕምነት አማኞች ንቅናቄ ........ 164
6.2.3. የካቶሊካዊያን ምላሽ ........ 166
6.3. የኢንዱስትሪ አብዮት ........ 167
6.4. ሁለቱ ታላላቅ የዓለም ጦርነቶች........ 170
6.4.1. የአንደኛው የአለም ጦርነት (1914-1918)........ 170
6.4.2. ሁለተኛው የአለም ጦርነት (1939-1945)........ 173
6.4.2.2. የጦርነቱ ሂደት........ 174
6.5. የቀዝቃዛው ጦርነት (1945-1991)........ 176

## ምዕራፍ-7

## ወቅታዊ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች

7.1. የአየር ንብረት ለውጥ ........ 182
7.1.1 የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ እና ውጤት ........ 182
7.2. የውሃ መጠን አቅርቦት መቀነስ ........ 188
7.3. የደኖች መመናመን ........ 190

## የመጻሕፍት አተገባበር

መጽሐፉ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ከሚያውቁትና ከአካባቢያቸው ይዘውት ከሚመጡት ተሞክሮና እውቀት በመነሳት ተግባር ተኮር እና አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲማሩ ሆኖ ስለተዘጋጀ ተማሪዎች ትምህርቱን በጥልቀት ይገነዘቡታል ወይም ይረዱታል ተብሎ ይታመናል:: ተማሪዎችና መምህራን አካባቢያቸውን እና ያካበቱትን ዕውቀትና ተሞክሮ መሰረት በማድረግ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ተማሪዎቻችን ይዘቶችን መማር ብቻ ሳይሆን የመማር ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ይጠበቃል:: በመሆኑም መምህራን ለይዘቱ ተስማሚ ተብለው የተጠቆሙ የማስተማሪያ እና መማሪያ ዘዴዎችን በአግባቡ በመተግበርና ሌሎች ተገቢ ዘዴዎችን ተጨባጭ ሁኔታንና የተማሪዎችን አቅምና ፍላጎት መሰረት አድርጎ በመምረጥ ተማሪተኮር /አሳታፊ አድርገው የመማር ማስተማሩን ተግባር መፈጸም የሚጠበቅባቸው ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ መጽሐፍቱን ከእጃቸው ሳይለዩ ትምህርቱን መከታተል ይኖርባቸዋል::

## ውድ ተማሪዎቻችን!

መጽሐፉን በጥንቃቄ በመያዝ በአግባቡ መጠቀም አለባችሁ:: በማንኛውም አገርና ሁኔታ መማር የትውልድን የወደፊት ሁኔታ ይወስናል:: መማር ለማንኛውም ማህበራዊ፣ ሰብዓዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሰረት ነው:: በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተግባራት፣ ይዘቶችና ጥያቄዎች በአግባቡ በመስራትና በማጥናት ጥልቀት ያለው ክህሎትን እና ግንዛቤን ማዳበር ይገባችኋል::

## ውድ ወላጆች /አሳዳጊዎች!

የተማሪዎችን መማር የተሳለጠ ለማድረግ የመማሪያ መጻሕፍት ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው:: ስለሆነም ተማሪዎች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዘው እንዲጠቀሙ ማድረግ ይኖርባችኋል:: ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች መጽሐፉን ት/ቤት ይዘው እንዲሄዱ ማበረታታት፣ ከመምህሮቻቸው የሚሰጡ ተግባራትን በትክክል እንዲፈጽሙና እንዲያጠኑ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ትምህርት ቤት በመሄድ ከመምህራን ጋር በመገናኘት ስለ ልጅዎ የመማር ዕውቀትና የባህሪ ለውጥ በመጠየቅ ክፍተቱን በመለየት ምክር በመሥጠት ማስተካከል ይጠበቅባችኋል:: በመሆኑም ትምህርት የሁሉም ነገር መሰረት መሆኑን በመገንዘብ መማርን ከመንግስት ስራ መያዝ ጋር ብቻ ሳታቆራኙት/ሳያያይዙት ልጆችን ሁልጊዜ ወደትምህርት ቤት መላክ አለባችሁ::

## መግቢያ

በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ሰባት ምዕራፎች ሲኖሩት የመጀመሪያዎች ሶስቱ ምዕራፎች የጂኦግራፊ ይዘቶችን የያዙ ሲሆን ቀጣይ ሶስቱ ምዕራፎች የታሪክ ትምህርት ይዘቶች ናቸው:: ሰባተኛው ምዕራፍ ደግሞ ወቅታዊ አለማቀፋዊ ጉዳዮች ያካተተ ነው::

የጂኦግራፊ ትምህርት ይዘቶችን በተመለከተ ምዕራፍ አንድ አህጉራት፣ ከባቢ አየር እና የካርታ ንባብ ምንነት የተዳሰሱበት ሲሆን ምዕራፍ ሁለት ደግሞ የባህል ምንነት እና ብዝሀነት፣ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች፣ ንግድ እና ገበያ እንዲሁም የመንግሰት ገቢ እና ግብር ምንነትን አካቶ የያዘ ነው:: በምዕራፍ ሶስት የተካተቱ ዋና ዋና ይዘቶች የአካባቢ እንክብካቤ እና አጠቃቀም ለዘላቂ እድገት፣ ከጊዜ ጋር የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም መለዋወጥ፣ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ እና ዘላቂ አጠቃቀም፣ እንክብካቤ የጎደለው የሀብት አጠቃቀም የሚስያስከትላቸው አሉታዊ ተፅእኖዎች፣ የተፈጥሮ ሀብቶች ተደራሽነት እና ግጭቶች አፈታት ተዳሰዋል:: ምዕራፍ ሰባት ውስጥ ሶስት ዋና ዋና አለም አቀፍ ጉዳዮች ተዳሰዋል:: እነርሱም የአየር ጠባይ ለውጥ፣ የውሀ መጠን መቀነስ እና የደኖች መመናመን ናቸው::

የታሪክ ትምህርትን በተመለከተ ሶስት ምዕራፎች ሲኖሩት ምዕራፍ አራት ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚዳስስ ሲሆን በውስጡም የሚከተሉትን ሶስት ዋናዋና ርዕሶችን ይዟል:: እነርሱም የማዕከላዊ መንግስት ዳግም ምስረታ፣ ኢትዮጵያ የውጭ ወራሪዎችን ለመመከት ያደረገቻቸው ትግሎች እና ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጦች ናቸው:: አምስተኛው ምዕራፍ ደግሞ ከ1500 ዓ.ም በኋላ ያለውን የአፍሪካ ታሪክ የሚዳስስ ነው:: በውስጡም ባርነትና የባሪያ ንግድን፣ የቅኝ ግዛት ምስረታ ሂደትና የአፍሪካዊያን ትግል እንዲሁም ሁሉን አቀፍ ትብብር ምስረታ ሂደትን የካትታል:: በስድሰተኛው ምዕራፍም የኢንዱስትሪ አብዮትን፣ ሁለቱን የዓለም ጦርነቶችን እና ቀዝቃዛው ጦርነትን የሚያካትተው ቅድመ ዘመናዊና ዘመናዊ የዓለም ታሪክ ላይ ያተኮረ ነው:: በዚህ መፅሐፍ የተጠቀሱት ቀናት፣ ወራትና ዓመታት እንደ ጎርጎሮሳዊያን (አውሮፓዊያን) የዘመን አቆጣጠር ናቸው::

# ምዕራፍ- 1

# አህጉራት፣ የመሬት ቀራጺ ሀይሎች፣ ከባቢ አየር እና የካርታ ንባብ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አህጉራት፣ የመሬት ቀራጺ ሀይሎች፣ ከባቢ አየር እና የካርታ ንባብ ምንነት የሚዳሰሱበት ይዘቶች ተደራጅተው ቀርበዋል:: አህጉራትን በተመለከተ የአህጉራት ትርጉም፣ ስፋትና የመሳሰሉትን የያዘ ሲሆን የእያንዳንዱ አህጉር ዋና ዋና ባህሪያትም ተዘርዝረዋል:: በተጨማሪም ዋና ዋና ውሃማ አካላት ማለትም ውቅያኖሶች፣ ባህሮች፣ ሀይቆች እና ወንዞች ተዳሰዋል:: በሁለተኛ ደረጃ የመሬት ውስጣዊ እና ውጫዊ ገፅታ ምንነት፣ ዋና ዋና ወስጣዊ እና ውጫዊ ገፅታዎች እንዲሁም እነዚህን የመሬት ገጽታዎችን የሰሯቸው ሀይሎች ተብራርተዋል:: በሶስተኛ ደረጃ የመሬት ከባቢ አየር ሲሆን የከባቢ አየር ምንነት፣ የከባቢ አየር ንጣፍ፣ የአየር ጠባይና የአየር ንብረት ይዘቶች እና ተቆጣጣሪዎች ተዳሰዋል:: በመጨረሻም የካርታ ንባብ ሲሆን በዚሁ ውስጥ የካርታ መስፈርት ምንነት፣ የካርታ መስፈርት አይነቶች፣ የካርታ መስፈርት አለዋወጥ፣ ስፋትን እና ርቀትን በካርታ ማስላት የሚሉት ተካተዋል::

### ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት:

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦**

- ☞ የዓለምን ካርታ በመጠቀም የአህጉራትን ስፋትና መገኛ ታሳያላችሁ::
- ☞ የመሬትን ቅርፅ የሚወስኑ ውስጣዊ እና ውጫዊ ኃይሎችን ትለያላችሁ::
- ☞ በውስጣዊ እና ውጫዊ ኃይሎች አማካኝነት የሚፈጠሩ የመሬት ቅርፅ ዓይነቶችን ንድፍ ሰርታችሁ ታሳያላችሁ::
- ☞ ሙቀትና ከፍታን መሰረት በማድረግ የመሬት ከባቢ አየር ንብብሮችን ታወዳድራላችሁ::

- ☞ በአየር ጠባይ እና በአየር ንብረት መካከል ያለውን ልዩነት ታነጻጽራላችሁ::
- ☞ የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት ይዘቶችን እና ተቆጣጣሪያዎችን ትተነትናላችሁ::
- ☞ ዕለታዊና ወቅታዊ የአየር ጠባይ መለዋወጥ የሚያስከትሉትን ጥቅምና ጉዳት ትገመግማላችሁ::
- ☞ የካርታ መስፈርት አይነቶችን በመለየት አንዱን የካርታ መስፈርት ወደ ሌላው ትቀይራላችሁ::
- ☞ ርቀት እና ስፋትን በካርታ ላይ ታሰላላችሁ::
- ☞ አለማቀፋዊ መገኛ ስርዓትን በመጠቀም መረጃ ማግኘት ትችላላችው::

## 1.1. አህጉራት እና ውሃማ አካላት

### ቁልፍ ቃላት:

| | |
|---|---|
| ☞ አህጉር | ☞ ውስጣዊ ሀይሎች |
| ☞ ውቅያኖስ | ☞ ውጫዊ ሀይሎች |
| ☞ ደሴት | ☞ ቅልብሽ |
| ☞ ገሞራዊ ትፍ | ☞ ዝንፈት |

### 1.1.1 አህጉራት

**ተግባር-1**


1. አህጉራት በምን በምን የሚለያዩ ይመስሏችኋል?

በስነ-መሬት ጥናት እይታ አህጉራት ሰፋፊ ደረቅ መሬቶችን ወይም የብሶችን ብቻ የያዙ ሳይሆን ስስ የሆነ ውሃ የሸፈነውን አህጉራዊ ሰጥንጌን (Continental Shelf) እና በዚሁ ክፍል ላይ ያሉ ደሴቶችን እንደሚያካትቱ ይገለፃል:: አህጉር ትልቅ ያልተከፋፈለ ነገር ግን ከሌሎች አህጉራት የተወሰነ ስፋት ባለው ውሃ የተለየ ግዙፍ ምድር ነው:: በአለም ላይ ሰባት አህጉሮች አሉ:: እነርሱም እስያ፣ አፍሪካ፣

ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ፣ አንታርክቲካ፣ አውሮፓ እና አውስትራሊያ ናቸው::

## ተግባር-2

1. ተማሪዎች! ጥንድ ጥንድ በመሆን በምስል-1 ላይ የቀረበውን የአለም ካርታ መሰረት በማድረግ የእያንዳንዱን አህጉር ስም ከጻፋችሁ በኋላ ያገኛችሁትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ::



ምስል1- አህጉራት 1:100,000,000

**የእስያ አህጉር:** እስያ በምስራቅ ሰላማዊ ውቅያኖስ፣ በደቡብ ህንድ ውቅያኖስ፣ በሰሜን አርክቲክ ውቅያኖስ፣ በምዕራብ አውሮፓ፣ በደቡብ ምዕራብ ከሜዲትራኒያን ምስራቃዊ ጫፍ፣ ከሲዊዝ ካናልና ከቀይ ባህር ጋር ይዋሰናል:: እስያ ባለው የቆዳ ስፋትና ህዝብ ብዛት በቀዳሚነት ይገኛል:: እስያ በሦስት ንዑሳን ክልሎች ትከፈላለች:: እነዚህም ምስራቅ እስያ፣ ደቡብ እስያና ደቡብ ምስራቅ እስያ ናቸው::

**የአፍሪካ አህጉር:** አፍሪካ በደቡብ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ፣ በሰሜን ሜድትራኒያን ባህር፣ በምስራቅ ከህንድ ውቅያኖስ እና በምዕራብ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ ጋር ይዋሰናል። አፍሪካ ከእስያ በመቀጠል በህዝብ ብዛትና በቆዳ ስፋት ሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። አፍሪካ እስከ አሁን ድረስ የሰው ልጅ መገኛ አህጉር በመባል ይጠራል። አፍሪካ በአምስት ንዑሳን ክልሎች ትከፈላለች። እነዚህም ሰሜን አፍሪካ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ምስራቅ አፍሪካ፣ ምዕራብ አፍሪካ እና መካከለኛው አፍሪካ ናቸው።

**የሰሜን አሜሪካ አህጉር:** ሰሜን አሜሪካ በምስራቅ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ፣ በደቡብ ከደቡብ አሜሪካ፣ በሰሜን ከአርክቲክ ውቅያኖስ እና በምዕራብ ከሰላማዊ ውቅያኖስ ጋር ይዋሰናል።

**የደቡብ አሜሪካ አህጉር:** ደቡብ አሜሪካን በስተሰሜን ሰሜን አሜሪካ፣ በስተደቡብ ከአንታርክቲክ ውቅያኖስ፣ በስተምስራቅ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ እና በስተምዕራብ ከሰላማዊ ውቅያኖስ ጋር ይዋሰናል።

**የአንታርክቲካ አህጉር:** አንታርክቲካ በደቡባዊ ውቅያኖስ የተከበበ አህጉር ነው።

**የአውሮፓ አህጉር:** አውሮፓ በስተምስራቅ እስያ፣ በስተምዕራብ አትላንቲክ ውቅያኖስ፣ በስተሰሜን አርክቲክ ውቅያኖስ፣ በስተደቡብ የሜዲትራኒያን ባህር እና አፍሪካ ያዋስኑታል።

**የአውስትራሊያ አህጉር:** አውስትራሊያ በምስራቅ እና በሰሜን ከሰላማዊ ውቅያኖስ፣ በምዕራብ ከህንድ ውቅያኖስ፣ እንዲሁም በደቡብ ከአንታርክቲክ ውቅያኖስ ጋር ይዋሰናል።

ሰንጠረዥ1. የአህጉራት ስፋት እና የህዝብ ብዛት

| ተ.ቁ | የአህጉር | የቆዳ ስፋት (ኪ.ሜ$^2$) | ስፋት ድርሻ | የህዝብ ብዛት | የህዝብ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰሜን አሜሪካ | 24, 490, 000 | 16.5% | 542,056,000 | 8.0% |
| 2 | አፍሪካ | 30, 370, 000 | 20.4% | 1,022,234,000 | 15.0% |
| 3 | አንታርክቲካ | 13, 720, 000 | 9.2% | 0 | 0.0% |
| 4 | ደቡብ አሜሪካ | 17, 840, 000 | 12.0% | 392,555,000 | 5.6% |
| 5 | አውስትራሊያ | 9, 008, 500 | 5.9% | 29,127,000 | 0.4% |
| 6 | አውሮፓ | 10, 180, 000 | 6.8% | 738,199,000 | 11.0% |
| 7 | እስያ | 43, 820, 000 | 29.5% | 4,164,252,000 | 60.0% |

ምንጭ: ኢንግሊሽ (1995)

**ተግባር-3**

1. ተማሪዎች! በየግላችሁ በመሆን የአህጉራትን ስፋት መሰረት በማድረግ ከትልቅ ወደ ትንሽ አስቀምጡና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

## 1.1.2. ዋና ዋና ውሃማ አካላት

**ተግባር-4**

1. ተማሪዎች! የአካባቢያችሁ ማህበረሰብ ውሀን ከምን ከምን እንደሚያገኙ በየግላችሁ አስቡና ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::

ውሃማ አካላት ብዙ ጊዜ የሚገለፁት በገፀ-ምድር ላይ በብዛት የተከማቹ ውሃዎችን ማለትም እንደ ውቅያኖሶች፣ ባህሮች፣ ሀይቆች፣ ኩሬዎች፣ ባህረ ሰላጤዎች፣ ወንዞች እና ምንጮችን በዋናነት ያካትታሉ:: በመሬት ላይ ከሚገኙ ውሃማ አካላት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

## ሀ) ውቅያኖሶች (Oceans)

ውቅያኖሶች ከሁሉም የውሃማ አካላት በላይ ትላልቅ የሆኑ አካላት ናቸው:: ይህም ሲባል የሚሸፍኑት የገፀ-ምድር ስፋት በጣም ሰፊ ሲሆን የሚይዙት የውሃ መጠን ደግሞ እጅግ በጣም ብዙ መሆኑን ለመግለፅ ነው:: በዓለማችን ላይ አምስት ውቅያኖሶች ይገኛሉ:: እነዚህም በሰንጠረዥ-2. ላይ ሰፍረው እናገኛቸዋለን::

ሠንጠረዥ-2. የዓለማችን ውቅያኖሶች

| ተ.ቁ | ውቅያኖስ | ስፋት (ሚሊዮን ኪ.ሜ$^2$) | የሚያዋስኑት ባህሮች |
|---|---|---|---|
| 1 | አትላንቲክ ውቅያኖስ | 76.8 | የሜዲትራኒያን ባህር፣ የካረቢያን ባህር፣ የባልቲክ ባህር |
| 2 | ደቡባዊ ውቅያኖስ | 20.3 | - |
| 3 | ሰላማዊ ውቅያኖስ | 155.1 | የኮራል ባህር፣ የጃፓን ባህር፣ የቻይና ባህር እና የጃቫ ባህር |
| 4 | ህንድ ውቅያኖስ | 68.1 | ቀይ ባህርና የፐርሺያ ባህረ ሰላጤ |
| 5 | አርክቲክ ውቅያኖስ | 14.1 | - |

**ተግባር-5**

1. ተማሪዎች! በየግላችሁ በመሆን የውቅያኖሶችን ስፋት መሰረት በማድረግ ከትንሽ ወደ ትልቅ አስቀምጡና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

## ለ) ባህር (Sea)

ባህር ባለው መጠን እና በሚይዘው የውሃ መጠን ከውቅያኖስ ያንሳል:: ባህር በአብዛኛው ክፍሉ በየብሶች የተከበበ ሲሆን በተወሰነ ጎኑ ግን በየብሶች መካከል በሚገኝ ጠባብ ክፍል ከውቅያኖሶች ጋር ይገናኛል:: ለምሳሌ: ሜዲትራኒያን ባህር አብዛኛው ክፍሉ በአፍሪካ፣ በአውሮፓና በእስያ አህጉራት የተከበበ ሲሆን በአፍሪካና በአውሮፓ መካከል በሚገኝ ጠባብ ቦታ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ ጋር የተገናኘ ነው::

የባህር ውሃ በአብዛኛው ጨዋማ ነው:: ስለሆነም ለመጠጥነት ሊውል አይችልም::

ሠንጠረዥ 3. የዓለማችን ታላላቅ ባህሮች

| ተ.ቁ | ባህር | ስፋት(ኪ.ሜ$^2$) |
|---|---|---|
| 1 | የሜክሲኮ ባህረ ሰላጤ | 1,507,600 |
| 2 | ካሪቢያን ባህር | 2,515,900 |
| 3 | የአረቢያን ባህር | 1,498,320 |
| 4 | ደቡብ ቻይና ባህር | 2,974,600 |
| 5 | ቤሪንግ ባህር | 2,261,100 |

### ተግባር-6

1. ተማሪዎች! በጥንድ በጥንድ በመሆን የባህሮችን ስፋት መሰረት በማድረግ ከትንሽ ወደ ትልቅ አስቀምጡና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::
2. ተማሪዎች! ጣና ሀይቅ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ሀይቆች አንዱ ሲሆን የሚገኝበትን ክልል እና ጠቀሜታውን በቡድን በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

## ሐ) ሀይቅ

ሀይቅ ማለት ዙሪያውን በሁሉም ክፍሉ በደረቅ መሬት (የብስ) የተከበበ የውሃ ክፍል ማለት ነው:: ሀይቅ በስፋት እና በሚይዘው የውሃ መጠን ከውቅያኖስ እና ከባህር እጅግ በጣም ያንሳል:: የሚይዘው ውሃ ግን በተወሰነ ደረጃ ንፁህ ውሃ ወይም ጨው-አልባ ነው:: ስለሆነም ለመጠጥነት ሊውል ይችላል::

ሠንጠረዥ 4. የዓለማችን ታላላቅ ሃይቆች

| ተ.ቁ | ሀይቅ | መገኛ አህጉር | ስፋት(ኪ.ሜ$^2$) |
|---|---|---|---|
| 1 | ካስፒያን ባህር | ኤሮ-ኤስያ | 371000 |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

### ተግባር-7

1. ተማሪዎች! ወደ ቤተ መጽሐፍት በየግላችሁ በመሄድ ከ2-5 በቅደም ተከተል የሚወከሏቸውን የዓለም ታላላቅ ሀይቆች ትክክለኛ መረጃ በመሰብሰብ ስፋታቸውን እና የሚገኙበትን አህጉር መሰረት በማድረግ ከትልቅ ወደ ትንሽ አስቀምጡና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## መ) ወንዞች (Rivers)

### ተግባር-8

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የምታውቋቸው ወንዞች አሉ? የአካባቢያችሁ ማህበረሰብ ወንዞችን ለምን ለምን አገልግሎት እንደሚጠቀሙባቸው ዘርዝሩ።

ወንዝ የሚፈስ ውሃ የያዘ አካል ሲሆን ውሃው የሚጓዝው በቋሚ ወይም በጊዜያዊ መጃረቻ ወይም መፋሰሻ ቦይ /channel/ ነው። ማንኛውም ወንዝ የራሱ የሆነ የተፋሰስ ቦታ /catchments area/ አለው።

ሠንጠረዥ-5. የዓለማችን ታላላቅ ወንዞች

| ተ/ቁ | የወንዝ ስም | ርዝመት (ኪ.ሜ) | መገኛ አህጉር |
|---|---|---|---|
| 1 | ናይል | 6671 | አፍሪካ |
| 2 | አማዞን | 6437 | ደ.አሜሪካ |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

### ተግባር-9

1. ተማሪዎች! በየግላችሁ ወደ ቤተ መጽሐፍት በመሄድ በሰንጠረዥ-5 መስረት ከ3-5 የሚወከሏቸውን የዓለም ታላላቅ ወንዞች ስም፣ ርዝመት እና አንፃራዊ መገኛ አህጉር ትክክለኛ መረጃ በማሰባሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::

## 1.2. የመሬት ገፅ ቀራፂ ኃይሎች

### ተግባር-10

1. ተማሪዎች! ስለመሬት መንቀጥቀጥ የሰማችሁትን ለክፍል ተማሪዎች ግለጹ::

### ሀ) የመሬት ገፅ ቀራፂ ውስጣዊ ኃይሎች እና ገፀ-ምድራዊ ውጤቶቻቸው

ውስጣዊ ኃይሎች ከመሬት ውስጥ የሚመነጩ ሲሆን የኅነት (Diastrophism) እና ገሞራዊ (Volcanism) ሂደቶችን ያከናውናሉ:: የኅነት ሂደቶች የመሬት ቅራፎን(crust) በመቀልበስ፣ በመሰንጠቅ፣ በማዛነፍና ወደ ላይ በማግዘፍ የተለያዩ ምድረ ቅርጾችን ይሰራሉ:: እነዚህ ሂደቶች የቅልብሽ፣ የዝንፈትና የማግዘፍ ሂደቶችን ያካትታሉ::

ገሞራዊ ሂደት በልጤ(mantle) ላይኛው ክፍል ወይም በዝቅተኛው ቅራፎ ክፍል ውስጥ የሚገኝ ገሞራ ህፅም የሚያከናውናቸውን ከቦታ ቦታ የመዘዋወር፣ የመቀዝቀዝና የመጠንከር ሂደቶች የሚያጠቃልል ሲሆን ገሞራዊ ቡልቅንና ገሞራዊ ስርገት እንቅስቃሴዎች ያካትታል።


የጎነት ሂደቶችና ገሞራዊ ሂደቶች በአጠቃላይ ንጥነጣዊ ሂደቶች (Tectonic Processes) ይባላሉ። እነዚህ ሂደቶች ኃይላቸውን የሚያገኙት በመሬት ውስጥ በሚከናወኑ ለውጦች አማካኝነት ነው። ለውጦቹ የሚከሰቱት በመሬት ውስጥ በሚኖር የሙቀት ዝውውር ወይም በራድዮ አክቲብ ወይም በሱፍሃን ምድረ እብን (Lithosphere) ቁሶች መስፋፋትና መኮማተር ምክንያት ነው። የውስጣዊ ኃይሎች ዋና ተግባር በገጸ-ምድር ላይ የሚገኑ ወጣገባዎችን መስራት ነው።

## ሀ) ቅልብሽ (folding)

ከመሬት ውስጥ የሚመነጨው ሀይል በውጨኛው ቅርፊተ መሬት ላይ የሚገኙትን አለቶች እንዲቀለበሱ እና እንዲዛነፉ ሲያደርግ በመሬት ገጽ ላይ የተቀለበሱ እና የተዛነፉ የተለያዩ የመሬት ቅርጾች ይፈጠራሉ። ቅልብሽ በመሬት ገጽ ላይ ተራራዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል። ለምሳሌ፦ በሰሜን ምዕራብ አፍሪካ አትላስ፤ በደቡብ ምዕራብ አፍሪካ ደግሞ ኬፕ ሬንጅ የተራራ ሰንሰለት፣ በአውሮፓ የአልፕስ የተራራ ሰንሰለት፤ በሰሜን አሜሪካ የሮኪ ተራራ፤ በእስያ የሂማሊያ ሰንሰለታማ ተራራ፤ በደቡብ አሜሪካ የኤንደስ ተራራ የተፈጠሩት በቅልብሽ አማካኝነት ነው።

### ተግባር-11

1. ተማሪዎች! ከምስል-2 ምን ምን ዓይነት የመሬት ገጽታ ተመለከታችሁ?




ምስል 2- የቅልብሽ አይነቶች


### ተግባር-12

1. ተማሪዎች! የምስል 2 የመሬት ቅርጾች በምን ምክንያት እንደተፈጠሩ ግለፁ::

## ለ) ዝንፈት (faulting)

### ተግባር-13


1. ታላቁ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ እንዴት እና በምን ምክንያት የተፈጠረ ይመስላችኋል?




ምስል 3- ቅልብሽ እና ዝንፈት

ዝንፈት የሚከሰተው የመሬት ንጥነጣዊ እንቅስቃሴ በሚፈጥረው ግፊት የተነሳ አለቶች ከተለያየ አቅጣጫ ወደ ተመሳሳይ አቅጣጫ ሲገፉ፤ አንዱ በሌላው ላይ ሲጫን ወይም አንዱ ከሌላው ስር ገብቶ ሲገኝ ነው:: ዝንፈት ለምቅማጥ ተራራዎች (Block mountain)፤ ለስምጥ ሸለቆ እና ለአምባ ምድር መፈጠር ምክንያት ነው:: ምቅማጥ ተራራዎች የሚፈጠሩት በአብዛኛው በሁለት ትይዩ ስንጥቆች መካከል ያለው መሬት ወደ ላይ ተገፍቶ በሚወጣበት ጊዜ ነው:: ወደ ላይ እንዲነሳ የተገደደው የቅርፊት መሬት አካል ምቅማጥ ተራራ ተብሎ ሲጠራ ወደታች በመስመጥ ዝቅ የሚለው የቅርፊት መሬት አካል ደግሞ ስምጥ ሸለቆ (Rift valley) ይፈጥራል:: ከስምጥ ሸለቆ ግራና ቀኝ የሚገኙ ያልሰመጡ የመሬት ክፍሎች ደግሞ አምባ ምድር ይፈጥራሉ::

የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ የአለም ትልቁ ስምጥ ሸለቆ አካል ነው:: ይህ ስምጥ ሸለቆ ርዝመቱ ከሶሪያ እስከ ሞዛምቢክ ይደርሳል:: ይህም በአጠቃላይ 7,200 ኪሎ ሜትር ርዝመት አለው:: በአፍሪካ 5,600 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን በኢትዮጵያ እና በኤርትራ ያለው ርዝመት ደግሞ 1,700 ኪሎ ሜትር ነው::




ምስል 4- የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ

### ተግባር-14

1. ተማሪዎች! የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ የተፈጠረበትን ምክንያት ለክፍል ተማሪዎች አስረዱ::
2. ስለኢተዮጵያ ስምጥ ሸለቆ መረጃዎችን በማሰባሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::

## ሐ) ገሞራዊነት (Volcanism)

### ተግባር-15


1. ተማሪዎች! በኢትዮጵያ የኤርታሌ እሳተ ገሞራ የት አካባቢ ይገኛል?

ገሞራዊነት የጠጣርነት፣ የፈሳሽነት ወይም የጋዝነት (የአየርነት) ባህሪ ያላቸው የማዕከለ መሬት አለቶች ወደ ቅርፊተ መሬት እንዲገቡ የሚገደዱበትን ወይም በቀጥታ ወደ መሬት ወለል ተገፍተው የሚወጡበትን ሂደት በሙሉ ያመለክታል:: ምንም እንኳን በማዕከለ መሬት አለቶች ከፍተኛ ሙቀት ያላቸው ቢሆንም ቅርፊተ መሬት በሚያሳድርባቸው ከፍተኛ ግፊት ምክንያት በከፊል በጠጣርነት መልክ ይገኛሉ:: ይሁን እንጅ በቅልብሽ እና በዝንፈት መፈጠር ሂደት ወይም በመሬት ስፍሀኖች (plates) ድንበር አካባቢ የመሬት የአግድም እንቅስቃሴ ሲኖር በማዕከለ


መሬት ላይ የተጫነው የግፊት መጠን በመቀነሱ ምክንያት በከፊል በጠጣርነት መልክ የነበሩት የማዕከለ መሬት አለቶች ሙሉ በሙሉ በመቅለጥ ወደ ቅርፊተ መሬት ደካማ አካባቢዎች ወይም በቀጥታ ወደ መሬት ወለል ይወጣሉ:: መሬት ወለል ላይ ከደረሱ በኋላ በመቀዝቀዝ እንደገና ወደ ጠጣር አለትነት ይቀየራሉ:: የቀለጠው አለት መሬት ውስጥ ገሞራ ህፅም (magma) ሲባል መሬት ወለል ላይ የደረሰው ደግሞ ገሞራ ትፍ (Lava) ይባላል::

## *ተግባር-16*

1. ተማሪዎች! እስኪ የሚከተሉትን ምስሎች በማየት መጀመሪያ በግል ቀጥሎ በጥንድ በመሆን ተወያዩ እና ከዚያም ያገኛችሁትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቀርቡ::




ምስል 5 - የውጫዊ እና ውስጣዊ ገሞራዊነት ባህሪያት




ምስል 6 - የእሳተ ገሞራ አፈጣጠር

## ውስን ጥናት

### ኤርታሌ

ኤርታሌ በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ንቁ እሳተ ገሞራ የሚገኝበት አካባቢ ነው:: ኤርታሌ የሚለው ቃል በአፋርኛ ቋንቋ የሚጨሰው ተራራ ማለት ነው:: ኤርታሌ በአፋር በረሃ አስደናቂ እና ማራኪ ውበት ያለው እና ተፈጥሯዊ የጎብኝዎች መስህብ ነው:: በአካባቢው የሚታዩት በርካታ ቆሬዎች (craters) ግዙፍ የእሳተ ገሞራ ምልክት ያሳያሉ እንዲሁም ሀይለኛ ሽታ ያለው ጭስ (fumes) ይተፋሉ:: በቆሬው ጠርዝ ላይ ህብረ-ቀለማት ያለው ገሞራ-ትፍ እና አመድ ሲወጣ ይታያል:: በተለይ በምሽት ሰዓት በኤርታሌ ዋድያት (caldera) ባለ ቀይ ቀለም ገሞራ ትፍ ሲፍለቀለቅ ማየት ልዩ ትንግርት ይፈጥራል:: በተለይ ደግሞ ኤርታሌ ንቅ እሳተ-ገሞራ መሆኑ እና በሁሉም ቦታ የማይገኝ መሆኑ ሲታሰብ ልዩ የደስታ ስሜት ይፈጥራል::



ምስል 7 - ኤርታሌ እሳተ ገሞራ

### መ) የመሬት መንቀጥቀጥ (Earth quake)

**ተግባር-17**

1. ተማሪዎች! ከባድ መኪና በአጠገባችሁ ሲያልፍ ምን ተሰማችሁ?

የመሬት መንቀጥቀጥ የሚከሰተው ሁለት ስፍሀኖች (Plates) በተቃራኒ አቅጣጫዎች ለመንቀሳቀስ ከሚሞክሩበት ቦታ ላይ ነው:: በስፍሃኖች ግጭት ምክንያት የሚከሰተው ሰበቃ (friction) እንቅስቃሴያቸውን ሲገታው ግፊት (pressure) ይፈጥራል:: በመጨረሻም በድንገተኛ የመሬት የአግድም እንቅስቃሴ የተነሳ

ቀደም ብሎ የተፈጠረው ግፊት ወደ ቅርፊተ መሬት ወለል ሲወጣ መሬት ላይ የሚደርሰው ንዝረትና መናጋት የመሬት መንቀጥቀጥ ይባላል:: የግፊት የመጀመሪያ ነጥብ የመሬት መንቀጥቀጥ መነሻ (focus) ሲባል በቀጥታ ከእናት ላይ (ከመሬት የላኛው ወለል አካባቢ) የሚገኘውና ከፍተኛ ንዝረት የሚከሰትበት ነጥብ ደግሞ አንቅጥፍጣፍ (epicenter) ይባላል:: የንዝረት ሞገድ ከመሬት መንቀጥቀጥ መነሻ ጀምሮ በሁሉም አቅጣጫዎች ይሰራጫል:: የመሬት መንቀጥቀጥ መጠንና ጥንካሬ የሚለካው በሬክተር ስኬል ነው::

## ለ) የመሬት ገፅ ቀራፂ ውጫዊ ኃይሎች እና ገፀ-ምድራዊ ውጤቶቻቸው

### ተግባር-18

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የትኞቹ የመሬት ገጽታዎች በወራጅ ውኃ ወይም የትኞቹ በነፋስ አማካኝነት እንደተፈጠሩ የምታውቁትን ግለጹ::

ውጫዊ ኃይሎች ከመሬት ውጭ የሚመነጩ ሲሆን በዋናነት በአየር ንብረት ተጽዕኖ አማካኝነት የሚከሰቱ ናቸው:: ውጫዊ ኃይሎች አለቶችን በመፈርፈር፣ በማንጓዝና በማከማቸት የተለያዩ ምድረ ቅርጾችን ይሰራሉ:: እነዚህ ኃይሎች በአጠቃላይ የድርጀታ ኃይሎች (Gradational Forces) ይባላሉ:: የድርጀታ ኃይሎች ከፀሀይ ኃይላቸውን ካገኙ በኋላ ተግባራቸውን በተንቀሳቃሽ ወኪሎች (Moving Agents) ለምሳሌ በወራጅ ውሃ፣ በነፋስ፣ በአንብጓቢ በረድ፣ በቀላይ ሞገድና በመሬት ውስጥ ወይም በከርሰ ምድር ውሃ ያከናውናሉ:: የድርጀታ ኃይሎች የሚያከናውኗቸው ሂደቶች ዋና ተግባር በውስጣዊ ኃይሎች የተሰሩትን ወጣገባዎችን ወይም ጉባጉቦችን ማስተካከል ነው:: ይህም የሚከናወነው በሂደቶቹ አማካኝነት ፍርፍር ዓለቶችን ከከፍተኛ ቦታዎች ወደ ዝቅተኛ ቦታዎች በማጓጓዝና በማደራጀት ነው::

ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱም የንጥነጣዊና የድርጀታ ሂደቶች ተግባራቸውን ለብዙ ሚሊዮን ዓመቶች ቀስ በቀስ በገጸ-ምድር ላይ በማከናዎን አብዛኞቹን ምድረ ቅርጾችን ሰርተዋል:: ውጫዊ ሀይሎች ሶስት አይነት ሂደቶችን ያከናውናሉ:: እነርሱም፦

## 1. ግጥግጦሽ (Denudation)

ይህ እንቅስቃሴ የመሬትን ወለል ዝቅ የማድረግ ወይም የማስተካከል እንቅስቃሴ ነው:: የግጥግጦሽ እንቅስቃሴ ፍርፈራንና ሽርሸራን ያጠቃልላል:: ፍርፈራ አለቶችን ቀስ በቀስ የመሰባበርና ወደ ትናንሽ አካላት የመቀየር ሂደት ነው:: ፍርፈራ በሁለት ይከፈላል:: እነርሱም:

### ሀ) የአለቶች መሰባበር (physical weathering)

የአለቶች መሰባበር አንዳንድ ጊዜ መካኒካዊ ፍርፈራ ይባላል:: የአለቶች መሰባበር ማለት ተፈጥሯዊ አለቶችን ወደ ደቃቅ አካልነት የመቀየር እንቅስቃሴ ነው:: አለቶች ለሙቀት እና ለቅዝቃዜ ሲጋለጡ መሰነጣጠቅ እና መሰባበር ይጀምራሉ:: የዛፍ ስሮች በአለቶች ስንጥቅ ጠልቀው በመግባት ስንጥቆቹን የበለጠ ያሰፏቸዋል:: ቀዝቃዛ የአየር ንብረት ባለበት አካባቢ በስንጥቆቹ መካከል ውሃ ይገባል:: ውሀው በቅዝቃዜ ምክንያት ወደ በረዶነት ስለሚቀየር አለቶቹን በማሳበጥ፣ በመሰነጣጠቅ እና በመሰባበር ወደ ደቃቅ አካልነት ይለውጣቸዋል::

### ለ) ኬሚካዊ ፍርፈራ (chemical weathering)

**ተግባር-19**

1. ተማሪዎች! በቤታችሁ ውስጥ የሚገኙት ብረቶች ለዝገታቸው ምክንያት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? እስኪ የምታውቁትን ተናገሩ::

ኬሚካዊ ፍርፈራ የአለቶችን ይዘት የሚለውጡ በርካታ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል:: እነዚህ እንቅስቃሴዎች ጎልተው የሚታዩት ሙቀት እና እርጥበት ባለበት ስፍራ ነው:: ቀዝቃዛ እና ደረቅ የአየር ንብረት በሚፈራረቅባቸው አካባቢዎች እንቅስቃሴዎቹ በጣም አዝጋሚዎች ናቸው:: ከእንቅስቃሴዎቹ በጣም የተለመደው ውክሰዳ (oxidation) ነው:: የመዳብ እና የብረት ዝገት የውክሰዳ ውጤት ነው:: ውክሰዳ ማለት የኦክስጅን እና የማዕድናት መዋሃድ ማለት ነው:: በሌላ በኩል በዝናብ ውስጥ የሚገኙ ደካማ አሲዶች እንደ ኖራ ድንጋይ ያሉትን አለቶች ያሟሟል:: ይህ እንቅስቃሴ ወይም ሂደት ከሰላ (carbonation) ይባላል::

የዝናብ ውሃ መሬት ውስጥ እየሰረገ የሚፈጥራቸው የመሬት ውስጥ ወንዞችን ከመሬት ስር የሚገኘውን የኖራ ድንጋይ በማሟሟት በሂደት የመሬት ውስጥ


መተላለፊያዎችን እና ዋሻዎችን ይፈጥራሉ:: ዋሻዎቹም በተራቸው ስርግርጌ (Stalactite)፣ ጉልት ካልሲት (stalagmite) እና አምዶች (pillars) የመሳሰሉትን አካላት ይፈጥራሉ::

- ስርግርጌ (Stalactite)፦ የሚባሉት ከዋሻዎቹ ጣራ ላይ ቁልቁል የሚንጠለጠሉ የኖራ ድንጋይ አካላት ናቸው::
- ጉልት ካልሲት (stalagmite)፦ የሚባሉት ከዋሻዎቹ ወለል በመጀመር ቀስ በቀስ ወደ ላይ እየተቆለሉ ሂደው በመጨረሻም የኖራ ድንጋይ አምድ የሚፈጠሩ አካላት ናቸው::
- አምዶች (pillars)፦ እነዚህ ደግሞ በዋሻዎቹ ውስጥ ስርግርጌ እና ጉልት ካልሲቶች ሲገናኙ የሚፈጥሯቸው የኖራ ድንጋይ ምሰሶዎች ናቸው::

*ተግባር-20:*

ተማሪዎች በምስል-6 መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. የተመለከታችሁትን የመሬት ቅርጾች ዘርዝሩ::
2. ጥያቄ ቁጥር አንድን መሰረት በማድረግ የመሬት ቅርጾች በምን እና እንዴት እንደተሰሩ አብራሩ::



ምስል 8 - በኖራ ድንጋይ ላይ የተፈጠሩ የመሬት ገፅታዎች

## 2. ሸርሸራ (Erosion)

### ተግባር-21

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የሚገኙት የመሬት መልክዓ ምድሮች በምን የተፈጠሩ ይመስላችኋል?
2. በአካባቢያችሁ ያሉ ታናናሽ እና ታላላቅ ወንዞች መፋሰሻ እየጠበቡ ወይስ እየሰፉ ነው የሚሄዱት? ለምን?

የተሰባበሩ አለቶች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በውሃ ፍሰት (running water)፣ በበረዶ፣ በንፋስ እና በውቅያኖስ ሞገድ ተጠርገው ወይም ታጥበው የሚወሰዱበት ሂደት ሸርሸራ ይባላል:: ውሃ በመሬት ወለል ላይ የጎርፍ መውረጃ ቦዮችን ይፈጥራል:: ቦዮቹ ጥልቀት እና ስፋት እያገኙ ሲሄዱ ከተራ ጎርፍ መውረጃነት አልፈው ታላላቅ ወንዞች ይሆናሉ::

በነፋስ ሃይል እየተወሰደ በሌላ ቦታ የሚከማች የደረቅ አሸዋ ክምችት (loess) ሌላኛው የሸርሸራ ውጤት ነው:: በነፋስ ሃይል እየተገፋ የተወሰደው አሸዋ ብዙ እርቀት ተጉዞ በሌላ ቦታ አዲስ አፈር ወይም አዲስ የአሸዋ ክምችት ይፈጥራል::

ከብዙ ሺህ አመታት በፊት ከተራራ ላይ በዝግታ የሚንሸራተት ግግር በረዶ (glaciers) በካናዳ፣ በምዕራብ አውሮፓ እና በሩሲያ መሬቱን ሲያርስ እና ገፀ-ምድሩን ሲለውጥ ቆይቷል:: በዚህ የተነሳ በአካባቢው ስስ አፈር የያዘ ገፀ-ምድር ተፈጥሯል:: በባህር ጠረፋማ አካባቢዎች ደግሞ ቀላይ ሞገድ እና ማዕበላዊ ሞገድ የመሳሰሉትን አዳዲስ ገፀ-ምድሮችን ከመፍጠራቸውም በላይ የሰውን ልጅ የአኗኗር ስርዓት የተለያየ ያደርጋሉ::

### ተግባር-22

1. ተማሪዎች! እስኪ የሚከተሉትን ምስሎች በየግላችሁ በማየት የተረዳችሁትን ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::



ምስል 9 - የቦይ ሸርሸራ



ምስል- 10. ወጥነት ያለው የሰፊ አካባቢ ሸርሸራ



ምስል 11 - የነፋስ ሸርሸራ

## 3. ክምችት (Deposition)

### ተግባር-23


1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ በወራጅ ውሃ የተጎዱ መሬቶችን ዘርዝሩ::

ክምችት የፍርፈራ እና የሸርሸራ የመጨረሻ ውጤት ነው:: የተሰባበሩ አለቶች፣ አሸዋ እና አፈር በውሃ፣ በነፋስ፣ በበረዶ፣ በውቅያኖስ እና በስበት ሀይል ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተጓጉዘው በአንድ ቦታ ላይ በተለያዩ መንገዶች ይከማቻሉ:: **ለምሳሌ** የስበት ሀይል ቅጽበታዊ የሆነ ግዝፈተ ንደት (mass movement) ያስከትላል:: አዲስ የተከማቸው አፈር በወንዞቹ መውረጃ ቦይ፣ ሜዳማ የባህር ዳርቻዎች፣ በኮረብታ እና በተራራዎች ግርጌ አካባቢ ሰተቶ ደለል (Alluvial

plains) ይፈጥራል:: ትላልቅ ወንዞች ለምሳሌ እንደ ናይል፣ ሚሲሲፒ እና አማዞን የመሳሰሉት ባሉበት ቦታ ሰፊ ደለል (Delta) ይሰራሉ:: አንዳንዴም ባህር ውሰጥ ርቀት ተጉዘው ይከማቻሉ::

## የሸርሸራ ውጤቶች

ውሃ፣ ነፋስ፣ ቀላይ ሞገድ፣ አጎብጓቢ በረድ፣ ከርሰ ምድር ውሃና በመሳሰሉት አንቀሳቃሽ ውኪሎች አማካኝነት ምድረ ቅርፅን ያስተካክላሉ::




ምስል 12 - ሸርሸራ፣ ፍርፈራ እና ክምችት

### ተግባር-24

1. ተማሪዎች! ከምስል 12 ምን ተመለከታችሁ? የተመለከታችሁትን ግለጹ::
2. ተማሪዎች! በትንንሽ ቡድን በመሆን ውስጠ መጥ እና ውስጣዊ ሀይሎች የሚሰሯቸውን

   የመሬት ቅርጾች ተወያይታችሁ የእያንዳንዱን ቅርጽ የሚያሳይ ንድፍ በማዘጋጀት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::

# 1.3 የመሬት ከባቢ አየር

## 1.3.1. የመሬት ከባቢ አየር ንጣፎች


**ቁልፍ ቃላት:**

- ☞ ከባቢ አየር
- ☞ ስሬ ህዋ
- ☞ ዝቄ ህዋ
- ☞ ማዕከለዊ ህዋ
- ☞ ሙቄ ህዋ

**ተግባር-25**

1. ተማሪዎች! ዛፎች ሲንቀሳቀሱ አይታችዋል? ምን የሚያንቀሳቅሳቸው ምን ይመስላችዋል?

የመሬት ከባቢ አየር 78% ናይትሮጅን (N)፣ 21% ኦክስጅን ($O_2$) እና 0.9 % አርገን (Ar) ሲሆን እንዱሁም 0.03 % ካርቦንዳይኦክሳይድ ($Co_2$) እና ሌሎችንም ጋዞች የያዘ ነው:: የከባቢ አየርን የሙቀትና የከፍታ ዝምድና መሰረት በማድረግ የመሬት ከባቢ አየር በአራት የተለያዩ ንጣፎች (Layers) የተከፈለ ነው::




ግራፍ-1. የከባቢ አየር ንጣፎች (በኪ..ሜ)

## ሀ) ስሬ ህዋ (Troposphere)

### ተግባር-26

1. ስሬ ህዋ ምን ምን ነገሮችን በውስጡ ይዟል? እስኪ የምታወቁትን በየግላችሁ አስቡና ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

ስሬ ህዋ ሁሉም የአየር ጠባይ ክንዋኔዎች የሚካሄድበት ማለትም የዝናብ፣ የደመናና የሌሎችም ነገሮች መፈጠሪያ ነው። ስሬ ህዋ አብዛኛው የአየር ክምችት የሚገኝበት የከባቢ አየር ክልል ነው። በስሬ ህዋና በዝቄ ህዋ መካከል ያለው ቀጭን ደንበር ልውጥ ወሰን (ትሮፖፖውዝ) ይባላል። በስሬ ህዋ ከፍታ ሲጨምር የሙቀት መጠን ይቀንሳል።

## ለ) ዝቄ ህዋ (Stratosphere)

ከስሬ ህዋ ቀጥሎ ያለው የላይኛው ንጣፍ ዝቄ ህዋ ሲሆን በዚህ ክፍል ስስ የኦዞን ንጣፍ ይገኛል። የኦዞን ንጣፍ ዋነኛ አገልግሎት ከፀሀይ የሚመጣውን አደገኛ ጨረሮች (የአልትራቫዮሌት ጨረር) በመምጠጥ ማስቀረት (Absorb) ነው። በአሁኑ ሠዓት የሰው ልጆች በሚፈጥሩት የካርበን ልቀት (CFC ) የኦዞን ንጣፍ እየተጎዳና እየሳሳ ሲሆን በዚህም በመሬት ላይ ያሉ ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ በአደጋ ውስጥ ወድቀዋል። የዝቄ ህዋ የመጨረሻው ክፍል ስትራቶፓውዝ ይባላል። በዝቄ ህዋ ከፍታ ሲጨምር የሙቀት መጠን ይጨምራል።

## ሐ) ማዕከላዊ ህዋ (Mesosphere)

ማዕከላዊ ህዋ ከዝቄ ተቋርጦሽ (እስትራቶፓውዝ) በላይ ያለው ሲሆን ቀዝቃዛው የከባቢ አየር ክፍል ነው። የማዕከላዊ ህዋ ማብቂያ የላይኛው ክፍል ሜሶፓውዝ ይባላል። በማዕከላዊ ህዋ ከፍታ ሲጨምር የሙቀት መጠን ይቀንሳል።

## መ) ሙቄ ህዋ (Thermosphere)

ሙቄ ህዋ የከባቢ አየር የመጨረሻው ንጣፍ ሲሆን ከፍታ ሲጨምር የሙቀት መጠን ይጨምራል።

### ተግባር-27

1. ተማሪዎች በዝቁ ህዋ ከፍታ ሲጨምር የሙቀት መጠን የሚጨምርበት፣ በስሬ ህዋ ከፍታ ሲጨምር የሙቀት መጠን የሚቀንስበት፣ በማዕከላዊ ህዋ ከፍታ ሲጨምር የሙቀት መጠን የሚቀንስበት እና በሙቁ ህዋ ከፍታ ሲጨምር የሙቀት መጠን የሚጨምርበት ምክንያቶችን ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

## 1.3.2. የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት ምንነት እና ይዘቶች

**ቁልፍ ቃላት:**

- ☞ የአየር ጠባይ
- ☞ የአየር ንብረት
- ☞ የአየር ጠባይ ይዘቶች

### ተግባር-28

ተማሪዎች! እስኪ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግላችሁ የተረዳችሁትን ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

1. በቆላማ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ለምን ነጭና ስስ ልብስ እንዲለብሱ ይገደዳሉ?
2. በቀዝቃዛ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ለምን ጥቁርና ወፍራም ልብስ ይለብሳሉ?
3. በቀዝቃዛና በሞቃት አካባቢዎች የምንመገባቸው ምግቦች በዓይነትና በመጠን ተመሳሳይ አይደሉም ምክንያታችሁን አስቀምጡ፡፡

እያንዳንዱ ቀን የራሱ የሆነ የልከ ሙቀት፣ የዝናብ፣ የወኃ ዝለትና የነፋስ ሁኔታዎች አሉት፡፡ አንዱ ቀን ሞቃት ሲሆን ሌላው ቀን ቀዝቀዝ ያለ ሊሆን ይችላል፡፡ በአንደኛው ቀን ዝናብ ቢጥል በሌላው ቀን ደረቅ ሁኔታ ይኖራል፡፡ ዛሬ ደመናማ ቢሆን ነገ ጥርት ያለ ሰማይን መመልከት ይቻላል፡፡ በሌላ መልኩ የተጠቀሱት የከባቢ አየር ይዘቶች ከወቅት ወቅት ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አንድ አካባቢ ሞቃትና ደረቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላው አካባቢ ደግሞ ሞቃትና ዝናባማ

ወይም ቀዝቃዛና ዝናባማ ይሆናል። የልከ ሙቀት፣ የዝናብ፣ የነፋስ፣ የውሃ ላቦት፤ የደመና ሁኔታዎች ከዕለት ዕለትና ከወቅት ወቅት እንዲሁም ከቦታ ቦታ ይለያያሉ።

ዕለታዊ የአየር ጠባይ ማለት በአንድ በተወሰነ ጠባብ የቦታ ክልል ውስጥ ለአጭር ጊዜ የሚከሰት የአየር ሁኔታ ነው። የአየር ጠባይ ተለዋዋጭ ነው። የአየር ንብረት በሌላ መልኩ በአንድ በተወሰነ ሰፊ የቦታ ክልል ውስጥ ለረዥም ጊዜ የሚከሰት የአየር ሁኔታ ነው። የአየር ንብረት በአንፃራዊ መልኩ ቋሚ ነው።

የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት አባላት የምንላቸው አንድ የተወሰነ የራሱ ባህሪ ያለው አየር ንብረትን እና የአየር ጠባይ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታዎችን የያዘ ነው። የአየር ጠባይ መለዋወጥም ሆነ የአየር ንብረት ከቦታ ቦታ መለያየት የሚከሰተው በአየር ንብረት ይዘቶች የመጠንና የስርጭት መለያየት ምክንያት ነው። የአየር ንብረት ዋና ዋና ይዘቶች ልከሙቀት፣ ርጥበት ጥዱፍ ውርድ፣ ውሃ ዝለት፣ ነፋስና የአየር ግፊት ናቸው።

*ተግባር-29*

1. ዕለታዊና ወቅታዊ የአየር ጠባይ መለዋወጥ የሚኖረው ጥቅም እና ጉዳቱን አስረዱ።

## 1.3.3 የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች

*ተግባር-30*

1. በደረቅ መሬት ከባህር ያለው ርቀት ሲጨምር ሙቀትና እርጥበት ምን ሊሆን ይችላል?

ለአየር ንብረት ይዘቶች መለያየት ዋና ዋና መንስኤዎች የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች ናቸው። እነዚህ ተቆጣጣሪዎች የአየር ንብረት ወይም የአየር ጠባይ ተቆጣጣሪዎች በመባል ይገለፃሉ። የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች በአየር ንብረት ይዘቶች ላይ ተጽእኖ በማሳደር የተለያዩ የአየር ንብረትና ጠባዮችን ይፈጥራሉ።

ሰንጠረዥ-6. የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች እና ይዘቶች

| የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች | የአየር ንብረት ይዘቶች |
|---|---|
| ኬክሮስ | ልከሙቀት |
| ከፍታ | ጥዱፍ ውርድ |
| ቀላይ ሞገድ | ውሃ ዝለት |
| ከባህር ያለው ርቀት | ነፋስ |
| ነፋስና የአየር ግፊት | የአየር ግፊት |
| ተራራ እግድ | |

ተግባር-31

1. ተማሪዎች! ኬክሮስ ልከ ሙቀትን እንዴት እንደሚቆጣጠረው በየግላችሁ አስረዱ::
2. ተማሪዎች! ከፍታ ከጥዱፍ ውርድ ጋር ያለውን ዝምድና በጥንድ በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

## 1.3.4 አለታዊ እና ወቅታዊ የአየር ጠባይ መለዋወጥ

ተግባር-32

1. አለታዊ የአየር ጠባይ ለውጥ ማለት ምን እንደሆነ ታወቃላችሁ?

የአየር ንብረት ለውጥ (Climate Change) ለበርካታ ዓመታት የተመዘገበ የአየር ንብረት አማካይ ጥቅል ውጤት መቀየርን የሚያመለክት ነው:: በአጭሩ ለረዥም ዓመታት የተመዘገቡ አጠቃላይ የእርጥበት፣ የቅዝቃዜ፣ የሙቀት፣ የነፋስ አቅጣጫ የአየር ግፊት ወዘተ የመሳሰሉት ባህሪያት መለወጥ ነው::

የአየር ጠባይ ለውጥ የምንለው በቀናትና በወራት የሚቀያየር የነፋስ፣ የዝናብ፣ የሙቀትና የቅዝቃዜ ለውጥ ሲሆን ለውጡም የሚገለጸው በአነስተኛ መልክዓ ምድር ላይ ነው:: በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የአየር ጠባይ መዋዠቅ ይከሰታል:: በዚህም አሉታዊ ተፅዕኖዎች ሳቢያ የሰዎች ደህንነትና የኢኮኖሚው እድገት መጓተትን ያስከትላል::

**ተግባር-33**

1. ተማሪዎች! በእለታዊ እና ወቅታዊ የአየር ጠባይ ለውጥ መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት አብራሩ::

## 1.4. የካርታ መስፈርት፣ ርቀትና ስፋትን ማስላት

### 1.4.1. የካርታ መስፈርት አገላለጽ አይነቶች

**ቁልፍ ቃላት:**

- ☞ የካርታ መስፈርት
- ☞ የካርታ ርቀት
- ☞ የካርታ ስፋት

**ተግባር-34**

1. ተማሪዎች! ካርታ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ::

2. የካርታ መስፈርት ለምን ያስፈልጋል?

የካርታ መስፈርት በመሬት ላይ ያለን የአንድን ቦታ ገጽታ በካርታ ላይ ለክተን ለማስቀመጥ የምንጠቀምበት ዘዴ ነው:: ይህ በመሬትና በካርታ ላይ የሚታየውን የቦታ ርቀት እና ስፋት መጠን የምናዛምድበት ልኬት የካርታ መስፈርት ይባላል:: **ለምሳሌ**: በመሬት ላይ ያለን ርቀት የምንለካው በሜትር ወይም በኪሎ ሜትር ሲሆን በካርታ ላይ የሚታይ ርቀትን የምንለካው ደግሞ በሳንቲ ሜትር ነው:: የካርታ መሰፈርትን የምናገኘው በካርታ ላይ የተቀመጠውን ርቀት በመሬት ላይ ለሚገኘው ርቀት በማካፈል ነው::

$$\text{የካርታ መስፈርት} = \frac{\text{የካርታ ላይ ርቀት}}{\text{የመሬት ላይ ርቀት}}$$

## ተግባር-35

1. ተማሪዎች! በሁለት ከተሞች መካከል ያለው የመሬት ላይ ርቀት 100 ኪሎ ሜትር ቢሆንና ካርታዊ ርቀቱ ደግሞ 10 ሳ.ሜ ነው:: ስለዚህ የካርታውን መስፈርት አስሉ:: የሰራችሁትን ለክፍል ተማሪዎች ተራ በተራ አቅርቡ::

የካርታ መስፈርትን በሶስት መንገዶች መግለጽ ይቻላል:: እነርሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል::

### ሀ) በክፍልፋይ የሚገለፅ መስፈርት

ይህ ዘዴ የካርታ ርቀትን ከምድራዊ ርቀት ጋር በማወዳደር በንጥጥር ወይም በክፍልፋይ የምንገልጽበት ነው:: ይህ መስፈርት አሃድ አልባ ነው:: የካርታው እና የመሬት ርቀት የሚወከሉትም በተመሳሳይ አሀድ ነው::

ምሳሌ 1፡ 1 ፡ 200,000 ወይም 1/200,000

በካርታ ላይ 1 አሀድ ርቀተ በመሬት ላይ 200000 ተመሳሳይ አሀድ ይወክላል ማለት ነው::

ምሳሌ 2፡ 1፡50000 ወይም 1/50000

በካርታ ላይ 1 አሀድ ርቀተ በመሬት ላይ 50000 ተመሳሳይ አሀድ ይወክላል::

### ለ) በዓረፍተ ነገር የሚገለፅ መስፈርት

ይህ መስፈርት በካርታ እና በመሬት መካከል ያለውን ግንኙነት በቃላት አማካኝነት ለመግለጽ ይጠቅማል:: የካርታውም ሆነ የመሬት ርቀት አሀዶች አሏቸው::

ለምሳሌ 1፡ 1ሳ.ሜ ለ1ኪ.ሜ

ይህ ማለት በካርታ ላይ አንድ ሳንቲ ሜትር በመሬት ላይ አንድ ኪሎ ሜትር ይወክላል ማለት ነው:: ስለዚህ አንድ ሳንቲ ሜትር ለአንድ ኪሎ ሜትር በማለት ይገለጻል::

**ምሳሌ** 2፡ 1ሳ.ሜ ለ10ኪ.ሜ

በካርታ ላይ 1ሳ.ሜ ርቀት በመሬት ላይ 10 ኪ.ሜ ርቀትን ይወክላል ማለት ነው።

**ምሳሌ** 3፡ 2ሳ.ሜ ለ8ኪ.ሜ


በካርታ ላይ 2ሳ.ሜ ርቀት በመሬት ላይ 8 ኪ.ሜ ርቀትን ይወክላል ማለት ነው።

## ሐ) በግራፍ ወይም በመስመር የሚገለፅ መስፈርት


በዚህ መስፈርት አንድ ቀጥተኛ መስመር በማስመር በአረፍተ ነገር መስፈርት መሰረት በአሀዶች (units) ይከፋፈላል። በስተግራ ያለው የመስመሩ አካል በአነስተኛ ክፍልፋዮች ይከፋፈላል። በዚህም የተነሳ ከካርታው የተወሰዱ ርቀቶችን ወደ መሬት ርቀት መቀየር ቀላል ይሆናል።

**ምሳሌ** 1፡ 1ሳ.ሜ ለ3ኪ.ሜ የተገለጸ የዓረፍተ ነገር መስፈርት

በመስመራዊ መስፈርት ሲገለጽ 1ሳ.ሜ በማስመር ከአናቱ ላይ ሚወክለውን የመሬት ርቀት 3ኪ.ሜ ማስቀመጥ ነው።




**ምሳሌ** 2፡ የዓረፍተ ነገር መስፈርቱ 1ሳ.ሜ ለ1ኪ.ሜ ቢሆን ካርታ ላይ 4ሳ.ሜ የሚወክለውን ርቀት በመስመራዊ መስፈርት ለማሳየት የሚሰመረው መስመር 4 እኩል ቦታ በ1ሳ.ሜ ርቀት ይከፋፈላል። ይህም ማለት ካርታ ላይ የሚታየው 1ሳ.ሜ በመሬት ላይ 1ኪ.ሜ ርቀት ይወክላል ማለት ነው።



**ተግባር-36**

1. 1ሳ.ሜ ለ 4 ኪ.ሜ የሚለውን የዓረፍተ ነገር መስፈርት በመስመራዊ መስፈርት በደብተራችው ስምራችው አሳዩ::

## 1.4.2. የካርታ መስፈርቶችን መለወጥ

**ተግባር-37**

1. አንድ የካርታ መስፈርት ወደ ሌላ የካርታ መስፈርት መለወጥ ጠቀሜታው ምንድን ነው?

### ሀ) ከክፍልፋይ መስፈርት ወደ ዓረፍተ ነገር መስፈርት መለወጥ

ከክፍልፋይ መስፈርት ወደ ዓረፍተ ነገር መስፈርት ለመለወጥ በመጀመሪያ አካፋዩን ለ100,000 ሳ.ሜ አካፍሎ በአንድ ኪሎ ሜትር ማባዛት ያስፈልጋል::

**ምሳሌ**: 1፡ 250,000 የሆነ ክፍልፋይ መስፈርት ወደ ዓረፍተ ነገር መስፈርት ሲለወጥ

$$1ሳ.ሜ \text{ ለ } \frac{250{,}000 \text{ ሳ.ሜ}}{100{,}000 \text{ ሳ..ሜ}} \times \text{ በ}1ኪ..ሜ$$

ስለዚህ የዓረፍተ ነገር መስፈርቱ = 1ሳ.ሜ ለ 2.5 ኪ..ሜ ይሆናል::

### ለ) ከዓረፍተ ነገር መስፈርት ወደ ክፍልፋይ መስፈርት መለወጥ


የተሰጠውን የዓረፍተ ነገር መስፈርት ወደ ክፍልፋይ መስፈርት ለመለወጥ የመሬት ላይ ርቀትን የሚያሳየውን 2ኛውን ቁጥር በ100,000 ሳንቲ ሜትር በመባዛት ያለ አሀድ ማስቀመጥ ይሆናል::

**ለምሳሌ**: 1ሳ.ሜ ለ 2 ኪ..ሜ የተሰጠን መስፈርት ወደ ክፍልፋይ መስፈርት ሲለወጥ በሚከተለው መንገድ መስራት ይቻላል::

2ኪ..ሜ x 100,000 ሳ.ሜ = 200,000 ሳ.ሜ ይሆናል::

= 1.ሳ.ሜ ለ200,000 ሳ.ሜ ይሆናል:: መለኪያ አሃዶችን እርስ በርስ ስናጠፋቸው ወካይ መስፈርቱ 1: 200,000 ይሆናል::

### ሐ) ከመስመራዊ መስፈርት ወደ ዓረፍተ ነገር መስፈርት መለወጥ




ከዚህ በላይ ያለው መስመራዊ መስፈርት ወደ ዓረፍተ ነገር መስፈርት ሲቀየር 2ሳ.ሜ ለ4ኪ.ሜ ይሆናል ማለት ነው:: ይህ ማለት ደግሞ የካርታው ርቀት ከ0 እስከ 4ኪ.ሜ የተሰመረው 2ሳ.ሜ ሲሆን የመሬት ርቀት ደግሞ ከመሰመሩ አናት ላይ በኪሎ ሜትር የተመለከው ነው:: ስለዚህ የዓረፍተ ነገር መስፈርት 2ሳ.ሜለ ለ4ኪ.ሜ ይሆናል ማለት ነው፡

**ተግባር-38**

1. 2.5 ሳ.ሜ ለ2 ኪ.ሜ የሆነ መስፈርት ወደ ክፍልፋይ መስፈርት ሲቀየር ስንት እንደሚሆን በጥንድ በመስራት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::
2. 1ሳ.ሜ ለ 20 ኪ.ሜ የሚለውን መስፈርት በየግላችሁ ወደ ክፍልፋይ ከቀየራችሁ በኋላ በተግባር ጥቁር ሰሌዳ ላይ ሰርታችሁ አሳዩ::

## 1.4.3. በካርታ ላይ ርቀትን እና ስፋትን ማስላት

### ሀ) በካርታ ላይ ርቀትን ማስላት

**ተግባር-39**

1. ተማሪዎች! የመማሪያ ክፍላችሁ ርዝመት እና ወርድ ስንት ሜትር ነው?

በካርታ ላይ የምንፈልጋቸው ርቀቶች እውነተኛ የመሬት ርቀትን እንደምንፈልግ መገንዘብ ይኖርብናል:: ስለዚህ ርቀትን በሁለት መንገድ መፈለግ ይቻላል:: እሱም በቀጥተኛ እና በኢ-ቀጥተኛ መስመሮች ነው::

## 1. በቀጥተኛ መስመር ላይ ርቀትን መፈለግ


በቀጥታ መስመር ላይ ርቀትን ለማስላት በመጀመሪያ ርቀቱን በማስመሪያ መለካት ከዚያም የካርታ መስፈርትን በመጠቀም በማስመሪያ የተገኘውን ርቀት ወደ መሬት ርቀት መቀየር ነው::

## 2. በጉብጥ መስመሮች ላይ ርቀትን መፈለግ::

በጉብጥ መስመሮች ርቀትን ለመለካት እና ለማስላት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ማስመሪያ እና ክር ሲሆኑ ክሩን በጉብጥ መስመሩ ላይ በማስቀመጥ የጉብጡን ርዝማኔ በክሩ በመለካት እንዲሁም ክሩን ደግሞ በማስመሪያ በመለካት የተገኘውን የጉብጥ ርዝማኔ የካርታውን መስፈርት በመጠቀም ወደ መሬት ርቀት/ኪሎ ሜትር/ መቀየር ነው::

### ተግባር-40

1. ቀጥሎ ከቀረበው ካርታ ላይ በነጥብ “ሀ” እና “ለ” መካከል ያለውን ርቀትን በማስመሪያ በመለካት የመሬት ላይ ርቀቱን ካሰላችሁ በኋላ የተከተላችኋቸውን ቅደም ተከተሎች እና አሰራሩን ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::
2. በመቀጠል በነጥብ “ሐ” እና “መ” መካከል ያለውን የመሬት ላይ ርቀት ከፈለጋችሁ በኋላ የተከተላችኋቸውን ቅደም ተከተሎች እና አሰራሩን ለክፍል ተማሪዎች አቅቡ::
3. በነጥብ “ሀ” እና “ለ” መካከል ያለው የመሬት ላይ ርቀት በነጥብ “ሐ” እና “መ” መካከል ካለው የመሬት ላይ ርቀት በምን እንደሚለይ አብራሩ::




ምስል፡ 13 ቀጥታ እና ጉብጥ መስመር

## ለ) በካርታ ላይ መደበኛ ቅርፅ ያላቸውን ምስሎች ስፋት መፈለግ

### ተግባር-41

1. ተማሪዎች! መደበኛ ቅርፅ ያላቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ካሬ፣ ሬክታንግል፣ ጎነሶስት እና ክብ መደበኛ ቅርፅ ያላቸው ሲሆኑ የስፋት አፈላለጋቸው ለቅርጻቸው ተስማሚ የሆነን የስፋት ማግኛ ሂሳባዊ ቀመር በመጠቀም ነው::

ምሳሌ፡

ካሬ = ርxር=ር$^2$


ሬክታንግል = ወxር

ክብ = πሬ$^2$

ጎነሶስት = ½ርxቁ

ር= ርዝመት ወ= ወርድ ቁ= ቁመት ሬ= ሬዲየስ π = 3.14

የሚከተሉትን የመደበኛ ቅርጽ ስፋት ለማግኘት የእያንዳንዳቸውን የአሰራር ቅደም ተከተል መከተል ተገቢነው::




ምስል፡ 14 መደበኛ ቅርጾች

**ምሳሌ** 1፡ የሬክታንግል(ሀ) ስፋት ለማስላት የሚከተለውን ቅደም ተከተል መከተል ያስፈልጋል::

1. የካርታውን መስፈርት ወደ ዐረፍተ ነገር መስፈርት መቀየር ያስፈልጋል:: ይህም 200000 ሳ.ሜ ወደ ኪ.ሜ ሲቀየር

1ኪ.ሜ=100000 ሳ.ሜ ከሆነ

? =200000 ሳ.ሜ

ስለዚህ የካርታው የዐረፍተ ነገር መስፈርት 1ሳ.ሜ ለ2 ኪ.ሜ ይሆናል ማለት ነው::

2. የሬክታንግሉ ርዝመት(ር) ወደ መሬት ርቀት መቀየር አለበት

ይህም ር=4 ሳ.ሜ ሲሆን የካርታው መስፈርት 1ሳ.ሜ= 2ኪ.ሜ ከሆነ

4ሳ.ሜ =?

ስለዚህ ር= 8ኪ.ሜ ነው

3. የሬክታንግሉ ወርድ(ወ) ወደ መሬት ርቀት መቀየር አለበት

ይህም ወ= 2 ሳ.ሜ ሲሆን የካርታው መስፈርት 1ሳ.ሜ= 2ኪ.ሜ ከሆነ

2ሳ.ሜ =?

ስለዚህ ወ= 4ኪ.ሜ ነው

4. ስለዚህ የሬክታንግሉ ስፋት= ርxወ

ስፋት= 8ኪ.ሜ x 4ኪ.ሜ= 32 ኪ.ሜ$^2$

ምሳሌ 2፡ የክብ(ለ) ስፋት ለማግኘት የአሰራር ቅደም ተከተል መከተል ተገቢነው።

1. የካርታውን መስፈርት ወደ ዐረፍተ ነገር መስፈርት መቀየር ያስፈልጋል። ይህም 200000 ሳ.ሜ ወደ ኪ.ሜ ሲቀየር

1ኪ.ሜ=100000 ሳ.ሜ ከሆነ

? =200000 ሳ.ሜ

ስለዚህ የካርታው የዐረፍተ ነገርመስፈርት 1ሳ.ሜ ለ2 ኪ.ሜ ይሆናል ማለት ነው።

2. የክቡ ሬዲየስ ርዝመት(ሬ) ወደ መሬት ርቀት መቀየር አለበት

ይህም ሬ= 3 ሳ.ሜ ሲሆን የካርታው መስፈርት 1ሳ.ሜ= 2ኪ.ሜ ከሆነ

3ሳ.ሜ =?

ስለዚህ ሬ= 6ኪ.ሜ ነው።

3. ስለዚህ የክቡ ስፋት= ∏ሬ$^2$


ስፋት= 3.14(6ኪ.ሜ)$^2$

=3.14x36ኪ.ሜ$^2$

= 113ኪ.ሜ$^2$

*ተግባር-42*

1. የአንድ ካርታ መስፈርት 1:100000 ሲሆን የካርታው የካሬ ርዝመት 2 ሳ.ሜ ቢሆን ስፋቱ ስንት ይሆናል?
2. ተማሪዎች! የቤታችሁን ወርድ እና ርዝመት በሜትር በመለካት እና የካርታ ሚዛን 1:100000 በመጠቀም ወርድ እና ቁመቱን በወረቀት ላይ ካስቀመጣችሁ በኋላ ስፋቱን አስሉ::
3. በሚከተለው ካርታ የሀ፣ የለ፣ የሐ እና የመን ምስሎች ማስመሪያን በመጠቀም የመሬት ላይ ስፋታቸውን አስሉ::




ምስል-15 መደበኛ ቅርጽያላቸው ምስሎች


## 1.4.4. ዓለማቀፋዊ መገኛ ስርዓት (Global Positioning System )

*ተግባር-43*

1. ተማሪዎች! ስለዓለማቀፋዊ መገኛ ስርዓት ታውቃላችሁ? እስኪ የምትችሉትን ያህል ግለፁ::

ዓለማቀፋዊ መገኛ ስርዓት(ጂፒኤስ) አንድን አካል በመሬት ላይ የሚገኝበትን ትክክለኛ ቦታ በማንኛውም ጊዜ፣ ስፍራና የአየር ሁኔታ የሚያሳይ ብቸኛው ስርአት ነው:: ይህ ስርአት ሳተላይቶችን፣ መረጃ ተቀባዮችን(Receivers) እና የኮምፒውተር ሶፍት ዌሮችን አካትቶ የያዘ ነው:: ዓለማቀፋዊ መገኛ ስርዓት ሳተላይቶችን በመጠቀም የትኛውንም አስቸጋሪ የአለም ተደራሽ ያልሆኑ ቦታዎች **ለምሳሌ:** ተራሮች፣ በረሃዎች፣ ውቅያኖሶች እና ሌሎችን በትክክል ያሳያል:: የመጀመሪያው ዓለማቀፋዊ መገኛ ስርዓት ናቫስታር መገኛ ስርዓት ይባላል:: ይህም በመጀመሪያ በአሜሪካ የመከላከያ ሚኒስቴር ለውትድርና አገልግሎት የተሰራ ነው ምስል 16ን ተመልከቱ::

ተማሪዎች! ምስል 15ን ተመልከቱ እና የተመለከታችውትን ለመምህራቸው ግለጹ::




ምስል-15 ዓለማቀፋዊ መገኛ ስርዓት(GPS)




ምስል -16. ናቫስታር መገኛ ስርዓት

ተማሪዎች! በስማርት ስልክ የGoogle earth መተግበሪያ በመጠቀም የአለምን ካርታ በቀጥታ በማምጣት የተኛውንም የአለማችን አገሮች፣ ከተሞች፣ መንገዶች፣ ታዋቂ ቦታዎች፣ ከዋና ከተማቸው ያላቸውን ርቀት እና አቅጣጫ ማወቅ ትችላላቸሁ::

## የዓለማቀፋዊ መገኛ ስርዓት (ጂፒኤስ) ዋና ዋና ጥቅሞች

### 1. አሰሳ

ጂፒኤስ በጣም የተለመደው አጠቃቀም በአሰሳ ስርዓቶች ውስጥ ሲሆን አቅጣጫዎችንም በቅጽበት ለማሳየት ያስችላል::

## 2.ዝቅተኛ ዋጋ

ጂፒኤስ የሚጠቀሙ እንደ ጎግል ካርታዎች ያሉ የስማርት ስልኮች መተግበሪያዎችም በተለምዶ ነፃ ናቸው።

## 3. ወንጀል እና ደህንነት

ጂፒኤስ በሕግ አስከባሪ አካላት ወንጀለኞችን ወይም አሸባሪዎችን ለመከታተል እና ስርቆትን ለመከላከል ጥቅም ላይ ይውላል።

## 4. ለመጠቀም ቀላል

ጂፒኤስን ለመጠቀም በጣም ቀላል እና አነስተኛ ችሎታ ብቻ ይጠይቃል፣

## 5. የአሰሪ ክትትል

አሰሪዎች የጂፒኤስ ክትትልን በመጠቀም ሾፌሮቻቸው ፈጣኑን መንገድ በመከተል እና ከመንገድ ላይ በመውጣት ጊዜን ወይም ነዳጅን እንዳያባክኑ እንዲሁም የፍጥነት ገደቦችን በመከተል የኃላፊነት ባህሪ እንደሚያሳዩ ለማረጋገጥ ያስችላል።

## 6. ደህንነት

ጂፒኤስ መከታተያ ልጆቻቸውን ለመከታተል እና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ወላጆች ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

## 7. የጎረቤት ፍለጋ

ጂፒኤስ በዙሪያው ላለው አካባቢ መረጃ ይሰጣል ወይም ይጠቁማል።

## 8. የትራፊክ እና የአየር ሁኔታ ማንቂያዎች

ስለ ጂፒኤስ ካሉት ታላላቅ ተግባራት አንዱ ሁሉም ነገር በትክክለኛ ሰዓት ውስጥ የሚከናወን መሆኑ ነው። ይህ ማለት የትራፊክ አደጋ ካለ፣ ወይም ሌላ አይነት ወደ ፊት የሚቆይ ሁኔታ ከሆነ፣ ወይም ከባድ የአየር ሁኔታ ወደ ሚከሰትበት አካባቢ እየቀረበ ከሆነ ማሳወቂያ ሊያደርስ ይችላል። ይህም የጉዞ ጊዜን ማሳጠር ብቻ ሳይሆን ደህንነትንም ያሻሽላል።

## ማጠቃለያ

- በስነ-መሬት ጥናት እይታ አህጉራት ሰፋፊ እና ደረቅ መሬቶችን ወይም የብሶችን ብቻ የያዙ ሳይሆን ስስ የሆነ ውሃ የሸፈነውን አህጉራዊ ሰጥንጌን (Continental shelf) እና በዚሁ ክፍል ላይ ያሉ ደሴቶችን እንደሚያካትቱ ይገለፃል:: በአለም ላይ ሰባት አህጉሮች አሉ:: እነርሱም እስያ፣ አፍሪካ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ፣ አንታርክቲካ፣ አውሮፓ እና አውስትራሊያ ናቸው::
- በገጸምድር ላይ የሚገኙትን የተለያዩ ምድረ ቅርጾችን የሚሰሩ ኃይሎች ሁለት ዓይነት ናቸው:: ኃይሎቹ ውስጠ-መጥ (ውስጣዊ) እና ውጪ-መጥ(ውጫዊ) ኃይሎች በመባል ይታወቃሉ:: ውስጠ-መጥ ኃይሎች ከመሬት ውስጥ የሚመነጩ ሲሆኑ የጎነት እና ገሞራዊ ሂደቶችን ያከናውናሉ:: የጎነት ሂደቶች የመሬት ቅራፎን በመቀልበስ፣ በመሰንጠቅ፣ በማዛነፍና ወደ ላይ በማግዘፍ የተለያዩ ምድረ ቅርጾችን ይፈጥራሉ:: እነዚህ ሂደቶች የቅልብሽ፣ የዝንፈትና የማግዘፍ ሂደቶችን ያካትታሉ::
- የውጪ መጥ ኃይሎች ከመሬት ውጭ የሚመነጩ ሲሆን በዋናነት በአየር ቅጥ ተጽእኖ አማካኝነት የሚከሰቱ ናቸው:: ውጪ መጥ ኃይሎች አለቶችን በመፈርፈር፣ በማጓጓዝና በማከማቸት የተለያዩ ምድረ ቅርጾችን ይሰራሉ:: እነዚህ ኃይሎች በአጠቃላይ የድርጀታ ኃይሎች ይባላሉ:: የድርጀታ ኃይሎች ከፀሀይ ኃይላቸውን ካገኙ በኋላ ተግባራቸውን በተንቀሳቃሽ ወኪሎች ማለተም በወራጅ ውሃ፣ በነፋስ፣ በአንግብጓቢ በረድ፣ በቀላይ ሞገድና በመሬት ውስጥ ወይም በከርሰ ምድር ውሃ ያከናውናሉ::
- የመሬት ከባቢ አየር 78% ናይትሮጅን (N)፣ 21% ኦክስጅን ($O_2$) እና 0.9% አርገን (Ar) ሲሆን እንዱሁም 0.03 % ካርቦንዳይኦክሳይድ ($Co_2$) እና ሌሎችንም ጋዞች የያዘ ነው:: የአየር ጠባይ ማለት በአንድ በተወሰነ ጠባብ የቦታ ክልል ውስጥ ለአጭር ጊዜ የሚከሰት የአየር ሁኔታ ነው::

- የአየር ጠባይ ተለዋዋጭ ነው:: የአየር ንብረት በሌላ መልኩ በአንድ በተወሰነ ሰፊ የቦታ ክልል ውስጥ ለረዥም ጊዜ የሚከሰት የአየር ሁኔታ ነው:: የአየር ንብረት በአንፃራዊ መልኩ ቋሚ ነው:: የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት ዋና ዋና ይዘቶች ልከሙቀት፣ እረጥበት ጥዱፍ ውርድ፣ ውሃ ዝለት፣ ነፋስና የአየር ግፊት ናቸው:: የአየር ጠባይ እና የአየር ንብረት ዋና ዋና ተቆጣጣሪዎች ኬክሮስ፣ ከፍታ፣ ከባህር ያለው እርቀት፣ ነፋስና የአየር ግፊት እና የተራራ እግድ ናቸው:: በመጨረሻም የካርታ መስፈርት፣ ርቀትና ስፋትን ማስላት እንዲሁም ስለዓለማቀፋዊ መገኛ ስርዓት ተብራርቷል::

## ክለሳ ጥያቄዎች

*ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን እውነት ወይም ትክክል ያልሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ::*

1. ቅልብሽ እና ዝንፈት ውስጣዊ የመሬት ገጽ ለዋጭ ሀይሎች ናቸው::
2. አፍሪካ በቆዳ ስፋት እና በህዝብ ብዛት ከአለም የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘች አህጉር ናት::
3. በውስጣዊ ሀይሎች የተቀረጹትን ውጫዊ የመሬት ገጽታዎች የሚያስተካክሉት ውጫዊ ሀይሎች ናቸው::
4. በዝቁ ህዋ ከፍታ ሲጨምር የሙቀት መጠን እየቀነሰ የሚሄድበት የከባቢ አየር ንጣፍ ነው::
5. ኤርታሌ ንቅ እሳተ ገሞራ ሲሆን በአፋር ብሄራዊ ክልል ውስጥ ይገኛል::

*ለ) የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በተስማሚ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::*

1. አፍሪካን በስተምዕራብ ______በስተምስራቅ ________ያዋስኑታል::
2. ለምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ መፈጠር ዋናው ምክንያት __________________ነው::
3. ወደ ገጸ ምድር የሚወጣው የቀለጠ አለት ______________________ ይባላል::
4. በመሬት ውስጥ የቀለጠ አለት ______________________ ይባላል::

*ሐ) የተግባር ስራ*

1. የሚከተሉትን የክፍልፋይ መስፈርት ወደ ዓረፍተ ነገር መስፈርት ቀይሩ::

   ሀ) 1: 280,000 ለ) 1: 1,000,000

   ሐ) 1:60,000 መ) 1:90,000

2. የሚከተሉትን የዓረፍተ ነገር መስፈርቶች ወደ ክፍልፋይ መስፈርት ቀይሩ::

   ሀ) 1ሳ.ሜ ለ 30ኪ.ሜ ለ) 20ሳ.ሜ ለ300ኪ.ሜ

   ሐ) 10ሳ.ሜ ለ200ኪ.ሜ

3. የሚከተሉትን የአረፍተ ነገር መስፈርት ወደ መስመራዊ መስፈርት ቀይሩ::

   ሀ) 1ሳ.ሜ ለ 30ኪ.ሜ ለ) 20ሳ.ሜ ለ 300ኪ.ሜ

   ሐ) 10ሳ.ሜ ለ 200ኪ.ሜ

4. ዕለታዊና ወቅታዊ የአየር ጠባይ መለዋወጥ የሚያስከትሉትን ጉዳት እና ሚሰጡትን ጥቅም ወላጆቻችሁን ወይም አዋቂ ሰዎችን በመጠየቅ እና መረጃዎችን በግል በማሰባሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍሉ ተማሪዎች አቅርቡ::

5. ውድ ተማሪዎች የአየር ንብረት እና የሰው ልጅ ያላቸውን ቁርኝት በጥንድ በመሆን ተወያዩ:: (ፍንጭ: የአየር ንብረት በአለባበስ፣ በአመጋገብ፣ በቤት አሠራር፣ በእርሻ እና በመዣሰሉት ላይ ያለውን ልዩነት ተወያይታችሁ ለክፍል አቅርቡ)

6. የአየር ንብረት ይዘቶች በጊዜና በቦታ ይለያያሉ? ልዩነታቸው ከምን የሚመነጭ ይመስላችኋል?

7. አንዱ ቀን ሞቃት ሲሆን ሌላው ቀን ቀዝቀዝ ያለ ሊሆን ይችላል:: በአንደኛው ቀን ዝናብ ቢጥል በሌላው ቀን ደረቅ ሁኔታ ይኖራል:: ይህ የሚሆንበት በምን ምክንያት ሊሆን ይችላል ብላችው ታስባላችሁ?

## የቁልፍ ቃላት ፍች

- ✍ አህጉር፡- ትልቅ፣ ያልተከፋፈለ ነገር ግን ከሌሎች አህጉራት የተወሰነ ስፋት ባለው ውሃ የተለየ ግዙፍ ምድር ነው።
- ✍ ውቅያኖስ፡- እጅግ ሰፊ እና የተነጣለለ የውሀ አካል ነው።
- ✍ ደሴት፡- ሙሉ በሙሉ በውሃ የተከበበ የመሬት አካል ነው።
- ✍ ውሰጠ-መጥ፡- ከመሬት ውስጥ የሚመነጩ ሲሆን የጎነት እና ገሞራዊ ሂደቶችን ያከናውናሉ።
- ✍ ውጨ-መጥ፡- ከመሬት ውጭ የሚመነጩ ሲሆን በዋናነት በአየር ንብረት ተጽእኖ አማካኝነት የሚከሰቱ ናቸው።
- ✍ ገሞራዊ ትፍ፡- ወደ መሬት ገጽ ሽቅብ ተወርውሮ የሚወጣ የቀለጠ አለት ነው።
- ✍ ቅልብሽ፡- ከመሬት ውስጥ የሚመነጨው ሀይል በውጨኛው ቅርፊተ መሬት ላይ የሚገኙትን አለቶች ሲቀለብስ የሚፈጠር ነው።
- ✍ ዝንፈት፡- የመሬት ንጥነጣዊ እንቅስቃሴ በሚፈጥረው ግፊት የተነሳ አለቶች ከተለያየ አቅጣጫ ወደ አንድ አቅጣጫ ሲገፉ የሚፈጠር ነው።
- ✍ ከባቢ አየር፡- መሬትን እንደ ብርድ ሸፍኖ የሚገኝ የተያዩ ጋዞች ክምችት ነው።
- ✍ ስሬ ህዋ፡- የታችኛው የከባቢ አየር ንጣፍ ነው።
- ✍ ዝቄ ህዋ፡- ከስሬ ህዋ ቀጠሎ የሚገኘው 2ኛው የከባቢ አየር ንጣፍ ነው።
- ✍ ማዕካለዊ ህዋ፡- በዝቄ እና በሙቄ ህዋ መካከል የሚገኝ የከባቢ አየር ንጣፍ ሲሆን ቀዝቃዛው የከባቢ አየር ንጣፍ በመባል የታወቃል።

- ✍ **ሙቁ ህዋ፡-** የመጨረሻው የከባቢ አየር ንጣፍ ሲሆን በጣም ሞቃታማው የከባቢ አየር ንጣፍ ነው።
- ✍ **የአየር ጠባይ፡-** የእለት ከእለተ የአየር ሁኔታዎች ከስተት እና በአጭር ጊዜ ሲጠናቀሩ የሚፈጠር ነው።
- ✍ **የአየር ንብረት፡-** የአየር ሁነታዎች ለረዥም ጊዜ ሲጠናቀሩ የሚፈጠር ነው።
- ✍ **የካርታ መስፈርት፡-** በመሬት ላይ ያለን የአንድን ቦታ ገጽታ በካርታ ላይ ለክተን ለማስቀመጥ የምንጠቀምበት ዘዴ ነው።
- ✍ **የካርታ ርቀት፡-** የካረታን ርቀት በማስላት በመሬት ላይ ያለ ርቀትን የምናገኝበት መንገድ ነው።

# ምዕራፍ- 2

# ስነ ሕዝብ እና የማህበረ-ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

## መግቢያ

በዚህ መዕራፍ ውስጥ የባህል ምንነት እና ብዝሀነት፣ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች፣ ንግድ እና ገበያ እንዲሁም የመንግሰት ገቢ እና ግብር ምንነትን በመዳሰስ ለተማሪዎች ለማስተዋወቅ አካቶ የያዘ ነው:: የባህል ምንነት እና ብዝሀነት በተመለከተ የባህል ትርጉም፤ ዋና ዋና የባህል ይዘቶችን እንደ ቋንቋ፣ ሀይማኖት እና የስው ልጅ ሰው ዘር፣ ዓለም አቀፋዊነት እና የማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶች ተከታታይ ለውጦች ተካተዋል:: በሁለተኛ ደረጃ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ማለትም የመጀመሪያ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ምጣኔ ሀብታዊ ተግባራት ተዳሰዋል:: በሶስተኛ ደረጃ በዚሁ በምዕራፍ ውስጥ የተካተተው ንግድ እና ገበያ ሲሆኑ የንግድ እና ገበያ ፅንሰ ሀሳብ፣ የንግድ ዓይነቶች እና ጠቀሜታዎች፣ አቅርቦትና ፍላጎት፣ የግብይት ዋና ተዋናዮች፣ የውድድር ግብይት ሃሳብ እና የሸማቾች መብት ጥሰት ተብራርተዋል:: በአራተኛ ደረጃ በዘሁ ምዕራፍ ውሰጥ የመንግሰት ገቢ እና ግብር የሚያትት ሲሆን የመንግሰት ገቢ የሚያስገኛቸው ጥቅሞች በኢትዮጵያ ተካተዋል::

### ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት:

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦**

- የባህል ምንነት እና ብዝሀነትን ታብራራላችሁ::
- አለማቀፋዊነትን፣ የማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶች ታደንቃላችሁ::
- የመጀመሪያ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን እና ውጤታቸውን ታወዳድራላችሁ::
- የሁለተኛ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን እና ውጤታቸውን ትተነትናላችሁ::

- ☞ *ሶስተኛ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን ከመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ጋር በምን እንደሚለያዩ ታነጻጽራላችሁ፡፡*
- ☞ *የመንግስት ገቢ እና ግብር አተገባበርን ትገመግማላችሁ፡፡*
- ☞ *የንግድ እና ገበያ ፅንሰ ሀሳብን ታብራራላችሁ፡፡*
- ☞ *የንግድ ዓይነቶችን በመዘርዝር ገቢና ወጪን ታሳያላችሁ፡፡*
- ☞ *የንግድ ዓይነቶችን እና ጠቀሜታዎችን ታወዳድራላችሁ፡፡*
- ☞ *የግብይት አቅርቦት፣ ፍላጎትን እና የግብይት ዋና ዋና ተዋናዮችን ትተነትናላችሁ፡፡*
- ☞ *በየአመቱ መጨረሻ መንግስት ከግብርና ቀረጥ የሚያስገኘውን ገቢ ከሚያወጣው ወጭ ጋር ታወዳድራላችሁ፡፡*

## 2.1. የባህል ምንነት እና ብዝሀነት

**ቁልፍ ቃላት፡**

- ☞ ባህል
- ☞ ቋንቋ
- ☞ ሀይማኖት
- ☞ ምልክት
- ☞ ቁሳዊ ባህል
- ☞ መንፈሳዊ ባህል

### 2.1.1. የባህል ምንነት እና ዋና ዋና ይዘቶች

***ተግባር-1***

1. ተማሪዎች! የምትናገሩት ቋንቋ ለምን ይጠቅማል?

ባህል በጥቅሉ የአንድ ማህበረሰብ ወይም ህዝብ የአኗኗር ዘይቤ ነው ተብሎ ሊገለጽ ይቻላል፡፡ ከዚህ ትርጉም አንጻር ባህል የማይገለጽባቸው የሰው ልጅ አሰራሮች፣ ባህሪዎች እና ልምዶች አሉ ማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ባህል ውበትን፣ ዕድገትን፣ ልምድን፣ ፈጠራን፣ ቋንቋን፣ ጥበብን እና ትውፊቶችን አጠቃሎ የሚይዝ ሰፊ ፅንስ ሀሣብ ነው፡፡ በመሆኑም በተፈጥሮ የሚገኝ ሳይሆን የሰው ልጆች በታሪክ

ሂደት በልምድ ያካበቱት የአሰራር፣ የአኗኗር፣ የአነጋገር እና የተሰሩ ቁሳዊ ነገሮች እንዲሁም መንፈሳዊ እሴቶችን በመስራትና በመማር የሚገኝ ነው፡፡

ባህል የሰው ልጆች የሥራና የልምድ ሀብት ነው፡፡ የጥንት ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ባደረጉት ትግል በሂደት መሳሪያ በመሥራትና በመጠቀም የምግብ ደህንነት ዋስትናቸውን እያጠናከሩ መጥተዋል፡፡ በመሆኑም ባህል እያደገ እና እየሰፋ የሚሄድ ነው፡፡ የባህል ዋና ዋና ይዘቶች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

## 1. ቋንቋ (language)

ሰዎች ሁሉ ለመኖር መግባባት መነጋገር አለባቸው፡፡ ቋንቋ ለሰው ልጆች ዕድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርገ መግባቢያ መስሪያ ነው፡፡ ነገር ግን በአለም ላይ ያሉ ሰዎች አንድ ቋንቋ አይናገሩም፡፡ ቋንቋዎች ባላቸው ርቀትና ቅርበት እየታዩና እየተገመገሙ በአንድ የቋንቋ ቤተሰብ ይመደባሉ፡፡ በመሆኑም ቋንቋ አስተሳሰብን፣ ዕድገትን እና ልምድን ለማስተላለፍ እና በሰራ ላይ ለማዋል ይረዳል፡፡ ስለሆነም ቋንቋ የጋራ እምነት፣ አሰተሳሰብ እና ስሜት የባህል መሰረቶች ናቸው፡፡ እነዚህም የተፈጠሩት እና ሊተሳሰሩና ሊኖሩ የቻሉት በቋንቋ አማካኝነት ነው፡፡ ከዚህም በላይ ቋንቋ ዋና የባህል ማስተላለፊያ መሳሪያ ነው፡፡ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ የሚተላለፈው ልምድ እውቀትና ቅርስ በቋንቋ አማካኝነት ነው፡፡ በእርግጥ አንዳንድ ቋንቋዎች የመጻፊያ ቋንቋ አይደለም፡፡ ቋንቋን በጽሑፍ ማስቀመጥ መጀመር ደግሞ የሰውን ልጅ ስልጣኔ በከፍተኛ ሁኔታ አሳድጓል፡፡ ሀሳብን በጽሑፍ ማስቀመጥና መግለፅ የተጀመረው ከ 5000 አመታት በፊት ነው፡፡

### ተግባር-2

1. ተማሪዎች! ወደ ቤተመጽሐፍት በመሄድ ወይም ታዋቂ ሰዎችን በግል በመጠየቅ ቋንቋ ለባህል ዕድገት ያለውን አስተዋጽኦ ትክክለኛ መረጃ በማሰባሰብ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡
2. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ስንት አይነት ቋንቋ ይነገራል? እናንተስ ስንት አይነት ቋንቋ ትናገራላችሁ? ከአንድ በላይ ቋንቋ መናገር ምን ጥቅም አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?

## 2. ባህላዊ እሴቶች (Cultural values)

**ተግባር-3**

1. ተማሪዎች! የአካባቢችሁ ማህበረሰብ በተለያዩ አወንታዊ ጉዳዮች ላይ ያለውን መረዳዳት እና መተጋገዝ አብራሩ።

ባህላዊ እሴቶች (Culture values) ማለት በአንድ ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ውስጥ ጥሩና መጥፎ፣ ቆንጆ እና መልከ ጥፉ ብሎ የሚለይበት የአስተሳሰብና የልምድ መሰረት ነው። በዚህም ባህላዊ እሴቶች በአንዱ ጥሩ እሴት ነው የሚባል በሌላ የማይኖርበት ወይም መጥፎ የሚሆንበት ሁኔታ ይኖራል። ነገር ግን ሁሉም ባህሎች የራሳቸው የሆነ አንዳንድ ጊዜ ተመሳሳይ በሌላ ጊዜ የሚለያዩ ባህላዊ እሴቶች አሉት። በእርግጥ አነዚህ እሴቶች በተለያዩ ባህሎች በተለያየ ሁኔታ ባህላዊ መርህ ሆነው በእያንዳንዱ ሰብአዊ ሁኔታና ህይወት የሚገለጹና የሚታዩ ናቸው። ማንም ሰው ከባህሉ የሚወርሰው ስለራሱና ስለአለም የተለየ አመለካከት አለው። ስለዚህ የሰው ልጆች ሲያድጉ ከቤተሰባቸው፣ ከት/ቤት እና ከሀይማኖት ተቋሞች እንዴት ማሰብና መፈፀም እንዳለባቸው ይማራሉ።

**ተግባር-4**

1. ተማሪዎች! የአካባቢያችሁን ባህላዊ እሴት ከሌላው አካባቢ ባህላዊ እሴት ጋር በማነጻጸር ውይይት አድርጉ ከዚያም ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

## 3. ምልክቶች (symbols)

**ተግባር-5**

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ በሀይማኖት ተቋማት፣ በህብረተሰቡ ባህል ማለትም አለባበስ፣ ሀይማኖታዊ በዓላት አከባበር እና በቤት አሰራር ላይ የሚተገበሩ ምልክቶች የምታውቁትን ተናገሩ።

እያንዳንዱ ባህል ምልክት አለው። ምልክት ማለት የተለያየ ትርጉም የያዘ ሆኖ በዚያ ህብረተሰብ ባህል የታወቀ አካል ወይም ድምፅ ወይም ምስል ሁኖ አንድን ነገር ሊወክል የሚችል ማለት ነው። ድምፅ፣ ምስል፣ አለባበስ፣ እምነት እና ሌሎች

ሰባዊ ድረጊቶች ሁሉ የምልክት ተምሳሌቶች ናቸው:: **ለምሳሌ:** በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ እልልልል....ማለት ደስታ መኖሩን ሲያመለክት፣ እሪሪ...እሪሪ...ወይም ኡ...ኡ...ኡ...ሀዘን ወይም ችግር መኖሩን ያመላክታሉ::

*ተግባር-6*

1. በምትኖሩበት አካባቢ የተለያዩ ክስተቶችን ለመወከል ህብረተሰቡ የሚጠቀማቸውን የድምፅ፣ የምስል፣ የአለባበስ ምልክቶችን በመዘርዘር ለእያንዳንዱ ማብራሪያ ስጡ::

የምልከት ትርጉም የአንድ ባህል መሰረት በመሆኑ ለተጨባጭ ማህበራዊ ሁኔታ ወሳኝ ነው:: የካህናት፣ የክርስትና፣ የእስልምና፣ የመንግሥት፣ የአገር እና የሌሎችም ሁሉ ምልክቶች አላቸው:: ምልክቶች ከባህል ባህል ይለያያሉ:: እነዚህ ባህላዊ ምልክቶች ሁሉ በጊዜ ሂደት የሚለወጡ እና የሚሻሻሉ ናቸው:: በአጠቃላይ ምልክቶች የሰው ልጅ የራሳቸውን ህይወት ትርጉም የሚገልጹበትና የሚጠቀሙበት ባህላዊ ዘዴ ነው:: በመሆኑም የሰው ህይወት ያለምልከት ማሰብ አስቸጋሪ ነው ማለት ይቻላል::

## 4. ሀይማኖቶች

ሀይማኖት የባህል ሌላው አካል ወይም ይዘት ነው:: ሀይማኖት የእምነትና የአመለካከት ነጻነት ማለት ነው:: ሰው የፈለገውን ሀይማኖት ወይም እምነት የመከተል እና የመስበክ ነጻነት አለው:: ስለዚህ ሰው የፈለገውን እምነት ይከተላል:: ማንም ሰው ከፍላጎቱ ውጭ የትኛውንም ሀይማኖት ወይም አምልኮ ለመከተል አይገደድም::

*ተግባር-7*

1. ተማሪዎች! ሀይማኖት የሰው ልጅ አብሮ የመኖር እና የመረዳዳት እሴትን ከማጎልበት አንፃር ያለውን ሚና ግለፁ::

## 5. የሰው ዘር አመጣጥ

### ተግባር-8

1. ተማሪዎች! የሰው ዘር አመጣጥን ለመረዳት አለማዊ ወይም ሀይማኖታዊ መጽሐፍትን አንብባችሁ ወይም ሰዎችን ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ የምትችሉትን ተናገሩ::

የሰው ልጅ አመጣጡ ሲታይ በሁለት ዋና ዋና ንድፈ ሀሳቦች ተከፍሎ ሊታይ ይቻላል:: እነዚህም፦

1. የስነ-ፍጥረት ንድፈ ሀሳብ (creationist theory) እና
2. የአዝጋሚ ለውጥ ንድፈ ሀሳብ (Evolutionary change theory)

### 1. የስነ-ፍጥረት ንድፈ-ሃሳብ

ይህ ንድፈ-ሃሳብ መለኮታዊ ወይም ሀይማኖታዊ ነው:: የሚያራምደው ሀሳብ ሰዎች የተፈጠሩት አሁን የያዙትን መልክና ቁመና እንደያዙ በፈጣሪ ነው ብሎ ይገልጻል:: ከዚህም በላይ የሰው ልጅ አኗኗር፣ ቋንቋ እንዲሁም በአጠቃላይ ሰብአዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ሁሉ ከላይ የተፈጠሩ ናቸው ብሎ ያምናል:: የንድፈ ሀሳቡ መሰረት ሀይማኖታዊ በመሆኑ ይህን አስተሳሰብ የሚቀበለው በመመራመር እና በመፈተሽ ሳይሆን በማመን ብቻ ነው::

### 2. የአዝጋሚ ለውጥ ንድፈ-ሃሳብ

ይህ ንድፈሃሳብ የሰው ልጆች አሁን ያላቸውን መልክና ቁመና የያዙት በጊዜ ሂደት (በአዝጋሚ ለውጥ) ከሌሎች እንስሳት በመለየት የመጣ ነው ብለው ያምናሉ:: የሰው ልጅ እንዴት ከሌሎች እንስሳት በጊዜ ብዛት እየተለያየ አሁን ያለውን መልክና ቅርፅ እንደያዘ ያስረዳል:: በዋነኝነት በምርምርና በመፈተሽ የተደገፈ ነው::

### ተግባር-9

1. ተማሪዎች! በሰው ዘር አመጣጥ ንድፈ ሀሳቦች ላይ በመወያየት በምትደግፉት ንድፈ ሀሳብ ላይ ማብራሪያ ስጡ::

መልካም! ተማሪዎች በጥያቄው እንደተከራከራችሁና የበኩላችሁን ግንዛቤ እንደያዛችሁ ይታመናል:: ከላይ የቀረቡት ንድፈ ሀሳቦች በአሁኑ ጊዜ ስለሰው ልጅ አፈጣጠር ተቀባይነት ያገኙ ናቸው:: ነገር ግን ፍጹም የተዋጣላቸው ስራዎች ያልሆኑ በመሆኑ እናንተና የወደፊቱ ትውልድ የእውቀቱን ክፍተት የመሙላት ሀላፊነት እንዳለባችሁ መረዳት ያስፈልጋል:: በአጠቃላይ የፍጥረትም ሆነ የአዝጋሚ ለውጥ ንድፈ ሀሳቦች የሰው ልጅ ማህበራዊ መሆኑን ይቀበሉታል:: የሰው ማህበራዊ ፍጡር በመሆኑ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የጋራ ባህል፣ ቋንቋ፣ አሰራር፣ አመጋገብ እና መስተዳድር ይኖራቸዋል ማለት ነው::

## ሀ) ባህል የሚያካትታቸው ተግባራት

### ተግባር-10

1. ተማሪዎች! የአካባቢያችሁ ማህበረሰብ በአለባበስ እና በአመጋገብ ከሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች እንደሚለዩ ታውቃላችሁ? እንዴት?

መልካም! ባህል በአንድ በተወሰነ አካባቢ ሰዎች እንዴት መኖር እንዳለባቸው፣ ምን ዓይነት ልብስ መልበስ እንዳለባቸው፣ የአካባቢያቸውን ሀበት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው፣ ምን ዓይነት የመገልገያ መሣሪያ መጠቀም እንዳለባቸው ወዘተ ነው:: ከዚህ አንጻር ባህል ሲታይ የማንነት መገለጫ ነው::

ሀገሮች፣ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ጐሣዎች አንዳንድ ጊዜም የተወሰኑ አካባቢዎች የራሳቸው ባህልና ባህላዊ ስርዓት ይኖራቸዋል:: ከዚህም በላይ እያንዳንዱ ቤተሰብ የራሱ የሆነ የባህል ልምድ ሊኖረው ይቻላል:: ነጋዴዎች፣ ማህበራዊ ቡድኖች፣ የሙያ ሰዎች ሁሉ የራሳቸው የሆነ የባህል ልምድ ሊኖራቸው ይችላል::

### ተግባር-11

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ ስለነጋዴዎች የባህል ልምድ ትክክለኛ መረጃ በማሰባሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::

## ለ) የባህል አይነቶች

### ተግባር-12

1. ተማሪዎች! የሰው ልጅ አስተሳስብ እና አመለካከት መንፈሳዊ ባህል ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? እንዴት?

ባህል በሁለት መሰረታዊ ጉዳዩች ተከፍሎ ሊታይ ይቻላል:: ይህም ቁሳዊ ባህልና ( material culture ) መንፈሳዊ ባህል (spiritual Culture) ናቸው:: ቁሳዊ ባህል ማለት የሰው ልጆች በታሪክ ሂደት የሰሯቸው፣ የተጠቀሙባቸው እና የሚጠቀሙባቸው ማናቸውም ቁሳዊ ነገሮች ወይም እቃዎች ማለት ነው:: ምሳሌ፡ የእርሻ መሳሪያዎች፣ የቤት መስሪያ ዕቃዎችና አሰራሮች፣ የምግብ እቃዎች አሰራርና አጠቃቀም፣ የልብስ አሰራርና አይነት የመሳሰሉት ሁሉ በቁሳዊ ባህል ስር የሚመደቡ ናቸው:: እነዚህ በአይን የሚታዩና በእጅ የሚዳሰሱ ሃብቶች ናቸው:: መንፈሳዊ ባህል ሊዳሰሱና ሊጨበጡ የማይችሉ ነገር ግን በሰዎች ክንውንና ድርጊት ገዝፈው የሚታዩ የሰው ልጅ ሃብቶች ናቸው:: እነዚህ ባህሎች ሰዎች ሲደሰቱ፣ ሲያዝኑ፣ ሲነጋገሩ፣ ሲያምኑ የሚያሳዩት የባህል መገለጫዎች ናቸው:: ለምሳሌ፡ ሙዚቃ፣ ልቅሶ፣ ሃይማኖት እና ሌሎችም ናቸው:: እነዚህ ሃብቶች በአይን የሚታዩ እና በእጅ የሚዳሰሱ ሃብቶች አይደሉም፤ ይልቁንም በህሊናችን ውስጥ የተቀመጡ ናቸው::

### ተግባር-13

1. ተማሪዎች! በምትኖሩበት ማህበረሰብ ከሚተገበሩ የባህል አይነቶች መካከል አንዱን በመምረጥ የስነ-ስርዓቱን ሂደት በጽሁፍ ካዘጋጃችሁ በኋላ በድራማ ሰርታችሁ አቅርቡ::

   ሀ) የሰርግ ስነ-ስርዓት ሐ) የእርቅ ስነ-ስርዓት

   ለ) የለቅሶ ስነ-ስርዓት መ) ባህላዊ አልባሳት (የሰርግ፣ የበዓል፣ የሃዘን)

2. በምትኖሩበት አካባቢ ውስጥ ህብረተሰቡ የሰራቸው እና የሚጠቀሙባቸው ቁሳዊ ባህሎች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ::

## 2.1.2. ዓለም አቀፋዊነት፣ የማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶች ተከታታይ ለውጦች

*ተግባር-14*

1. ተማሪዎች! የሰው ልጅ አስተሳሰብ እና እውቀት እያደገ ሲሄድ ቋንቋ ይለወጣል ብላችሁ ታስባላችሁ? እንዴት?

አለማቀፋዊነት ማለት አገሮች በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ወዘተ በመሳሰሉት ነገሮች መተሳሰር ወይም ቅንጅት መፍጠርን የሚያመለክት ሲሆን በተለይም በንግድ፣ በገንዘብ ዝውውር እንዲሁም አዳዲስ የቴክኖሎጅ ውጤቶችን ማሰራጨት እና በጋራ መጠቀምን ያከተተ ጽንሰ ሀሳብ ነው:: ይህ ደግሞ ለባህል መለወጥ የራሱን አስተዋጽ ያደርጋል::

ማንኛውም ባህል ያለማቋረጥ በለውጥ ሂደት ላይ ይገኛል:: የለውጡ ዓይነት እንደተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ዘገምተኛ ወይም ፈጣን ሊሆን ይችላል:: ባህሎች የተወራረሱ የተለያዩ ክፍሎች ስለሏቸው የአንዱ መለወጥ የሌላውንም ለውጥ ሊያመጣ ይችላል:: የአንድ ማህበረሰብ ባህል ሊለወጥባቸው የሚችልባቸው የተለያዩ ምክንያች ሲኖሩ እነዚህም ከአካባቢ አካባቢ የሚለያዩ ሲሆን የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

- የሳይንስና የቴክኖሎጂ ለውጥ
- ትምህርት፣ የህዝብ ፍልስትና ግንኙነት መኖር
- የተለያዩ ብዙሀን መገናኛዎች
- አንድ ባህል ከሌላው ባህል ጋር ሲገናኝ በመወራረስ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል።

በጊዜው የተፈጠሩት ቴክኖሎጂዎች እና የመገናኛ ዘዴዎች ሰዎች ከቦታ ቦታ በቀላሉ እንዲንጓዙና የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች በጋራ እንዲኖሩ አድርጓል:: ስለዚህ፡

- ባህል ከባህል የመወራረስ የመበዳደርና አንዱ አንዱን በመዋጥ የባህል ለውጥ ያስከትላል:: ይህ የባህል ስርፀት (diffusion) ይባላል:: ሥርፀት ለባህል ለውጥ

ከሚያስከትሉት ምክንያቶች አንዱ ነው፡፡ የሀይማኖት፣ የምግብ እህሎች፣ የእንስሳት፣ አለባበስ፣ የቋንቋ መስፈርት ሁሉ በዚህ ይካተታሉ፡፡

- የተራዘመ ግንኙነት መፍጠርም አንዱ ባህል ብዙ ነገሮችን ወይም የባህል ስብስቦችን ከሌላው እንዲቀበል ያደርገዋል፡፡ ይህ አንዱ ህብረተሰብ የሌላን ህብረተሰብ ባህል ሲቀበልና ሲጠቀም የራሱን እየተወ ይሄዳል፡፡ ይህ የባህል መወራረስ ሂደት / acculturation/ ይባላል፡፡
- ሌላው የባህል ለውጥ ደግሞ የሚመጣው አንድማህበረሰብ የራሱን ባህል ትቶ የሌላውን ጠቅልሎ ሲቀበል መመሳሰል ወይም መዋሀድ (assimilation) ይባላል፡፡ ይህ ዓይነት መመሳሰል የሚመጣው አብዛኛውን ጊዜ ግለሰቦች ወይም ማህበረሰቦች ዋና መኖሪያቸውን ትተው ወደ ሌላ ባህል (አገር) ሲቀላቀሉ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት መቀላቀል የአናሳ ማህበረሰቦች ማንነት (ባህል ) የሚጠፋበት መንገድም አለ፡፡
- ፈጠራ (Invention)፡ ፈጠራ ማለት አዲስ ነገር (መሳሪያ፣ አስተሳሰብ፣ ምግብ፣ ልብስ እና የመሳሰሉት) መፈጠር ማለት ነው፡፡ ከሰው ልጅ ታሪክ እንደምንረዳው ብዙ ፈጠራዎችና ግኝቶች የአስተሳሰብ ለውጦች በተለያየ የታሪክ ጊዜ ብቅ ብለዋል፡፡ እነዚህም በከፍተኛ ሁኔታ የባህል ለውጥ አስከትለዋል፡፡

### ተግባር-15

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የሰው ልጅ ፈጠራዎች ናቸው ያላችዋቸውን በመዘርዘር ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ጠቀሜታ አብራሩ፡፡
2. ከፈጠራዎች አንዱን በመወሰድ እንዴትና በምን መንገድ የባህል ለውጥ እንዳስከተለ አብራሩ፡፡
3. ተማሪዎች! በኢትዮጵያ የሚገኙ ባህሎች እየተወራረሰና እየተቀላቀለ ነው ወይስ በነበረበት እየቀጠለ ነው በሚለው ላይ በመወያየት የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል አቅርቡ፡፡

## ብዝሃ ባህልነት (Multiculturalism)

### ተግባር-16

1. ተማሪዎች! የተለያዩ ቋንቋዎች እና ልማዳዊ ህጎች በአንድ አገር ውስጥ በብዛት መኖራቸው ለማህበረሰቡ ሀብት ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?
2. ብዝሃ ባህልነት የተለያዩ ተሞክሮዎችን፣ የፈጠራ ስራዎችን፣ አመለካከቶችን እና እውቀቶችን የመለወጥ እድል ይፈጥራል? እንዴት?

ብዝሃ ባህልነት ስንል በአንድ በተወሰነ አካባቢ የተለያዩ የባህል አይነቶች መገኘት ነው:: ይህም በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በጎሳ፣ ልማዳዊ ህጎች፣ ወጎች፣ እሴቶች ወ.ዘ.ተ የተለያየ ሁኖ መገኘት ነው:: በዚህ ረገድ ሃገራችን ኢትዮጵያ በዋናነት ልትጠቀስ ትችላለች:: በተለያዩ መዛግብቶች እንደገለጸው በኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ይገኛሉ:: ስለሆነም እነዚህ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸው የተለያየ ባህል አላቸው:: በብዝሃ ባህልነት ውስጥ ትልቁና ወሳኙ የሆነው ነገር የመከባበር እና የመቻቻል እሴት ነው:: ከዚህ አንጻር በአንድ ሀገር ውስጥ ብዝሃ ባህልነት መኖር ለዚያች ሃገር ውበት ነው ይባላል::

### ተግባር-17

1. ተማሪዎች! ሰዎች በአካባቢያችሁ እንዴት ተከባብረው እና ተቻችለው እንደሚኖሩ በድራማ መልክ ካቀረባችሁ በኋላ ስለሰራችሁት ተግባራት ሰፊ ውይይት በማድረግ ድምዳሜ ላይ ድረሱ::

## 2.2. ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

### ተግባር-18

1. ተማሪዎች! ወላጆቻችሁ ገቢ የሚያገኙት ምን እየሰሩ ነው?

ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ማለት የሰው ልጅ ፍላጎቱን ለማርካት ጠቃሚ የሆኑ እቃዎችን እና አገልግሎቶች የሚመረቱበትን፣ የሚሰራጩበትንና በፍጆታ ላይ

የሚውሉበትን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያጠቃልል ሲሆን ሶስት አይነት ምጣኔ ሀበታዊ እንቅስቃሴዎች አሉ:: እነርሱም የመጀመሪያ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች፣ ሁለተኛ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች እና ሶስተኛ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅሰቃሴዎች ናቸው::

## 2.2.1. የመጀመሪያ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

የመጀመሪያ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የሰው ልጅ በቀጥታ ከተፈጥሮ ሃብቶች መካከል የሚፈልጋቸውን ነገሮች ያመርታል:: ምሳሌ: ስንዴ፣ ብረት፣ ዓሣ፣ እንሰሳት፣ ጣውላ፣ ወዘተ--- የመሳሰሉት የሚመረቱት በእነዚህ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅሰቃሴዎች ነው:: በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የግብርና፣ የማእድን ቁፋሮ፣ የአሳ ማስገር፣ የደን ሀብት ልማት፣ የአደን አና ፍራፍሬ ለቀማ ወዘተ የመሳሰሉ ስራዎችን ያጠቃልላሉ::

### ሀ) የግብርና ምንነት

**ተግባር-19**

1. የአካባቢያችሁ ህብረተሰብ የሚጠቀምባቸውን የግብርና አይነቶችን በመለየት እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው የምታውቁትን ተናገሩ::

ግብርና እንደ ምጣኔ ሃብታዊ እድገት ደረጃዎች የተለያየ ትርጉም ቢሰጠውም የአዝዕርት ማምረትና የእንስሳት እርባታ ተግባራትን ያጠቃልላል:: በአንዳንድ ታዳጊ አገሮች ውስጥ ደግሞ ከእነዚህ ተግባራት በተጨማሪ የአሳ ማስገር፣ የንብ ማነብና የደን ልማት ሰራዎችን ያጠቃልላል:: ከመጀመሪያ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች መካከል ግብርና በጣም ሰፊው የስራ መስክ ነው:: ይህም የሆነበት ምክንያት በታዳጊ አገሮች ውስጥ ወደ 75% የሚሆነው ህዝብ ተሰማርቶ የሚገኘው በዚሁ ስራ በመሆኑ ነው:: ከዚህ የምንረዳው አብዛኛው የአለም ህዝብ የሚተዳደረው በግብርና ስራ ላይ መሆኑን ነው::

### የግብርና አይነቶች

በአለም ላይ የተለያዩ የግብርና አይነቶች አሉ:: በሚመረተው የምርት ዓይነት የግብርና ተግባራት በ3 ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ:: እነርሱም የአዝርዕት ግብርና፣ የከብት ርባታ አና ድብልቅ ግብርና ናቸው::

ምርቱ የሚመረትበትን ዓላማ መሰረት በማድረግ የግብርና ተግባራት በ2 ዋና ዋና ንዑሳን ክፍሎች ይከፈላሉ:: እነርሱም፡ ሰብል ገበያ ግብርና መቆያ ግብርና ናቸው:: ለግብርና ስራ በሚውለው የካፒታል፣ የሰው ጉልበትና የመሬት መጠንን መሰረት በማድረግ ደግሞ ኀርፌ እርሻ/ግብርና /extensive farming/ እና ክብካቤ እርሻ/ ግብርና /intensive farming/ በመባል ይመደባሉ::



ምስል-1. የከብት ርባታ ግብርና



ምስል-2. የአዝርዕት ግብርና

### ተግባር-20

1. ተማሪዎች! ቤተሰቦቻችሁ ወይም የአካባቢው ህብረተሰብ የትኛውን የግብርና አይነት እንደሚጠቀሙ መረጃ በመሰብሰብና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::
2. ከላይ ያለውን ምስል በየግላችሁ በአትኩሮት ከተመለከታችሁ በኋላ የተረዳችሁትን ሀሳብ ለተማሪዎች አካፍሉ::

## ለ) የደኖች ውጤት አጠቃቀም

### ተግባር-21

1. ተማሪዎች! ቤተሰቦቻችሁ ወይም የአካባቢው ህብረተሰብ ደኖችን እንዴት ይንከባከባሉ? ለምን ለምን አገልግሎት ያውሏቸዋል? እስኪ የምታውቁትን ያህል ተናገሩ::

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ በየዓመቱ ከሚቆረጠው ግንድ ውስጥ ወደ 900 ሚሊዮን ሜትር ኩብ የሚሆነው ለማገዶነት ይውላል:: ወደ 1100 ሚሊዮን ሜትር ኩብ የሚሆነው ደግሞ ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃነት ይውላል:: ለማገዶ በጥቅም ላይ ከሚውለው እንጨት ውስጥ አብዛኛው ምግብን ለማብሰልና ቤትን ለማሞቅ ያገለግላል:: ለኢንዱስትሪ ግብዓት ከሚውለው ውስጥ ደግሞ ለጣውላ መሰንጠቂያ ኢንዱስትሪዎች፣ ለፐልፐና ወረቀት ስራዎች ያገለግላል:: የማገዶ ፍጆታን በተመለከተ ብራዚል፣ ቻይናና ሩሲያ በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰለፉ ተጠቃሚዎች ናቸው:: በሁለተኛ ደረጃ የሚፈረጁ ተጠቃሚዎች ኢንዶኔዥያ፣ ዩ.ኤስ.ኤ፣ ፈረንሳይ፣ ጃፓንና ፊንላድ ናቸው:: በልማት ያደጉና ያላደጉ አገሮችን የማገዶ ፍጆታ ስንመለከት ደግሞ በልማት ወደኋላ የቀሩ አገሮች አብዛኛውን የማገዶ ፍጆታ ድርሻ እየተጠቀሙ እናገኛቸዋለን:: በማገዶነት በቀጥታም ሆነ ወደ ከሰል ተለውጠው በጥቅም ላይ የሚውሉት እንጨቶች ባለጠንካራ ግንድ እንጨቶቸ ናቸው:: የእነዚህ ዓይነቶች እንጨቶች ደግሞ የሚገኙት በሀሩር ክልል ውስጥ ነው:: የኢንዱስትሪ እንጨቶች ፍጆታን ስንመለከት በቴክኖሎጅ ልማት ወደፊት የገፉ አገሮች ፍጆታ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል::

### ተግባር-22

1. ተማሪዎች! ቤተሰቦቻችሁ ወይም የአካባቢው ህብረተሰብ የደን መመናመንን ለመከላከል ስለሚወስዷቸው እርምጃዎች ትክክለኛ መረጃ በመሰብሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል አቅርቡ::

## ሐ) የማዕድን ቁፋሮ

### ተግባር-23

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የሸክላ አፈር አይታችሁ ታውቃላችሁ? ካለ ለምን አገልግሎት ይውላል?
2. ተማሪዎች! በእናንተ አካባቢ ጥቅም ላይ የዋሉ የማዕድን አይነቶች አሉ? ለመሆኑ ማዕድን ምን ምን ያካትታል?

ማዕድናት በቅራፎ ውስጥ ወይም በቅራፎ ላይ በተፈጥሮ የሚገኙ የኬሚካል ንጥረ ነገሮች ስብስቦች ወይም የኬሚካል ንጥረነገሮች ውህዶች ሲሆኑ በጠጣርነት ወይም

በፈሳሽነት ወይም በጋዝነት ይገኛሉ:: **ለምሳሌ፡** ኢ-ብረት አስጠኔዎች፣ ብረት አስጠኔዎች፣ ነዳጅ ዘይት፣ የተፈጥሮ ጋዝ እና የደንጋይ ክሰል ወዘተ ያጠቃልላል::

ማዕድን የማውጣት ተግባር፡- የሰው ልጅ ማዕድናትን ከቅራፎ ውስጥ ወይም ከቅራፎ ላይ የማንጠር ወይም የማውጣት ተግባር ነው:: የተወሰኑ ማዕድናት በቅራፎ ውስጥ በጥልቀት ሲገኙ የተወሰኑት ደግሞ በቅርብ ጥልቀት ላይ ይገኛሉ::

## ማዕድናትን ለማውጣት ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ደንቢዎች

በማዕድናት ማውጣት ተግባራት ላይ ተጽእኖ የሚያሳርፉ አያሌ ደንቢዎች አሉ:: እነሱም የማእድኑ ክምችት መጠን፣ የሚገኝበት የጥልቀት ደረጃ፣ የጥራት ደረጃ፣ ዋጋ፣ የቴክኖሎጅ እድገት ደረጃ፣ ክህሎት ያለው የሰው ኃይል መኖር ወይም አለመኖር፣ የካፒታል መጠን፣ የገበያ መኖር ወይም አለመኖር፣ የፖለቲካ ሁኔታ፣ የአየር ንብረት ሁኔታ እና መጓጓዣ ወዘተ ናቸው::

### ተግባር-24

1. ተማሪዎች! በግል ወደ ቤተ መጽሐፍት በመሄድ ማዕድናትን ለማውጣት ተጽዕኖ ስለሚያሳድሩ ደንቢዎች እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ መረጃዎችን በመሰብሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::

## መ) በዓለም የዓሳ ማስገር ተግባር

### ተግባር-25

1. ተማሪዎች! ጣና ሀይቅ ለአካባቢው ማህበረሰብ ምን ምን አገልግሎት ይሰጣል ብላችሁ ታስባላችሁ? እስኪ የምታውቁትን ግለፁ::

በዓለም ላይ በየዓመቱ 50 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የዓሳ ምርት እየተመረተ በፍጆታ ላይ ይውላል:: ከዚሁ ውስጥ የሰው ልጅ 25 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሚሆነውን በምግብ ፍጆታ ላይ ሲያውለው ወደ 16 ሚሊዮን የሚሆነው ደግሞ ለዶሮ መኖነት፣ ለማዳበሪያ አገልግሎት፣ ለአሳ ማጥመጃ የመንጠቆ ስጋነት፣ ወ.ዘ.ተ. ይውላል:: ቀሪው ደግሞ ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃነት ይውላል:: (1 ሜትሪክ ቶን= 1 ቶን = 1000 ኪሎ ግራም)፤፤

## 1. በዓለም ዋና ዋና የዓሳ ምርት ተጠቀሚ ክልሎች


ዋና ዋና የዓሳ ምርት ተጠቀሚ ክልሎች ከፍተኛ የህዝብ ጥግግት ያለባቸውና በባህር ጠረፍ አካባቢ የሚገኙ ክልሎች ናቸው:: እነዚህ ቦታዎች የሚገኙት 75% የሚሆነው የዓለም የዓሳ ምርት በሚመረትበት በሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ነው:: በዓለም ላይ ከሚመረተው የዓሳ ምርት 1/3ኛው መጠን ያለው ምርት በጥቅም ላይ የሚውለው በእስያ ሲሆን 1/5ኛው ደግሞ በአውሮፓ ውስጥ በፍጆታ ላይ ይውላል:: 1/10ኛው በሩሲያ ውስጥ በጥቅም ላይ ሲውል ይህንኑ የሚያህል መጠን በአሜሪካና በካናዳ ውስጥ በፍጆታ ላይ ይውላል:: በደቡብ ንፍቀ ክበብ ውስጥ ፔሩ በተወሰነ ደረጃ በዓሳ ምርቷና ፍጆታዋ እየታወቀች በመምጣት ላይ ትገኛለች::

## 2. ዋና ዋና የዓሳ ማስገሪያ ቦታዎች

### ተግባር-26

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የዓሳ ማስገሪያ ቦታዎች አሉ? እስኪ ካሉ የምታውቋቸውን ስማቸውን ዘርዝሩ::

በዓለም ላይ አምስት ዋና ዋና የዓሳ ማስገሪያ ቦታዎች /ክልሎች/ ይገኛሉ እነርሱም፡ የሰሜን ምዕራብ ፓሲፊክ፣ የሰሜን ምስራቅ አትላንቲክ፣ የደቡብ ምስራቅ ፓሲፊክ፣ የምዕራብ ማዕከላዊ ፓሲፊክ ክልል እና የሰሜን ምዕራብ አትላንቲክ ናቸው::




1:100,000,000

ምስል-3. የአለማችን ዋና ዋና የዓሳ አምራች ክልሎች

*ተግባር-27*

1. ተማሪዎች! በምስል-3 መሰረት የአለማችንን ዋና ዋና የአሳ አምራች ክልሎች ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች አሳዩ::

## 2.2.2. ሁለተኛ ደረጃ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች

*ተግባር-28*

1. ተማሪዎች! የሸመና እና የዳቦ መጋገሪያ ኢንዱስትሪዎች ለማህበረሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ምንድን ነው?

ሁለተኛ ደረጃ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች በመጀመሪያ ደረጃ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ምርቶችን በጥሬ ዕቃነት በመጠቀም ወደ ጠቃሚ አቃዎች የመለወጥ ወይም የማዘጋጀት ተግባራትን ያካትታሉ:: በአጠቃላይ የሰው ልጅ በቀጥታ በፍጆታ ላይ ሊያውላቸው የሚችሉ እቃዎችንና ሸቀጣሸቀጦችን እንዲሁም የፍጆታ እቃዎችን ለሚያመርቱ ፋብሪካዎች የሚያስፈልጓቸውን መሳሪያዎች የማምረት ተግባራት ሁለተኛ ደረጃ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች ይባላሉ:: እነዚህ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች በዋነኛነት የማኑፋክቸር ተግባራትን ያጠቃልላሉ:: በተጨማሪ የግንባታና የኃይል ማመንጨት ስራዎችንም ያካትታሉ:: የመፈብረክ ተግባራት ጥሬ ዕቃዎችን በተለያዩ ደረጃዎች በመለወጥ በቀጥታ ለሰው ልጅ ፍጆታ እንዲውሉ ወይም ለሌሎች ፋብሪካዎች በግብዓትነት የማዘጋጀት እንቅስቃሴዎች ናቸው:: የመፈብረክ ተግባር የሚከናወነው በፋብሪካዎች ውስጥ በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ነው:: ኢንዱስትሪ የሚገልፀው መፈብረክ የሚገኝበትን ቦታ ሲሆን መፈብረክ ደግሞ በፋብሪካዎች ውስጥ የሚከናወኑ ጥሬ እቃዎችን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ወደ አለቀላቸው እቃዎች የመለወጡን ሂደት ነው::

## የኢንዱስትሪ ዓይነቶች ምደባ

### ተግባር-29

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የእደጥበብ ውጤቶች የሚመረቱባቸው ኢንዱስትሪዎች አሉ? እስኪ ስማቸውን ዘርዝሩ፡፡

ከእድገት ደረጃ አኳያ ኢንዱስትሪዎች በሁለት ዋና ዋና ምድቦች ይመደባሉ፡፡ እነርሱም የጎጆ ኢንዱስትሪዎችና ዘመናዊ ኢንዱስትሪዎች በመባል ይታዎቃሉ፡፡

### 1. የጎጆ ኢንዱስትሪዎች (Cottage industries)

የጎጆ ኢንዱስትሪ የሚባሉት የተወሰነ የሰው ጉልበት በመጠቀም የእደጥበብ ውጤቶች የሚመረቱባቸው ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡ የብረት ስራ፣ የአናጢነት ስራ፣ የብር አንጣሪነት ስራ፣ የሸማ ስራ፣ የቅርጫት ስራ፣ የሸክላ ስራ፣ ወዘተ የመሳሰሉት ተግባራት በጎጆ ኢንዱስትሪ ውስጥ ይካተታሉ፡፡ የማምረት ሂደቶቹ የሚከናወኑት ደግሞ በቤት ውስጥ ነው፡፡



ምስል-4 የእደጥበብ ውጤት

## ውስን ጥናት

### የአውራምባ ማህበረሰብ

የአውራምባ ማህበረሰብ በአማራ ክልል በደቡብ ጎንደር ዞን ፎገራ ወረዳ ከወረታ ከተማ ወደ ደብረታቦር በሚወስደው ጎዳና ላይ 8 ኪሎ ሜትሮች በኋላ ገባ ብሎ በአነስተኛ የገጠር መሬት ላይ የሚገኝ ማህበረሰብ ነው:: ይህ ማህበረሰብ 104 አካባቢ አባወራዎች 388 አካባቢ የሚደርሱ የቤተሰብ አባላትን ያካተተ ማህበረሰብ ሲሆን ይህም በ1972 ዓ.ም አቶ ዙምራ ኑሩ በተባለ ግለሰብ የተመሰረተ ማህበረሰብ ሲሆን ከሌላው የክልሉም ሆነ የሀገራችን ማህበረሰብ ለየት ባለ መልኩ የፆታ እኩልነትን በተግባር ያሳየ፣ ስራን የማህበረሰቡ እምነት ያደረገ፣ እንደ ማህበረሰብ የሚተዳደሩበት የራሳቸው የሆነ መተዳደሪያ መርሆዎችን በማስቀመጥ የሚተዳደር ማህበረሰብ ነው::

የአውራአምባ ማህበረሰብ የገበሬዎች፣ እደጥበባትና ሁለገብ ህብረት ሥራ ማህበር፣ ተባብሮ መስራትን መሰረት ያደረገና በጥቂት አቅም ባላቸው ሰዎች በርካታ ደካሞችን በመተጋገዝ ሸፍኖ መስራትን ዓላማው ያደረገ እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግርን ለመፍታት የተቋቋመ ማህበር ነው:: የማህበሩ አባላት በሙሉ እንደየ አቅሙና እንደየ ችሎታው የሚሰራበትና እኩል ተከፋይ የሚሆንበት ማህበር እንደሆነ ሲያስረዱ አቅም ያለው አቅም ለሌለው ድጋፍ በመሆን በመረዳዳትና በመተጋጋዝ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ማምጣት ነው:: ኢኮኖሚያዊ ለውጡም ሁሉን የሚያቅፍና እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን ይናገራሉ::

አቶ ዙምራ በኢንዱስትሪም መስራትና ማደግ መለወጥ ይቻላል በሚል አስተሳሰብ የሚያውቀውን የሽመና ሙያ አብረዋቸው ላሉ ተከታዮቻቸው በማሰልጠን ወደ ሥራ ተሰማርተዋል:: በዘርፉ የተለያዩ ስልጠናዎችን ማግኘት በመቻላቸውም ሥራውን ማስፋት ችለው ዛሬ ላይ በርካታ ባለሙያዎችን በማፍራት እንዲሁም በኢንዱስትሪው ዘርፍ ተሰማርተው ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ ስኬታማ መሆን ችለዋል::




ምስል-5. የአውራምባ ማህበረሰብ እደ ጥበብ

### ተግባር-30

1. ተማሪዎች! ከላይ የቀረበውን ምስል በተገቢው በማስተዋል እና በመወያየት የተረዳችሁትን ሀሳብ ለክፍል ተማሪዎች ተራ በተራ አብራሩ::

## 2. ዘመናዊ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች

### ተግባር-31

1. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የጨርቃጨርቅ፣ የምግብ፣ የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች አሉ? እስኪ ስማቸውን ዘርዝሩ::

ዘመናዊ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የተለያዩ እቃዎችን ወይም ሸቀጣ ሸቀጦችን በፋብሪካዎች ውስጥ የኤሌትሪክ ኃይል ወይም ሌላ ኃይል በሚጠቀሙ ማሽኖች የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ናቸው:: ከፍተኛ መጠን ያለው ምርት ማምረት፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ካፒታል መጠቀም፣ ከፍተኛ ኃይል የሚጠቀሙ ማሽኖችን መጠቀም፣ የስራ ክፍፍል በከፍተኛ ደረጃ መኖር፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሙሉ በሙሉ የሰለጠነና በከፊል የሰለጠነ የሰው ኃይል በጥቅም ላይ መዋል እና የመሳሰሉት ናቸው::

ዘመናዊ ማኑፋክቸሪንግ (መፈብረክ) አንዱስትሪዎች ቀላልና ከባድ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በመባል ይከፈላሉ:: ቀላል ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚባሉት ጥቂት ጥሬ እቃዎችን የሚፈልጉ እና በመጠን ጥቂት የሆኑ ናቸው::

እነዚህ ኢንዱስትሪዎች የሚያመርቷቸው ምርቶች የፍጆታ ምርቶች ናቸው:: ለምሳሌ፡ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪዎች፣ የምግብ ኢንዱስትሪዎች፣ የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወዘተ ናቸው::

ከባድ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚባሉት ደግሞ ከባድና ግዙፍ የሆኑ ምርቶችን/እቃዎችን/ የሚያመረቱ ኢንዱስትሪዎች ሲሆኑ በማምረት ሂደት ወቅት ከባድና መጠነ ብዙ የሆኑ የጥሬ ዕቃ ግብአቶችን የሚጠቀሙ ናቸው:: የብረታ ብረት ኢንጀነሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ የመርከብ ግንባታ፣ የባቡር ሀዲድ ኢንጅነሪንግ፣ የአውሮፕላን ስራ፣ የተሽከርካሪዎች ስራ እና የመሳሰሉት በዚህ ስር ይካተታሉ:: ከባድ ኢንዱስትሪዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ካፒታልና ጥሬ እቃዎችን በግብአትነት የሚጠቀሙ ናቸው::



ምስል-6. ዘመናዊ ኢንዱስትሪ

*ተግባር-32*

1. ተማሪዎች ከላይ የምትመለከቱት የኢንዱስትሪ አይነት የምን ማምረቻ ፋብሪካ ነው?

## 2.2.3. ሶስተኛ ደረጃ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች

የሶስተኛ ደረጃ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃዎች የሚያካትቷቸው እንቅስቃሴዎች አገልግሎት ሰጭ በሆኑ የስራ መስኮች ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ናቸው:: በዚህ ውስጥ የሚካተቱት ተግባራት በቀጥታ እቃዎችን በማምረት ላይ የተመሰረቱ ሳይሆኑ ለእቃዎች መሰረት፣ ጥራት፣ ስርጭትና ፍጆታ የሚያገለግሉ

አገልግሎቶችን መስጠት ነው። በዚህም ምክንያት የምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች /ተግባራት/ የአገልግሎት ሰጭ ተግባራት ይባላሉ። በዚህ ውስጥ የሚጠቃለሉት አገልግሎቶች መጓጓዣ፣ መገናኛ፣ ቱሪዝም፣ ንግድ እና ሙያዊ የሆኑና ሙያዊ ያልሆኑ የቢሮ አገልግሎቶች ናቸው።

## 1. መጓጓዣ (Transport)

መጓጓዣ ለአለም የንግድ እንቅስቃሴ የጀርባ አጥንት ነው። መጓጓዣ አምራችንና ተጠቃሚን የሚያገናኝ መሰረታዊ ነገር ነው። መጓጓዣ የክልላዊ የምርት አይነትን ያሰፋል፣ የመጓጓዣና የምርቶችን ወጭ ይቆጣጠራል እንዲሁም አዳዲስ ፈጠራዎችን እንዲስፋፉ ያደርጋል።

### የመጓጓዣ አይነቶች

የየብስ መጓጓዣ፡ የብስን የሚያቋርጡ የመጓጓዣ አይነቶች ባቡርና የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ለአንድ አገር እድገት ምትክ የማይገኝለት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። የውሃ መጓጓዣ ታላላቅ ውቅያኖሶችና ባህሮችን የሚያቋርጡ መርከቦችና ጀልባዎች ሰዎችን፣ ከባድና ውድነት ያላቸውን እቃዎችና የነዳጅ ዘይት ድፍድፍን ከቦታ ቦታ ያጓጉዛል። የአየር መጓጓዣ የቅርብ ጊዜ ክስተት ሆኖ እናገኘዋለን። አውሮፕላን ውድና ቶሎ የሚበላሹ እንደ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ሰዎችን ከተፈለገው ቦታ በፍጥነት ያደርሳል። ይህ የመጓጓዣ አይነት ውድ ሲሆን እንደ ሰው፣ አልማዝ፣ ወርቅና ሌሎች ውድና ቀላል እቃዎችን ለማጓጓዝ ይጠቅማል።

**ተግባር-33**

1. ከላይ የተዘረዘሩትን የመጓጓዣ አይነቶች ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመገምገም የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ።
2. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች አብዛኛውን ጊዜ እቃዎቻቸውን ከቦታ ቦታ የሚያጓጉዙት በየትኞቹ የመጓጓዣ አይነቶች ነው? መረጃዎችን በማሰባሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል አቅርቡ።

## 2.ቱሪዝም (Tourism)

**ተግባር-34**

1. ተማሪዎች! በአካበያችሁ የቱሪዝም ቦታዎች አሉ? እስኪ ስማቸውን ዘርዝሩ::

ቱሪዝም "ቱር" ከሚለው የእንግለዘኛ ቃል የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም ከቦታ ቦታ እየሄዱ ሃገርን፣ አካባቢን ወይም ታሪካዊና መንፈሳዊ(ሃይማኖታዊ) ስፍራዎችን መጎብኘት ማለት ነው:: በዚህ ስራ ላይ የተሰማራው ቱሪስት ወይም ጎብኝ ይባላል:: ቱሪዝም ሰዎችን የማስደሰት፣ መንፈሳዊና አካላዊ እርካታ የመስጠትና የማዝናናት አገልግሎት ነው::

**ተግባር-35**

1. ተማሪዎች! ቱሪዝም ለአገር ኢኮኖሚ ያለውን ጠቀሜታ አብራሩ::
2. የቱሪዝም ዋና ዋና ችግሮች ምን ምን እንደሆኑ ግለጹ::

# 2.3. ንግድ እና ገበያ

## 2.3.1. የንግድ ምንነት እና ዕንሰ ሀሳብ

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የሰው ልጅ የሚኖረው በተለያዩ አካባቢዎች በተወሰኑ ተግባራት ተመስርቶ ነው:: በመሆኑም ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐቱን የሚያሟሉለት በሁሉም ቦታ ተሟልተው አያገኛቸውም:: ስለዚህ ወሰን የሌለው ፍላጐቱን ለማሟላት የንግድ እንቅስቃሴን ይፈጥራል:: ንግድ ዕቃንና ሸቀጣሸቀጥን የመግዛት፣ የመሸጥና የመለወጥ እንቅስቃሴ ነው:: የንግድ እንቅስቃሴ በአካባቢ፣ በሃገር ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ይከናወናል::

## 2.3.2. የንግድ አይነቶች እና ጠቀሜታዎች

**ተግባር-36**

1. ተማሪዎች! የምትኖሩበት አካባቢ ማህበረሰብሰ በምን አይነት ንግድ ይተዳደራል? እስኪ የምታውቁትን ተናገሩ::

የማንኛውም አገር ንግድ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይጠቃለላል:: እነሱም የሃገር ውስጥ እና የውጭ ወይም አለማቀፋዊ ንግድ ናቸው:: የሃገር ውስጥ ንግድ፡ የሚባለው በሃገር የሚካሄደውን የንግድ ሂደት ነው:: ይህ ንግድ በማህበረሰብ ወይም በግለሰቦች መካከል የሚካሄደውን ዕቃንና ሸቀጣሸቀጥን የመግዛት፣ የመሸጥና የመለወጥ እንቅስቃሴ ነው:: የሃገር ውስጥ ንግድ መጠን ከአገር አገር ይለያያል:: በአንድ አገር የቆዳ ስፋት፣ በመሰረተ ልማት ማለትም በትራንስፖርትና በመገናኛ እድገት ይወሰናል:: አለም አቀፋዊ /የውጭ/ ንግድ የሚባለው በተለያዩ አገሮች መካከል የሚካሄደውን ሸቀጦችን የመግዛትና የመሸጥ እንቅስቃሴ ነው:: የውጭ ንግድ ሁለት መልኮች አሉት:: እነዚህም ገቢ እቃ ንግድ እና ወደ ውጭ የሚላክ ሸቀጥ ንግድ ናቸው::

### የንግድ ዋና ዋና ጠቀሜታዎች

ንግድ የሚከተሉት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች አሉት፡

- የሰው ልጅ ፍጎቱን ለማርካት የሚያስፈልጉት ነገሮችን በገበያ አማካኝነት ማግኘት ያስችላል::
- ከፍተኛ ምርት ከተመረተበት ወደ ዝቅተኛ ምርት እና ከፍተኛ ፍላጎት ወደ አለበት በማቅረብ ትርፍ ለማግኘት ያስችላል::
- ለብዙ ማህበረሰብ የስራ እድል መፍጠር እና የስራ ክፍፍል እንዲኖር ያደርጋል::
- አገሮች ለንግድ እና ለትረፍ ሲባል ለአለም ገበያ የሚሆኑ ምርቶችን እንዲያመርቱ ያደርጋል::
- አገሮች ጥራት ያለው ምርት እንዲያመርቱ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋል::
- አገሮች የእራሳቸውን ምርት እንዲያመርቱ እና የውጭ የንግድ ጫና እንዲቀንሱ ያስችላል::
- የእውቀት፣ ክህሎት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር በአገራት መካከል እንዲኖር

ማስቻል ናቸው።

## የሃገር ወይም የአለማቀፋዊ ንግድ እንዲካሄድ የሚያስገድዱ መሰረቶች

በሃገር ውስጥ ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ንግድ እንዲካሄድ የሚያስገድዱ መሰረቶች በርካታ ናቸው። በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ምርቶች መመረት፣ በተወሰኑ አካባቢዎች ከመጠን በላይ መመረትና በሌሎች ቦታዎች ደግሞ ከበቂ በታች መመረት፣ የጥሬ ዕቃዎች /ምርት/ ፍላጐት መኖር እና በቂ የሆኑ የመገናኛ አገልግሎቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

**ተግባር-37**

1. አለማቀፋዊ ንግድ ከአገር ውስጥ ንግድ የሚለይባቸውን ባህሪያቶች በመገምገም የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

## 2.3.3 የግብይት አቅርቦትና ፍላጎት፣ የግብይት ዋና ተዋናዮች እና የሸማቾች መብት ጥሰት

**ተግባር-38**

1. ተማሪዎች! የምርቶች አቅርቦት እጥረት የሚከሰተው በምን ይመስላችኋል?

የምርቶች አቅርቦት እና ፍላጎት አለመጣጣም የእየሀገራቱን የተዛባ የንግድ ሥርዓት በተለይም የወጪና የገቢ ንግድ አለመመጣጠን ለእጥረቱ መባባስ ምክንያትም ሆኗል። የፍላጎት መጨመር እና የአቅርቦት እጥረት ሲከሰት በምጣኔ ሃብቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ በማሳረፉ በርካታ አምራች ድርጅቶች በሙሉ አቅማቸው እንዳያመርቱ እንዲሁም ህልውናቸውን ፈተና ላይ ይጥለዋል። ይህ ሁኔታ አብዛኛውን ጊዜ ሊከሰት የሚችለው የነዳጅ እና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እና ፍላጎት ሳይጣጣም ሲቀር ይሆናል።

ግብይት፦ ግለሰቦች ወይም ድጅቶች ምርትና አገልግሎቶችን ለመለዋወጥ ካላቸው ፍላጎትና የመግዛት አቅም በመነሳት ፍላጎታቸውን ለማርካት የሚያስችላቸው ልውውጥ ለማድረግ የሚገናኙበት ተቋም ነው። በግብይት ስርዓት ውስጥ ግብይቱን በዋናነት የሚመሩት የግብይት ተዋናዮች(market actors) ሲባሉ እነርሱም

አምራቾች፣ ሀብረትስራ ማህበራት፣ ጅምላ ነጋዴዎች፣ ቸርቻሪ ነጋዴዎች እና ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

መንግሥት የኑሮ ውድነት በሚከሰትበት ወቅት ገብያውን ለማረጋጋት እና ሚዛን የጠበቀ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ ሊወስድ ከሚገባቸው የኢኮኖሚ እርምጃዎች ጎን ለጎን የሸማቾችን ደህንነት ለማስጠበቅ እና በተከሰተው የኢኮኖሚ አለመረጋጋት ውስጥ የከፋ ጉዳትን ሳያስከትሉ እንዲያልፉ ለማድረግ ሊወሰዱ የሚገባቸው ህጋዊ መፍትሔዎች በየሀገራቱ የሸማቾች ጥበቃ ህጎች ላይ ተካተው እንመለከታለን፡፡

የኢትዮጵያ ሸማቾች ጥበቃ የሕግ ማዕቀፍም ለእንደዚህ አይነቱ ምክንያታዊ የሆነ የመንግሥት በጣልቃ ገብነት በተወሰነ መልኩ እውቅና ሰጥቶት እንመለከታለን፡፡ የአዋጅ ቁጥር 813/2006 ስናነብ የምንገነዘበው ነገር ቢኖር የአልተገባ የንግድ እንቅስቃሴ ሲኖር እና የሸማቹን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲፈጠር በመንግሥት ሊወሰዱ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎች በሕጉ ተካተዋል፡፡ እርምጃዎችን ለመወሰድ እና ለማስፈፀም በዋነኝነት ሥልጣን የተሰጠው በፌደራል ደረጃ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ሲሆን በክልሎች ደግሞ የንግድ እና ገበያ ልማት ቢሮዎች ናቸው፡፡

*ተግባር-39*

1. ስለኢትዮጵያ ሸማቾች ጥበቃ የሕግ ማዕቀፍ ምን ቁምነገር ተረዳችሁ? የተረዳችሁትን መረጃ በማስደገፍ አብራሩ፡፡

## 2.4. የመንግሰት ገቢ እና ግብር

### 2.4.1 የመንግሰት ገቢ እና ግብር የሚያስገኛቸው ጥቅሞች በኢትዮጵያ

*ተግባር-40*

1. ተማሪዎች! መንግስት ግብር ለምን የሚሰበስብ ይመስላችዋል?

ግብር ለሀገራችን አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ግብር ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ

የመጣ ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ በሕግ በተወሰነው መሠረት ለመንግሥታቸው የሚከፍሉት ገንዘብ ነው፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ህብረተሰቡ ግብር ለልማት፣ ለእድገት፣ ለብልፅግና የሚከፈል መዋጮ መሆኑን እየተረዳው መጥቷል፡፡ ስለዚህ ግብር ለሀገር ልማትና እድገት ከገቢ ላይ የሚከፈል ገንዘብ መሆኑን በመረዳት የአገራችን ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ግብር እየከፈሉ ይገኛሉ፡፡

በፌደራል የመንግሥት አወቃቀር ሥልጣን በፌደራል መንግሥቱና በክልሎች መካከል የተከፋፈለ በመሆኑ በዚህ የስልጣን ክፍፍል መሰረት ሁለቱም አካላት ግብር የሚሰበስቡባቸው አካባቢዎች ተለይተው ተዘርዝረዋል፡፡ ሁለቱም አካላት በህጉ ተደንግጎ በተሰጧቸው የግብር አካባቢዎች እንዳሉ ሁሉ የሚጋሯቸው የጋራ የግብር ዓይነቶችም አሉ፡፡ እነዚህ በጋራ የሚሰበሰቡ የግብር ዓይነቶች የጋራ ገቢዎች ተብለው ይታወቃሉ፡፡

በሀገራችን የፌደራሉ መንግሥትና ክልሎች በተናጠልና በጋራ የተሰጣቸው የገቢ ዓይነቶች በሕገ-መንግስቱ ውስጥ ተዘርዝረው ተቀምጠዋል፡፡

የፌደራል መንንግስት ዋና የገቢ ምንጮች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡ እነርሱም፡

- ከሀገር በሚወጡና በሚገቡ እቃዎች ላይ የሚጣል ቀረጥ እና ግብር፤
- ከፌዴራል መንግሥትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጣሪዎች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር፤
- በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት በሚተዳደሩ ድርጅቶች ላይ የገቢ፣ የትርፍ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስና የኤክሳይዝ ታክስ፣
- ከብሔራዊ ሎተሪ እና ሌሎች የእድል ሙከራ ገቢዎች ላይ የሚሰበሰብ ታክስ፣
- ከአየር፣ ከባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የሚሰበሰብ ታክስ ወዘተ ናቸው።

የክልል መስተዳድር ዋና የገቢ ምንጮች፡

- ከክልል መንግሥታት ተቀጣሪዎች ላይ የሚሰበሰብ፣
- ከመሬት መጠቀሚያ የሚሰበሰብ፣
- በክልል ከሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች ላይ የሚሰበሰብ፣
- በክልል መስተዳድር በግል ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች የሚሰበሰብ፣
- በክልል መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች ከሚመነጩ ክፍያዎች የሚሰበሰቡ ናቸው።

የፌደራል እና የክልል መንግስታት የጋራ ግብር ዋና የገቢ ምንጮች

- የፌዴራል መንግሥትና ክልሎች በጋራ ከሚያቋቁማቸው የልማት ድርጅቶች ላይ የሚሰበሰብ፣
- ከግል ድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና ከባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ የሚሰበሰብ፣
- ከፍተኛ የማዕድን ሥራዎች እና ከማናቸውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ ከሚጣል የሮያሊቲ ክፍያዎች የሚሰበሰብ ወዘተ ናቸው።

ግብር ኢንቨስትመንትን በማስፋፋቱ ሂደት የላቀ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ይህም የሚሆነው መንግሥት ከግብር በሚያገኘው ገቢ መሠረተ ልማትን ማለትም መንገዶችንና መብራትን ይዘረጋል፤ ድልድዮችን፣ የውሃ እና የኃይል ማመንጫዎችን ወዘተ…ይገነባል፡፡ እነዚህ መሰረተ ልማቶች በተስፋፉ መጠን ሁኔታዎች ስለሚመቻቹላቸው የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጪ ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ ይሰማራሉ፡፡ በሌላ በኩል ኢንቨስትመንት ሲስፋፋ የግብር ምንጭም በዚያው መጠን ያድጋል፡፡ ስለዚህ ግብርና ኢንቨስትመንት ተደጋጋፊ ሥራዎች ናቸው ማለት ነው፡፡

## ተግባር-41

1. ተማሪዎች! ግብር ከፋዮች ምን መብት አላቸው? ግዴታቸውስ ምንድን ነው? በሚለው ሀሳብ ላይ በመወያየት የደረሳችሁበትን ማደማደሚያ አብራሩ::
2. መንግስት ግብር በመሰብሰቡ ምክንያት ማህበረሰቡ የሚያገኛቸውን ጥቅሞች ለክፍል ተማሪዎች አስረዱ::
3. ኢንቨስትመንት ለአገር እድገት ያለውን ፋይዳ መጽሐፍትን በማንበብ ወይም በየነ መረብ በመጠቀም በትክክለኛ መረጃ አሰባስባችሁ ለክፍል አቅርቡ::

## ማጠቃለያ

- ባህል የአንድ ማህበረሰብ ወይም ህዝብ የአኗኗር ዘይቤ ነው ተብሎ ሊገለጽ ይቻላል:: የባህል ዋና ዋና ይዘቶች የሚባሉት ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣ ምልክት፣ ባህላዊ እሴቶች እና የመሳሰሉት ናቸው:: የመጀመሪያ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ የሰው ልጅ ፍላጎቱን ለማሟላት በቀጥታ የተፈጥሮ ሀብትን የመጠቀም ሂደት ነው:: ሁለተኛ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ምጠኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ምረቶችን እና አገልግሎቶችን የማሻሻል ሂደት ነው:: በመጨረሻም ሶስተኛ ደረጅ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ለሁለተኛ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች እና ለመጀመሪያ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው::
- መንግሥት የኑሮ ውድነት በሚከሰትበት ወቅት ገበያውን ለማረጋጋት እና ሚዛን የጠበቀ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ ሊወስድ ከሚገባቸው የኢኮኖሚ እርምጃዎች ጎን ለጎን የሸማቾችን ደህንነት ለማስጠበቅ የሸማቾች ጥበቃ ህጎች ላይ ተካተዋል::

➢ ግብር ለሀገር ልማትና እድገት ከገቢ ላይ የሚከፈል ገንዘብ መሆኑን በመረዳት የአገራችን ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ግብር እየከፈሉ ይገኛሉ። ስለዚህ የፌደራል የመንግሥት አስተዳደር ዋና መለያ ባህሪ ሥልጣን በፌደራል መንግሥቱና በክልሎች መካከል የተከፋፈለ በመሆኑ በዚህ የስልጣን ክፍፍል መሰረት ሁለቱም አካላት ግብር የሚሰበስቡባቸው አካባቢዎች ተለይተው ተዘርዝረዋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

*ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ወይም ስህተት የሆነውን ሃሰት በማለት መልሱ።*

1. ምንም እንኳ ሁሉም ባህል ሰው ሰራሽ ቢሆንም ተፈጥሯዊ የሆኑ ነገሮችን አካትቶ ይይዛል።
2. የስነ-ፍጥረት ንድፈ-ሃሳብ መሰረቱ ሃይማኖት በመሆኑ በቂ በሆነ ምርምር የተደገፈ ነው።
3. ባህል ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ነገሮችን ያካትታል።
4. እያንዳንዱ ባህል የራሱ የሆነ ምልክት አለው።
5. ሀዘንና ደስታ ቁሳዊ ባህሎች ናቸው።
6. ሙያዊና ሙያዊ ያልሆኑ የቢሮ አገልግሎቶች በሁለተኛ ደረጃ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ይጠቃለላሉ።

*ለ) ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ብቻ ምረጡ።*

1. ከሚከተሉት ውስጥ ቁሳዊ ባህል ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ) የምግብ እቃዎች   ለ) የቀብር ስነስርዓት
   ሐ) የእርሻ መሳሪያዎች   መ) መልስ የለም
2. ከሚከተሉት ውስጥ የባህሎች የጋራ ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ) የሚማማሩበት መሆኑ   ለ) የማይለወጥ መሆኑ
   ሐ) የጋራና የተወራረሰ መሆኑ   መ) መልስ የለም

3. ከሚከተሉት መካከል አንዱ ለባህል መቀየር ምክንያት ሊሆን አይችልም

ሀ) የህዝብ ፍልሰት ሐ) ትምህርት

ለ) ቴሌቪዥን መ) የፈጠራ መኖር ሠ) መልስ የለም

4. በትክክል ያልተዛመደው የትኛው ነው?

ሀ) መንፈሳዊ ባህል-ለቅሶ ሐ) መንፈሳዊ ባህል-የሚዳሰስ (ት/ቤት)

ለ)ቁሳዊ ባህል-መስጊድ መ) መንፈሳዊ ባህል-እስክስታ

ሠ) ቁሳዊ ባህል--ሽመና

5. ከዋና ዋና አሳ ማስገሪያ ቦታዎች ውስጥ ከአውሮፓ ጋር የሚዋሰነው የቱ ነው?

ሀ) ሰሜን ምዕራብ አትላነቲክ ለ) ሰሜን ምስራቅ አትላንቲክ

ሐ) ሰሜን ምዕራብ ፓስፊክ መ) ሰሜን ምስራቅ ፓስፊክ

ሠ) መልስ የለም

*ሐ) የሚከተሉትን ንድፈ ሀሳቦች ከሚሰማማቸው ጋር በማዛመድ በክፍት ቦታው ፊደሉን ብቻ ጻፉ::*

| ሀ) የአዝጋሚ ለውጥ ንደፈ ሃሳብ | ለ) የስነ-ፍጥረት ንደፈ ሃሳብ |
|---|---|

1. ----መለኮታዊ ነው::
2. ------በምርምርና በፍተሻ የተደገፈ ነው::
3. ------ሰዎች የተፈጠሩት አሁን የያዙትን መልክና ቁመና አንደያዙ ነው ብሎ ያምናል::
4. ------የሰው ልጅ በጊዜ ብዛት ከሌሎቹ አንሰሳት እንዴት እንደተለየ ያስረዳል::

*መ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ማብራሪያ ስጡ::*

1. በክልላችሁ የመንግስት ገቢ እና ግብር የሚያስገኛቸው ጥቅሞችን አስረዱ::
2. የትራንስፖርት አይነቶችን ለመጠቀም የሚወስኑ ምክንያቶችን በመዘርዘር ማብራሪያ ስጡ::
3. ተማሪዎች ወደ ቤተ መጽሐፍት በመሄድ ስለጎጀ ኢንዱስትሪ ባህሪያት

ትክክለኛ መረጃ በማሰባሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

4. ተማሪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በአብዛኛው የሚታዩት የኢንዱስትሪ አይነቶችን በመዘርዘርስለእያንዳንዱ ማብራሪያ ስጡ።

5. ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ አይነቶች በታዳጊ ሀገራት እጅግ በጣም በጥቂቱ የሚገኙት የትኞቹ ናቸው? ለምን?

6. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የጋራ ወይም የተለያየ ባህል መኖርና መስፋፋት ያለውን ጥቅምና ጉዳት ታወዋቂ ሰዎችን በመጠየቅ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

7. ቴክኖሎጂ በባህል መወራረስና ለውጥ ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ ያስከትላል? እስኪ ማብራሪያ ስጡበት።

8. ተማሪዎች! የአንድ ሀገር ባህላዊ እሴቶች ይለዋወጣሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? የሚለዋወጡ ከሆነ ምክንያቶች ምን ምን ይመስሏችኋል? እስቲ እናንተ በምትኖሩበት አካባቢ ከምታውቁት ባህላዊ እሴት የተለወጠ ካለ አብራሩ።

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

- ባህል፡- የአንድ ህዝብ የአኗኗር ዘይቤ ነው።
- ቋንቋ፡- አስተሳሰብን፣ ልምድን፣ አድገትን እና አመካከትን ለማሰተላለፍ የሚያስችል ነው።
- ሀይማኖት፡- እምነትና አመለካከትን የሚገልፅ ነው።
- ምልክት፡- አንድ የታወቀ አካል ወይም ድምፅ ወይም ምስል ሁኖ አንድን ነገር ሊወክል የሚችል ማለት ነው።
- ቁሳዊ ባህል፡- ሊታይና ሊዳሰስ የሚችል የባህል አይነት ነው።
- መንፈሳዊ ባህል፡- ሊታይና ሊዳሰስ የማይችል የባህል አይነት ነው።
- የአዝዕርት ግብርና፡- የሰብል ምርት የሚከናወንበት ግብርና አይነት ነው።
- የከብት ርባታ ግብርና፡- የወተትና የስጋ ከብት ርባታን የሚገልፅ ነው።
- ድብልቅ ግብርና፡- ሰብል ማምረት እና ከብት ርባታን የሚገልፅ ነው።
- ሰብል ገበያ ግብርና፡- ለገበያ የሚሆኑ ሰብሎች የሚመረቱበት የግብርና አይነት ነው።
- መቆያ ግብርና፡- ከእጅ ወደ አፍ የሆነ የግብርና አይነት ነው።
- ጉርሬ እርሻ/ግብርና፡- በሰፊ መሬት አነስተኛ ወይም ካፒታል በመጠቀም የሚከናወን የግብርና አይነት ነው።
- ክብካቤ እርሻ/ግብርና፡- በትንሽ መሬት ከፍተኛ ገንዘብ ወይም የሰው ጉልበት የሚጠቀም የግብርና አይነት ነው።

# ምዕራፍ-3

# የተፈጥሮ ሀብቶች እና የማህበረ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ዋና ዋና ርእሰ ጉደዮች አካቷል:: የአካባቢ እንክብካቤ እና አጠቃቀም ለዘላቂ እድገት፣ ከጊዜ ጋር የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም መለዋወጥ፣ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ እና ዘላቂ አጠቃቀም፣ እንክብካቤ የጎደለው የሀብት አጠቃቀም የሚያስከትላቸው አሉታዊ ተፅእኖዎች፣ የተፈጥሮ ሀብቶች ተደራሽነት እና ግጭቶች አፈታት ተዳሰዋል::

በአካባቢ እንክብካቤ እና አጠቃቀም ለዘላቂ እድገት በተመለከተ የተፈጥሮ ሀብቶች ትረጉም እና የተፈጥሮ ሀብት አይነቶች እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠቀም የሚረዱ ሁኔታዎች፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ ለመጠቀም እና ለመንከባከብ የሚረዱ ዘዴዎች ተቃኝተዋል:: በተጨማሪም የተፈጥሮ ሃብቶች ጥቅም ማለትም የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ፍላጎቶች እንዲሁም እንክብካቤ የጎደለው የሀብት አጠቃቀም የሚያስከትሏቸው አሉታዊ ተፅእኖዎች ተብራርተዋል:: በመጨረሻም የፈጥሮ ሀብቶች ተደራሽነትን የያዘ ሲሆን በዚህም ውስጥ የግጭት መንስኤዎችን፣ የግጭት አይነቶች እና የግጭት አፈታት ዘዴዎች ተብራርተዋል::

*ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት:*

***ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-***

- ☞ *የተፈጥሮ ሀብቶችን አጠቃቀም እና ጥቅሞች ትተነትናላችሁ::*
- ☞ *የተፈጥሮ ሀብቶችን እንክብካቤ ትገመግማላችሁ::*
- ☞ *የተፈጥሮ ሀብቶች ለዘላቂ ልማት ያላቸውን አስተዋጽኦ ታደንቃላችሁ::*
- ☞ *የተፈጥሮ ሀብት ችግሮችን በመለየት ለችግሮች የመፍተሄ ሀሳብ ታመነጫላችሁ::*

- ☞ የተፈጥሮ ሀብቶች ተደራሽነት እና የግጭት መንስኤዎችን ትለያላችሁ::
- ☞ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ታደንቃላችሁ::

## 3.1 የአካበቢ እንክብካቤ እና አጠቃቀም ለዘላቂ አድገት

**ቁልፍ ቃላት:**

| | |
|---|---|
| ☞ የተፈጥሮ ሀብት | ☞ ታዳሽ |
| ☞ እንክብካቤ | ☞ ኢ-ታዳሽ |

### 3.1.1. የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀምና ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅሞች

#### የተፈጥሮ ሀብቶች

**ተግባር-1**

1. ተማሪዎች! የእጽዋቶችን ጥቅም ምን ምን እንደሆኑ ታውቃላችሁ? እስኪ የምታውቁትን ዘርዝሩ::

የተፈጥሮ ሀብቶች ማለት በተፈጥሮ የሚገኙ የሰው ልጅ እውቀቱን ተጠቅሞ ወደ ጠቃሚ ሊለውጣቸው የሚችል ቁሳዊ እና ቁሳዊ ያልሆኑ ሀብቶች ናቸው:: በዓለማችን ያሉ ሁሉም ሀገራት የተፈጥሮ ሀብቶችን ተጠቅመው የህዝቦችን ፍላጎቶች ያሚላሉ:: የእድገትና የብልፅግና ልዩነት የሚመጣው ሀገራት ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ መጠቀም ወይም አለመጠቀማቸውን ተከትሎ ነው:: በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሀብቶች ለህይወት አስፈሊጊ የሆኑ የተፈጥሯዊ አካባቢ አባላት፣ ለሁለም ህይወታዊ ዘአካላት በቁሳዊነትና በኃይል ምንጭነት በጥቅም ላይ የሚውሉ ነገሮች /substances/፣ መሰረታዊና መሰረታዊ ያልሆኑ ፍሊጎቶችን ለማርካት የሚጠቅሙ በተፈጥሮ የሚገኙ የገፀ-መሬት ፀጋ የሆኑ ቁሶች ናቸው ማለት ይቻላል::

## የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች

የተፈጥሮ ሃብቶች በዓይነታቸው፣ በባህሪያቸውና በጥቅማቸው እጅግ በጣም ይለያያሉ። ከተፈጥሮ ሃብቶች ትንታኔና እንክብክቦሽ አይታ አንፃር የተፈጥሮ ሃብቶች ብዛታቸውን፣ ሊጠፉ ወይም ላይጠፉ መቻላቸውን፣ ሊታደሱ ወይም ላይታደሱ መቻላቸውን እንደ መስፈርት በመጠቀም እንመድባቸዋለን።

ሠንጠረዥ 1- የአፈርና የእፅዋት አይነት እና ጥቅም

| አፈር | | እፅዋት | |
|---|---|---|---|
| የአፈር አይነቶች | የአፈር ጥቅም | የእፅዋት አይነቶች | የእፅዋት ጥቅም |
| ሸክላማ አፈር | | | |
| ለም አፈር (loam soil) | | | |
| አሸዋማ አፈር | | | |

### ተግባር-2

1. ተማሪዎች! በደብተራችሁ "ሠንጠረዥ -1"ን በመጻፍ በጥንድ በመሆን በመጀመሪያ የአፈርን ጥቅም በክፍት ቦታው ሙሉ። በ2ኛ ደረጃ ደግሞ የምታውቁትን እጽዋት ከነጥቅሙ በተሰጠው ክፍት ቦታው ሙሉ እና ለክፍላችሁ አቅርቡ።
2. ተማሪዎች! የሰው ልጅ ከደረቅ መሬት፣ ከውኃማ አካል፣ ከከባቢ አየር እና ከምድረ ህይወት ጋር የሚያደርገውን መስተጋብር መጻህፍትን በማንበብ መረጃዎችን በማሰባሰብ ሪፖርት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

## ሀ) ታዳሽ የተፈጥሮ ሃብቶች

### ተግባር-3

1. ተማሪዎች! ቤተሰቦቻችሁ ወይም የአካባቢያችሁ ማህበረሰብ ስለ ውሃ አጠቃቀም ያላችሁ ግንዛቤ ምን ይመስላል? እስኪ የምትችሉትን ያህል ግለፁ::
2. ተማሪዎች! የሚከተለውን ሠንጠረዥ በየግልችሁ ተመልከቱ እና አናንተ የምታውቋቸውን በመጨመር የሚሰጡትን ጥቅም ግለጹ::

**ሠንጠረዥ 2- የተፈጥሮ ሀብቶች እና የሚሰጡት ጥቅም**

| ተ. ቁ | ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብቶች | የሚሰጡት ጥቅም |
|---|---|---|
| 1 | የፀሐይ ሀይል | የውሃ ዑደት እንዲቀጥል፣ መሬትን በማሞቅ ህይወት እንዲቀጥል ማድረግ |
| 2 | የነፋስ ኃይል | |
| 3 | የከርሰ ምድር ሙቀት ኃይል | |
| 4 | የውሀ ዑደት | |
| 5 | ከባቢ አየር | |
| 6 | ጥዱፍ ውርድ (precipita-tion) | |

ታዳሽ የተፈጥሮ ሃብት በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ ራሱን በራሱ በተፈጥሮ ሂደቶች የሚተካና የሚያድስ በመሆኑ መስጠት የሚገባውን ሃብት ያለምንም ማቋረጥና መቀነስ መስጠት የሚችል የተፈጥሮ ሃብት ነው:: የስው ልጅ ተገቢ የሆኑ ወይም እንክብካቦሽን መሰረት ያደረጉ አጠቃቀሞችን በመከተል ታዳሽ ሃብቶችን ያለምንም ማቋረጥ መጠቀም ይችላል::

ታዳሽ የተፈጥሮ ሃብቶች በሰው ልጅ የዘመን አቆጣጠር ደረጃ ሊጠፉ የማይችሉ ናቸው:: ሃብቶቹ በርካታ በሆነ መጠን ይገኛሉ:: ስለሆነም የሰው ልጅ ከእነዚህ ሃብቶች የሚጠቀመው የሃብት መጠን ከአቅርቦታቸው አንፃር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው:: ስለዚህ የሰው ልጅ በእነዚህ ሃብቶች ላይ የሚኖረው አጠቃቀም አይወሰንም:: የማያልቁ የተፈጥሮ ሃብቶች አጠቃላይ የመሬት ውሃን፣ ከባቢ

አየርን፣ የተፈጥሮ ውበትን፣ ጥዱፍ ውርድን፣ የነፋስ ኃይልን፣ የባህር ሞገድንና ማዕበሎችን፣ የአቶሚክንና የከርሰ ምድር ሙቀት ኃይልን ይዘት ይይዛሉ:: እዚህ ላይ መታወቅ የሚገባው ጉዳይ የሰው ልጅ የማያልቁ የተፈጥሮ ሃብቶችን ሲጠቀም በመጠናቸውና በውስጣዊ ይዘታቸው ላይ ለውጥ ባያስከትልም በጥራታቸው ላይ ግን አሉታዊ የሆነ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል:: ይህም ማለት የተፈጥሮ ሃብቶችን ጥራት ሊጎዳ ወይም ሊያዛባ ይችላል ማለት ነው::



ምስል 1- የከርሰ ምድር ሙቀት



ምስል2- አዳማ የነፋስ ኃይል ማመንጫ

## ተግባር-4

1. ተማሪዎች! በምስል1 እና 2 ላይ ያሉትን የማያልቁ የሀይል ምንጮችን በየግላችሁ በትኩረት ተመልከቱ እና ስለእያንዳንዳቸው የተገነዘባችሁትን አብራሩ::

አንዳንዶቹ ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብቶች ደግሞ እርስ በእርሳቸው የሚደጋገፉ ናቸው:: በመሆኑም የአንደኛው ሃብት በአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ ደረጃ መነካት ሌሎቹም እንዲነኩ ያደርጋል:: ከአቅማቸው በላይ በጥቅም ላይ ከዋሉ ሊመናመኑ ወይም ሊጎዱ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊጠፉ ይችላሉ:: ምሳሌ እጸዋቶች፣ እንስሳት እና አፈር ናቸው::

## ተግባር-5

1. ተማሪዎች! የአካባቢያችሁ ማህበረሰብ በአካባቢያቸው የሚገኙ የዱር እንስሳትን እንዴት ይንከባከባሉ?

## ለ ኢ-ታደሽ የተፈጥሮ ሃብቶች

## ተግባር-6

1. "ሰንጠረዥ-3"ን በመጠቀም ከተዘረዘሩት ማእድናት በተጨማሪ እናንተ የምታውቋቸን በመዘርዘር ጥቅማቸውንም አብራሩ።

**ሠንጠረዥ 3- የማዕድናት አይነት እና ጠቀሜታ**

| ተ. ቁጥር | የማዕድናት ዓይነት | የሚሰጠው ጠቀሜታ |
|---|---|---|
| 1 | አልማዝ | ለጌጣጌጥ |
| 2 | መዳብ | ለኤሌክትሪክ ቁሳቁስ መስሪያ |
| 3 | ነዳጅ ዘይት እና የተፈጥሮ ጋዝ | |
| 4 | ዩራኒየም | |
| 5 | ቆርቆሮ | |

ኢ-ታዳሽ የተፈጥሮ ሃብቶች የሚባሉት በውስን መጠን የሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶች ሲሆኑ አንድ ጊዜ በጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ በነበሩበት ቦታ ላይ ራሳቸውን መተካት ወይም የሰው ልጅ እንደነበሩ ሊያደርጋቸው የማይችሉ ሃብቶች ናቸው። አንዳንዶቹ በጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ ሙሉ በሙሉ ይጠፋሉ። አንዳንዶቹ ግን የተሰሩባቸውን ቁሶች/እቃዎች/ ሲያረጁ እንደገና በማቅለጥና በመስራት በጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ስለዚህ ሃብቶቹ በሁለት ይመደባሉ።

ሀ) ምንም አማራጭ ካልተገኘ ሙሉ በሙሉ በጥቅም ላይ ሊውሉና ሊጠፉ የሚችሉ ሃብቶች፣

ምሳሌ፡ ነዳጅ ዘይት እና ኢ-ብረት አስተኔዎች.

ለ) ከተጠቀምንባቸው በኋላ እንደገና በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የተፈጥሮ ሃብቶች፡፡

ምሳሌ፡ ብረት-አስተኔዎች

በአጠቃላይ ኢ-ታዳሽ የተፈጥሮ ሃብቶች በጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ ራሳቸውን በራሳቸው አይተኩም፣ በመጠንም ሆነ በጥራት አይታደሱም፣ በሰው ልጅ የጊዜ ስሌት እንደገና እንደነበሩ አይሰሩም ምክንያቱም እነዚህ የተፈጥሮ ሃብቶች በብዙ መቶ ሚሊዮኖች ዓመታት ውስጥ በሚከናዎኑ ሥነ መሬታዊ፣ ፊዚካዊና ኬሚካዊ ሂደቶች የሚሰሩ በመሆናቸው ነው፡፡

የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠቀም ከሚረዱ ሁኔታዎች መካከል የካፒታል አቅም፣ የሚገኙበት ቦታ፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ የቴክኖሎጅ ሁኔታ፣ የመንግስት ፖሊሲ እና የሀብቱ ተፈጥሯዊ ሁኔታ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ ለመጠቀምና ለመንከባከብ ከሚረዱ ዘዴዎች መካከል የሕዝብ እድገትን መቆጣጠር፣ አማራጭ የኃይል ምንጮችን መጠቀም (የነፋስ ሀይል፣ ጅኦተርማል ሀይል፣ የፀሀይ ኃይል)፣ የእፅዋት ሽፋንን መጨመርና ያለውንም መጠበቅ፣ የተጋለጡ መሬቶችን መሸፈን እና ዘመናዊ የመሬት አጠቃቀም (የአፈርና ውሃ ጥበቃ፣ የእፅዋት ሽፋንን መጨመር፣ ጥብቅ ቦታዎችን) መከለል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

*ተግባር-7*

1. ተማሪዎች! ታደሽ የተፈጥሮ ሀብቶች ከኢ-ታዳሽ የተፈጥሮ ሃብቶች ጋር ያላቸውን ልዩነት በማወዳደር አብራሩ፡፡
2. የተፈጥሮ ሀብቶች ማህበረሰቡ በአግባቡ ለመጠቀምና ለመንከባከብ የሚጠቀማቸውን ዘዴዎች መረጃ በማሰባሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል አቅርቡ፡፡

## የተፈጥሮ ሃብቶች ጥቅም

የተፈጥሮ ሃብቶች ለመኖር አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችንና የደህንነት አቅም (ራስን የመከላከልና ሉዓላዊነትን የማስከበር አቅም፣ ህግና ደንብን የማስከበር አቅም፣

የእውቀትና የፈጠራ አቅም፣ ወዘተ…) እንዲኖር ያደርጋሉ:: የሰው ልጅ እነዚህን ሁኔታዎች ለማሟላትና ለማሳካት የተለያዩ ሃብቶችን ይፈልጋል:: የሰው ልጅ የሃብት ፍላጎቶች በሁለት ምድቦች ተከፍለው ይታያሉ:: እነዚህም የመጀመሪያ ደረጃ የሀብት ፍላጎቶችና ሁለተኛ ደረጃ የሃብት ፍላጎቶች ናቸው::

## ሀ) የመጀመሪያ ደረጃ የሃብት ፍላጎቶች

የመጀመሪያ ደረጃ የሃብት ፍላጎቶች መሰረታዊ የሆኑ የሃብት ፍላጎቶችን ያጠቃልላሉ:: የሀይል ሰጭ ምግቦች፣ ገንቢ እና በሽታ ተከላካይ ምግቦች ፍላጎት፣ አስፈሊጊ ማዕድናትን የያዘ ከበካይና ጎጅ ነገሮች ነፃ የሆነ ውሃ ፍላጎት፣ ከብክለት ነፃ የሆነና በቂ ኦክስጅን የያዘ ንፁህ አየር ፍላጎት፣ የተስተካከለ ዕለታዊ የአየር ሁኔታ የአለበት የአየር ንብረት ፍላጎት፣ ልብስና መጠለያ የሚሰራባቸው የተለያዩ ቁሶች ፍላጎት እና ለምግብ ማብሰያና ቤትን ለማሞቂያ የሚሆን የሀይል ፍላጎት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

## ለ) ሁለተኛ ደረጃ የሃብት ፍላጎቶች

እነዚህ ፍላጎቶች በመጀመሪያ ደረጃ የሃብት ፍላጎቶች የምንፈልጋቸውን ቁሶች በተፈሊጊ መጠንና ጥራት ለማግኘት እንዱሁም ለደህንነትና አቅምን በአስተማማኝ ደረጃ ለማደራጀት የሚያስችሉ የሃብት ፍላጎቶች ናቸው:: እነዚህ ፍላጎቶች የማዕድናትና የኃይል ምንጮች ፍላጎት፣ የሰው ልጅ የሳይንስና ቴክኖሎጅ ተሞክሮ ፍላጎት እንዲሁም ምርት የማምረት፣ የመለወጥና የፍጆታ ተግባራት የሚከናወኑባቸው ፍላጎት ናቸው::

### ተግባር-8

1. ተማሪዎች! ወደ ቤተ መጽሐፍት በመሄድ የተፈጥሮ ሀብቶች በሀገር ደረጃ የሚሰጡትን ምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ ጥቅሞች ትክክለኛ መረጃ በማሰባሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ::
2. በመጀመሪያ ደረጃ እና በ2ኛ ደረጃ የሀብት ፍላጎት መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት አብራሩ::

## 3.1.2. ከጊዜ ጋር የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም መለዋወጥ

### ተግባር-9

1. በአካባቢያችሁ በእንክብካቤ ጉድለት ምክንያት የተጎዱ የተፈጥሮ ሀብቶች አሉ? ካሉ ለክፍሉ ተማሪዎች ምን ምን እንደሆኑ ግለፁ::

እንደሚታወቀው ሁሉም የገፀ-ምድር ክፍሎች ለሰው ልጅ ጠቃሚ ሀብቶች ናቸው:: ሁሉም ክፍሎች ለሰው ልጅ ፍላጎቶች ማርኪያ የሆኑ ቁሳቁሶችን ለማምረት አስተዋጽኦ አላቸው:: ከዚህ እውነታ ስንነሳ ሰው የማይኖርባቸው ከባቢ አየር፣ ውቅያኖሶች፣ በርሃዎችና የዋልታ አካባቢዎች እንኳ ሳይቀሩ ለወደፊቱ ትውልድ እንዲተላለፉ በጥንቃቄ መያዝ የሚገባቸው በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሃብቶች ናቸው::

የጥንታዊ ሰው መሰረታዊ ፍላጎቶች ተፈጥሮ በምትለግሳቸው ሃብቶች የሚረኩ ነበሩ:: ምንም እንኳ የአሁኖቹ መሰረታዊ ፍላጎቶች ከጥንቶቹ ጋር ተመሳሳይ ቢሆኑም ከሕዝብ እድገት፣ ከስልጣኔ ምጥቀት፣ ከቴክኖሎጅና ከከተማዎች መስፋፋት ጋር በቁጥር በጣም ብዙ የሆኑ መሰረታዊ ያልሆኑ ፍላጎቶች /wants/ በማደግና በመስፋፋት ላይ ናቸው:: ስለዚህ የሰው ልጅ ለተፈጥሮ ሃብቶች ያለው ፍላጎት በየጊዜው እያደገ፣ እየተስፋፋ እና እየተለወጠ በመሄድ ላይ ነው:: የሰው ልጅ በአሁኑ ወቅት ሸቀጣ ሸቀጦችን (እቃዎችን) ለማምረትና ኃይልን ለማመንጨት ሲል እጅግ መጠነ ብዙ የሆኑ የተፈጥሮ ሃብቶችን በጥቅም ላይ ያውላል:: አጠቃቀሙን ስናይ ደግሞ እጅግ መጠነ ብዙ የሆነ ብክነት የተሞላበት ነው:: በመሆኑም በእነዚህ የተፈጥሮ ሃብቶች ላይ ግዙፍ የሆነ ጫና እያሳደረ ይገኛል:: ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ የዓለም ሃብቶች የሚሰጡትን ጥቅሞች ሊያቋርጡ የሚችሉበት ሁኔታ እንደሚኖር ይገመታል:: ስለዚህ ቀጣይ የሆነ የሃብትና የኃይል አቅርቦት በአስተማማኝ ደረጃ እንዲኖር ለማድረግ የእንክብካቤ ትግበራ ወሳኝ እየሆነ መጥቷል::

### ተግባር-10

1. ተማሪዎች! በአካባያቸሁ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶች በማህበረሰቡ የአጠቃቀም ጉድለት ምክንያት የሚጎዱበትን መንገድ በቡድን በመወያየት ለክፍሉ ተማሪዎች አቅርቡ::

## 3.1.3. የተፈጥሮ ሃብቶች እንክብካቤ እና ዘላቂ አጠቃቀም

### 1. የእንክብካቤ ምንነት


እንክብካቤ የተለያዩ ትርጉሞች ያሉት ሲሆን በሚከተለው መንገድ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

መዝገበ-ቃላታዊ ትርጉም፡ -

- ✍ እንክብካቤ የተፈጥሮ ሃብቶችን መጠበቅና ከአደጋ መከላከል ማለት ነው።
- ✍ እንክብካቤ የተፈጥሮ ሃብቶችን ከብልሽት፣ ከጉዳት፣ ያላግባብ ከመጠቀም፣ ከጥፋት፣ ከብክነትና ከመሳሰሉት መከላከል ነው።

ሌሎች ትርጉሞች፦

- ✍ እንክብካቤ የተፈጥሮ ሃብቶችን ለወደፊት ለመጠቀም ሲባል መጠበቅና ከአደጋ መከላከል ማለት ነው።
- ✍ እንክብካቤ የተፈጥሮ ሃብቶችን ለተፈላጊ ነገር፣ በሚፈለግ መጠን እና ለረጅም ጊዜ በአግባቡ መጠቀም ማለት ነው።
- ✍ እንክብካቤ የሰውን ልጅ ኑሮ ምቹ ለማድረግ የተፈጥሮ ቁሶችንና የኃይል ምንጮችን በአግባቡ መጠቀም ማለት ነው።
- ✍ እንክብካቤ ማለት እጽዋት፣ እንስሳትና ሌሎች ኢ-ህይዎታዊ ቁሶች የሚሰጡት ምርት እንዳይቋረጥና እንዳይቀንስ ማለትም ሚዛናዊ የሆነ ምርት የመስጠትና የመታደስ ሁኔታ እንዲቀጥል በሰው ልጅና በተፈጥሮ ሀብቶች መካከል መልካም ግንኙነት መፍጠር ማለት ነው።

|  |  |
| --- | --- |
| ምስል-3 ክትር | ምስል-4 በተጎዳ መሬት ላይ የተተከለ እፅዋት |

### ተግባር-11

1.. ተማሪዎች! ጥንድ ጥንድ በመሆን ምስል 3 እና 4ን በመመልከት እና በመወያየት ልዩነታቸውን እና አንድነታቸውን አብራሩ::

## 3.2 እንክብካቤ የጎደለው የሀብት አጠቃቀም እና የሚያስከትላቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች

### ተግባር-12

1. እንክብካቤ የጎደለው የሀብት አጠቃቀም ሲኖር ምን ሊከሰት ይችላል?
2. በአካባቢያችሁ ውሃ በምን በምን ይበከላል ብላችሁ ታስባላችሁ? እስኪ ለመግለፅ ሞክሩ::

የሰው ልጅ የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ ባለመጠቀሙ ምክንያት በአካባቢ እና በሰው ልጅ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን እያደረሰ ይገኛል:: ስለዚህ የእያንዳንዱን ተፈጥሮ ሀብት ችግር መነሻ በማድረግ አሉታዊ ተጽዕኖዎቹን እንደሚከተለው ማየት ይቻላል::

የውሃ ዋነኛ ችግሮች የውሃ ብክለት/Water Pollution/ እና እጥረት ናቸው::

ብክለት ማለት በሰውና በሌሎች ህይወታዊ ዘአካላት ጤንነት ወይም አኗኗር ወይም ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያደርስ ሲሆን በውሃ፣ በአየር፣ በአፈር ወይም በምግብ ፊዚካዊ፣ ኬሚካዊ እና ህይወታዊ ባህርያት ላይ የሚፈጠር አላስፈላጊ ለውጥ ማለት ነው።

ውሃ በተፈጥሮው ሽታ፣ ጣዕም እና ቀለም የለውም። ስለዚህ ንፁህ ነው። የውሃ ብክለት የሚያመለክተው በውሃ ውስጥ የውሃን ንጽህና ሊያበላሹ የሚችሉ የማይፈለጉ ነገሮች መኖር ማለት ነው። ስለዚህ የብክለት መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ባለመጠቀማችን ምክንያት ውሃው ለምንም ነገር በጥቅም ላይ ሊውል አይችልም። ከዋለም ህይወት ሊጎዳ ይችላል። ሌላው የውሀ ችግር ደግሞ የውሀ እጥረት ሲሆን ያለውን መጠነኛ ውሃ በአግባቡ፣ በቁጠባ እና ሳያባክኑ ባለመጠቀም የሚመጣ ችግር ነው። ስለዚህ በእጥረቱ የተነሳ በአካባቢው የሚገኙ እንስሳት እና እፅዋት የከፋ የውሃ እጥረት ስለሚያጋጥማቸው ይጠፋሉ ወይም ይደርቃሉ። በተጨማሪም ሰውም ሆነ ሌሎች እንስሳት ውሃ ፍለጋ ወደ ሌላ ቦታ ይሰደዳሉ ማለት ነው። ስለዚህ የውሃ እጥረትን በተመለከተ ምዕራፍ ሰባት በሰፊው ታዩታላችሁ ወይም ትማሩታላችሁ።



ምስል-5. የተበከለ ውሃ

እጽዋት ሰፋ ባለ መልኩ ደኖች፣ ሳሮች፣ እጽዋተ ጮቄ፣ የበረሃማ እጽዋትና የከፍታ ምድር እጽዋቶች በመባል ይመደባሉ። ከእነዚህ ውስጥ የሰው ልጅ በከፍተኛ ደረጃ ተጽዕኖ ያሳረፈባቸው ደኖችና ሳሮች ናቸው። እነዚህን በአግባቡ ባለመንከባከብ እና በአግባቡ ባለመጠቀም የሚመጡ አሉታዊ ተጽዕኖዎች በርካታ ናቸው። የእጽዋት መመናመንን በተመለከተ ምዕራፍ ሰባት በሰፊው ትማራላችሁ።


## ተግባር-13

1. ውሀን ማክም ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ይታከማል? መጽሐፍ በማንበብ ሪፖርት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡
2. ተማሪዎች! "ምስል-5"ን በአትኩሮት ተመልከቱ፡፡ በመቀጠል ከምስሉ የተረዳችሁትን ሀሳብ አጋሩ፡፡


የአፈር ዋነኛ ችግር የአፈር መሸርሸር (Soil Erosion) ነው፡፡ አፈር መሸርሸር በተንቀሳቃሽ ወኪሎች አማካኝነት አፈርን ከቦታ ቦታ የማንቀሳቀስ ወይም የማጓጓዝ ሂደት ነው፡፡ የአፈር መሸርሸር በተፈጥሮ ሂደት ውስጥ የማይቀርና አስፈላጊ የሆነ ሂደት ነው ምክንያቱም አዳዲስ አፈሮች እንዲሰሩ ከድንጋይ በላይ ያሉት አሮጌዎቹ አፈሮች መነሳት አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የአፈር መስራትና መከማቸት ሚዛን የተመጣጠነ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ነገር ግን አፈር መሸርሸር አፈሮች ከሚሰሩበት ሂደት ጋር ሳይመጣጠን በፍጥነት የሚከናወን ከሆነ አንድ በተፈጥሮ ያልተለመደ ተፈጥሮን የሚያቃውስ ነገር አለ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሁለት የአፈር መሸርሸር አገላለጾች ይኖራሉ፡፡ በመሆኑም አፈር መሸርሸር መደበኛ ወይም ጂኦሎጃዊ አፈር መሸርሸርና የተፋጠነ አፈር መሸርሸር በመባል ይታወቃሉ፡፡

መደበኛ ወይም ጅኦሎጂካል አፈር መሸርሸር- ይህ አፈር መሸርሸር በተፈጥሮ የሚከናወን ሂደት ሲሆን ከአፈር መሰራት ሂደት ፍጥነት ጋር የተጣጣመ ነው፡፡ ይህም የአፈር መሸርሸር ሂደት ከአፈር መሰራት ሂደት በመጠኑ ያነሰ ይሆናል ማለት ነው፡፡

የተፋጠነ አፈር መሸርሸር ማለት የተሰራ አፈር ከሚሰራበት ሂደት በፈጠነ ሁኔታ እየተጠረገ ይወሰዳል፡፡ የተፋጠነ አፈር መሸርሸር ሊከሰት የሚችለው በእጽዋት ሽፋን ላይ ተጽዕኖ ሊያደርስ በሚችል የአየር ንብረት ለውጥ ወይም በሰው ልጅ የሚከሰተው ደኖችን በማውደም፣ ሳሮችን ደጋግሞ በማስጋጥ እና በኋላቀር የአስተራረስ ዘዴዎች ምክንያት ነው፡፡ በተግባር እንደሚታወቀው ሁሉም የተፋጠነ አፈር መሸርሸር በሰዎች ጣልቃገብነት የሚፈጠር ነው፡፡ ስለዚህ የተፋጠነ አፈር መሸርሸር ሰው-ፈጠር አፈር መሸርሸር ይባላል፡፡ ይህ ደግሞ የአፈሩን ለምነት ያሳጣል እንዲሁም አጸዋቶች ጠቃሚ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን አያገኙም፡፡ ስለዚህ የግብርና ምርት ይቀንሳል ማለት ነው፡፡



ምስል 6- የተጎዳ መሬት



ምስል 7- የተጎዳ መሬት

## ተግባር-14

1. ተማሪዎች! ምስል 6 እና 7ን በአንክሮ ከተመለከታሁ በኋላ እያንዳንዳቸውን የመሬት ክፍሎች በምን በምን እንደተጎዱ እና የጉዳት መጠናቸውን መሰረት በማድረግ አወዳድሩ።

## ውስን ጥናት

### ኮንሶ

ኮንሶ ከአዲስ አበባ ደቡባዊ ምዕራብ ክፍል በ595 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ሲሆን ባጠቃላይ 9 ጎሳዎችን ይዛለች። በብዛት "አፋኾንሶ" የተባለ ቋንቋ የሚናገሩት ኮንሶዎች አስቸጋሪ የሆነውን መልክአ ምድር በባህላዊ እርከን አፈሩን ከመሸርሸር ጠብቀው ሰፊ በሆነ ግብርና የሚተዳደር ማህበረሰብ ነው። የኮንሶ ታታሪው ማህበረሰብ ድንጋያማ፣ ደረቅ፣ ተራራማ እና ወጣ ገባ የሆነውን መሬት በባህላዊ መንገድ እርከን እየሰሩ እና እያረሱ አፈሩ እንዳይሸረሸር በማድረግ ውጤታማ በመሆናቸው "Konso Cultural Landscape" በሚል በዩኔስኮ በ2011 ተመዝግቦ ይገኛል። የኮንሶ ህዝብ የሞራ የሚባል 3 የማህበረሰቡ መሰብሰቢያ አደባባዮች አሉአቸው። አንደኛው ከስራ በኋላ በዚህ አደባባይ ተሰባስበው ገበጣ የሚባለውን ጨዋታ እየተጫወቱ ጨቃ የተባለውን ባህላዊ መጠጥ እየጠጡ የሚዝናኑበት ነው።

ሁለተኛው የእምነት አገልግሎት የሚካሄድበት እና የተጣሉ ሰዎች ለመተማመን የሚማማሉበት ነው:: ሶስተኛው ደግሞ ትልቅ የዓመት በዓል የሚከበርበት ነው:: በኮንሶ ትልቅ ስራ ወይም ታሪክ ሰርቶ ላለፈ ሰው ሶስት ረጃጅም ድንጋይ የሚተከልላቸው ሲሆን እነዚህም ሰዎች ዋካዎች በመባል ይታወቃሉ:: በሌላ በኩል የኮንሶ ህዝብ ከትውልድ ትውልድ ስልጣን ሲረካከብ ኦላሂታ የሚባል የትውልድ ማስታወሻ የእንጨት ፖል ይተክላሉ::





ምስል-8 የኮንሶ እርከን ስራ

## ተግባር-15

1. ተማሪዎች አንዱ የተፈጥሮ ሀብት ሲጎዳ ሌላው የተፈጥሮ ሃብት ይጎዳል:: ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል በምሳሌ በማስደገፍ አብራሩ::
2. ስለኮንሶዎች የቀረበውን ምንባብ ካነበባችሁ በኋላ የቀረቡትን ምስሎች በአትኩሮት ተመልከቱ:: ቀጥላችሁ የተረዳችሁትን ሀሳብ የአካባቢያችሁ ማህበረሰብ ከሚያከናውነው የአፈር ጥበቃ ስራ ጋር በማዛመድ አብራሩ::

## 3.3. የተፈጥሮ ሀብቶች ተደራሽነት እና የግጭቶች አፈታት

### ቁልፍ ቃላት:

- ☞ ምጣኔ ሀብታዊ ግጭት
- ☞ ግለሰባዊ ግጭት
- ☞ ደርድር
- ☞ ቡድናዊ ግጭት
- ☞ ሽምግልና
- ☞ አለማቀፋዊ ግጭት
- ☞ ዳኝነት

### ተግባር-16

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ ሽምግልና ለምን ያስፈልጋል?

የተፈጥሮ ሀብቶች በሁሉም ቦታ ተደራሽ አይደሉም። አንዱ አካባቢ ስርጭቱ ክፍተኛ ሲሆን ሌላው አካባቢ ደግሞ ዝቅተኛ ወይም የሌለው ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች የተፈጥሮ ሀብት ውስንነት ሲያጋጥማቸው አንዳቸው ከአንዳቸው የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያደርጉት ጥረት ወደ ግጭት እንዲገቡ ምክንያት ይሆናሉ ማለት ነው።

### ሀ) የግጭት ምንነት እና አፈታት

ግጭት ምንድን ነው? መነሻውስ? ግጭት እንዴት ይፈታል? ወዘተ ለሚሉ ጥያቄዎች ቀጥተኛና ወጥ መልስ መስጠት ቢያዳግትም በተለያዩ የግጭት መስኮች ጥናት የሰሩ ምሁራንን መሰረት በማድረግ ስለጉዳዩ ማብራርያ መስጠት ይቻላል። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ግጭትን ‹‹ጥል ጠብ›› በሚል ይተረጉመዋል። የ “Lesiu” (1973) አማርኛ እንግሊዝኛ አውዳዊ መዝገበ ቃል ግጭትን ‹‹ትግል፣ ልዩነት፣ አለመስማማት፣ ጠብ፣ ውጊያ፣ አለመግባባት በማለት ይገልፀዋል።

## ለ) የግጭት መነሻ ምክንያቶች

ካርት የተባለው ምሁር ግጭት በሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ማለትም በኢኮኖሚ፣ በእሴት እና በስልጣን እንደሚከሰቱ ይገልፃል፡፡

ምጣኔ ሀብታዊ (Economic)፡ መነሻው ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ነው ስንል ቡድኖች ወይም ግለሰቦች የተፈጥሮ ሀብት ውስንነት ሲያጋጥማቸው አንዳቸው ከአንዳቸው የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያደርጉት ጥረት ወደ ግጭት እንዲገቡ ምክንያት ይሆናል ማለት ነው፡፡ ሁለቱ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ያላቸው ፍላጎት እየናረ ሲመጣ ይህን ፍላጐት ለማሳካት ፉክክር ውስጥ ስለሚገቡ መጨረሻቸው ግጭት ይሆናል፡፡

እሴቶች (Values):- ለዚህ ዓይነት ግጭት መነሻ ምክንያቶች በሰው ልጆች የአኗኗር ዘይቤ፣ የርዕዮተ ዓለም ምርጫና ፍላጐት መቃረን ማለትም የኑሮ መርህና እምነት መለያየት የሚፈጥሯቸው ናቸው፡፡ ይህም ማለት የአንድ ማህበረሰብ አመለካከትና እምነት ከሌላው ጋር አልጣጣም ሲል ወይም የሌሎችን የአኗኗር ዘይቤ በግድ እንዲከተሉ ጫና ሲደርስባቸው ይህ አይነቱ ግጭት ይፈጠራል፡፡

ስልጣን (Power)፦ ይህ የግጭት ዓይነት የሚፈጠረው አንድ ቡድን ወይም ግለሰብ በሌላኛው ቡድን ወይም ግለሰብ ላይ የበላይ ለመሆን ተፅዕኖ ሲያሳርፍ ነው፡፡ አንዱ ወገን በሌላኛው ላይ የበላይ ለመሆን የሚያደርገው ጥረት ሁሌም የግጭት መንስኤ ነው፡፡ ተፅዕኖ የደረሰባቸው ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች የተነጠቁትን የሀይል ሚዛን ወደ ራሳቸው ለማስመለስ ጥረት ማድረጋቸው ስለማይቀር የስልጣን ሽኩቻው ይኖራል፡፡ ይህ ግጭት እልባት የሚያገኘው አንዱ ወገን ተሸናፊነቱን ተቀብሎ የሌለኛውን ወገን የበላይነት ሲያምን ነው፡፡

## ሐ) የግጭት ዓይነቶች

የግጭት ዓይነት የተለያየ ቢሆንም "Fisher" እንደገለፀው በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ እነርሱም ግለሰባዊ፣ ቡድናዊ እና ዓለም አቀፋዊ በሚል ከፍሏቸዋል፡፡

1. ግለሰባዊ ግጭት (Interpersonal conflict)፦ ይህ የግጭት ዓይነት የሚፈጠረው ሁለት ሰዎች በፍላጎት፣ በዓላማ፣ በአቀራረብ፣ በተግባቦት ማጣጣም ሲያቅታቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ልዩነታቸውን ለማጥበብና የዓላማ ልዩነታቸውን አቻችለው ማስኬድ ከቻሉ በመካከላቸው ያለው ተቃርኖ ይቀንሳል፡፡

2. ቡድናዊ ግጭት (Intergroup conflict)፦ ይህ የግጭት ዓይነት አንድ አይነት አመለካከት፣ ባህልና ዝርያ ባላቸው ሰዎች የተፈጠረ ቡድን በተመሳሳይ ከተፈጠረ ከሌላ ቡድን ጋር የሚያደርጉትን ግጭትን ያጠቃልላል። ይህ አንድ ቡድን በሌላኛው ላይ የበላይ ለመሆን ሲፈልግ፣ ሲያገልና ሲንቅም የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው። መገለልና ንቀት የደረሰበት ቡድን ይህን የበታችነት ስሜት አምኖ ሳይቀበል ሲቀር ተቃርኖው የከፋ ይሆናል። በአቅም ውሱንነት ወይም በተለያዩ አመለካከቶች ሳቢያ ዝቅተኛነቱን አምኖ ሲቀበል ግን ግጭቱ ዘላቂ መፍትሄ ባይኖረውም ይረግባል።

3. አለማቀፋዊ ግጭት (International conflict)፦ እነዚህ ግጭቶች በአለምአቀፍ ደረጃ የሚታዩ ሲሆን በሀገራት መካከል የሚከሰቱ ናቸው። የእነዚህ ግጭቶች ምክንያት የተለያዩ ቢሆንም አንድ ሀገር በሌላኛው ሀገር ላይ የሚከፍተው ጦርነትና ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ ዋነኛ መገለጫዎቹ ናቸው።

### ተግባር-17

1. ተማሪዎች! በምትኖሩበት አካባቢ ስለግለሰባዊ እና ቡድናዊ ግጭቶች መነሻ ምክንያቶች ላይ መረጃዎችን ከታዋቂ ሰዎች በማሰባሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል አቅርቡ።

## መ) የግጭት አፈታት ዘዴዎች

በግጭት አፈታት ላይ የተለያዩ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ግጭት የሚፈታባቸውን ስልቶች በየራሳቸው መንገድ ያስቀምጣሉ። እንደ ኢምቦግሂ ገለፃ ዋና ዋና የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሚባሉት ድርድር፣ ሽምግልና እና ዳኝነት ናቸው።

**ሠንጠረዥ 4- የግጭት አፈታት ዘዴዎች እና ሂደቶች**

| ተ.ቁ | የግጭት አፈታት ዘዴዎች | ግጭቱ የሚፈታባቸው ሂደቶች |
|---|---|---|
| 1 | ሽምግልና | |
| 2 | ድርድር | |
| 3 | ዳኝነት | |

### ተግባር-18

1. ተማሪዎች! በቡድን እና በአለማቀፋዊ ግጭቶች መካካል ያለውን ልዩነት እና አንድነት አብራሩ::
2. ተማሪዎች! በሠንጠረዥ-4 መሰረት የአካባቢያችሁ ማህበረሰብ በአብዛኛው የሚገለገሉባቸው የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመግለፅ እንዴት እንደሚፈቱ ሂደቱን አብራሩ::

1. ድርድር /Negotiation/፦ ድርድር በግለሰብ፣ በቡድን፣ በብሄርና በሀገር መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ከሚያገለግሉ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች አንዱ ነው:: ይሁን እንጂ ዘዴው የሁለቱን ተቃራኒ ወገኖችን ፍላጐት ይፈልጋል:: ይህም ማለት ተቀራርቦ ለመነጋገርና ልዩነታቸውን በውይይት ለመፍታት መፈለግ ይኖርባቸዋል ምክንያቱም ሁለቱም ወገኖች ተስማምተው ወደ ድርድር ካልገቡ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም:: በመሆኑም አብዛኛውን ጊዜ ሁለቱን አካላት አቀራርቦ ለድርድር ዝግጁ የሚያደርግ ሶስተኛ ወገን የሚያስፈልግ ሲሆን ሂደቱም በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው::
2. ሽምግልና (Mediation)፦ ሽምግልና ከግጭት መፍቻ ዘዴዎች አንዱ ሲሆን የሁለቱም ወገኖች ይሁንታ የተሰጠው አካል ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚጓዝበት መንገድ ነው:: በዚህ የግጭት መፍቻ ስልት ሽምጋይ ሆኖ የሚቀርበው አካል ሶስተኛ ወገን ቢሆንም የመጨረሻው የእርቅ ውሳኔ የሚተላለፈው በሁለቱ አካላት የጋራ ስምምነት ነው:: ይህን የግጭት አፈታት ስልት ከድርድር የሚለየው በተጋጩት መካከል ገብቶ የማስታረቅ ስራ የሚሰራው ሽማግሌ ሁለቱን አግባብቶ ወደ ቀድሞው ሁኔታቸው ለመመለስ እስከ መጨረሻው ድረስ የሚሄድ መሆኑ ነው:: ድርድር ከአንዱ ወገን እንቢታ ሲሰማ ይቋረጣል:: ሽምግልናን ውጤታማ የሚያደርገው ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት ለሽምጋዩ የሚሰጡት ክብርና እውቅና ነው:: በሁለቱም ወገን ይሁንታ ካላገኘና ቃሉንም ለማክበር ዝግጁነት ከሌለ እርቁ ዘላቂ አይሆንም::

3. ዳኝነት (Arbitration)፦ ይህ ከላይ ከቀረቡት የግጭት ስልቶች የሚለየው ሶስተኛው ወገን ለግጭቱ እልባት ይሆናል የሚለውን ውሳኔ የመስጠት ህጋዊ አቅም ያለው መሆኑ ነው። በመሆኑም ሁለቱን ወገኖች በአንድ ላይ አወያይቶ ጥፋተኛ የተባለውን አካል ለይቶ ወደ ነበሩበት ሰላማዊ ጊዜ የሚመልስ ውሳኔ ያስቀምጣል እንዲሁም አጥፍቷል በተባለው ላይ ቅጣት ያስተላልፋል። ዳኝነት ከሌሎቹ የሚለየው ግጭት ውስጥ የገቡትን ይሁንታ ሳይፈልግ ጉዳዩን ማየቱና ህግን ተከትሎ ውሳኔ የመስጠት አቅም ያለው በመሆኑ ነው።

## ውስን ጥናት

### የአባይ ግጭት

አባይ የአለም ረጅሙ ድንበር ተሻጋሪ ወንዝ ሲሆን 11 ተፋሰስ ሀገራትን የሚያቋርጥ ነው። የወንዙ የላይኛው ተፋሰስ ሀገራት የሚባሉት ኢትዮጵያ፣ ታንዛንያ፣ ኡጋንዳ እና ኬንያ ሲሆኑ የመሀል ተፋሰስ ሀገራት ድግሞ ደቡብ ሱዳን፣ ኤርትራ፣ ሩዋንዳና ብሩንዲ ናቸው። በመጨረሻም የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት የሚባሉት ደግሞ ሱዳን እና ግብፅ ናቸው። የአባይ ገባር ወንዞች ነጭ አባይ እና ተከዜ (አትባራ) ወንዞች ናቸው። ነጭ አባይ ከታንዛንያ፣ ኡጋንዳና ኬንያ ድንበሮች አካባቢ ከሚገኘው ከቪክቶርያ ሀይቅ ተነስቶ ወደ አባይ ወንዝ የሚቀላቀል ሆኖ 15% ውሃ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

አባይ ደግሞ ከጣና ሀይቅ የሚነሳና 70% አካባቢ የውሃ ድርሻ ያለው ሲሆን ተከዜ ወንዝ ደግሞ ከሴቲት ወንዝ ገባሪነት ከኤርትራ እና ከኢትዮጵያ ተነስቶ በሱዳን በኩል አድርጎ አባይን የሚቀላቀልና 15% አስተዋጽኦ የሚያደርግ ነው። አባይና ተከዜ ከኢትዮጵያ ሉአላዊ ግዛት ተነስተው ካርቱምን አቋርጠው ግብፅ የሚገቡና 85% የውሀ ይዘት የሚሸፍኑ ናቸው። በአጠቃላይ አባይ ከነጭ አባይ ጋር በሱዳን ከተማ ካርቱም አካባቢ ይገናኙና ተቀላቅለው ግብፅን በማቋረጥ ሜዲትራንያን ባህርን ይገባሉ።

የአባይ ወንዝ ተፋሰስ ሀገራት ወንዙ የምጣኔ ሀብታዊ እድገት መሰረት እንደሆነ በማመን በዚሁ የተፈጥሮ ሀብት ተጠቃሚ ለመሆን ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች ጀምረዋል:: የአባይ ወንዝ ለቀጠናው ሀገራት የእርሻና የመስኖ ማልሚያ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ የውኃ አቅርቦትና የአሳ ልማት፣ የቱሪዝም መስህብና የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን በመገንዘብ ሀገራቱ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ገብተዋል:: ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫን በዋነኛነት የመስኖ ስራዎችን ደግሞ በመጠኑ ለማስፋፋት ታላቁ የህዳሴ ግድብን በመገንባት ላይ ትገኛለች:: ታንዛንያም ለንጹህ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት አላማ በቪክቶርያ ሀይቅ ላይ የጀመረችው የልማት እንቅስቃሴ ተጠቃሽ ነው:: ምንም የውሃ አስተዋጽኦ የሌላት ግብፅ ግን እነዚህ ሀገራት በውሃ ሀብታቸው ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እንቅፋት እየፈጠረች ትገኛለች::

ይህ የግብፅ አቋም በአንድ በኩል የሌሎች ተፋሰስ ሀገራት ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት መብት በሌላ በኩል የፈጠረውን ውጥረት በቀጠናው ላይ ግጭት እንዳይወልድ የአካባቢው ማህበረሰብ ስጋት ላይ ሲሆን በግብፅ መሪዎች በኩል የጦርነት ታምቡር ሲደለቅና የቀረርቶ ዘፈን ሲሰማ የነገሮችን አቅጣጫ ወደ ግጭት እየገፋ እንደሆነ መገመት ይቻላል::



ምስል-9. የታላቁ ህዳሴ ግድብ በአባይ ወንዝ ላይ

## ተግባር-19

1. የኢትዮጵያ እና የግብፅ በአባይ ወንዝ የሚያደርጉት አለመስማማት በየትኛው የግጭት አይነት ይመደባል? በየግላችሁ ካሰባችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።
2. ተማሪዎች! በምስል-9 ላይ ጥልቅ ውይይት በማድረግ ስለተመለከታችሁት ጉዳይ ማብራሪያ ስጡ።
3. ግብፅ የህዳሴውን ግድብ ብትቃወምም ኢትዮጵያ የአባይ ውሃ የመጠቀም ሙሉ መብት አለኝ በማለት አባይ ወንዝ ላይ ግድብ ገንብታለች። ምክንያቱ ምን ይመስላችኋል?

## ማጠቃለያ

- የተፈጥሮ ሀብቶች ማለት በተፈጥሮ የሚገኙ የሰው ልጅ እውቀቱን ተጠቅሞ ወደ ሀብት ሊለውጣቸው የሚችሉ ቁሳዊ እና ቁሳዊ ያልሆኑ ሀብቶች ናቸው። በዓለማችን ያደጉ፣ በማደግ ላይ ያሉና ደሀ ሀገራት ሁሉም የተፈጥሮ ሀብቶችን ተጠቅመው የህዝቦችን ፍላጎቶች ያሟላሉ።
- ለህይወት አስፈሊጊ የሆኑ የተፈጥሯዊ አካባቢ አባላት፤ ለሁለም ህይወታዊ ዘአካላት በቁሳዊነትና በኃይል ምንጭነት በጥቅም ላይ የሚውሉ ነገሮች፣ መሰረታዊና መሰረታዊ ያልሆኑ ፍሊጎቶችን ለማርካት የሚጠቅሙ በተፈጥሮ የሚገኙ የገፀ-መሬት ፀጋ የሆኑ ቁሶች ናቸው ማለት ይቻላል።
- ከተፈጥሮ ሃብቶች ትንታኔና እንክብክቦሽ እይታ አንፃር የተፈጥሮ ሃብቶች ብዛታቸውን፣ ሊጠፉ ወይም ላይጠፉ መቻላቸውን፣ ሊታደሱ ወይም ላይታደሱ መቻላቸውን ወይም የቱን ያህል ልንጠቀምባቸው ወይም ላንጠቀምባቸው መቻላችንን እንደ መስፈርት በመጠቀም የማያልቁ እና ሊያልቁ የሚችሉ የተፈጥሮ ሃብቶች ተብለው በሁለት ይመደባሉ። የሰው ልጅ የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ ባለመጠቀሙ ምክከንያት በአካባቢ እና በሰው ልጅ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን እያደረሰ ይገኛል። ስለዚህ የእያንዳንዱን የተፈጥሮ ሀብት ችግሮች መነሻ በማድረግ አሉታዊ ተጽዕኖዎቹን ለመቋቋም የተለያዩ የመንከባከቢያ ዘዴዎች መተግበር አለባቸው።

- የተፈጥሮ ሀብቶች በሁሉም ቦታ ተደራሽ አይደሉም። አንዱ አካባቢ ስርጭቱ ክፍተኛ ሲሆን ሌላው አካባቢ ደግሞ ዝቅተኛ ወይም የሌለውም ሊሆን ይችላል። ስለዘህ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች የተፈጥሮ ሀብት ውሱንነት ሲያጋጥማቸው አንዳቸው ከአንዳቸው የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያደርጉት ጥረት ወደ ግጭት እንዲገቡ ምክንያት ይሆል ማለት ነው።
- ዋና ዋና የግጭት መነሻ ምክንያቶች ሶስት ሲሆኑ አነርሱም የኢኮኖሚ፣ የእሴት እና የስልጣን ናቸው። የግጭት ዓይነቶች ደግሞ በሶስት ዋና ዋና ዋና ክፍሎች ሲመደቡ እነርሱም ግለሰባዊ፣ ቡድናዊና ዓለም አቀፋዊ በሚል ተከፍለዋል።
- በግጭት አፈታት ላይ የተለያዩ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ግጭት የሚፈታባቸውን ስልቶች በየራሳቸው መንገድ ያስቀምጣሉ። እንደ ኢምቦግሂ (Imboighe) ገለፃ ዋና ዋና የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሚባሉት ድርድር፣ ሽምግልና እና ዳኝነት መሆናቸውን አስቀምጧል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

*I. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ።*

1. ከባቢ አየር ከሚይዛቸው ውስጥ 99% የሚሆነው ናይትሮጅን እና ካረቦንዳይኦክሳይድ እንደሆኑ ተረጋግጧል።
2. ከተፈጥሯዊ ሀብቶች መካከል የአፈር ዋነኛ ችግር የአፈር ብክለት ነው።
3. ማንኛውም አግባብ ያለው የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና አስተዳደር በአጭር ጊዜ ውስጥ በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ጥፋት ያስከጥላል።
4. ማነኛውንም ግጭት በሽምግልና መፍታት ይቸላለል።
5. በሀሳብ አለመግባባት ለግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል።

*II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።*

1. ከሚከተሉት ውሰጥ የተፈጥሮ እፅዋት ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ) የካረቦንዳይኦክሳይድ እና የኦክስጅን ምጥጥን እንዲኖር ማስቻል

   ለ) ለኢንዱስትሪ ግብዓት መዋል መ) የአፈር መሸርሸርን መከላከል

ሐ) ለዱር እንሰሳት መጠለያ

ሠ) መልሱ አልተሰጠም

2. ከሚከተሉት ውስጥ ታዳሽ የተፈጥሮ ሃብቶች የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ) የከርሰ ምድር ሙቀት ሀይል ለ) በገፀ-ምድር ላይ የሚፈስ ውሀ

ሐ) የከርሰ ምድር ውሀ ሠ) መልስ የለም

መ) የባህር ሞገድ

3. የደኖች መመናመን ከሚያስከትለው የስነ-ምህዳር መቃወስ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ) የእፅዋት ዝርያዎች መጥፋት

ለ) የሲልት ክምችት መፋጠን

ሐ) ደኖች የእፅዋት መራቢያ ሁነው መቀጠላቸው

መ) የተፋጠነ የአፈር መከላት መኖር ሠ) መልስ የለም

*III. ለሚከተሉት ክፍት ቦታዎች በተስማሚው ቃላት ወይም ሀረግ ሙሉ::*

1. ____የሚፈጠረው አንድ ቡድን ወይም ግለሰብ በሌላኛው ቡድን ወይም ግለሰብ ላይ የበላይ ለመሆን ተፅኖ ሲያሳርፍ ነው::

2. _____ሶስተኛው ወገን ለግጭቱ እልባት ይሆናል የሚለውን ውሳኔ የመስጠት ህጋዊ አቅም ያለው ነው፡

3. ______በውስን መጠን የሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶች ሲሆኑ አንድ ጊዜ በጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ በነበሩበት ቦታ ላይ ራሳቸውን መተካት የማይችሉ ሃብቶች ናቸው::

4. ______የተፈጥሮ ሃብቶችን ከብልሽት፣ ከጉዳት፣ ያላግባብ ከመጠቀም፣ ከጥፋት፣ ከብክነትና ከመሳሰሉት መከላከል ነው::

*IV ለሚከተሉት ጥያቄች ማብራረያ ስጡ::*

*1. አንዱ የተፈጥሮ ሀብት ሲጎዳ በሌላው የተፈጥሮ ሀብት ተጽዕኖ ያሳድራል:: እንዴት? በምሳሌ አብራሩ::*

*2. የሰው ልጅ አካባቢን ለራሱ ምቹ ላማድረግ በአካባቢ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል ሲባል ምን ማለት ነው? በምሳሌ አብራሩ::*

# የቁልፍ ቃላት መፍቻ

የተፈጥሮ ሀብት፦ የሰው ልጅ እውቀቱን ተጠቅሞ ወደ ሀብት ሊለውጣቸው ሚችሉ ቁሳዊ እና ቁሳዊ ያልሆኑ ሀብቶች ናቸው።

እንክብካቤ፦ የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅ እና ከአደጋ መከላከል ማለት ነው።

ታዳሽ፦ የሰው ልጅ ሲጠቀምባቸው ሊቀንሱ፣ ሊጠፉ እና በተፈጥሮ ራሳቸውን ሊተኩ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው።

ኢ-ታዳሽ፦ በውስን መጠን የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ሲሆኑ የሰው ልጅ አንዴ ከተጠቀመባቸው በኋላ ከነበሩበት ቦታ ላይ ራሳቸውን መተካት የማይችሉ ናቸው።

# ምዕራፍ-4

# ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ማዕከላዊ መንግስት የምስረታ ሂደት የተጀመረበትን 1855 መነሻ ያደረገ ሲሆን የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነትን ለማስጠበቅ የተደረጉ ትግሎችን ይዳስሳል:: በዚህም ዋና ዋና የታሪክ ክስተቶችን ማለትም የአፄ ቴዎድሮስ አነሳስ፣ በአፄ ዮሐንስ 4ኛ እና በዳግማዊ አፄ ምኒልክ የአስተዳደር ዘመን የነበረውን የውጭ አገሮች ወረራ ላይ ያተኩራል:: በተጨማሪም ከአድዋ ጦርነት በኋላ በኢትዮጵያ የነበረውን ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊና ፖለቲካዊ ለውጦችን፣ የጣሊያንን ወረራ ዘመን (1936-1941) እንዲሁም የሶማሊያ ወረራ የዚህ ምዕራፍ ይዘቶች ናቸው::

*ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡-*

*ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-*

- ☞ *ዘመናዊ የኢትዮጵያን አመሰራረት ዘገባ ታቀርባላችሁ::*
- ☞ *የሲራራ የንግድ መስመሮችን በካርታ ላይ ታሳያላችሁ::*
- ☞ *ኢትዮጵያ ከውጪው ዓለም ጋር ስለነበራት ግንኙነት ትተነትናላችሁ::*
- ☞ *ኢትዮጵያዊያን የውጭ ወራሪዎችን ለመመከት ያደረጓቸውን ተጋድሎዎች ታደንቃላችሁ::*
- ☞ *በድህረ አድዋ ዘመን የታዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን ትገመግማላችሁ::*

# 4.1. የዘመናዊ ኢትዮጵያ ምስረታ

**ተግባር-1**

1. ዘመነ መሳፍንት ምን ዓይነት መገለጫዎች ነበሩት? የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

በኢትዮጵያ ከ1769-1855 ባለው ጊዜ ውስጥ ማዕከላዊ መንግስት በእርስ በርስ ጦርነት የተዳከመበት ዘመን ነበር፡፡ ይህ ዘመን "ዘመነ መሳፍንት" በመባል ይታወቃል፡፡ ዘመነ መሳፍንት ያከተመው በአፄ ቴዎድሮስ መነሳት ሲሆን ንጉሰ ነገስቱ ማዕከላዊ መንግስት ለመመስረትና ዘመናዊ ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡

## 4.1.1 የዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ዘመን (1855-1868)

### ሀ) የካሳ ኃይሉ አነሳስ

ካሣ ሀይሉ ከደጃዝማች ሀይሉ ወ/ጊዮርጊስና ከወይዘሮ አትጠገብ ቋራ ውስጥ በ1818 አካባቢ ተወለዱ፡፡ ከወላጆቻቸው ሞት በኋላ የልጅነት ጊዜያቸውን ከቋራው ገዥ ደጃዝማች ክንፉ ጋር አሳለፉ፡፡ ከደጃዝማች ክንፉ ጋር በነበሩ ጊዜ የቤተክህነት ትምህርት እና ሀገር በቀል ወታደራዊ ስልጠና አግኝተዋል፡፡ ደጃዘማች ክንፉ በ1839 ከሞቱ በኋላ ካሳ ኃይሉ ሸፈቱ፡፡ ከደጃዝማች ክንፉ ጋር በነበሩበት ወቅትና በሽፍትነት ዘመናቸው ወታደራዊ አደረጃጀትና የአስተዳደር ስራን ተለማምደዋል፡፡ በ1848 ከግብፆች ጋር የደበርኪ ጦርነትን ተዋግተው ለመጀመሪያ ጊዜ ተሸነፉ፡፡ ነገር ግን ይህ ሽንፈት የወደፊቱን የውጭ ፖሊሲ፣ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ እና ስነ-ስርዓት ያለው ሠራዊት ግንባታ ላይ የነበራቸውን እቅድ እንዲቀርጹ ምክንያት ሆኗል፡፡

ካሣ ላቅ ያለ የጦር ስትራቴጅ ዕውቀት ባለቤት መሆናቸውን ያስመሰከሩባቸው ተከታታይ ድሎችን በጎጃሙ ገዥ ደጅአዝማች ጎሹ ጉርአምባ ላይ በ1852፣ በብሩ አሊጋዝና በሌሎች ሶስት የደጅአዝማች ማዕረግ በነበራቸው ባላባቶች ላይ በጎርጎራ ቢችኝ በ1853 ድል አግኝተዋል፡፡ በ1853 በአይሻል ጦር ሜዳ የመጨረሻውን የየጁ ባላባት ትንሹ ራስ አሊን አሸነፉ፡፡ በ1855 የስሜኑን ጠንካራ ገዥ ደጅአዝማች ውቤን ደራስጌ ላይ በማሸነፍ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉስ ነገስት ዘኢትዮጵያ በመሆን በደራስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በአቡነ ሠላማ ተቀብተው ዘውድ ደፉ፡፡




ምስል 1፡ ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ እና ዘውዳቸው

## ለ) ዳግማዊ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን አንድነት ለመመለስ ያደረጉት ጥረት

አፄ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ አንድነት ለማምጣት የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደዋል። በዚህም መሠረት ከፓትሪያርኩ ጋር በመሆን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ዕምነት የኢትዮጵያ ሃይማኖት እንዲሆን ሞክረዋል። ቴዎድሮስ በወሎ፣ ጎጃም፣ ሸዋ እና ትግሬ ግዛቶች ተከታታይ ወታደራዊ ዘመቻዎችን በማካሄድ የአካባቢ ባላባቶችን አስወግደው የራሳቸውን ታማኝ የአካባቢ ገዥዎችን ሰይመዋል።

ብዙ ዘመናዊ ለውጦችን ለማምጣት አልመው የተነሱት አፄ ቴዎድሮስ በቤተክህነት ውስጥ የነበረውን ክፍፍል እና ገበሬው በሽፍታና በወታደር መዘረፉን ለማስቆም ታግለዋል። በተጨማሪም ባርነትን፣ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባትን እና ሌሎች ጎጂ ማህበራዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ ጥረዋል። የአውሮፓን የቴክኖሎጂ ዕድገት በኢትየጵያ በማምጣት ህዝቡ እንዲሰለጥን ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ከሁሉም በላይ አፄ ቴዎድሮስ አንድነቷ የተጠበቀ፣ ጠንካራ መስተዳድር ያላትና የውጭ ወረራን መቋቋም የምትችል ኢትዮጵያን ለመገንባት ደክመዋል።

አፄ ቴዎድሮስ ሊያሳኩ ከፈለጓቸው ዘመናዊ ለውጦች መካከል ደመወዝ የሚከፈለው ቋሚ ሰራዊት መገንባት፣ የጦር መሳሪያ ማምረት፣ እና ሌሎችም ነበሩ። ይህንንም ለማሳካት የመንግስትን ገቢ ለማሳደግ አስበው ነበር። ከግብር ነፃ ከነበረው የቤተክርስቲያን መሬት ላይ ግብር ለመሰብሰብ ሞክረዋል። እንዲሁም በአንድ ቤተክርስቲያን 2 ቄሶችና 3 ዲያቆናት ብቻ በቂ ናቸው በማለት ትዕዛዝ

አስተላልፈዋል፡፡ ካህናቱም ድርጊቱን በጽኑ በመቃወም በንጉሱ ላይ ስም የማጥፋት ዘመቻ ከፈቱ፡፡ ሀገራቸውን ለማዘመን ካላቸው ፍላጎት በመነሳት በአውሮፓ ቴክኒካዊ እርዳታ መድፍና ጠመንጃ ለማምረት በተለይም ለእንግሊዝ መንግስት ተደጋጋሚ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ከአውሮፓ የሰለጠነ የሠው ሀይል ለማግኘት ያደረጉት ያላሰለሰ ጥረት ፍሬ አልባ በመሆኑ አፄ ቴዎድሮስ በሀገራቸው የሚገኙትን የአውሮፓ ሚሲዮናዊያንን ሰብስበው በማሰር ጋፋት (ደብረታቦር አጠገብ) ባቋቋሙት የብረታብረት ማቅለጫ ማዕከል ጠመንጃና መድፍ እንዲሠሩ አዘዙ፡፡ ሚሲዮናዊያኑም ከኢትጵያውያን ባለሙያዎች ጋር በመሆን ጠመንጃዎችን እና መድፎችን የሠሩ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ ሴባስቶፖል ይባላል፡፡



ምስል 2፡ ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ያሰሩት ሴባስቶፖል መድፍ

አፄ ቴዎድሮስ አላማቸውን ለማሳካት በወሰዱት እርምጃ ምክንያት በሀገር ውስጥና በውጭ ጠላቶቻቸው በረከቱ፡፡ የአካባቢ ገዥዎችን በሀይል ለማንበርከክ መሞከራቸው ተቀናቃኞቻቸውን ስላበዛው ተደጋጋሚ ወታደራዊ ዘመቻዎች ለማካሄድ ተገደዋል፡፡ በ1867 በአወጧቸው አዋጆች እና ባደረጉት ተደጋጋሚ ወታደራዊ ዘመቻ የተሰላቸው የአፄ ቴዎድሮስ ሠራዊት ቁጥሩ በጣም ቀንሶ ነበር፡፡

በዚህ ወቅት እስረኞች እንዲፈቱ እንግሊዝ በተደጋጋሚ መልክተኛ ብትልክም ንጉሰ ነግስቱ ጥያቄውን አልተቀበሉትም ነበር፡፡ በመሆኑም በ1868 እንግሊዝ በጀኔራል ሮበርት ናፒየር የሚመራ ሠራዊት ወደ ኢትዮጵያ ላከች፡፡ ለእንግሊዝ ጦር አቅጣጫ በማሳየትና ተባባሪ በመሆን የዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ መንግስት እንዲወድቅ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት የትግሬ ገዥ ደጃዝማች ካሳ ምርጫ ነበሩ፡፡ ለተደረገላቸው ውለታም የእንግሊዝ ጦር ለካሳ ምርጫ በርካታ የጦር መሳሪያ እና ሙያተኛ ሰጧቸው፡፡ ከሙያተኞች ውስጥ የጦር አማካሪ ሆነው ያገለገሉት

ኪረከሀም አንዱ ናቸው፡፡ በሁለቱ ሀይሎች መካከል የመጀመሪያውና የመጨረሻው ታላቅ ጦርነት የተካሄደው መቅደላ አምባ ስር በሚገኘው እሮጊ ሜዳ ላይ ኤፕሪል 10/1868 ነበር፡፡ በጦርነቱ በፊታውራሪ ገብርየ የሚመራው የአፄ ቴዎድሮስ ሠራዊት ላይ ከባድ ጉዳት ከመድረሱ በተጨማሪ የጦሩ መሪም ተሰውተዋል፡፡ ይህ ክስተት በአካባቢ ገዥዎችና በካህናቱ ተቃውሞ የተዳከሙትን የአፄ ቴዎድሮስን ውድቀት አፋጠነው፡፡ የእንግሊዞችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እጅ ስጥ ጥያቄ ባለመቀበል ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ኤፕሪል 13/1868 ራሳቸውን በሽጉጣቸው ገደሉ፡፡ እንግሊዞች ካደረሱት ውድመት በተጨማሪ ከፍተኛ የቅርስ (የንጉሰ ነገስቱን ዘውድ ጨምሮ በሌሎችም ቅርሶች) ላይ ዘረፋ ፈፅመዋል፡፡

ምንም እንኳ ከአፄ ቴዎድሮስ ህልፈት በኋላ አለመረጋጋትና የስልጣን ሽኩቻ ቢሰፍንም ወደ ዘመነ መሳፍንት የመመለስ ሁኔታ ግን አልነበረም፡፡ በቀጣይነት የተካሄዱት ጦርነቶች ለንጉሰ ነገስትነት እንጂ ወደ ዘመነ መሳፍንት ለመመለስ አይደለም፡፡ ዘውዱን ለመድፋት ተፎካካሪ የነበሩት የላስታው ዋግሹም ጎበዜ ገብረ መድህን፣ የትግራዩ ካሳ ምርጫ እና የሸዋው ንጉስ ምኒልክ ነበሩ፡፡ ተተኪዎቻቸው የተዋሃደች ኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ለመሆን መፈለጋቸው ከአፄ ቴዎድሮስ የወረሱት ህልም ነበር ማለት ይቻላል፡፡ አፄ ቴዎድሮስ በሕይወት ባይኖሩም እንኳ የውህደት ሀሳባቸው ግን በኋላ በዳግማዊ አፄ ምኒልክ እውን ሆኗል፡፡

## ተግባር-2

1. አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ለማዋሃድ ከተጠቀሙት ስልት ምን ተማራችሁ?
2. እንግሊዞች አፄ ቴዎድሮስን ካሸነፉ በኋላ ኢትዮጵያን ለምን በቅኝ ግዛት አልያዙም?
3. የዘመናዊት ኢትዮጵያ ምስረታ እውን ለማድረግ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በግል ዘርዝሩ፡፡
4. አፄ ቴዎድሮስ የወሰዷቸው እርምጃዎች ትክክል ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ? በቡድን ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡
5. ስለ አፄ ቴዎድሮሰ ዘመን በመማራችሁ ያገኛችሁትን ጥቅም ለክፍል ጓደኞቻችሁ ማብራሪያ ስጡ፡፡

## 4.1.2. የአፄ ዮሐንስ 4ኛ ዘመን (1872-1889)

**ተግባር-3**

1. ተማሪዎች ከመቅደላ ጦርነት በኋላ በአፄ ቴዎድሮስ ስለተተኩት ንጉሰ ነገስት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።

ከመቅደላ ጦርነት በኋላ ዘውድ የደፉት ዋግሹም ጎበዜ ገብረ መድህን ሲሆኑ በንግስና ስማቸውም አፄ ተክለጊዮርጊስ (1868- 1871) በመባል ይታወቃሉ። ነገር ግን በጁላይ 1871 ትግራይን ለማስገበር በዘመቱበት ወቅት በአሰም ጦርነት ካሳ ምርጫን ገጥመው ተሸንፈው ተማረኩ። ካሣ ምርጫ በጥር 1872 አፄ ዮሐንስ 4ኛ በመባል የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ሆኑ።



ምስል 3፦ አፄ ዮሐንስ 4ኛ

በአፄ ቴዎድሮስ የተጀመረው የማዕከላዊ መንግስት ምስረታና የኢትዮጵያን አንድነት የማስጠበቅ ሙከራ በአፄ ዮሐንስ 4ኛ ዘመንም ቀጥሏል። እንደ አፄ ቴዎድሮስ ሁሉ አፄ ዮሐንስም ሀገርን የማዋሃድ ጥረታቸውን የቀጠሉ ሲሆን በጎንደር፣ ጎጃም፣ የጁ እና ሐማሴን ለማስገበር ዘመቻ አካሄደዋል። አፄ ዮሐንስ ከአዳል ተሰማ (ንጉስ ተክለ ሃይማኖት) ጋር ሠላም በማውረድ የጎጃም ገዥነታቸውን ተቀበሉ። በተጨማሪ በ1881 ተክለ ሃይማኖት በሚል ስም የጎጃምና ከፋ ንጉስ በማድረግ

አነገሷቸው። አፄ ዮሐንስ ዘውድ በደፉበት ወቅት ንጉስ ምኒልክ ራሳቸውን ንጉሰ ነገስት በማለት ይጠሩ የነበረ ሲሆን ግዛታቸውንም ወደ ወሎ በማስፋፋት ከውጪ መንግስታት ጋር በግል ግንኙነት ማድረግ ጀምረው ነበር። ለንጉሰ ነገስቱም ግብር አይከፍሉም ነበር። አፄ ዮሐንስ ከንጉስ ምኒልክ ጋር የነበራቸው ልዩነት በሜይ 20/1878 በተፈፀመው የልቼ ስምምነት ተቋጨ። በልቼ ስምምነት መሠረት ንጉስ ምኒልክ ለዮሐንስ ግብር ለመክፈል፣ ንጉሰ ነገስት የሚለውን ማዕረግ በመተው የሸዋ ንጉስ የሚለውን ለመጠቀምና ከውጭ ሀይሎች ጋር በግል የሚያደርጉትን ስምምነት ለማቆም ተስማምተዋል። ስምምነቱን ተከትሎ ንጉስ ምኒልክ ከሸዋ በተጨማሪ ወሎን እንዲያስተዳድሩ ተሰጥቷቸዋል። በተጨማሪም ሁለቱም የጋራ ጠላቶቻቸው ላይ ተመሳሳይ አቋም ለመያዝ ተስማምተዋል።

አፄ ዮሐንስ በፖለቲካው ያሳዩት መለሳለስ በሃይማኖታዊ ጉዳዮች አላሳዩም። የሃይማኖት ልዩነትን በተመለከተ በሜይ 1878 በጠሩት የቦሩ ሜዳ የሃይማኖት ጉባኤ የተለያዩ እምነት ተከታዮች ልዩነታቸውን በውይይት እንዲፈቱ ጋበዙ። የሃይማኖት ውይይት ከተደረገ በኋላ በቦሩ ሜዳ ጉባኤ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ብቸኛው እምነት እንዲሆን ታወጀ። ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች እና የሌሎች እምነት ተከታዮች ኦርቶዶክስ ተዋህዶን እንዲቀበሉ ቢታወጅም የግዴታ የሃይማኖት ለውጥ ትዕዛዝ በዋናነት ያተኮረው ግን በወሎ ነበር። ይህ ውሳኔ የተላለፈበት ዋናው ምክንያት የሀገር አንድነትን ለማስጠበቅ የሃይማኖት አንድነት ወሳኝ ሚና አለው ብለው ስለሚያምኑም ጭምር ነበር። በውሳኔው መሰረት የኦርቶዶክስ እምነት ያልተቀበሉት እርምጃ ተወስዶባቸዋል። በመሆኑም የወሎ ሙስሊሞች ሀብት ንብረታቸውን ተነጥቀው ወደ ሌላ አካባቢዎች ለምስሌ፦ ወደ ጅማ፣ ባሌ፣ ጉራጌ ወዘተ ተሰደዋል።

## ተግባር-4

1. አፄ ዮሐንስ በፖለቲካው እና በእምነቱ ዙሪያ የነበራቸውን አቋም በቡድን በመገምገም የደረሳችሁበትን ስምምነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።
2. የልቼ ስምምነት ዋና ዋና ነጥቦችን ዘርዝሩ።
3. የአፄ ዮሐንስ አራተኛ ሀገርን የማዋሃድ ስትራቴጂ ምን ይመስላል?

# 4.2. የ19ኛው ክፍለ ዘመን የሲራራ ንግድ

## ቁልፍ ቃል


- ☞ የሲራራ ንግድ

### ተግባር-5

1. የወረቀት ገንዘብ ከመታተማቸው በፊት ዋና ዋና የመገበያያ ግብአቶች ምን ምን እንደነበሩ ዘርዝሩ፡፡

በኢትዮጵያ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ንግድ ወሳኝ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ነበር፡፡ ይህ የንግድ እንቅስቃሴ የአካባቢ,ና የሲራራ ንግድ በመባል ይታወቃል፡፡ የንግድ ልውውጡ ሲካሄድ የነበረው በዋናነት ሸቀጥን በሸቀጥ በመለወጥ ነበር፡፡ በተጨማሪም እንደ አሞሌ ጨው እና የመሳሰሉ ሸቀጦች እንደመገበያያ ገንዘብ በመሆን ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በኢትዮጵያ እንዲሁም በአፍሪካ ቀንድ ለነበሩ የተለያዩ ህዝቦች ንግድ ዋና የግንኙነታቸው መድረክ ነበር፡፡ ለብዙ ህዝቦች የኢኮኖሚ መሠረታቸው ንግድ ነበር፡፡ የሲራራ ንግድ ኢትዮጵያን ከውጭው ዓለም ጋር የሚያገናኝ እንቅስቃሴ ነበር፡፡

የሲራራ ነጋዴዎች ረጅም ርቀት ዘልቀው ስለሚሄዱ በቡደን በቡድን ተደራጅተው ይጓዙ ነበር፡፡ የቡድኑ አለቃ ነጋድራስ ተብሎ ይጠራል፡፡ የነጋድረስ ዋና ተግባሩ ጉዞውን ማስተባበር፣ የሚያርፉበትን ቦታ መምረጥ እና ረጅም ርቀት አቋርጠው ስለሚጓዙ ማንኛውንም አዳጋ ለመከላከል ቡድኑን ማስተባበር ነበር፡፡ ከቦንጋ የሚነሳው የሲራራ ንግድ መስመር የተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎችን የሚያቋርጥ ነበር፡፡ ከቦንጋ ወደ ጂረን እና ሰቃን አቋርጦ አንዱ ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ማለትም አሰንዳቦ-ባሶ-ዳሪታ-ይፋግ-ጎንደር ይቀጥልና አንዱ ወደ መተማ ሲሄድ ሁለተኛው በአድዋ ወደ ምፅዋ ይሄዳል፡፡ ሌላው ከሰቃ ተነስቶ ወደ ሶዶ-አልዩአምባ-አብዱልረሱል-ሀረር ዘይላ እና በርበራ ይገባል፡፡




ምስል 4- የ19ኛው ክፍለ ዘመን የንግድ መስመሮች (ምንጭ፡ ባህሩ ዘውዴ፣ 2002)

## ተግባር-6

1. መፅሐፍትን በማንበብ ወይም ሰዎችን በመጠየቅ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልካቸውን እና ወደ ሀገር ውስጥ የምታስገባቸውን ዋና ዋና ምርቶች በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡
2. በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልካቸውን እና ወደ ሀገር ውስጥ የምታስገባቸውን ዋና ዋና ምርቶች በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

# 4.3. ኢትዮጵያውያን ለሀገር አንድነትና ሉዓላዊነትን ለማስጠበቅ ያደረጉት ትግል

## 4.3.1. የግብፅ መስፋፋት እና የኢትዮጵያ ምላሽ

### ተግባር-7

1. የኢትዮጵያና የግብፅ ቀደምት ግንኙነት ምን ላይ የተመሰረተ ነበር?

ኢትዮጵያና ግብፅ በባህል፣ በንግድና በሃይማኖት የረዥም ጊዜ ግንኙነት ነበራቸው:: ነገር ግን ግብፅ በ19ኛው ክፍለ ዘመን በጀመረችው መጠነ ሠፊ የግዛት ማስፋፋት ዘመቻ የአፍሪካን ቀንድ እንዲሁም የአባይ መነሻ የሆነችውን ኢትዮጵያን የሚያካትት በመሆኑ ግንኙነታቸው ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል::

የግብፅ መሪዎች የዘመናት ምኞት የአባይ ወንዝ ተፋሰስን መቆጣጠር ነበር:: በዚህም መሠረት የመሐመድ ዓሊ መንግስት በ1821 ሱዳንን ተቆጣጠረ:: የአባይ ወንዝ መነሻ እንደመሆኗ መጠን ኢትዮጵያም የግብፅ ወረራ ሠለባ ሆናለች:: ሱዳንን መነሻ በማድረግ ግብፅ ቀስ በቀስ የኢትዮጵያ ሰሜን ምዕራብ ግዛቶች ማለትም ስሜን፣ ደምቢያ እና የአሶሳ ሼክደሞች (Shiekdoms) ላይ ጥቃት ፈፀመች:: የግብፅ የመጀመሪያው የመስፋፋት አደጋ ኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንት የፖለቲካ ምስቅልቅል ውስጥ ሆና ቢሰነዘርም የአካባቢ ገዢዎች ለመመከት ጥረት አድርገዋል:: ግብፃዊያን በኢትዮ-ሱዳን ድንበር የሚገኘውን ህዝብ ከባድ ቀረጥ በመጣል፣ በባርነት በመውሰድ፣ ቤትና ሰብሎቻቸውን በማቃጠል ጥፋት አድርሰዋል:: የግዛት ማስፋፋቱ ተባብሶ በ1872 የግብፅ ወታደሮች ሌሎች የቀይ ባህር ወደቦችን በመያዝ ምጽዋንና የምጽዋ አዋሳኝ ግዛቶችን እንዲሁም የቦጎስ አካባቢዎችን ተቆጣጠሩ:: ከዲቭ እስማኤል ፓሻ (1863-79) የረዥም ጊዜ ዓላማ ለማሳካትና ታላቋ ግብፅን በሰሜን አፍሪካ ለመገንባት የአባይ መነሻን መቆጣጠር በሚል እሳቤ የኃይል እርምጃ ነድፎ ተነሳ:: ለዚህ የወረራ ዕቅድ የአውሮፓውያንን ድጋፍ ለማግኘት “የምዕራባዊያንን ስልጣኔ ለማስፋፋትና የባሪያ ንግድን ለማስቆም” የሚል እቅድ አወጣ::

የመጀመሪያው የግብፅ ወራሪ ሀይል በመሀመድ ራውፍ ፓሻ መሪነት የሐረር ከተማን በ1875 ተቆጣጠረ:: ሁለተኛው ወርነር ሙንዚንገር የተባለ የስዊዘርላንድ

እና ጀርመን ተወላጅ እንዲሁም በኢትዮጵያ የግብፅ ወረራ ዕቅድ አውጪ ከታጁራ ተነስቶ ወደ መሀል ሀገር ገሰገሰ። ነገር ግን የሙንዚንገር 500 ሠራዊት ሸዋ ከመድረሱ በፊት በአፋር ህዝብ ተደመሰሰ። ሦስተኛ በደንብ የታጠቀውና በዴንማርካዊ ኮሎኔል አረንድረፕ የሚመራው ሀይል የመረብ ምላሽን ክልል በማቋረጥ 1875 የመረብ ወንዝ ዳርቻ ላይ ደረሰ።

አፄ ዮሐንስ ጉዳዩን በሰላም ለመፍታት ያደረጉት ጥረት ባለመሳካቱ ወደ ጦርነት ገቡ። ንጉሰ ነገስቱም የክተት አዋጅ አወጁ። ንጉሰ ነገስቱ ባደረጉት የክተት አዋጅ 20,000 የሚገመት ጦር ምላሽ ሰጥቶ ነበር። አፄ ዮሐንስ ጦሩን እየመሩ መረብ ወንዝን አቋርጠው ኖቨምበር 16/1875 የጉንደትን ጦርነት ተዋጉ። በጦርነቱም ኮሎኔል አረንድረፕና በርካታ ግብፃዊያን ተገደሉ እንዲሁም የጦር መሳሪያዎች ተማረኩ። ግብፅ አሳፋሪ ሽንፈት ብትከናነብም በጉንደት ድል ምክንያት ከኢትዮጵያ የያዘቻቸውን ግዛቶች ለቃ አልወጣችም። ከዲቭ ኢስማኤል ለሌላ ዙር የብቀላ ጦርነት መዘጋጀት ጀመረ። በቀጣዩ ዓመትም በደንብ የታጠቀና በመሀመድ ረቲብ ፓሻ እና በአሜሪካዊው ጀኔራል ሎሪንግ የሚመራው ጦር የሰሜናዊ ኢትዮጵያ ግዛቶችን ወረረ። ሁለተኛው የኢትዮ-ግብፅ ጦርነት ጉራዕ በሚባል ከጉንደት አቅራቢያ ላይ ከማርች 7-9/1876 ተደረገ። በጦርነቱ ግብፅ ዳግም ተሸነፈች።

የግብፅ ሽንፈት ከባድ የፖለቲካ ኪሳራ ሲሆን በ1879 ከዲቭ እስማኤል ከሥልጣን ከመውረዱም በተጨማሪ በ1882 በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሥር ወደቀች። ግብፅ በጦርነቱ ብትሸነፍም እንደ ኢትዮጵያ ያለች ሉዓላዊት ሀገር የማትቀበለውን ሀሳብ አቀረበች። ከነዚህም ውስጥ የጦር ካሳ እንዲከፈላት፣ የጦር ምርኮኞቹ እንዲፈቱ፣ የተማረኩ የጦር መሳሪያዎች እንዲመለሱ እና የተያዙትን ግዛቶች ኢትዮጵያ መጠየቅ እንድትተው የሚሉ ነበሩ። በእነዚህም ምክንያቶች ግጭቱን በሰላም ለመፍታት የማይታሰብ በመሆኑ ሠላምም ጦርነትም የሌለበት ሁኔታ ተፈጠረ።

በ1880ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ግብፅ ከኢትዮጵያ ጋር ዲፕሎማሲያዊ ህብረት መፍጠር ፈለገች። ለዚህ የአቋም ለውጥ ሁለት ክስተቶች አስተዋጽኦ አድርገዋል። የመጀመሪያው ግብፅ ከ1882 ጀምሮ በእንግሊዝ መያዟ ነበር። ሁለተኛው በሱዳን የሃይማኖታዊና ብሔርተኛ ንቅናቄ በማህዲስቶች ተነስቶ የግብፅን ጦር በመበታተን ሱዳንን ተቆጣጠረ። ከምዕራብ ሱዳን የተጀመረው የማህዲስቶች ጥቃት የግብፅን ጦር በማሸነፍ የተወሰኑ የግብፅ ወታደሮችን በኢትዮ-ሱዳን ድንበር ከበቡዋቸው። ግብፅና ቅኝ ገዢዋ እንግሊዝ የማህዲስቶችን ጥቃት ማስቀም ስለተሳናቸው የተከበበውን ሠራዊት ለማስለቀቅ ሌላ ዘዴ መፈለግ ጀመሩ። በዚህም መሠረት

እንግሊዞች ኢትዮ-ግብፅ ግጭትን በሠላም ውል በመቋጨት የኢትዮጵያን እርዳታ መጠቀም ፈለጉ። ለዚህም የእንግሊዙ መልዕክተኛ ሪር አድሚራል ሰር ዊሊያም ሒወት ከአፄ ዮሐንስ ጋር 1884 የሒወት (አድዋ) ስምምነት የተባለውን ተፈራረሙ። የስምምነቱ የመጀመሪያ አንቀፅ ኢትዮጵያ የምጽዋን ወደብ በነፃ መጠቀም እንደምትችል የሚገልጽ ነበር። ሁለተኛው ኢትዮጵያ የተያዙባት ግዛቶች እንደሚመለሱላት ይጠቅሳል። በሶስተኛው አንቀጽ ኢትዮጵያ የተከበበውን የግብፅ ጦር በግዛቷ በኩል ወደ ምጽዋ ከዚያም ወደ ግብፅ እንዲወጣ ለማገዝ ቃል መግባቷን ያትታል።

የሒወት ስምምነት ለኢትዮጵያ የባህር በርና የተያዙባትን ግዛቶች የሚያስመልስ ቢሆንም ኢትዮጵያን የማህዲስቶች ጠላት አደረጋት። አፄ ዮሐንስ የሒወት ስምምነት ግዴታቸውን ለመወጣት ራስ አሉላን የግብፅን ጦር ከከበባው እንዲያተርፉት አዘዙ። በ1885 ራስ አሉላ ከማህዲስቶች ጋር የኩፊትን ጦርነት በመዋጋት ተልዕኳቸውን ተወጡ። ነገር ግን ይህ የኢትዮ-ግብፅ ህብረት በሰሜን-ምዕራብ ኢትዮጵያ ግዛቶች ላይ የማህዲስቶችን ጥቃት አስከትሏል። ከምንም በላይ ደግሞ ስምምነቱ ጣሊያን ምጽዋን እንድትይዝ በር ከፍቷል።

> ### ተግባር-8
>
> 1. የሒወት ስምምነት ያስከተላቸውን ሁነቶች በቡድን ገምግማችሁ ሪፖርት አቅርቡ።
> 2. የአፄ የሐንስ 4ኛ የክተት አዋጅን ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

## 4.3.2. ከሒወት ውል በኋላ የተከሰቱ ሁኔታዎች

በውሉ መሰረት በጎስ ለኢትዮጵያ ቢመለስም ምጽዋ ለጣሊያኖች ተሰጠ። የአፄ ዮሐንስን ጥያቄ ችላ በማለትና የሒወት ስምምነትን በማፍረስ በ1885 በእንግሊዝ ጋባዥነት ጣሊያን ምጽዋን ግብፆች እንደለቀቁ ያዘችው። ከዚህ የከፋው ደግሞ ጣሊያኖች ወደ ኢትዮጵያ መሣሪያ እንዳይገባ አገዱ፣ ከባድ ግብር ጣሉ እንዲሁም ወደ መረብ ምላሽ (የዛሬዋ ኤርትራ) መስፋፋት ጀመሩ። እንግሊዝ ጣሊያን በሚስጢር ምጽዋን እንድትይዝ የጋበዘች ሲሆን ዓላማውም የፈረንሳይን በቀይ ባህር ክልል መስፋፋት ለማስቆም ነበር። ጣሊያን የተመረጠችው ደካማና እንግሊዝን መፎካከር ስለማትችል ነበር።

## ተግባር-9

1. ጦርነትን በሰላም መፍታት የሚኖረውን ፋይዳ አብራሩ።

ጣሊያኖች ከምጽዋ ወደ መረብ ምላሽ መስፋፋት ሲጀምሩ የመረብ ምላሽ ገዥ ራስ አሉላ እንግዳ ተቃውሞ አሰሙ። ጣሊያኖች ተቃውሞውን ችላ በማለት በድርጊታቸው በመቀጠላቸው ራስ አሉላ 20,000 የሚገመት ጦር ይዘው በመዝመት በሁለቱ ቦታዎች ሰሐጢና ዊአ የሠፈሩትን ጣሊያኖች ለማስለቀቅ ሞከሩ። በምሽጎቻቸው የነበሩትን ጣሊያኖች ማስለቀቅ ከባድ ቢሆንም በ1887 ዓ.ም 500 የጣሊያን ወታደሮችን በአሉላ ጦር ዶጋሊ ላይ ተደመሰሱ። ይህ የዶጋሊ ድል በመባል የሚታወቅ ሲሆን ለጣሊያኖች አስደንጋጭ ክስተት ነበር።

እንግሊዝ ጉዳዩን በሠላም ለመፍታት ጀራልድ ፖርታል የሚባል መልዕክተኛ የላከች ቢሆንም ሊሳካ አልቻለም። ለዚህም ምክንያቱ የፖርታል የሠላም ሀሳብ ለዶጋሊው ግጭት አፄ ዮሐንስ በይፋ ይቅርታ እንዲጠይቁ እና ጣሊያኖች ሰሐጢ፣ ዊአ፣ ከረንንና ሌሎች የቀይ ባህር ጠረፎችን እንዲይዙ የሚጠይቅ ነበር። ጣሊያኖች የሠላም ድርድሩ በመካሄድ ላይ እያለ ሰሐጢን እንደገና ያዙ። የአፄ ዮሐንስን መንግስትም ቀለበት ውስጥ አስገቡት። በኢትዮጵያ ነጻነት ላይም አደጋ ተደቀነ። አፄ ዮሐንስ ከሒወት ስምምነት በኋላ ዙሪያ-ገብ የሆኑ ችግሮች ያጋጠማቸው ሲሆን ጣሊያኖች በሰሜን፣ ማህዲስቶች በሰሜን ምዕራብ እንዲሁም ከንጉስ ሚኒሊክ እና ከንጉስ ተክለ ሃይማኖት ጋር ውስጣዊ ችግር ተፈጠረ። በመሆኑም ከ1887-1889 አፄ ዮሐንስ በሦሥት አቅጣጫ ውጥረት ገጠማቸው።

በ1888 ከጣሊያኖች ጋር የነበራቸውን ግጭት እልባት ለመስጠት አፄ ዮሐንስ 80,000 ወታደሮችን አስከትለው ወደ ሰሐጢ ዘመቱ። አፄ ዮሐንስ ጣሊያኖችን ሰዓቲ ላይ ቢከቡም ከምሽጋቸው ባለመውጣታቸው በሁለቱ መካከል ወሳኝ ፍልሚያ ሊደረግ አልቻለም። ከአንድ ወር ከበባ በኋላ የአፄ ዮሐንስ ጦር የስንቅ ችግር ስላጋጠመው፣ እንዲሁም በማህዲስቶች የጎንደርን መቃጠል በመስማታቸው ንጉሰ ነገስቱ ወደ መሀል ሀገር ሊመለሱ ተገደዋል።

### ተግባር-10

1. ከሒወት ውል በኋላ አፄ ዮሐንስን የተገዳደሯቸውን ዋና ዋና ችግሮችን ግለፁ?
2. በአፄ ዮሐንስ አስተዳደር ዘመን የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበር በጥንድ በጥንድ ከተወያያችሁ በኋላ ዘገባ አቅርቡ፡፡

## 4.3.3. የደርቡሽ እና የኢትዮጵያ ግንኙነት

**ቁልፍ ቃላት:**

- ☞ ማህዲስት
- ☞ አንሳር

### ተግባር-11

1. ከ1880ዎቹ በፊት የኢትዮጵያና የሱዳን ግንኙነት ምን ይመስል ነበር? በጥንድ ቡድን ከተወያያችሁ በኋላ መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

ማህዲስቶች የሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ግዛቶችን በመውረራቸው ንጉስ ተክለ ሃይማኖት በጃንዋሪ 1887 ተዋግተው መተማን ተቆጣጠሩ፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ግንባሮች የሚመራው የደርቡሾች ጦር የንጉስ ተክለ ሃይማኖትን ጦር ሳርውሃ ላይ በ1888 አጠቃ፡፡ የደርቡሽ ጦርም ድንቢያን ወረረ፣ የማህበረ-ሥላሴ ገዳምንና ጎንደር ከተማን አወደመ፡፡

አፄ ዮሐንስ በማርች 9/1889 መቶ ሺ የሚገመተውን ጦራቸውን እየመሩ በመተማ ሲዋጉ በጽኑ ቆሰሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የንጉሰ ነገስቱ ጦር ተበታተነ፡፡ በማግስቱ ዮሐንስ የሞቱ ሲሆን አንሳሮች አስከሬኑን በመማረክ ጭንቅላታቸውን ቆርጠው ኦምድሩማን ለሚገኘው መሪያቸው ላኩት፡፡ በ1889 አፄ ዮሐንስ በመተማ ጦርነት ህይወታቸውን ካጡ በኋላ አፄ ምኒልክ “ባለህበት እርጋ ገዥህ እኔ ነኝ” ብለው አዋጅ አስነግረው ንጉሰ ነገስት ሆኑ፡፡

ተግባር-12

1. የመተማ ጦርነት ያስከተላቸውን ውጤቶች ገምግሙ::

## 4.3.4. የኢትዮጵያ እና የጣሊያን ግንኙነት

ተግባር-13

1. የጣሊያንና የንጉስ ምኒልክ ግንኙነት መቼና እንዴት ተጀመረ?

የንጉስ ምኒልክና የጣሊያኖች ይፋዊ ግንኙነት የተጀመረው በ1876 ሲሆን የጣሊያ ጂኦግራፊያዊ ማህበር ወደ ሸዋ ከመጣ በኋላ ነበር:: የማህበሩ መሪ ማርኩይስ ኦራዚዮ አንቲኖሪ ነበር:: የአንቲኖሪ ተልዕኮ በሳይንሳዊ ጥናት ሽፋን ኢትዮጵያን ለቅኝ ግዛት መስፋፋት ዓላማቸው ለማጥናት ነበር:: በንጉስ ምኒልክ በኩል ጣሊያኖች የተፈለጉት ከውጭ ጠመንጃ ለማግኘት ስለሚረዷቸው በዚህም ለዘውድ የሚያደርጉትን ትግል ለማጠናከር ነበር::

በዚህም መሠረት ንጉስ ምኒልክ ለጣሊያኖች አንኮበር አጠገብ የሚገኝ ልጥ ማረፊያ የተባለ ቦታን የሰጧቸው ሲሆን ጣሊያኖች በበኩላቸው ለንጉሱ ከውጭ መሳሪያ ለሚገዛ ወኪል በአሰብ ቦታ ሊሰጡ ተስማሙ:: ቀደም ሲል የተጀመረው ግንኙነት የበለጠ መቀራረብ ያሳየው በ1882 ፔትሮ አንቶኔሊ የጣሊያን ልዑክ ሆኖ ከመጣ በኋላ ነበር:: ንጉስ ምኒልክና ጣልያን በ1883 የወዳጅነትና የንግድ ስምምነትን ተፈራረሙ:: ስምምነቱ የቆንስላዎች ልውውጥን፣ ነፃ የንግድና የዜጎች እንቅስቃሴንና በነጻነት ሃይማኖትን የመስበክ የሚሉ አንቀጾች ይገኙበታል:: ሶስተኛው የጣሊያኖችና ሸዋ ስምምነት በ1887 የዶጋሊን ግጭት ተከትሎ የተፈረመ ሲሆን በዚህ ወቅት ጣሊያኖች የምኒልክን እርዳታ በጣም ይፈልጉ ነበር:: ከዮሐንስ ጋር ለመዋጋት ፈቃደኛ ያልነበሩትን ንጉስ ምኒልክን ጣሊያኖች ገለልተኛ እንዲሆኑ አግባቧቸው:: በዚህም መሠረት የገለልተኛነት ስምምነት ተብሎ የተጠራውን ውል በ1887 ተፈራረሙ::

የንጉስ ምኒልክ እና የጣሊያኖች ግንኙነት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው የውጫሌ ውልን ሜይ 2/1889 ከተፈራረሙ በኋላ ነበር:: ይህ ውል የወዳጅነታቸው ማብቂያ መጀመሪያ ነበር ማለት ይቻላል:: የውጫሌ ውል የተፈረመው ወሎ ውስጥ ውጫሌ በተባለ ቦታ ሲሆን ስያሜውን ያገኘውም ከቦታው ነው:: የውጫሌ ውል ሃያ

አንቀጾች ያሉት ሲሆን ለኢትዮ-ጣሊያን ግጭት ትልቅ ምክንያት የሆኑት አንቀጾች ሶስተኛውና አስራ ሰባተኛው ነበሩ:: አንቀፅ ሶስት (3) ጣሊያን በያዘቻቸው የመረብ ምላሽ ግዛቶችና በቀሪው የኢትዮጵያ ግዛቶች መካከል የሚኖረውን ወሰን የሚለይ ነበር:: በዚህም መሠረት ጣሊያኖች ከመረብ ወንዝ ማዶ የሚገኙትን አብዛኞቹን ቆላማ ቦታዎችና ጥቂት ደጋማ ቦታዎችን በይዞታነት እውቅና ተሰጣቸው:: ነገር ግን የቅኝ ግዛት መሠረታዊ ፍላጎት ስላላቸው ወሰኑን እየጣሱ ወደ ውስጥ መግባት ጀመሩ::

አንቀፅ አስራ ሰባት (17) በኢትዮጵያና በጣሊያን መካካል ሊኖር ስለሚችለው ግንኙነት ይገልጻል:: የቅኝ ግዛት ህልም ስለነበራቸው በጣሊያንኛ የተፃፈውን ውል አጣመው ንጉሱን አስፈረሟቸው:: በዚህ ሂደት ኢትዮጵያ የጣሊያን የሞግዚት አስተዳደር እደሆነች የዲፕሎማሲ ዘመቻ ከፈቱ:: ይህንን ለመተግበር የውጫሌ ውል አንቀጽ አስራ ሰባትን የተቀነባበረ የአማርኛና ጣሊያንኛ የትርጉም ተቃርኖ ለመጠቀም ሞከረች:: የአንቀጹ የአማርኛ ትርጉም ኢትዮጵያ ከሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች ጋር በሚኖራት ግንኙነት የጣሊያንን እርዳታ መጠቀም ትችላለች የሚል ነበር:: ጣሊያንኛው ጽሁፍ ግን ኢትዮጵያ ማንኛውንም የውጭ ግንኙነት በጣሊያን መንግስት በኩል ብቻ ማድረግ አለባት የሚል የአስገዳጅነት መንፈስ የነበረው ቃል ነው:: የዚህ አንቀጽ አንደምታ ኢትዮጵያን በጣሊያን የሞግዚት አስተዳደር ሥር ያለች ሀገር እንደሆነች የሚገልጽ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚጋፋ ነበር::




ምስል 5፦ የውጫሌ ውል የተፈረመበት ቦታ

አፄ ምኒልክ ለጣሊያኑ ንጉስ ኡምቤርቶ አንቀጽ 17 እንዲያስተካክሉ የሚገልጽ ደብዳቤ ቢልኩም ፈቃደኛ አልሆኑም። ምኒልክ በኤፕሪል 1891 የዲፕሎማሲ ዘመቻ የጀመሩ ሲሆን ለሁሉም የአውሮፓ ሀገሮች ደብዳቤዎችን ላኩ። በደብዳቤዎቻቸውም የጣሊያንን የሞግዚትነት መብት ለማክበር እንደማይገደዱ ገልፀዋል።

ጣሊያን ውሉን ከማስተካከል ይልቅ ማሳመንና ከፋፋይ የሆኑ ፖሊሲዎችን መተግበር ጀመረች። የማሳመን ፖሊሲን የሚመራው አንቶኔሊ ዋና ዓላማውም አፄ ምኒልክ ውሉን እንዲቀበሉ መገፋፋት ነበር። ይህ ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ውድቅ የሆነው ንጉሰ ነገስቱ በፌብሩዋሪ 1893 የውጫሌ ውልን በይፋ በመሰረዛቸው ነበር። የጣሊያኖች የመከፋፈል ፖሊሲ ከትግሬ መሳፍንት ጋር ጊዜያዊ ስኬት አስገኝቶላቸዋል። ለምሳሌ በ1891 የመረብ ስምምነት የትግሬ መሳፍንት በራስ መንገሻ ዮሐንስ መሪነት ከጣሊያኖች ጋር ለመስራት ቃል ገብተዋል። ራስ መንገሻ ዮሐንስ ንጉሰ ነገስቱ ወራሼ ናቸው ያሏቸው ነበሩ። ራስ መንገሻ የጣሊያኖች የመከፋፈል ፖሊሲ ሴራ ስለተረዱ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርገው ለአፄ ምኒልክ ታማኝ ሁነዋል። በሰኔ 1894 ራስ መንገሻ እና ራስ አሉላ ወደ አዲስ አበባ በመሄድ ለምኒልክ ያላቸውን ታማኝነት አረጋገጡ። በ1895 ራስ መንገሻና ራስ አሉላ የመረብን ወንዝ በማቋረጥ ጣሊያኖችን ቆአቲትና ሰንአፈ ላይ ተዋግተዋል።

በዚህም በኢትዮጵያ በኩል የጦርነቱ አይቀሬነት ግልጽ እየሆነ መጣ። እቴጌ ጣይቱ፣ ፊታውራሪ ገበየሁ እና ሌሎችም ንጉሰ ነገስቱ ወታደራዊ እርምጃ እዲወስዱ ግፊት ያደረጉ ሲሆን አፄ ምኒልክም ለጦርነቱ ዝግጅት ማድረጋቸውን ቀጠሉ። አፄ ምኒልክ የፈረንሳይንና ሩሲያን አጋርነት እንዲሁም ከእነዚህ ሀገሮች መሳሪያ ለማግኘት ሞክረዋል። በሲፕቴምበር 17/1895 የክተት አዋጅ ያወጡ ሲሆን በዚህም ከሁሉም ግዛቶች ህዝቡ ለመዝመት ተነሳ። አፄ ምኒልክ በጣሊያን ላይ ያዘመቱት መላውን የኢትዮጵያን ህዝብ ነበር ለማለት ይቻላል። መላው ህዝብ ለጦርነት ሲዘምት ጳጳሳትና ካህናት ሠራዊቱን አጅበው ዘመቱ። እቴጌ ጣይቱ ለጦርነቱ ዝግጅታቸውን ቀድመው የጀመሩ ሲሆን ሴቶችን በቤተመንግስቱ በመሰብሰብ ምግብ፣ መጠጥ፣ የማብሰያ ቁሳቁስ፣ ባህላዊ መድኃኒቶች፣ የቁስል መጠገኛ ወዘተ እንዲዘጋጅ አዘዙ። እቴጌይቱ በሰሜን ኢትዮጵያ ለሚገኙ መሳፍንቶች ሠራዊቱ በግዛታቸው ሲያልፍ ምግብ እንዲያቀርቡ አዝዘው ነበር። በአድዋ ዘመቻ እቴጌ ጣይቱ በግላቸው ከ6000 በላይ ሠራዊት መርተዋል። ሴቶች ለተዋጊው ሠራዊት የሞራል ድጋፍ መስጠት ብቻ ሣይሆን በመዋጋት፣ የቆሰሉትን በማከም፣ ለሠራዊቱ ምግብና መጠጥ በማቅረብ፣ ካምፕ በመጠበቅ ወዘተ አገልግለዋል።




ምስል 6፦ ዳግማዊ አፄ ምኒልክና ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ብጡል

## 4.3.4.1. የአድዋ ጦርነት

ከዋናው አድዋ ጦርነት በፊት ኢትዮጵያዊያን እና ጣሊያኖች ሁለት ቦታዎች ላይ ተዋግተዋል:: የመጀመሪያው በ1895 በፊታውራሪ ገበየሁ እና ሌሎችም መኮንኖች የሚመሩት የኢትዮጵያ ጦር በደቡብ ትግራይ አምባላጌ ላይ በሻለቃ ቶሲሊ የሚመራውን የጣሊያንን ጦር ድል አድርጓል:: ጣሊያኖች ሙሉ በሙሉ የተሸነፉ ሲሆን ቶሲሊን ጨምሮ ብዙዎቹ ሲገደሉ የተረፉት የጣሊያኖች ጠንካራ ምሽግ ወደ ሚገኝበት መቀሌ ሸሹ:: ሁለተኛ በራስ መኮንን አዝማችነት ከተለያዩ የኢትዮጵያ ግዛቶች የተውጣጣ በመሳፍንቶች የሚመራ ጥምር ጦር በመቀሌ የጣሊያኖችን ምሽግ ከበበ:: የኢትዮጵያ ጦር በጣሊያኖች ምሽግ አጠገብ የሚገኘውን ለወታደሮቻቸው ጥቅም የሚሰጠውን ትንሽ ምንጭ እንዲቆጣጠር ከእቴጌ ጣይቱ ምክር በማግኘታቸው የበላይነትን ተቀዳጁ:: ከጃንዋሪ 7-21/1895 መቀሌ የተከበበች ሲሆን በእርግጥም የጣሊያን ወታደሮች በውሃ እጦት ተሰቃዩ:: ጣሊያኖች የመቀሌን ምሽግ ለመልቀቅ ሲገደዱ ምኒልክም ጣሊያኖች በሠላም እንዲሄዱ ፈቀዱላቸው:: ነገር ግን በጀኔራል ኦሬስቴ ባራቴሪ የሚመራው በአራት ብርጌዶች የተከፈለው ሠራዊታቸውን ለጦርነት ዝግጁ አደረጉ:: ሶስቱ የጣሊያን ብርጌዶች በሦስት ጀኔራሎች ማለትም አልቤርቶኒ፣ አሪሞንዲ እና ዳቦርሜዳ የሚመሩ ሲሆን ብርጋዴር ጀኔራል ኤሊና የተጠባባቂ ጦር አዛዥ ነበር::

**የኢትዮጵያና የጣሊያ ጦር ሠራዊት የተዋጋበትን የዓድዋንና የአካባቢውን ሠፈር የሚያሳይ ሠሌዳ**




ምስል 7፡- የአድዋ ጦርነት ግምባሮች እና የጦርነቱ አሰላለፍ

በቁጥር የጣሊያን ወታደሮች አነስተኛ ቢሆኑም ከኢትዮጵያዊያን የተሻለ መሳሪያ ነበራቸው:: በተጨማሪም ዘመናዊ ስልጠና የወሰደ ጦር እና የሰለጠኑ አዛዦች ነበሩት:: ጣሊያኖች በሚገባ የተዘጋጁ ቢሆንም ስለኢትዮጵያ ጦር ብዛትም ሆነ ወታደራዊ ታክቲክ ትክክለኛ መረጃ አልነበራቸውም:: ጀኔራል ባራቴሪ የተወሰኑ ወታደሮችን በመላክ የኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ትንኮሳ እንዲካሄድ ላከ:: ዓላማውም ኢትዮጵያዊያን ከምሽጋቸው ወጥተው ለጣሊያኖች መድፍ ኢላማ እንዲሆኑ ተፈልጎ ነበር:: የአካባቢው ህዝብ የመረጃ ማሰባሰብ ሥራ ኢትዮጵያዊያንን ጠቅሟቸዋል:: ለጠላት የተሳሳተ መረጃ ማቀበል አንዱ የነበረ ሲሆን ለምሳሌ ጣሊያኖች በሁለት ወገን ሰላይ በነበሩት ባሻ አውአሎም በደረሳቸው መረጃ መሠረት የኢትዮጵያ ጦር በበዓላት የማይዋጋ በመሆኑ እሁድ ማርች 1/1896 በቅዱስ ጊዮርጊስ መታሰቢያ በዓል ላይ ጀኔራል ባራቴሪ ጦርነቱ እንዲጀመር መከሩት:: ባራቴሪ በደረሰው መረጃ ተታሎ የጣሊያን ጦር ማጥቃት እንዲጀመር ትዕዛዝ ሰጠ:: በመሆኑም በዚሁ ቀን ንጋት ላይ በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ጣሊያኖች ጥቃት በመሰንዘራቸው ጦርነቱ ተጀመረ:: ከፍተኛ ጦርነት ተካሂዶ ኢትዮጵያዊያኑ በታላቅ ጀግንነት ተዋግተው ከሰዓት በኋላ አስደናቂ ድል ሊያገኙ ችለዋል:: ባራቴሪ ከባድ ሽንፈት የደረሰበትን ሠራዊቱን ከትግራይ በሙሉ ለቆ እንዲያፈገፍግ ትዕዛዝ ሰጠ:: ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት የማድረግ ህልም የነበራት ጣሊያንም እቅዷ ከሸፈ::

*ተግባር-14*

1. በጣሊያን እና በንጉስ ምኒልክ መካከል የተደረጉት ውሎች ምን ይዘት ነበራቸው?
2. የውጫሌ ውል ይዘት ምን ነበር? ለአድዋ ጦርነት ምክንያት እንዴት ሊሆን ቻለ?
3. በአድዋ ጦርነት ኢትዮጵያ ድል ልታደርግ የቻለችባቸው ምክንያቶች ምን ምን እንደነበሩ በቡድን ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

### 4.3.4.2 የአድዋ ድልና ፋይዳው

የአድዋ ድል ኢትዮጵያ በአፍሪካ ነፃነቷን በጦርነት ያስከበረች ብቸኛ ሀገር እንድትሆን አድርጓታል። እንዲሁም ኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሀገር መሆኗን አለምአቀፋዊ እውቅና አስገኝቶላታል። ይህ እውቅና በሁለት መንገድ ይገለፃል። አንደኛ የተለያዩ ኃያል አገሮች ኤምባሲዎቻቸውን/ቆንስላዎቻቸውን በአዲስ አበባ የከፈቱ ሲሆን እነዚህም ጣሊያን (1896)፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ (1897) አሜሪካ (1903) ጀርመን (1905) እና ሌሎችም ነበሩ። ሁለተኛው በኢትዮጵያና አዋሳኝ በሆኑ ቅኝ ገዥ የአውሮፓ ሀገሮች መካከል የጋራ ድንበሮቻቸው በካርታ ላይ የተሰመረ ሲሆን ይህም ከ1897-1908 ባለው ጊዜ ውስጥ ተጠናቋል። ከፈረንሳዮች ጋር የጅቡቲን ድንበር በ1897፣ ከእንግሊዝ ሶማሊላንድ ጋር በ1897፣ ከጣሊያን ጋር የኤርትራ ድንበር በ1900፣ 1902ና 1908፣ ከሱዳን ጋር በ1902፣ ከኬንያ ጋር በ1907 ከጣሊያን ሶማሊላንድ ጋር በ1908 ተፈርመዋል። ይህ ድልም የዛሬዋ ኢትዮጵያን ቅርጽ ሰጥቷታል።

አድዋ የዓለምአቀፍ ማህበረሰብን ትኩረት ወደ ኢትዮጵያ እንዲሆን ያደረገ ክስተት ሲሆን ይህም ጥቁሮች በነጮች ላይ የተቀዳጁት ታላቅ ድል ነበር። በአውሮፓ የሚታተሙ ዋና ዋና ጋዜጦች የአፄ ምኒልክንና የእቴጌ ጣይቱን ምስል በፊት ገጾቻቸው ላይ ይዘው ወጥተዋል። የአድዋ ድልን ተከትሎ የውጭ ሀገር ተጓዦች፣ ነጋዴዎችና ሌሎች አውሮፓዊያን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ነበር። በአጠቃላይ የአድዋ ድል ብሔራዊ ኩራት ምልክት ሆኗል። ሀገር ተረካቢው ተከታይ ትውልድም የሀገሩን ነጻነት ለመጠበቅ ቁርጠኛ የሆነ አቋም እንዲኖረው አድርጓል። የአድዋ ድል በጣሊያኖች ላይ ከባድ ድንጋጤና ቀውስ አስከትሏል። በዋና ዋና የጣሊያን ከተሞች ህዝቡ ሠላማዊ ሰልፍ ያደረገ ሲሆን አፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱን የሚያወድሱ መፈክሮችን ይዞ ወጥቷል። ሰልፈኞቹ ጀኔራል ባራቲየሪ ጦር ፍርድ

ቤት እንዲቀርብ፣ ምርኮኛ ጣሊያናዊያን እንዲለቀቁ እና ጣሊያን አፍሪካን ለቃ እንድትወጣ ጠይቀዋል፡፡ በዚህ ጠንካራ ተቃውሞ ምክንያት የጣሊያኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንሲስኮ ክሪስፒ ስልጣን እንዲለቁ ጠይቀዋል፡፡ ባራቴየሪ ደግሞ ሥልጣኑን በመልቀቅ ወህኒ ወርዷል፡፡

የአድዋ ድል በአፍሪካና በመላው ዓለም ፀረ-ቅኝ ግዛት ትግል እንዲካሄድ ንቃተ-ህሊናን በጥቁር ህዝቦች ላይ ከፍ አድርጓል፡፡ በአሜሪካ የጥቁሮች ድሉ የኩራት ምንጭ የሆነ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ የነጮች የበላይነት በነገሰበት ደቡብ አፍሪካም ለጥቁሮች ኩራትን ፈጥሮላቸዋል፡፡ ኢትዮጵያ ነፃነቷን የማስጠበቋ ጉዳይ የመጀመሪያዎቹ የፓን-አፍሪካ ጉባኤዎች አጀንዳ ቀዳሚ ርዕስ ነበር፡፡ ሌላው የአድዋ ድል በጥቁር ብሔርተኞች ትግል ውስጥ ከነጮች ቤተክርስቲያናት የተገነጠሉ የጥቁሮች ሃይማኖታዊ ንቅናቄዎች መጀመር ምክንያት ሆኗል፡፡ ለምሳሌ ኢትዮጵያኒዝም በመባል የሚታወቀውን እንቅስቃሴ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ከላይ ሲታዩ እነዚህ ንቅናቄዎች ሃይማኖታዊ ቢመስሉም የነጮችን የበላይነት በጽኑ የሚታገሉ ነበሩ፡፡

ኦክቶበር 2/1896 የጣሊያን ዲፕሎማሲያዊ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት የአዲስ አበባ ውል ተፈራረሙ፡፡ በስምምነቱ የውጫሌ ውል የተሰረዘ ሲሆን ጣሊያን የኢትዮጵያን ነፃነት ዕውቅና ሰጥታለች፡፡ ኢትዮጵያም የጦር ምርኮኞችን ለመልቀቅ ተስማምታለች፡፡

## ተግባር-15

1. የአድዋ ድል ዓለም አቀፋዊ ፋይዳዎችን ግለፁ?
2. የ1896ቱን አዲስ አበባን ውል ጠንካራና ደካማ ጎን ገምግሙ?
3. የአድዋ ድል ለኢትዮጵያ ህዝቦች ያስገኘውን ጥቅሞች እና ገጽታዎች በተመለከተ በትንንሽ ቡድን በመሆን ክርክር አድርጉ፡፡
4. የአፄ ምኒልክን የክተት አዋጅ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

# 4.4. ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች

## ተግባር-16

1. ከአድዋ ጦርነት በፊት የንግድ፣ የግብርና ኢኮኖሚ እንቀስቃሴ ምን ይመስል ነበር?
2. በኢትዮጵያ ከዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎች መጀመር በፊት ማህበረሰቡ ይጠቀምባቸው የነበሩትን የመገናኛ አማራጮች ከሚያውቁ ሰዎች በመጠየቅ ዘገባ አቅርቡ።

የ20ኛው ክፍለ ዘመን ሶስት አስርት ዓመታት የተሻለ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች የታዩበት ነበር። እነዚህ ለውጦች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የ19ኛው ክፍለ ዘመን የማዕከላዊ መንግስት ምስረታ ሂደትና የውጭ ወረራ የመከላከል ዘመቻዎች ጋር የተያያዙ ነበሩ። በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያዎቹ ዓመታት ባርነትና ባሪያ ንግድን ለማስቀረት ወሳኝ ፊልሚያ ተካሂዷል። የባሪያ ንግድ ዋና ሰለባ የነበረው የህብረተሰብ ክፍል ወጣቱ ሲሆን ባሪያ በሚፈነገልባቸው አካባቢዎች የህይወትና ንብረት ዋስትና ባለመኖሩ የህዝቡን የማምረት ተነሳሽነት የገደበ ነበር። የባሪያ ንግድ የውጭ ሀይሎችን ጣልቃ ገብነት አስከትሏል። ኢትዮጵያም የመንግስታቱን ማህበር በ1923 ከተቀላቀለች አንድ አመት በኋላ ባሪያዎችን ነፃ ያወጣና ባሪያ መሸጥና መግዛትን ህገ ወጥ ያደረገ አዋጅ አወጣች። የግዳጅ ስራን የሚያግድ ህግም በ1935 ወጣ።

በተጨማሪም ግብርን በገንዘብ የመክፈል ድንጋጌ የወጣ ሲሆን ይህም በአንድ ጋሻ 30 ብር ነበር። የማዕከላዊ መንግስት ምስረታን መጠናቀቅና የአድዋ ድልን ተከትሎ በኢትዮጵያ የሰፈነው ሠላምና መረጋጋት ንግድ እንዲያንሰራራ አድርጓል። ኢትዮጵያ ከበርካታ ሀገሮች ጋር የፈጠረችው ሠፊ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከአድዋ ድል በፊት ከነበረው የተሻለ የንግድ ትስስርን ፈጥሮላታል።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያና በ20ኛ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ የንግድ ፍሰት አቅጣጫ ወደ ምስራቅና ምዕራብ ያጋደለ ሲሆን ለዚህም የዘመኑ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች አስተዋጽኦ አድርገዋል። በ1882 የእምባቦ ጦርነት ላይ የሸዋ ድል ማድረግ እና በአፄ ምኒልክ ዘመን ሸዋ ማዕከል መሆኗን ተከትሎ የሰሜን የንግድ አቅጣጫ ወደ ደቡብ ትኩረት አደረገ። ከእነዚህ ምክንያቶች በተጨማሪ የጅቡቲ - አዲስ አበበ የባቡር መስመር መከፈቱ እና እንግሊዞች በጋምቤላ የከፈቱት

የንግድ ጣቢያ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ድረስ የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ በጅቡቲ በኩል ሊሆን ችሏል። ከጅቡቲ በመቀጠል በ1904 እንግሊዞች በጋምቤላ የከፈቱት የንግድ ጣቢያ በተለይም የቡና የውጭ ንግድ የሚከናወንበት ቦታ ነበር።

ከአድዋ ድል በኋላ የውጭና የውስጥ ንግዶችን በዋናነት የተቆጣጠሩት ከተለያዩ ሀገሮች የመጡ ነጋዴዎች ሲሆኑ የተወሰኑ የገዥ መደብ አባላትም ወደ ንግዱ ገብተዋል። እቴጌ ጣይቱ በስማቸው የሚጠራውን በአዲስ አበባ የመጀመሪያውን ሆቴል በ1907 ከፍተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ንጉሰ ነገስቱና ንግስቲቱ ከታላላቅ ባላባቶች ጋር በመሆን ለንግድና ለግብርና መዳበር አስተዋጽኦ የሚያደርግ የመጀመሪያ የሆነውን አቢሲንያ ባንክ በ1905 አቋቁመዋል። የጎጃሙ ገዥ ራስ ሀይሉ ተክለ ሃይማኖት በአዲስ አበባ ሲኒማ ቤትና የታክሲ አገልግሎት ጀምረው ነበር። የመንግስት ምስረታን እና የንግድ ማንሰራራትን ተከትሎ የከተሞች እድገት አንፃራዊ ለውጥ አሳይቷል። በአፄ ምኒልክ ኢትዮጵያን እንደገና የማዋሀድ ዘመቻ ወቅት የሠራዊታቸው ማዕከል የነበሩ እንደ ጎሬ እና ጎባ ታላላቅ ከተማ ሆነዋል። በ1917 አዲስ አበበ የደረሰው የባቡር መስመር ድሬዳዋ፣ ናዝሬትና ሞጆ ከተሞች ለመመስረታቸው ምክንያት ሆኗል።

በተጨማሪም ወደ ኢትየጵያ ከገቡ ዘመናዊ የስልጣኔ ውጤቶች ውስጥ በ1904 መኪና፣ በ1908 ትምህርት ቤት፣ በ1910 ሆስፒታል፣ በ1912 የማተሚያ ማሽን እና በ1929 አውሮፕላን ይጠቀሳሉ። ቴሌግራምና የፖስታ አገልግሎቶችም ተጠቃሽ ናቸው። የጣውላ ፋብሪካዎች፣ የጥይት ፋብሪካ እና የምግብ ማቀነባበሪያዎችም ተከፍተው ነበር።

## ተግባር-17

1. የዳግማዊ ምኒልክ ሀገርን ለማዘመን ያደረጓቸውን ጥረቶች በማህበራዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊ እና ፖለቲካዊ ክፍሎች በመለየት በሰንጠረዥ ዘርዝሩ።
2. በአካባቢያችሁ በእድሜ ታላላቅ ሰዎችን በመጠየቅ በሀገራችን የነበረው ጭሰኝነት አጠቃላይ ገጽታ እና የግብር አዋጅ ምን ይመስል እንደነበር አብራሩ።

# 4.5. የፋሽስት ጣሊያን ወረራ (1936-1941)

## ቁልፍ ቃላት:

- ☞ ፋሽስት
- ☞ አስካሪስ
- ☞ የውስጥ አርበኞች
- ☞ ባንዳ

### ተግባር-18

1. ከአድዋ ጦርነት በኋላ በኢትዮጵና በጣሊያን መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት ነበር?

ከአድዋ ጦርነት በኋላ ጣሊያን ረዥም ዝግጅት ስታደርግ ቆይታ ኢትዮጵያ ላይ በ1935 ዳግም ወረራ ፈፀመች፡፡ ለዳግም ወረራ ዋናው መነሻ ጣሊያኖች በታሪካቸው አሳፋሪ የሆነውን የአድዋ ሽንፈታቸውን መበቀልና የቅኝ ግዛት ህልማቸውን ለማሳካት ነበር፡፡

ፋሽስቶች ዓላማቸውን ድብቅ በማድረግ ኢትዮጵያን ለመውረር ሁኔታዎችን ለማመቻቸት በማሰብ በአድዋ፣ ጎንደር፣ ደብረማርቆስ እና ደሴ የቆንስላ ጽ/ቤቶችን በመክፈት መረጃ ያሰባስቡ ነበር፡፡ በኤርትራው ገዥ ኮራዶ ዞሊ አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጣዊ ክፍፍል ለመፍጠር ተንቀሳቅሰዋል፡፡ የትግራይ፣ የወሎ፣ የቤጌምድርና የጎጃም መሳፍንቶችን በንጉሰ ነገስቱ ላይ እንዲያምጹ መደለያ በመስጠትና በመቀስቀስ ጥረት አድርገዋል፡፡ የኃይለ ስላሴ ማዕከላዊ አስተዳደር ላይ ቅሬታ የነበራቸው ለምሳሌ የጎጃሙ ራስ ኃይሉ፣ የጅማው አባጆቢር፣ የትግራዩ ደጃዝማች ኃይለስላሴ ጉግሳን ጨምሮ የጣሊያኖች ተባባሪ ሆነዋል፡፡ ጣሊያን በኤርትራና ሶማሊላንድ ቅኝ ግዛቶቿ ወታደሮችና የጦር መሳሪያ ማከማቸት ጀመረች፡፡

ሙሶሊኒ ከላይ የተዘረዘሩትን ዝግጅቶች ካደረገ በኋላ ወረራውን ለመጀመር ሰበብ በመፈለግ ላይ ነበር፡፡ በ1908 በተደረሰው የኢትዮጵያና ጣሊያን የድንበር ስምምነት መሠረት ወልወል የምትገኘው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ነበር፡፡ ነገር ግን ጣሊያኖች ወልወል ውስጥ ዲሴምበር 5/1934 ጥቂት የኢትየጵያ ጠረፍ ጠባቂ ፖሊሶች ላይ ጥቃት ፈፀሙ፡፡ ይህ የወልወል ግጭትም ጣሊያን ያሰበችውን ለማሳካት ስለፈለገች ኢትዮጵያን ወንጀለኛ አድርጋ ከሰሰች፡፡ ወልወል የጣሊያን ሶማሊላንድ ክፍል ነው

ስትል ክስ አቀረበች፡፡ በዚህም መሠረት ኢትዮጵያ በይፋ ይቅርታ እንድትጠይቅ እና የጦር ካሳ እንድትከፍል የሚል ክስ አቀረበች፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ጉዳዩን በሠላም ለመፍታት ለመንግስታቱ ማህበር አቀረበ፡፡

## ተግባር-19

1. ጣሊያን ኢትዮጵያን የወረረችበትን መስመር ካርታ ሰርታችሁ አመልክቱ፡፡

የመንግስታቱ ማህበርን በበላይነት የሚያንቀሳቅሱት እንግሊዝና ፈረንሳይ ስለነበሩ የወልወልን አጀንዳ ለበርካታ ጊዜያት አዘገዩት፡፡ ሁለቱ ሀገሮች በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ ላይ ጣሊያን ጀርመንን እንዳትቀላቀል ማባበል ስለፈለጉ ኢትዮጵያን በምስጢር መስዋዕት ማድረግ ፈልጉ፡፡ በመጨረሻም የመንግስታቱ ማህበር በሁለቱም ሀገሮች ላይ የጦር መሳሪያ ማዕቀብ ጣለ፡፡ ማዕቀቡ ጣሊያንን አልጎዳትም ምክንያቱም ከጀርመንና ገለልተኛ ከነበረችው አሜሪካ ነዳጅና መሳሪያ ማስገባቷን ቀጥላለች፡፡ በማህበሩ የደከመ አቋም በመደፋፈር ሙሶሊኒ ከወልወል ግጭት አንድ ዓመት በኋላ ኢትዮጵያን ወሯል፡፡

ጣሊያን ወረራውን የጀመረችው በሁለት አቅጣጫ ሲሆን በሰሜን ከኤርትራ እና በደቡብ ከጣሊያን ሶማሊላንድ ነበር፡፡ በሰሜን ከኤርትራ የተንቀሳቀሰውን የፋሽስት ሀይል በመጀመሪያ ይመራ የነበረው ማርሻል ኤሚሊዮ ዲ ቦኖ ሲሆን ቆየት ብሎ የጦርነቱን አስከፊ ምዕራፍ በመራው ፔትሮ ባዶግሊዮ ተተክቷል፡፡ ወታደሮቹ በቅኝ ግዛታቸው በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል እንደ ድንበር የሚያገለግለውን የመረብ ወንዝ በፍጥነት አቋርጠው ወደ ትግራይ ሲገሰግሱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከለከለውን መርዛማ ጋዝ እየተጠቀሙ ነበር፡፡ በሰሜን የጣሊያን ወረራ ኦክቶበር 3/1935 ተጀመረ፡፡ በደቡብ የፋሽስት ወታደሮች አዛዥ ጀኔራል ሩዶልፍ ግራዚያኒ ነበር፡፡ በደቡብ ወረራው ከሰሜኑ ዘግይቶ ተጀመረ፡፡ ወደ ውስጣዊ የኢትዮጵያ ግዛቶች በአውሮፕላን ድብደባ እየታገዙ ገሰገሱ፡፡

## ተግባር-20

1. የኢትዮጵያ መንግስት ለወረራው ምላሽ የሰጠው ዘግይቶ ነበር፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት አብራሩ፡፡

በሰሜን ግንባር የኢትዮጵያ ሰራዊት አዛዥ ራስ ካሳ ሀይሉ እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ በዚህ ግንባር ጣሊያኖችን በሦሥት አቅጣጫ የተጋፈጡ ሲሆን የመጀመሪያው በጦር ሚኒስትሩ በራስ ሙሉጌታ ይገዙ የሚመራው ሀይል በምስራቅ አቅጣጫ የአምባ አራዶምን ጦርነት ተዋጋ፡፡ መሀል ላይ (በተምቤን ግምባር) ራስ ካሳ እና ራሰ ስዩም መንገሻ የሚመሩት ጦር እንዲሁም ራስ እምሩ ኃይለስላሴ በምዕራብ በኩል የሽሬን ጦርነት መርተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ጦር መጀመሪያ ላይ በሰነዘረው መልሶ ማጥቃት ራስ ካሳ እና ራስ ስዩም በመጀመሪያው የተምቤን ጦርነት አሸንፈዋል፡፡ አምባአራዶም ላይ ፋሽስቶች የአውሮፕላንና መድፍ ድብደባ ለ6 ቀናት ያህል አካሂደው ራስ ሙሉጌታን ጨምሮ በጣም በርካታ ወታደሮችን ገደሉ፡፡ ሙሶሊኒ ክረምቱ ከመግባቱ በፊት የኢትዮጵያን ዘመቻ ለመጨረስ ስለቸኮለ ጀኔራል ባዶግሊዮን አዛዥ አድርጎ ሾመው፡፡ ይህ አዛዥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከለከለውን መርዛማ ጋዝ በሠፊው ጥቅም ላይ አዋለ፡፡ በኦክቶበር 1936 ራስ ካሳና ራስ መንገሻ ስዩም በሁለተኛው የተምቤን ጦርነት ጣሊያኖችን ቢፋለሙም የቁጥርና የጦር ስልት የበላይነት የነበራቸው ጣሊያኖች ይህንን ሀይል ከጥቅም ውጭ አድርገውታል፡፡ አዛዦቹም የጣሊያኖችን ከበባ ለጥቂት በማምለጥ ኮረም የሚገኙትን ንጉሰ ነገስት ተቀላቅለዋል፡፡

በምዕራቡ የሽሬ ግንባር ራስ እምሩ የሚመሩት ጦር የጣሊያንና አስካሪስ ወታደሮችን እንዳባጉና ላይ ማሸነፍ ችሏል፡፡ ይህ ጦር ውስጣዊ ችግር የነበረበት ሲሆን ይህም የጎጃምና ስሜን መሳፍንቶች በንጉሰ ነገስቱ ላይ በነበራቸው ቅሬታ ምክንያት የተወሰነ ኃይል ከመንገድ ከድቶ ተመልሷል፡፡ ቢሆንም ራስ እምሩ ጦሩን በብቃት መርተው በኤፕሪል 2/1936 ሽሬ ላይ ጦርነቱን ቢያሸንፉም ድሉ ዘላቂ አልነበረም፡፡

በሰሜን ግንባር የመጨረሻው ወሳኝ ጦርነት የተካሄደው ሜይ 31/1936 ማይጨው ላይ ሲሆን የተረፈውን ሀይል በማደራጀት ጦሩን የመሩት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ነበሩ፡፡ በማይጨው ጦርነት ላይ የተሳተፈው 6000 የክቡር ዘበኛ ጦር ነበር፡፡ ኢትዮጵያዊያን የመሸገውን የኢጣሊያ ጦር ለ13 ሰዓታት ያህል በጀግንነት ቢዋጉም በአውሮፕላን ድጋፍ ፍጹም የሆነ የበላይነት የነበራቸውን ጣሊያኖችን ማሸነፍ አልቻሉም፡፡ በመጨረሻም በጦር ሜዳ የተሸነፉት የኢትዮጵያ ወታደሮች የተበታተነ ማፈግፈግ ሲያደርጉ የጣሊያን ቦምብና ጋዝ ጥቃት ሰለባ ሆኑ፡፡

የደቡብ ግንባር የኢትዮጵያ ሠራዊት ዕጣ ፈንታ ልክ እንደሰሜኑ ተመሳሳይ ነበር፡፡ የጣሊያን ጦር በአዛዡ ሩዶልፎ ግራዚያኒ እየተመራ ወታደራዊ የበላይነት ስለነበረው በኦጋዴን በኩል ወደ መሀል ገባ፡፡ የኢትዮጵያን ጦር ደጅአዝማች

ነሲቡ፣ ራስ ደስታ ዳምጠው፣ ደጅአዝማች ባልቻ ሣፎ፣ ደጅአዝማች እንዳልካቸው መኮንን እና ሌሎች ወጣት እና ከፍተኛ የውጊያ ልምድ ያላቸው አዋጊ ጄኔራሎች ይመሩት ነበር:: የግራዚያኒ የመጀመሪያው የጥቃት ኢላማ ጅጅጋና ሐረርን ለመያዝ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላትን ኦጋዴን ውስጥ የምትገኘው ቆራሂ ላይ ያነጣጠረ ነበረ:: ይህንኑ በመረዳት የኢትዮጵያ ጦር በአዛዡ ግራአዝማች አፈወርቅ አስደናቂ ጠንካራ የመከላከል ጦርነት ቢያደርጉም ቆራሄ በጠላት እጅ ወደቀች:: ከቆራሄ በኋላ የፋሽስት ወታደሮች ጅጅጋና ሐረርን ለመያዝ አስችሏቸዋል::



ምስል 8፦ ግራአዝማች አፈወርቅ ወልደሰማዕት

ሌላ በዚህ ግንባር ያጋጠመው ተግዳሮት የራስ ደስታ ዳምጠው ሠራዊት በኢትዮ-ሶማሊ ድንበር ወደምትገኘው ዶሎ አዶ ያደረገው ዘመቻ አስከፊ ውጤት አስከትሏል:: ያለበቂ ስንቅ በረሃውን ያቋረጠው ሠራዊት በወረርሽኝ መነሳት ምክንያት በርካታ አባሎቹን አጥቷል:: የተረፈው እና የተዳከመው ሠራዊት ገናሌ ዶሪያ ላይ ለሶስት ቀናት ቢዋጉም ተሸንፏል:: የተረፈውን ጥቂት ወታደር በመያዝ ራስ ደስታ ወደ መሀል ሀገር በማፈግፈግ የመጀመሪያውን የሽምቅ ውጊያ ጀመሩ::

በሁለቱም ግንባር የነበረው ጦርነት በዚህ ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ግርማዊ ቀደማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ከታላላቅ የቤተ-መንግስት ሰዎች ጋር ከተመካከሩ በኋላ በጅቡቲ በኩል አደርገው ወደ እንግሊዝ ሀገር ተሰደዱ::

የሄዱበትም ምክንያት ለዓለም መንግስታት ማህበር ጣሊያን የፈፀመችውን ወረራ በአካል ተገኝተው ለማስረዳት ነበር፡፡ ንጉሰ-ነገስቱ በዓለም መንግስታቱ ማህበር በአካል ተገኝተው አጅግ በጣም አስደናቂ የሆነ ንግግር አድርገዋል፡፡ ነገር ግን አውሮፓዊያን ጣሊያን ወረራ እንድትፈፅም ይሁንታ ስለነበራቸው አጥጋቢ ምላሽ አልሰጡም፡፡

## ተግባር-21

1. ኢትዮጵያዊያን በሰሜኑም ሆነ በደቡብ ግንባር ሊሸነፉ የቻሉበት ምክንያት ምንድን ነበር?

ለኢትዮጵያዊያን ሽንፈት በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ጣሊያኖች በወታደራዊ ቴክኖሎጂና በቁጥር የነበራቸው የበላይነት ነበር፡፡ የጣሊያኖች ሠራዊት ዘመናዊ ጠመንጃ፣ መትረየስ፣ መድፍ፣ ታንክና ከሁሉም በላይ ቦምብና መርዛማ ጋዝ የሚጥሉ አውሮፕላኖች ነበሩት፡፡ በአንፃሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች ጊዜ ያለፈባቸው በአድዋ ዘመቻ የነበሩ ጠመንጃዎችን የታጠቀ ሲሆን ከፍተኛ የጥይት እጥረትም ነበረባቸው፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያዊያን የተደራጀ የስንቅና ትጥቅ አቅርቦት አልነበራቸውም፡፡ ሠራዊቱ የተቀናጀ ጥቃት ለመሰንዘር የሚያስችለው የራዲዮ ግንኙነት አልነበረውም፡፡ ሌሎቹም በርካታ ሹማምንት የእርስ በርስ ፉክክር የነበራቸው ሲሆን ይህም በጦርነቱ ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅኖ አሳድሯል፡፡ በንጉሰ ነገስቱ ያኮረፉ ባላባቶች ከልብ አለመዋጋት፤ የወታደራዊ አመራር ልምድና ብቃት አለመኖርና ኃይለ ስላሴ በመንግስታቱ ማህበር ላይ የነበራቸው የተሳሳተ እምነት እና ኢትዮጵያ በሽግግር ወቅት መሆኗ ለሽንፈቱ ዋና ምክንያቶች ነበሩ፡፡

ጣሊያንም የወረረቻቸውን ግዛቶች በስድስት አስተዳደራዊ ክፍፍሎች አዋቀረች፡፡ በዚህም መሠረት ሁለቱን ትግረኛ ተናጋሪ ግዛቶች ኤርትራና ትግራይን በማዋሃድ ኤርትራ በሚል ስያሜ ዋና ከተማ አስመራ፣ የበጌምድር፣ ጎጃም እና ወሎን ጨምሮ ዋና ከተማ ጎንደር ሲሆን አዲስ አበባ የሸዋ አስተዳደራዊ ግዛት ነበረች፡፡ ሁሉም የደቡብ ምዕራብና ደቡብ ክፍሎች ባንድ ላይ ተጠቃለው ዋና ከተማቸው ጅማ ሆነች፡፡ ሐረርና የባሌ አንዳንድ አካባቢዎችን ጨምሮ ዋና ከተማቸው ሐረር ሲሆን የጣሊያን ሶማሊላንድ ኦጋዴንን በማካተት ሶማሊያ በመባል ዋና ከተማዋም ሞቃዲሾ ሆነ፡፡ የምስራቅ አፍሪካ ጣሊያንና የሙሶሊኒ እንደራሴ ዋና መቀመጫው አዲስ አበባ እንዲሆን ተደረገ፡፡

*ተግባር-22*

1. ጣሊያን ዳግም ኢትዮጵያን ለመውረሯ ዋናው መሰረታዊ ምክንያቷ ምንድን ነበር?
2. ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር ስበብ የሆነውን ምክንያት ግለጹ።
3. የዓለም መንግስታት ማህበር (League of Nations) ግጭቱን ለመፍታት የሄደበትን መንገድና ለኢትዮጵያ የሰጠው ምላሽ ምን ይመስል ነበር?
4. በዳግም የጣሊያን ወረራ የኢትዮጵያንና የጣሊያንን ጦር በማወዳደር ትንታኔ ስጡ፡፡

## 4.6. የአርበኞች ተጋድሎና የኢትዮጵያ የነጻነት መመለስ

*ተግባር-23*

1. ተማሪዎች አርበኛ ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ምን ማለት ነው? የሚያውቁ ሰዎችን ጠይቃችሁ ዘገባ በማዘጋጀት ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

የጣሊያን አገዛዝ በከተሞች አካባቢ የተወሰነ ሲሆን ሀገር አቀፍ የነፃነት ትግሉ በገጠር አካባቢዎች ይካሄድ ነበር፡፡ የአርበኝነት ትግሉ በመላ ኢትዮጵያ የተካሄደ ቢሆንም በሸዋ፣ ጎንደርና ጎጃም ጠንካራ ነበር፡፡ የአርበኝነት ትግሉ ሁለት ደረጃዎች ነበሩት፡፡ የመጀመሪያው የዋናው ጦርነት ቅጥያ ሲሆን እስከ 1937 መጀመሪያ ድረስ ያለውን ጊዜ ይሸፍናል፡፡ የትግሉ መሪዎች ከፍተኛ ስልጣን የነበራቸው መሳፍንቶች ሲሆኑ በዋናው ጦር ሜዳ ላይ ተሳታፊ የነበሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ራስ እምሩ ወደ ጎሬ አፈግፍገው ጥቂት የሆለታ ወታደራዊ አካዳሚ ወጣት መኮንኖች እና የተማሩ ኢትዮጵያዊያን በመሰባሰብ "የጥቁር አንበሳ ማህበር" ድርጅትን መስርተው ትግሉን ለመቀጠል ሞክረዋል፡፡ በመጀመሪያው የአርበኞች ተጋድሎ አዲስ አበባን ከፋሽስቶች ነፃ የማውጣት ሙከራ ተካሂዶ ነበር፡፡ እቅዱ በ1936 ክረምት ላይ የተተገበረ ሲሆን ዓላማው ከተለያዩ አቅጣጫዎች አዲስ አበባ ላይ የተቀናጀ ጥቃት በመሰንዘር ህዝባዊ አመጽ ለመቀስቀስ የታለመ ነበር፡፡ የዚህ ወታደራዊ ዘመቻ መሪዎች የራስ ካሳ ሀይሉ ሁለት ልጆች ደጃዝማች አበራ ካሳና አስፋወሰን ካሳ፣ የአድዋው ጀግና ደጃዝማች ባልቻ፣ ባላምባራስ (በኋላ ራስ) አበበ

አረጋይ እና ደጃዝማች ፍቅረማርያም ይናዱ ነበሩ። ጥቃቱ በደንብ ያልተቀናጀና ያልተደራጀ በመሆኑ እያንዳንዱ ቡድን ለየብቻ ፋሽስቶቹን ተዋግቷል። አቡነ ጴጥሮስ ህዝቡ ለጣልያን እንዲገዛ እንዲያሳምኑ ቢጠየቁም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በጥይት ተደብድበው ተገደሉ።



ምስል 9፦ አቡነ ጴጥሮስ

ሁለተኛው የአርበኞች የትግል ዘመን የተጀመረው ከየካቲት 1937 የግራዚያኒ ጭፍጨፋ በኋላ ነበር። አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም የተባሉ ሁለት ወጣቶች እንደራሴውን ማርሻል ግራዚያኒን ለመግደል በማሰብ ቦምብ ወረወሩበት። ፍንዳታው ግራዚያኒን ያቆሰለው ሲሆን ሌሎች ጥቂት ጣሊያናዊ ባለስልጣኖችንም ገድሎ ነበር። የግድያ ሙከራውን ተከትሎ ፋሽስቶች ለሶስት ቀናት ያህል ጅምላ ጭፍጨፋ በአዲስ አበባ እና ዙሪያዋ አካሄዱ። የጭፍጨፋው ዋና ኢላማዎች ግድያውን አቀነባብረዋል ተብለው የተጠረጠሩ የተማሩ ኢትዮጵያዊያን ላይ ነበር። በዚህ ጅምላ ጭፍጨፋ 30,000 የሚደርሱ ኢትዮጵያዊያን በአዲስ አበበ ብቻ ተገድለዋል። ነገር ግን ይህ ጭፍጨፋ በኢትዮጵያ ሁለተኛውን ዙር የአርበኝነት እንቅስቃሴ አጠናክሮታል። የግራዚያኒ ጭፍጨፋ በህይወት ለተረፉት ኢትዮጵያዊያን የፋሽዝምን እውነተኛ ገጽታ ያሳየ ነበር። ሁለተኛው ዙር የአርበኝነት ተጋድሎ ከመጀመሪያው የሚለየው የገጠር አካባቢዎችን ማዕከል ያደረገ የሽምቅ ውጊያ መሆኑ ነበር። አርበኞች የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅመው የጠላት ጦር ላይ ድንገተኛ ጥቃት መሰንዘር፣ የመገናኛ መስመሮችን መቆራረጥ እና ሁኔታዎች ሲመቻቹላቸው በጠላት ጦር ላይ ጥቃት መሰንዘር ዋነኛ ስልታቸው ነበር።


አርበኞች የስንቅና ትጥቅ ችግሮች ነበሩባቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት አርበኞች በገበሬ ቤቶች ውስጥ በመቆየት እና የጠላትን ጦር በማጥቃት ስንቅና መሳሪያ ያገኙ ነበር፡፡ መድኃኒትና ጠቃሚ የጠላት ጦር እንቅስቃሴዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን የሚያገኙት ከጣሊያኖች ጋር ከሚኖሩና ከሚሠሩ የውስጥ አርበኞች ነበር፡፡ ከውስጥ አርበኞች መካከል በጣም ታዋቂዋ ወ/ሮ ሸዋረገድ ገድሌ አንዷ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በርካታ የሴት አርበኞች የነበሩ ሲሆን ከበደች ስዩም፣ ልክየለሽ በያን፣ ሙሉነሽ ፍርዴ እና ሌሎችም ከፍተኛ ተጋድሎ ፈፅመዋል፡፡

የአርበኞች ትግል የጠላትን አቅም አዳክሞ የጣልያን እንቅስቃሴ በከተማ አስተዳደር ተገደቦ እንዲቀር አድርጎታል፡፡ ከታወቁ የአርበኞች እንቅስቃሴ መሪዎች ውስጥ ራስ አበበ አረጋይ፣ ደጃዝማች ኃይለማርም ማሞ፣ ደጃዝማች በቀለ ወያ፣ ደጃዝመች ገረሱ ዱኪ፣ ደጃዝመች በላይ ዘለቀ፣ ቢትወደድ መንገሻ ጀምበሬ፣ ቢትወደድ አያሌው መኮንን፣ ራስ አሞራው ውብነህ፣ ቢትወደድ አዳነ መኮንን፣ ብላታ ታከለ ወ/ሃዋሪያት፣ ራስ ደስታ ዳምጠው፣ ሌ/ጀነራል ኃይሉ ከበደ፣ ጃጋማ ኬሎ እና ሌሎችም በርካቶች ይገኙበታል፡፡





ምስል 10፡ ኢትዮጵያዊያን አርበኞች



ምስል 11፡ ደጃዝመች በላይ ዘለቀ ከአርበኞች ጋር



ምስል 12፡ ራስ አበበ አረጋይ



ምስል 13፦ ሌ/ጀነራል ኃይሉ ከበደ



ምስል 14፦ ራስ ደስታ ዳምጠው



ምስል 15፦ ደጃዝመች ገረሱ  ዱኪ



ምስል 16፦ ራስ አሞራው ውብነህ



ምስል 17፡ አርበኝት ሸዋረገድ ገድሌ



ምስል 18፦ አርበኝት ልክየለሽ በያን



ምስል 19፡ ቢትወደድ አዳነ መኮንን



ምስል 20፦ ጃጋማ ኬሎ



ምስል 21፡ ቢትወደድ መንገሻ ጀምበሬ



ምስል 22፦ ደጃዝማች ኃይለማርያም ማሞ

የአርበኞች እንቅስቃሴ የመጨረሻው ወሳኝ ምዕራፍ ላይ የደረሰው ጦርነቱ አለምአቀፋዊ መሆን ሲጀምር ነበር፡፡ ይህም በ1940 ሞሶሎኒ ከናዚ ጀርመን ጎን በመሰለፍ የተባበሩት ሀይሎች (እንግሊዝና ፈረንሳይ) ላይ ጦርነት ያወጀበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በጦርነቱ ማብቃት ጋር ተያይዞ በሚኖረው የድል ውጤት ሀገሩን ከጀርመን ጋር ተጋሪ ለማድረግ አስቦ ነበር፡፡ ንጉሰ ነገስቱ በሀገር ውስጥና በውጭ የአርበኞችን እንቅስቃሴ በማስተባበር ቁልፍ ሚና እንደሚጫወቱ የተገነዘቡት እንግሊዞች ንጉሱን ሱዳን ካርቱም ጁን 25/1940 ይዘዋቸው መጡ፡፡ የኢትዮጵያ አርበኞችን ወደ ሱዳን ድንበር መጥተው መሳሪያና ሌሎች ትጥቆችን እንዲወስዱ ተደረገ፡፡ የእንግሊዝ ከፍተኛ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ባለስልጣናት ከሱዳንና ኬንያ በመነሳት በፋሽስቶች ላይ ከሶስት አቅጣጫ ጥቃት ለመሰንዘር ወሰኑ፡፡

በጄኔራል ፕላት የሚመራው ሀይል ኤርትራ ከረን ውስጥ ያለውን የጣሊያኖች ጠንካራ ይዞታ ከ53 ቀናት ውጊያ በኋላ አስለቀቀ፡፡ ሌላው የእንግሊዞች ሃይል ንጉሰ ነገስቱን አጅቦ በጎጃም በኩል ወደ ኢትዮጵያ የገባ ሲሆን አዛዦቹም ኮሎኔል ሳንፎርድ እና ሻለቃ ቻርልስ ዊንጌት ነበሩ፡፡ ይህ “የጌድዮን ሀይል” ተብሎ የሚጠራው ሠራዊት ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር በመሆን ፋሽስቶችን ከጎንደርና ጎጃም ጠራርጎ አስወጣ፡፡ ሶስተኛው የእንግሊዞች ሀይል ኬንያ ውስጥ የተደራጀውና በጄኔራል ካኒንግሃም የሚመራው ነበር፡፡ ይህ ሀይል በፈጣን ግስጋሴ የጣሊያን ሶማሊላንድን ተቆጣጥሮ ወደ ሀረር በመገስገስ ጣሊያኖችን እጅ እንዲሰጡ አደረገ፡፡ ከእንግሊዞች ዘመቻ በተጓዳኝ የኢትዮጵዊያን አርበኞች ጥቃታቸውን በማጠናከር የፋሽስት ሠራዊትን ውድቀት አፋጥነውታል፡፡ በጄኔራል ካኒንግሃም የሚመራው የእንግሊዞች ሠራዊትና ኢትዮጵያዊያን አርበኞች በኤፕሪል 1941 የፋሽስት ወታደሮችን ከአዲስ አበባ ማባረር ችለዋል፡፡ ከአንድ ወር በኋላ ሜይ 5/1941 ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ወደ አዲስ አበባ የገቡ ሲሆን ኢትዮጵያም ከአምስት ዓመታት ትግል በኋላ የወራሪውን ሀይል አባራለች፡

### ተግባር-24

1. በሽምቅ ውጊያና በመደበኛ ጦርነት መካከል ያለውን ልዩነት ግለጹ?
2. የግራዚያኒ ጭፍጨፋ የአርበኞችን እንቅስቃሴ እንዴት ሊያጠናክረው ቻለ?
3. ከአርበኞች ተጋድሎ ምን ተማራችሁ? በመማራችሁ ያገኛችሁትን ጥቅም ለመምህራችሁ በፅሁፍ አቅርቡ።

## 4.7. የሶማሊያ ወረራ

### ተግባር-25


1. ተማሪዎች ሶማሊያ የት እንደምትገኝ በካርታ ላይ አመልክቱ።

የኢትዮጵያና ሶማሊያ ጦርነት መነሻ የሚጀምረው በ1940ዎቹ አካባቢ ነው። ከጣሊያን ወረራ በኋላ ኦጋዴን በእንግሊዝ አስተዳደር ስር ነበር። ከብዙ የዲፕሎማሲ ጥረት በኋላ አብዛኛውን የኦጋዴን አካባቢ እንግሊዝ በ1948 ለኢትዮጵያ አስረክባ ከወጣች ጀምሮ በኢትዮጵያ መንግስት ስር መተዳደሩን ቀጠለ። በ1954 እንግሊዝ የኦጋዴንን ክፍል ሙሉ በሙሉ ለኢትየጵያ አስረከበች። እንግሊዝ ኦጋዴንን ለኢትዮጵያ ስትመልስ ሶማሊያ ደስተኛ አልነበችም። ተበታትነው የቆዩትን የሶማሌ ጎሳዎችን (እንግሊዝ ሶማሊላንድ፣ የፈረንሳይ ሶማሊልንድ፣ ጣሊያን ሶማሊላንድ፣ ኦጋዴን እና የሰሜን ኬንያ አካባቢዎችን) በአንድ ሰንደቅ አላማ ስር ማሰባሰቡን ዋና አላማ ያደረገው የሶማሊያ ሪፑብሊክ መንግስት ከፍተኛ እንቅስቃሴ አደረገ። በ1960 የጣሊያን ሶማሊላንድና የእንግሊዝ ሶማሊላንድ ተዋህድው ሀገር ከመሰረቱ በኋላ ኦጋዴንን ለመውሰድ ኢትዮጵያ ላይ ጦርነት አወጁ። ሁለቱ መንግስታት በ1964 ለመጀመሪያ ጊዜ ጦር ተማዘዙ፣ ጦርነትም በኢትዮጵያ አሸናፊነት ተጠናቀቀ።

የኦጋዴን ጉዳይ እንደገና በ1977 ላይ አገረሸ። በወቅቱ የሶማሊያ ሪፑብሊክ ፕሬዚዳንት የነበሩት ዚያድ ባሬ የመሬት ይገባኛል ጥያቄያቸውን በማንሳት “እስከ አዋሽ ድረስ የኛ ነው” በማለት ታላቋን ሶማሊያ እገነባለሁ የሚል ፖሊሲ በማራመድ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ከፈቱ። ደርግ ስልጣን እንደያዘ ብዙ የሀገር ውስጥ ፈተናዎች እና የውጭ ሀገሮች ተጽዕኖ ክፍተኛ ስለነበር ኢትየጵያ አጣብቂኝ ውስጥ ነበረች። ኢትዮጵያ የነበራት ጦር ብዛትና ትጥቅ ከሶማሊያ ጋር በቁጥርና

በዘመናዊነት አይመጣጠንም ነበር፡፡

በሌላ በኩል ሶማሊያ ቀደም ብላ በቂ የወታደራዊ ዝግጅት በማድረግ ከሶቭየት ህብረት ጋር ግንኙነቷን በማጠናከር የወታደራዊ ድጋፍ አግኝታለች፡፡ ዝግጅታቸውን ከጨረሱ በኋላና ኢትዮጵያ በ1977 የሶማሊያ መደበኛው ጦር ሰራዊት የምስራቅ ኢትዮጵያን ግዛት በመውረር 700 ኪሎ ሜትር ዘልቆ በመግባት ተቆጣጠረ፡፡




ምስል 23፦ የሶማሊያ የወረራ አቅጣጫ

የኢትዮጵያ መንግስት ወዲያውኑ አጸፋውን ለመመለስ እጅግ አስደናቂ ዝግጅት አደረገ፡፡ በእናት ሀገር ጥሪ 300,000 የሚሊሻ ጦር በአጭር ጊዜ በማሰልጠን ለመደበኛው ጦር አጋዥ ሰራዊት አዘጋጀ፡፡ በሌላ በኩል በኢትዮጵያ የማርክሲስት ሌኒንስት ርእዮተአለም ስለታወጀ ደርግ ከሶቭየት ህብረት ጋር ግንኙነት በመመስረት የጦር መሳሪያ ድጋፍ አገኘ፡፡ ሶቭየቶች ከሶማሊያ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ካቋረጡ በኋላ የኢትዮጵያን ጦር በማስታጠቅ ከፍተኛ እገዛ አደረጉ፡፡ በተጨማሪም ኩባና ደቡብ የመን ወታደሮቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ በመላክ ከኢትዮጵያ ሰራዊት ጎን ተሰልፈው ተዋግተዋል፡፡ በመሆኑም በኩባ፣ በደቡብ የመንና በሶቭየት ህብረት ወታደራዊ መኮንኖች እርዳታና ትብብር የኢትዮጵያ ሰራዊት የመልሶ ማጥቃት ጦርነቱን በማድረግ የሶማሊያን ወረራ ቀለበሰ፡፡ የኢትዮጵያ አየር ሃይልና

የኢትዮጵያ ሚሊሻ ጦር ታላቅ ሚና በመጫወት በእብሪተኛው የሶማሊያ ሰራዊት ላይ አሸናፊነቱን ተቀዳጅቷል። በማርች 1978 የሶማሊያ ሰራዊት በካራመራ ላይ ድባቅ ከተመታ በኋላ ከኢትዮጵያ ግዛት ሙሉ በሙሉ ለቀቀ።



ምስል 24፦ ጓድ ሊቀ መንበር መንግስቱ ኃይለማርያም (የወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ)

## ተግባር-26

1. ኢትዮጵያ ሀገራችንን ከወራሪዎች ለመታደግ አርበኞቻችን ከፍተኛ ተጋድሎ ፈፅመዋል። አሁን እየገጠመን ያለውን ችግር ለማሸነፍ ምን አይነት የአርበኝነት ተጋድሎ እንደሚያስፈልግ በቡድን ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።
2. ተማሪዎች በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል ለተደረገው ጦርነት ምክንያቱ ምን እንደነበር በየግላችሁ አብራሩ።
3. በ1977 በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል በተካሄደው ጦርነት የሁለቱን ሀገሮች የጦር ዝግጅት አወዳድሩ።
4. በሶማሊያ ተወሮ የነበረውን የኢትዮጵያ ግዛት በንድፍ ካርታ አመልክቱ።

## ማጠቃለያ

➢ በኢትዮጵያ የዘውዳዊ አገዛዝ ረዥም ታሪክ ያለው ቢሆንም የማዕከላዊ መንግስት ስልጣንን መገዳደር የታሪካችን አንዱ መገለጫ ነበር፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የዘመነ መሳፍንት ጊዜ ነው፡፡ የጎንደር ነገስታት ሀይል የተዳከመበትና የአካባቢ ባላባቶች ሀይል የገነነበት ዘመን ነበር፡፡ ይህ ዘመን ያከተመው በ1855 ካሣ ሀይሉ ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ተብለው ዘውድ በደፋበት ጊዜ ነበር፡፡ ከዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ በኋላ የተለያዩ የውጭ ኃይሎች ማለትም ግብፅ፣ ደርቡሾች፣ ጣሊያንና ሶማሊያ በኢትዮጵያ ላይ ተከታታይ ወረራ ፈፅመዋል፡፡ ኢትዮጵያም እነዚህን የውጭ ሀይሎች አሳፍራ በመመለስ ነጻነቷን አስጠብቃ ቆይታለች፡፡ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ የጀመረው ኢትዮጵያን የማዋሀድ እንቅስቃሴ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት ያላት ሀገር በመመስረት ተጠናቋል፡፡ በተጨማሪም ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ፖሊቲካዊ ዕድገቶች ተመዝግበዋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

I. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ መልሶቻችሁን በትክክል ፃፉ፡፡

1. የአፄ ቴዎድሮስን ኢትዮጵያን የማዋሃድ ስልትን ገምግሙ፡፡
2. የአፄ ዮሐንስና አፄ ምኒልክ ኢትዮጵያን አንድ የማድረግ ጥረቶችና እርምጃዎችን አወዳድሩ፡፡
3. ግብፅ ኢትዮጵያ ላይ ወረራ የፈፀመችበት ዋና ምክንያት ምን ነበር?
4. የመንግስታቱ ማህበር በኢትዮ-ጣሊያን ግጭት ላይ የነበረውን ሚና እንዴት ታዩታላችሁ?
5. በጣሊያን ወረራ ዘመን የኢትዮጵያዊያን የአርበኝነት ተጋድሎ ምን ይመስል ነበር?
6. ስድስቱ የምስራቅ አፍሪካ ጣሊያን የአገዛዝ ክፍፍሎች የተከለሉት ምንን መሠረት በማድረግ ይመስላችኋል?
7. የኢትዮጵያ አርበኞችን ተጋድሎ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ገምግሙ፡፡

8. በ1978 ኢትዮጵያ በሶማሊያ ላይ ድል ለመቀዳጀት ያስቻላትን ምክንያቶች ዘርዝሩ::

*II. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ*

1. ካሳ ኃይሉ (በኋላ ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ) በ1848 ከግብፆች ጋር የተዋጉበት ቦታ ______ ይበላል

   ሀ) ደበርኪ    ለ) መተማ    ሐ) እሮጌ    መ)ጉንደት

2. ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ያሰሩት ትልቁ መድፍ ______ በመባል ይታወቃል::

   ሀ) ስናይፐር    ለ) ዲሽቃ    ሐ) ሴባስቶፖል    መ) መትረየስ

3. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በ1889 አፄ ዮሐንስን ያጋጠማቸው ችግር አይደለም::

   ሀ) የጣሊያን ወረራ

   ለ) የግብፆች ጥቃት

   ሐ) የማህዲስቶች ጥቃት

   መ) የንጉስ ምኒልክና የንጉስ ተክለ ሃይማኖት አመፅ

4. ለአድዋ ጦርነት መነሻ ሰበብ የሆነው ምንድን ነበር?

   ሀ) በአማረኛ የተፃፈው አንቀፅ 17

   ለ) በጣሊያንኛ የተፃፈው አንቀፅ 17

   ሐ) በፈረንሳይኛ የተፃፈው አንቀፅ 3

   መ). መልስ የለም

5. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የአድዋ ድል ውጤት አይደለም::

   ሀ) የአውሮፓዊያን ኢምባሲዎች በአዲስ አበባ መከፈት

   ለ) የወሰን ስምምነት

   ሐ) በአፍሪካ የፀረ-ቅኝ ግዛት ትግል መፋፋም

   መ) የፓን-አፍሪካኒዝም ትግል መዳከም

III. ፈታኝ ጥያቄዎች

1. ሰዎችን በመጠይቅ ወይም መፃህፍትን በማንበብ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትርጓሜ አቅርቡ፡፡

   ሀ) ፊታውራሪ
   ለ) ራስ
   ሐ) ቢትወደድ
   መ) ደጃዝማች
   ሠ) ግራዝማች
   ረ) ልጅ

2. በአካባቢያችሁ በዘመቻ የተሳተፉ፣ ስለሁኔታው የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ ወይም መጽሐፍትን በማንበብ ኢትዮጵያዊያን ሶማሊያን እንዴት ድል ማድረግ እንደቻሉ ለመምህራችሁ ሪፖርት አቅርቡ፡፡

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

- የሲራራ ንግድ፡- በግመል እና በጋማ ከብቶች ጭነት የሚደረግ ረጅም እና አገር አቋራጭ ንግድ ነው።
- ማህዲስት፡- ማህዲ ከሚለው መሥራች ስም የተወሰደ ሲሆን በሱዳን ውስጥ የግብፅን አገዛዝ በመቃውም የተመሰረተው ሃማኖታዊ ይዘት ያለው የፖለቲካ ንቅናቄ ነው።
- አንሳር፡- ለማህዲስት ወታደሮች የተሰጠ ስያሜ ነበር።
- ፋሽስት፡- ፌሰስ ከሚለው የላቲን ቃል የተወሰደ ሲሆን በ1920ዎቹ በጣሊያን ወደ ስልጣን የመጣ ፅንፈኛ ብሔርተኛ እና ፈላጭ ቆራጭ መንግስታዊ ስርዓት ነው።
- የውስጥ አርበኞች፡- በጣሊያን ወረራ ጊዜ ከጠላት ጋር ተመሳስለው ለአርበኞች በሚስጥር መረጃ የሚያደርሱ ናቸው።
- አስካሪስ፡- ከቅኝ ተገዥ ቦታዎች የተመለመሉ የጥቁር ወታደሮች መጠሪያ ነው።
- ባንዳ፡- ከጠላት ጋር አብሮ ሆኖ ሀገሩን የወጋ ሀይል ነው።

# ምዕራፍ-5

# አፍሪካ ከ1500 በኋላ

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ከ1500ዎቹ በኋላ በአፍሪካ ውስጥ የተከሰቱ ዋና ዋና የታሪክ ሁነቶችን ማለትም የባሪያ ንግድ፣ ቅኝ ግዛት፣ የቅኝ ግዛት አስተዳደር፣ ፀረ-ቅኝ ግዛት ትግል እና ድህረ-ነፃነት ሁኔታዎችን ይዳስሳል። ከነፃነት በኋላ በአፍሪካ የተከሰቱ ዋና ዋና ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ክስተቶችንም ያካትታል።

*ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት:*

***ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦***

- *ባርነትና የባሪያ ንግድ በአፍሪካ ያደረሰውን ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ጉዳት ትገመግማላችሁ።*
- *አፍሪካዊያን በቅኝ ግዛት ዘመን ስላሳለፏቸው ጉዳዮች ታብራራላችሁ።*
- *አፍሪካዊያን ከቅኝ ግዛት ነጻ ለመውጣት እና በመካከላቸው ሁሉን አቀፍ ትብብር ለመፍጠር ስላደረጓቸው ትግሎች ትተነትናላችሁ።*

## 5.1 ባርነትና የባሪያ ንግድ በአፍሪካ

### *ተግባር-1*

1. ከ1500 በፊት በአፍሪካ እና በአውሮፓዊያን መካከል የነበረው ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበር አብራሩ።
2. ተማሪዎች ባሪያ ምንድን ነው? የባሪያ ንግድስ? በጥንድ በጥንድ በመሆን ተወያዩ።

ባርነት ከዘር፣ ከቆዳ ቀለም ወይም ከአፍሪካ አህጉር ጋር ብቻ የተያያዘ ጉዳይ አይደለም። በአውሮፓ በተለያዩ አካባቢዎች በተለያዩ ጐሣዎች የውስጥ ግጭቶች ምክንያት የጦር ምርኮኞች በባርነት ይሸጡ ነበር። ለረዥም ዘመን ከምስራቅና መካከለኛው አውሮፓ በተለይም የስላቭ ነገድ አባላት ወደ መካከለኛው ምስራቅና ሰሜን አፍሪካ ይላኩ ነበር። የአውሮፓዊያን ስሌቭ (slave) የሚለው ቃል የተገኘው ስላቭ (slav) ከሚለው የነገዱ መጠሪያ ነው።

ከጥንት ዘመን ጀምሮ ከሰሐራ በስተደቡብ ያሉ የአፍሪካ ግዛቶች ወደ ሜዲትራኒያን አካባቢ ባሪያዎችን ይልኩ ነበር። ይህ የባሪያ ንግድ ከ9ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እየጨመረ ቢመጣም ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው ግን ከአሰሳ ዘመን መጀመር በኋላ ነበር። አውሮፓዊያን አሜሪካን እንዳገኙ ለእርሻና ማዕድን ቁፋሮ እምቅ ሐብት እንዳለው ተገነዘቡ። ይህንን ሀብት ለመጠቀም በርካታ የሠራተኛ ሀይል በመፈለጋቸውም የሀገሬው ነዋሪዎች የአሜሪካን ሕንዶችን በባርነት ጉልበታቸውን ለመጠቀም ሞክረው ነበር። ነገር ግን የአሜሪካን ሕንዶች (Red Indians) በመጀመሪያ በአውሮፓዊያን በመሰቃየታቸውና አዳዲስ በሽታዎች መቋቋም ባለመቻላቸው ተፈላጊውን የሰው ሀይል ሊያሟሉ አልቻሉም። ከእነዚህ ሙከራዎች በኋላ ነበር አውሮፓዊያን ወደ አፍሪካ ፊታቸውን በማዞር የባሪያ ጉልበት ፍላጐታቸውን ለማሟላት ያሰቡት።

አውሮፓዊያን ባሪያዎችን ከአፍሪካ ለማግኘት ከፈለጉባቸው ምክንያቶች መካከል አፍሪካዊያን በሐሩር ክልል ስለሚኖሩ ከአዲሱ ዓለም ጋር ተመሣሣይ የአየር ንብረት ስላለው እና ከወጭ አንፃር ነበር። ከዚህም ሌላ የአፍሪካ የጐሣ አለቆች የጦር ምርኮኞችንና በህብረተሰቡ የተለያዩ ሰዎችን በባርነት ለመሸጥ ያላቸው ዝግጁነት አውሮፓዊያን ንግዱን እንዲገፉበት አደፋፍሯቸዋል። አብዛኞቹ ባሪያዎች መዳረሻ የአሜረካ አህጉር ሲሆን ባሪያዎች በብራዚል ቡና እና የስኳር ምርት፣ በካሪቢያን የሥኳር ምርት እንዲሁም በሰሜን አሜሪካ ደቡባዊ ክፍል ጥጥና ትምባሆ እርሻዎች ላይ ያገለግሉ ነበር።

የመጀመሪያዎቹ ባሪያዎች አትላንቲክን አቋርጠው ወደ አሜሪካ የተጓዙት በ1532 ዓ.ም ነበር። በቀጣዮቹ መቶ ዓመታት የሚጋዙት ባሪያዎች ቁጥር አነስተኛ ሆኖ የቀጠለ ሲሆን ከ1630ዎቹ በኋላ ግን ደቾች፣ ፈረንሳዮችና እንግሊዞች በንግዱ ውስጥ በመግባታቸው ከፍተኛ ዕድገት አሣይቷል። ከ1532 ጀምሮ ለተከታታይ 300 ዓመታት በተካሄደው የባሪያ ንግድ ከ10 ሚሊዮን በላይ አፍሪካዊያን በባርነት ተሸጠዋል። ይህ ቁጥር በጉዞው ላይ የሞቱ 2 ሚሊዮን ባሪያዎችን አያካትትም። ከአፍሪካ የጠረፍ ግዛቶች በ16ኛው ክፍለ ዘመን ዋና የባሪያ ምንጭ የነበረው

የሴኔጋል ጠረፍ ሲሆን የአንጐላ ጠረፍ ደግሞ ከ16ኛው እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን የባሪያ ምንጭ ሆኖ ነበር። የሌሎች አውሮፓዊያን ተሣትፎ ሲጨምር "ስሌቭ ኮስት" ይባል የነበረው ጠረፍ ሌላው የባሪያ ምንጭ ሆኗል። ንግዱ ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት በ18ኛው ክፍለ ዘመን ከሴኔጋል እስከ አንጐላ ያለው የአትላንቲክ ጠረፍ ባጠቃላይ የባሪያ ምንጭ ሆኗል።

አውሮፓዊያን የባሪያ ፍንገላ ዘመቻዎችን ለማካሄድ በሞከሩባቸው አጋጣሚዎች በሐሩር በሽታዎች ይዳከሙ ወይም በአፍሪካዊያን ጦር ይሸነፉ ነበር። በዚህም የተነሳ ራሣቸው ቀጥታ ከመሳተፍ ይልቅ በአፍሪካ ተቀናቃኝ የጎሳ አለቆች መካከል ጦርነት እንዲነሳ የጦር መሳሪያ ያቀርቡላቸው ነበር። የጦር መሳሪያዎችንም የሚለውጡት በባሪያዎች ነበር። ለምሣሌ ፖርቱጋሎች በኮንጐና ንዶንጐ የጎሳ መሪዎች ያስነሱት ግጭት በርካታ ሰዎች ጠረፍ ላይ በሽያጭ ማግኘት አስችሎአቸዋል። በአፍሪካዊያን የጎሳ መሪዎች መካከል የጦርነቱ መነሻ ባህሪ የተለያየ ቢሆንም ውጤቱ ግን በርካታ ሰዎችን ለባርነት ዳርጓል።

### ተግባር-2

1. አውሮፓዊያን ባሪያዎችን ከአፍሪካ ለማግኘት ለምን ፈለጉ?
2. የባሪያ ፍንገላ ተሣታፊዎች እነማን እንደነበሩ ዘርዝሩ።

የፀረ-ባሪያ ንግድ እንቅስቃሴ፦ በ18ኛው ክፍለ ዘመን የስኳር ምርት ከፍተኛ እድገት አሣየ። የምርቱ መትረፍረፍ በበኩሉ ለዋጋው መርከስ አስተዋፅኦ አደረገ። የኢንዱስተሪ አብዮትን ተከትሎ በተለይም በእንግሊዝና ፈረንሳይ ዘመናዊ ማሽኖች በሰፋፊ እርሻዎቻቸው ጥቅም ላይ ውለው የተትረፈረፈ የስኳር ምርት በማግኘት ገበያውን አጥለቀለቁት። በሌላ በኩል የምዕራብ አፍሪካ የባሪያ ነጋዴዎችና የጐሣ አለቆች የባሪያ ዋጋን ከፍ አደረጉት። የባሪያ ዋጋ መወደድ የአውሮፓ ባለ ስፊ እርሻ ባለቤቶች ባሪያዎችን መተካት አላስቻላቸውም። በዚህም ምክንያት ባለ እርሻዎቹ የሚያገኙት ገቢ ቀነሰ። የባሪያ ንግድ እንዲቆምም ምክንያት ሆነ። በዚህ መንገድ አውሮፓዊያን ከባሪያ ንግድ የበለጠ ትርፍ እንደማያገኙ ተገነዘቡ። ስለዚህ ከ1800ዎቹ በኋላ አውሮፓዊያን የባሪያ ንግድን ለማቆም ተነሣሱ። እንግሊዝ ባርነትንና የባሪያ ንግድን በ1807 ህገ ወጥ መሆኑን አወጀች። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ "የፀረ-ባርነት የባህር ሀይል" አቋቁማ የምዕራብ አፍሪካ ጠረፎችን በማሰስ በሀይል ለማስቆም ወሰና ተንቀሳቀሰች።

የአፍሪካዊያን የፀረ-ባርነት ትግልም የባሪያ ንግድ እንዲቆም አስተዋፅኦ አድርጓል:: አፍሪካዊያን ከባርነት ነፃ ለመውጣት ያደረጉት አስተዋፅኦ ቀላል ግምት የሚሰጠው አልነበረም:: የባሪያን ንግድን አሰቃቂ ገፅታ በፅሁፋቸው ያጋለጡት ሁለቱ ከምዕራብ አፍሪካ ተሸጠው የተወሰዱ የቀድሞ ባሪያዎች ኦላዳህ ኡኩያኖና ኦቶባህ ኩጆዋኖ ተጠቃሽ ናቸው:: በተጨማሪም አፍሪካዊያን አሜሪካና ካሪቢያን ደሴቶች ከደረሱም በኋላ አመፃቸውን አላቋረጡም ነበር:: ለምሳሌ በፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ሴይንት ዶሚኒክ (ሐይቲ) የባሪያ አመጽ የተካሄደ ሲሆን በዚች ግዛትም በ19ኛው ክፍለ ዘመን 400,000 ባሪያዎች ይገኙ ነበር:: የሐይቲ ባሪያዎች በ1791 አምፀው ነጭ አሣዳሪዎቻቸውንም ገድለዋል::

### ተግባር-3

1. ባርነትና የባሪያ ንግድ በአፍሪካ ውስጥ እንዴት ተጀመረ?
2. የሸንኮራ እርሻ መስፋፋት ከባሪያ ንግድ ማደግ ጋር ያለውን ትስስር በቡድን በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ::
3. በባሪያ ንግድ ክፉኛ የተጎዳው የትኛው የአፍሪካ ክፍል ነበር? ለምን?
4. የባሪያ ንግድ በአፍሪካ አህጉር ላይ ያስከተላቸውን ችግሮች በጭውውት መልክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

## 5.2 የአውሮፓዊያን ቅኝ ግዛት በአፍሪካ

### 5.2.1. የአውሮፓውያን የቅኝ አገዛዝ ምስረታ ሂደት

### ተግባር-4

1. ስለ ቅኝ ግዛት ሲወራ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ የሰማችሁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. ነፃነት ምንድን ነው? ቅኝ ግዛት ነፃነትን በምን መልኩ ይጋፋል? በትንንሽ ቡድን ተወያዩ::


በአፍሪካ የአውሮፓዊያኑ ቅኝ አገዛዝ እንዲጀመር በር የከፈቱት ፖርቱጋሎች ሲሆኑ በ15ኛው ክፍለ ዘመን በአህጉሪቱ ጠረፎች ባካሄዷቸው የአሰሳ ጉዞዎች ሰበብ ነበር:: በመቀጠልም ደቾች፣ እንግሊዞች፣ ፈረንሳዮች እና ስፔኖች የፖርቱጋሎችን

ዱካ ተከትለው መጡ:: ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ አፍሪካ ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ ምንጭነት፣ ለሸቀጦቻቸው ገበያ እንዲሁም ርካሽ የሰው ኃይል መገኛ ናት በሚል እሳቤ የአውሮፓዊያንን ትኩረት ስባለች:: ከአፍሪካ የሚገኘውን ጥቅም ለማሳደግ አውሮፓዊያን ስለ አህጉሪቱ እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶች መረጃ ማሰባሰብ ችለዋል:: የአፍሪካን የተፈጥሮ ሀብቶች፣ ለትራንስፖርት አገልግሎት አመቺነት ያላቸውን ወንዞች እንዲሁም ለገበያ ማዕከል ሊሆኑ የሚችሉ ህዝብ የሰፈረባቸውን አካባቢዎች ለይተው ማወቅ ችለዋል:: አሳሾቹ እነዚህን ወንዞች ከአፍሪካ ውስጣዊ ክፍሎች ጋር ለሚካሄዱ የንግድ እንቅስቃሴዎች የትራንስፖርት መስመሮች ሊሆኑ ይችላሉ የሚለው ግምታቸው ትኩረታቸውን ወደ ወንዞቹ እንዲያደርጉ አስገድዷቸዋል::

አውሮፓዊያን ነጋዴዎች ከጠረፍ ጣቢያዎቻቸው በመነሳት ወደ አህጉሪቱ ውስጣዊ ግዛቶች ዘልቀው በመግባት የንግድ መስመሮችን መቆጣጠሩን ተያያዙት:: ለምሳሌ በ1860ዎቹ የፈረንሳይ ነጋዴዎች በሀገራቸው መንግስት እርዳታ በሴኔጋል ወንዝ ዳርቻ ትንሽ ቅኝ ግዛት መስርተዋል:: በጎልድ ኮስት የእንግሊዝ መንግስት ከፋንቴ መንግስት ባገኘው ድጋፍ የአሻንቴን ጦር በ1874 ማሸነፍ ችሏል:: በደቡብ አፍሪካ የደች ሰፋሪዎችም የእርሻ ስራ ጀምረዋል:: በ1814 ኬፕታውንን እንግሊዝ ስትቆጣጠር የደች ሰፋሪዎቹ ወደ ውስጣዊ የደቡብ አፍሪካ ግዛቶች በማፈግፈግ ከእንግሊዝ ቁጥጥር ለመሸሽ ሞክረዋል:: በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ፈረንሳይ ሰሜን አፍሪካን በቅኝ ግዛት ለማስገበር ተንቀሳቅሳለች:: ቅኝ-አገዛዝ በአፍሪካ ታሪክ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ የደረሰው ግን በ1880ዎቹ ነበር:: ይህ የታሪክ ክስተት የተፈጸመበትን ጊዜ "አፍሪካን መቀራመት" ተብሎ ይታወቃል::

የቤልጀሙ ንጉስ ሊዎፖልድና ጀርመን በፉክክሩ መግባት አፍሪካን የመቀራመቱን ሩጫ አፋጥኖታል:: አፍሪካን የመቀራመቱ ሂደት በአውሮፓውያን መካካል ግጭት ስለፈጠረ ጉዳዩን በሰላም ለመፍታት የበርሊንን ጉባዔ ከ1884-1885 አካሄዱ:: የበርሊን ጉባኤ በኦቶ ቮን ቢስማርክ አስተባባሪነት ከ1884-85 አስራ አራት የአውሮፓ ሀገሮች አፍሪካን የቅኝ አገዛዝ በተመለከተ ለመወያየት የተካፈሉበት ስብሰባ ነበር::

ፌብሩዋሪ 25/1885 የኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች የበርሊን ጉባዔ አጠቃላይ ድንጋጌ የተባለ ሰነድ የተፈራረሙ ሲሆን ድንጋጌው በርካታ አንቀጾች ነበሩት:: አንቀጽ 34 እንደሚለው ማንኛውም አውሮፓዊ ሀገር በአፍሪካ ቅኝ ግዛት ሲይዝ ለጠቅላላ ድንጋጌው ፈራሚ ሀገሮች ማሳወቅ ይኖርበታል:: ሀገሮቹም ይዞታውን ማጽደቅ፣ ውድቅ ማድረግ ወይም ይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ::




ምስል 1፡ አውሮፓውያን አፍሪካን በቅኝ ግዛት ሲቀራመቱ

## ተግባር-5

1. አፍሪካን ለመቀራመት መሠረታዊ ምክንያቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. በበርሊን ጉባኤ ላይ ተሳታፊዎቹ ምን ምን ይዘት ያላቸው ውሳኔዎች አሳለፉ?

የበርሊን ጉባዔ ሲጠናቀቅ ሰሜናዊ የአፍሪካ ክፍል በአውሮፓዊያን እጅ ወድቆ ነበር፡፡ በ1882 ግብፅ በእንግሊዝ ተይዛ የነበረ ሲሆን አልጀሪያና ቱኒዚያም በፈረንሳይ የበላይነት ስር ወድቀው ነበር፡፡ ከጉባኤው በኋላ ፈረንሳይ በምዕራብ አፍሪካ የነበራትን ይዞታ በማጠናከር ዳሆሜን፣ አይቬሪኮስትንና ጊኒን ያዘች፡፡

እንደ ፈረንሳይ ሁሉ የእንግሊዝ፣ ጀርመንና ቤልጀም መንግስታት በአፍሪካ ቅኝ ግዛት በመያዝ ተግባር ተጠምደው ነበር፡፡ በእንግሊዙ አዛዠ ሎርድ ኪችነር የሚመራው የእንግሊዝና ግብፅ ጣምራ ጦር በ1898 ማህዲስቶችን በኦምድሩማን

ጦርነት አሸነፈ:: ይህ ከሆነ ከሳምንት በኋላ በማርቻንድ የሚመራ የፈረንሳይ ጦር ፋሾዳ መድረሱን ኪችነር መልዕክት ደረሰው፡፤ ይህ ፍጥጫ የፋሾዳ ውዝግብ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን በዲፕሎማሲ ጥረት በሰላም ተጠናቋል:: ከ1898 በኋላ ሱዳን በእንግሊዝና ግብፅ ጥምር አገዛዝ ስር ወደቀች:: ጀርመንም በፊናዋ የቅኝ-ግዛት ማስፋፋት አድርጋለች:: በደቡብ ምዕራብ አፍሪካ (ዛሬ ናሚቢያ) እና ታንጋኒካን ተቆጣጥራለች::

## ተግባር-6

1. በአፍሪካ በእንግሊዝና ፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ሀገሮች የትኞቹ ነበሩ? በንድፍ ካርታ አመልክቱ::
2. ቅኝ ግዛት አስተዳደር በባህሪይው ምን ይመስል እንደነበረ ገምግሙ::

በ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያዎቹ ሁለት አስርት ዓመታት የቅኝ ገዢዎች ዋና ተግባራት ቅኝ ግዛቶችን መቆጣጠር፣ ድንበር ማካለልና አመጾችን መቆጣጠር ላይ ያተኮሩ ነበሩ:: ስለሚገዙት ህዝብ ግንዛቤ ሳይኖራቸው አስተዳዳራቸውን ለማዋቀር ሞክረዋል:: በዚህም ሁለት የቅኝ ግዛት አስተዳደር አይነቶች ተመስርተዋል:: እነርሱም ቀጥተኛና(Direct) ቀጥተኛ ያልሆነ(Indirect) አሰተዳደሮች ነበሩ::

እንግሊዞች የአፍሪካ ልማዳዊ መስተዳደሮች ህዝባቸውን እየመሩ እንዲመስል በማሰብ ቀጥተኛ ያልሆነ አሰተዳደር መስርተዋል:: ይህ ቀጥተኛ ያልሆነ አስተዳደር ተብሎ የሚታወቀው ዋና ቀራፂ ፍሬደሪክ ሉጋርድ ሲሆን መጀመሪያ ተግባር ላይ የዋለውም ሰሜን ናይጀሪያ ላይ ነበር:: በሌሎችም ቅኝ ግዛቶች የተጠቀሙበት ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ የሚያስፈልገውን ወጪ እንዲሁም የሰለጠነ የሰው ሀይል(ወታደራዊና ሲቪል) እጥረት ችግር በማቃለሉ ነበር:: እንግሊዞች ለጎሳ አለቆች ስልጣንና ነጻነት ሰጥተዋቸው የነበረ ሲሆን ይህም ለእነርሱ ታማኝ ሆነው እስከቆዩ ድረስ ብቻ ነበር::

በተቃራኒው ፈረንሳዮች ቀጥተኛ አስተዳደር መስርተዋል:: ይህንን ፖሊሲ ያዳበረው አልበርት ሳሮት ሲሆን በጣም የተማከለ አስተዳደርን የሚደግፍ ሰው ነበር:: ፈረንሳዮች ጠንካራ የራስ ገዝ መብት ያለው ግዛት ለመንግስት ህልውና ችግር ይፈጥራል የሚል ድምዳሜ ላይ ደረሱ:: እንደ ፈረንሳይ እሳቤ ጥቅምን ማስከበር የሚቻለው ቅኝ ተገዢ ህዝቦችን ፈረንሳይኛ ቋንቋ በማስተማር፣ በፈረንሳይ ህግ በማስተዳደር፣ ፖለቲካዊና ሰብዓዊ መብቶችን በማጎናጸፍ ነው የሚል ዕምነት

ነበራቸው:: ይህንን ለማሳካት የፈረንሳይ ዜጎች መብቶችን ለቅኝ ተገዢ ህዝቦችም እንዲተገበሩ ደነገጉ::

*ተግባር-7*

2. የእንግሊዝና የፈረንሳይ የቅኝ አስተዳደርን ስርዓቶችን አነፃፅሩ::

## 5.2.2. ቅኝ አገዛዝ በአፍሪካዊያን ላይ ያስከተለው ተፅዕኖ

*ተግባር-8*

1. የቅኝ አገዛዝ በአፍሪካዊያን ላይ ምን ዓይነት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ያስከተለ ይመስላችኋል?

የቅኝ ግዛት አስተዳደር በአፍሪካ የሚከተሉት ተፅዕኖዎች ነበሩት:: እነርሱም የአፍሪካን፡

- ኢኮኖሚና ባህል እንዲዳከም አድርጓል::
- ሀብት ለብዝበዛ ዳርጓል::
- መለያየት እና የባዕድ ባህል እንዲቀበሉ አስገድዷል::
- የተሳሳተ የድንበር አከላለል በመጠቀሙ ለሀገራት ግጭት ምክንያት ሆኗል::

## 5.2.3. የአፍሪካዊያን ፀረ ቅኝ ግዛት ተጋድሎ

*ተግባር-9*

1. ኢትዮጵያዊያን ለአዎሮፓዊያን የቅኝ ግዛት ሙከራ የሰጡት ምላሽ ምን እንደነበር በጥንድ ቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አብራሩ::

በአፍሪካ ውስጥ የተቀናጀና ለብሔራዊ ነፃነት የሚደረገው ትግል ወደ ወሳኝ ምዕራፍ የተሸጋገረው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነበር:: የረጅም ጊዜ የትግል ልምድ፣ የትምህርት እድል ማግኘት እና ከመጠን ያለፈ የቅኝ ገዥዎች የብዝበዛ ስርዓት አፍሪካዊያን የትግላቸውን ስልት በተቀናጀ ፖለቲካዊ አደረጃጀት እንዲመሩ አነሳሳቸው:: የአፍሪካዊያን ብሄርተኝነት በሁሉም የአፍሪካ ክልሎች

ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መጣ:: ብሄርተኝነት ቀድሞ ማደግ የጀመረው ከሌሎች የአፍሪካ ክልሎች ይልቅ በሰሜንና በደቡብ አፍሪካ ነበር::

## ሰሜን አፍሪካ

**የግብፅ የነጻነት ትግል፦** የግብፅ የነጻነት ትግል የተመራው ሰዓድ ዛግሉል በተባለ ግብፃዊ ብሔርተኛ ነበር:: ዛግሉል ዋፍድ የሚባል ፓርቲ በመመስረት ግብፆች ለነፃነታቸው እንዲታገሉ ይቀሰቅስ ነበር:: ይህ ትግሉ ፍሬ አፍርቶ እንግሊዝ ለግብፃዊያን የራስ-ገዝ አስተዳደር በ1922 ዓ.ም አወጀች:: ነገር ግን ይህ አዋጅ የግብፃዊያንን ሙሉ ነፃነት የመለሰ አልነበረም:: በመጨረሻም የዋፍድ ፓርቲ አሸናፊ በመሆኑ በ1936 ግብፃዊያን ነፃነታቸውን ለማስመለስ ችለዋል::

**የሊቢያ ነጻነት ንቅናቄ፦** ሊቢያ የጣሊያን ቅኝ ግዛት የነበረች ሲሆን ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጣሊያንን ከሊቢያ እንድትለቅ ስለአደረጋት እስከ 1949 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በእንግሊዝ የባለአደራ አስተዳደር ስር እንድትሆን ወሰነ:: በመጨረሻም በ1952 ሊቢያ ነጻ መሆኗ ታወጀ::

**ሱዳን፦** በሱዳን የነፃነት ትግል አል-አሽጋ እና አል-ኡማ የተባሉ ፓርቲዎች ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል:: በእንግሊዝና ግብፅ ጥምር አገዛዝ ስር የነበረችው ሱዳን በየካቲት 1953 ራስን በራስ ለማስተዳደር የሶስት ዓመት የሽግግር ጊዜ ተሰጣት:: በዚሁ ዓመት በተካሄደ ምርጫ ህዝቡ የፓርላማ ተወካዮችን መርጦ መስተዳደር ተዋቀረ:: በ1955 የመጨረሻዎቹ የእንግሊዝ ወታደሮች የወጡ ሲሆን ሱዳን በጥር 1956 ነጻነቷን አወጀች::

**ሞሮኮ፦** ሞሮኮ በፈረንሳይና ስፔን ቅኝ ገዥዎች ተከፋፍላ ነበር:: በሙስሊም ብሄርተኞች የተቋቋሙ የሞሮኮ ብሄራዊ ግንባር (1947) እና ኢስቲቅላል ፓርቲ (1928) ትግሉን መምራት ጀምረው ነበር:: ፓርቲዎቹ ሙሉ ነጻነትን ሲጠይቁ ሱልጣን መሐመድ አምስተኛ ጥያቄውን ደግፈው ተቀላቀሉ:: ብሄርተኞቹም ሰራዊት በማደራጀት በሽምቅ ውጊያ የትጥቅ ትግል ጀመሩ:: በ1955 የሪፍ እና አትላስ ጎሳዎች ትግሉን በመቀላቀላቸው ወታደራዊ አመጹ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ:: በዚህም የፈረንሳይ ጦር በአርበኞቹ በመሸነፉ ለሞሮኮ ነጻነትን ለመስጠት ተስማማች:: ፈረንሳይ በ1956 የሞሮኮን ነጻነት የሚያውጀውን ሰነድ ፈረመች:: በዚያው ጊዜ ስፔን የያዘችውን የሞሮኮ ግዛት ነጻነት በመቀበሏ ሱልጣን የተዋሀደችው ሞሮኮ የመጀመሪያ ንጉስ ሆኑ::

**ቱኒዚያ፦** በቱኒዚያ የነጻነት ትግሉን የመሩት የኒዎዳትሱር ፓርቲ በሀቢብ ቡርጊባ መሪነት እና የቱኒዚያ ኮሚዩኒስት ፓርቲ በሙሀመድ ኢናፋ መሪነት ነበር፡፡ ከ1952-54 ባሉት ጊዜያት ቱኒዚያዊያን ባካሄዱት የትጥቅ ትግል ፈረንሳይን ለድርድር እንድትቀርብ አስገደዷት፡፡ በመጨረሻም በ1956 ቱኒዚያ ነጻ ስትወጣ ሀቢብ ቡርጊባም የመጀመሪያው ፕሬዚደንት ሆኑ፡፡

**አልጀሪያ፦** ከ1945 በፊት ተቋቁሞ የነበረው የኮምዩኒስት ፓርቲ በአልጀሪያ የነጻነት ትግሉ ግንባር ቀደም መሪ ነበር፡፡ ይህን ትግል "ኮሎን" (ቅኝ ገዢዎች) ተብለው የሚጠሩት ነጭ ሰፋሪዎች ለማጨናገፍ ሞክረዋል፡፡ አልጀሪያዊያን የአልጀሪያ አርበኞች ብሄራዊ ነጻ አውጪ ግንባር የተባለ ድርጅት አቋቁመው ከ1954 እስከ 1962 የዘለቀ መራር ትግል አካሂደዋል፡፡ አልጀሪያዊያንም በካይሮ ጊዜያዊ የስደት መንግስት አቋቁመው በ1954 ትግል ጀመሩ፡፡ በትግሉ የተቸገረችው ፈረንሳይ በ1961 ህዝበ ውሳኔ እንዲካሄድ በመስማማቷ ህዝቡ ነጻነቱን መረጠ፡፡ የብሄራዊ ነጻ አውጪ ግንባር መሪ የነበሩት አህመድ ቤን ቤላህ በ1962 የመጀመሪያው የሀገሪቱ መሪ ሆኑ፡፡

## ምዕራብ አፍሪካ

**ጋና፦** ለጋና ነፃነት በ1947 የተመሰረተው ዩናይትድ ጎልድ ኮስት ኮንቬንሽን ትግሉን የመራ ሲሆን ክዋሜ ንክሩማህ ከመሪዎቹ አንዱ ነበሩ፡፡ በ1948 ንክሩማህ ህዝባዊ መሰረት ያለው ፒፕልስ ኮንቬንሽን ፓርቲን መሰረቱ፡፡ በዚህ ፓርቲ ህዝቡን በሰላም እንዲታገል ቢያደርጉም ከእንግሊዝ እስራት አላመለጡም ነበር፡፡ ፓርቲው የስራ ማቆም አድማ፣ ሰልፎችንና በእንግሊዝ ሸቀጦች ማእቀብ መጣልን በመሳሰሉ ስልቶች ትግሉን አቀጣጠለ፡፡ በዚህም እንግሊዝ ለመደራደር በመስማማቷ በ1951 ጋና የራስ ገዝነት ለማግኘት ችላለች፡፡ በተጨማሪ በተካሄዱ ድርድሮች በ1957 ጋና ከሰሐራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገሮች መካከል ነጻ በመውጣት ቀዳሚ ልትሆን ችላለች፡፡ ንክሩማህም የመጀመሪያው መሪ ሆኑ፡፡

ሌሎች የምዕራብ አፍሪካ ሀገሮች ማለትም ናይጀሪያ በ1960፣ ሴራሊዮን በ1961 እና ጋምቢያ በ1965 ነጻነታቸውን ተጎናፀፉ፡፡

**ደቡብ ምስራቅ አፍሪካ፦** በኬንያ ለብሄርተኞች ንቅናቄ መጀመር ወሳኝ ሚና የነበረው በጥቁሮችና በነጮች መካከል የተፈጠረው የመሬት ማፈናቀል ነበር፡፡ በ1901 እንግሊዞች ከኬንያዊያን መሬት የመውረስና ለነጭ ሰፋሪዎች መስጠት የሚያስችል ህግ አወጡ፡፡ መሬት በመነጠቃቸው ክፉኛ የተጎዱት ኪኩዮዎች

በሐሪቱኩ አደራጅነት የወጣት ኪኩዩ ማህበር አቋቁመው ተቃውሞና የቅኝ ግዛቱ አስተዳደር ለውጥ እንዲካሄድ ጥያቄ አቀረቡ:: ከብዙ የትግል ሂደት በኋላ ኬንያ 1963 ላይ ነጻነቷን ተጎናፀፈች::

በደቡባዊ የአፍሪካ አገሮች በተለይ በደቡብ አፍሪካ፣ ዝምባቡዌ እና ናሚቢያ የፀረ-ቅኝ ግዛት ትግል በሰፊው የተካሄደ ሲሆን ትግሉም ረጅም ዓመታትን የወሰደ ነበር:: በደቡብ አፍሪካ የቅኝ አገዛዝ ያበቃው በ1994 ሲሆን የመጀመሪያው ጥቁር ፕሪዝዳንት የፀረ-አፓርታይድ መሪ የነበሩት ኔልሰን ማንዴላ ነበሩ::

### ተግባር-10

1. ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የአፍሪካዊያን የነፃነት ትግል የተፋፋመው ለምን ይመስላችኋል?
2. የነጮች የዘረኝነት አመለካከት በአፍሪካዊያን ላይ ያደረሰው ተጽእኖ ምን ነበር?
3. ተማሪዎች የቅኝ አገዛዝ ስርዓት ላደረሰው ብዝበዛና ጭቆና የአፍሪካዊያን ምላሽ ምን እንደነበር መፅሐፍትን በማንበብ አጭር ዘገባ ሰርታችሁ አቅርቡ::

## 5.3. ነጻ የሆኑ የአፍሪካ ሃገሮች ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ውህደት ለማምጣት የተደረጉ እንቅስቃሴዎች

### ተግባር-11

1. በድህረ ነፃነት ዘመን በአፍሪካ እና በአውሮፓ መካካል ምን ዓይነት ግንኙነት እንደተፈጠረ ተወያዩ::

### 5.3.1. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አ.አ.ድ)

ብሄራዊ የነጻነት ንቅናቄ እንደተጀመረ ብዙ አፍሪካዊያን አንድ አህጉራዊ ድርጅት ለመመስረት ፍላጎት አሳዩ:: ይህ አይነቱ አመለካከት የአፍሪካ አንድነት ንቅናቄ እንዲያቆጠቁጥና የአፍሪካ ህብረት ጽንሰ ሀሳብ እንዲስፋፋ አስተዋጽኦ አበርክቷል:: ምንም እንኳ የአፍሪካ አንድነት ንቅናቄ በ1919-1921፣ 1927 እና 1945 ጉባኤዎች

ቢያካሂድም ሁሉም ከአፍሪካ ውጭ የተጠሩ ነበሩ:: ለመጀመርያ ጊዜ በ1958 አፍሪካዊያን በጋራ ጉዳያቸው ላይ ለመወያየት የአክራን ጉባኤ አዘጋጅተዋል:: በዚሁ ጉባኤ ላይ ቀድሞ ከቅኝ ግዛት ነጻ በወጡ 6 የአፍሪካ ሀገሮች ማለትም ጋና፣ ግብፅ፣ ሱዳን፣ ቱንዝያ፣ ሞሮኮ፣ ሊቢያ እና ሁለቱ ነፃዎች ላይቤሪያና ኢትዮጵያ ተነሳሽነት የተካሄደ ነበር:: ጉባኤው አፍሪካ የአንድነት አስተሳሰብ እና ስድስተኛው የአፍሪካ አንድነት ጉባኤ ሆኖ የሚገለጽ ነበር::

ነገር ግን የአፍሪካ አንድነት ምስረታ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ወደቀ:: አፍሪካዊያን መንግስታት በሀገሮች መካከል ፓለቲካ ውህደት መፍጠር በሚለው ሃሳብ እና ከቀድሞ ቅኝ ገዥዎቻቸው ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት በተመለከተ ልዩነት ነበራቸው:: በዚህም የሞኖሮቪያና የካዛብላንካ ብለው ለሁለት ተከፈሉ:: በናይጀርያና በላይቤርያ የተመሰረተው የሞኖሮቪያ ቡድን ቆይቶ አይቮሪኮስት፣ ካሜሮን፣ ቶጎ፣ ሴኔጋል፣ ማላጋሲ፣ ጋቦን፣ ኢትዮጵያ፣ ሴራሊዮን፣ ሶማሊያ፣ መካከለኛው የአፍሪካ ሪፐብሊክ፣ ሞሪታኒያ፣ ኒጀር፣ ሊቢያ፣ የላይኛው ቮልታ፣ ቱንዝያና ኮንጎም ተሳትፈዋል:: ጋና፣ ማሊ፣ ግብፅ፣ አልጀርያና ሞሮኮ ደግሞ የካዛብላንካ ቡድን አባላት ነበሩ::

ይህንን ክፍፍል በማስወገድ የአፍሪካ አንድነት ደርጅትን ለመመስረት የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለ ስላሴ፣ የግብፁ ገማል አብዱል ናስር እና የጋናው ክዋሜ ንክሩማህ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል:: እነዚህ መሪዎች በአፍሪካ ህዝቦች መካከል የባህል፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ልዩነትን በማስወገድ በጋራ አላማቸው ላይ እንዲቆሙ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል:: በ1963 አፄ ኃይለ ስላሴ ነጻ የሆኑ የሁሉንም የአፍሪካ ሀገሮች መሪዎችን በማሰባሰብ በአፍሪካ አንድነት ላይ ያላቸውን የተለያየ አመለካከት ለማስታረቅ ሙከራ አድርገዋል:: በመጨረሻም ኢትዮጵያ በጁን 1963 የአዲስ አበባ ጉባኤን አዘጋጅታለች::

የአፍሪካዊያንን ትግል አንድ እርምጃ ወደ ፊት የሚያሸጋግር ስለሆነ ልዩነታቸውን ማጥበብ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል:: ስለዚህ የካዛብላንካና የሞኖሮቪያ ሁለቱ ቡድኖች ለጊዜው የአፍሪካን የመዋሃድ ፖለቲካዊ ጥያቄን በማስወገድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አ.አ.ድ) እንዲመሰረት ተስማምተዋል:: ስለሆነም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በይፋ ጁን 25/1963 በአዲስ አበባ ተመሰረተ:: በጉባኤው ነጻነታቸውን የተጎናፀፉ 31 ሀገራት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሰነድን አርቅቀዋል:: አዲስ አበባ የድርጅት ማዕከል ወይም መቀመጫ እንድትሆንም ተወስኗል::



ምስል 2፡ ዋና ዋና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መስራቾች

አ.አ.ድ የሚከተሉትን አላማና ግቦች ለማሳካት የተመሰረተ ድርጅት ነበር፡፡

- በአፍሪካ ህዝቦች መካከል መግባባትና አንድነትን ማጎልበት።
- ከኢምፔሪያሊዝምና ከቅኝ አገዛዝ የአፍሪካን ነጻነት ማፋጠን።
- የአፍሪካዊያን የፖለቲካ እና መሰረታዊ የሰብአዊ መብት ጥሰትን በተመለከተ ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ አስተያየት ማሰባሰብ።
- በአፍሪካ ህዝቦች መካከል አንድ ማህበረሰብ በመፍጠር ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አፍሪካን መመስረት የሚያስችል ስሜትን ማጎልበት።

## ተግባር-12

1. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሰረት አንግቦ የተነሳው ዓለማ ምንድን ነው?
2. በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ ላይ ግንባር ቀደም የአፍሪካ መሪዎች በጉባኤው ላይ እንዴት ልዩነታቸውን ሊፈቱ ቻሉ?

## ማጠቃለያ

- አፍሪካ በአውሮፓ ነጋዴዎችና ቅኝ ገዥዎች ተፅዕኖ ስር ወድቃ ነበር:: የአውሮፓ ነጋዴዎች በሚሊዮን የሚቆጠሩ አፍሪካዊያንን በባርነት ወደ ሰሜንና ደቡብ አሜሪካ እንዲሁም ካረቢያን አጓጉዘዋል:: በተጨማሪም አውሮፓዊያን የአፍሪካን ጥሬ ዕቃዎች ለኢንዱስትሪዎቻቸው አግዘዋል:: ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የአውሮፓ ሀገሮች አፍሪካን በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ይዘው ነበር:: ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የአፍሪካን ነፃ መውጣት ያፋጠነ ሲሆን በዋናነት ቅኝ ገዥ ሃገሮችን ክፉኛ በማዳከሙ እንደ ቀድሞ ሠፋፊ ግዛቶችን መቆጣጠር አላስቻላቸውም ነበር:: በተጨማሪም ሁለተኛው የአለም ጦርነት የአፍሪካዊያን ፖለቲካዊ ንቃተ-ህሊና እንዲዳብር አስተዋጽኦ አበርክቷል::
- በ1950ዎቹና 60ዎቹ ዓመታት የለውጥ ሂደት አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገሮች ነፃነታቸውን ተጎናፅፈዋል:: አፍሪካዊያን አሸናፊዎቹን የህብረቱ ሀይሎችን ደግፈው ባደረጉት አስተዋጽኦ የቅኝ ገዥዎችን ቀልብ ስቦ ስለነበር አፍሪካዊያንን በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ውሳኔ ሰጪነት ለማሳተፍ ወስነው ነበር:: ለዚህም ሲባል በወሰዷቸው ህገ-መንግስታዊና ሌሎች ጥገናዊ ለውጦች የቅኝ አገዛዙ ሥርዓት እንዲንኮታኮት መንገድ ጠርገዋል:: የነፃነት ትግሉ በተፋፋመበት ጊዜ አፍሪካዊያን ለጋራ ዓላማ የጋራ ተቋም ለመመስረት ጥረት አድርገዋል:: ይህ ህልማቸው በርካታ መሰናክሎችን አልፎ በ1963 የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን መስረተዋል::

## የክለሳ ጥያቄዎች

I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ስህተት ከሆኑ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ::

1. የባሪያ ጉልበት ተፈላጊነቱ በአዲሱ ክፍለ ዓለም እንዲጨምር ካደረጉት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የሸንኮራ አገዳ እርሻ መስፋፋት ነበር::
2. በምዕራብ አፍሪካ ጠንካራ የሆነ የፀረ-ቅኝ ግዛት ንቅናቄ ካካሄዱት ውስጥ ሳሞሪ ቱሬ ተጠቃሽ ናቸው::
3. የአክራ ጉባኤ ዋና አዘጋጅ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ-ሥላሴ ነበሩ::

4. በ1884-1885 የተካሄደው የበርሊን ጉባኤ ዋና ዓላማ አፍሪካን ያለጦርነት ለመቀራመት ነበር።
5. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና መቀመጫ አዲስ አበባ ነበር።

*II. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ መልስ የምትሉትን ሃሳብ በፅሁፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።*

1. ባርነትና የባሪያ ንግድ በአፍሪካ ላይ ያደረሰውን ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ጉዳት አብራሩ።
2. ግብፅ እና ጋና ለነፃነት ያደረጉትን ተጋድሎ በማወዳደር አብራሩ።
3. የአፍሪካዊያን የፖለቲካ ንቃተ ህሊና እንዲያድግ ቀዳሚዎቹ ማህበራት ምን ዓይነት አስታዋጽኦ ያበረከቱ ይመስላችኋል?
4. አውሮፓውያን "አፍሪካን ለማሰልጠን" የሚለው ተልኳቸው ለአፍሪካ ሥልጣኔን አበርክቷል ወይስ አላበረከተም? በደገፋችሁት ሀሳብ ላይ ትንታኔ ፃፉ።
5. በሁለቱ የአለም ጦርነቶች መካከል የአፍሪካዊያን ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል ስልቶችን ዘርዝሩ።
6. ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች በተለየ ሁኔታ የአልጀሪያ የነጻነት ትግል ደም አፋሳሽ ሊሆን የቻለው ለምን ይመስላችኋል? ምክንያቶችን ዘርዝሩ።
7. የምዕራብ አፍሪካ ሀገሮችን በቅኝ ግዛት ይዘው የነበሩ የአውሮፓ ሀገሮችንና ቅኝ ግዛቶቻቸውን ዘርዝሩ።

*III. ፈታኝ ጥያቄ*

1. ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ እንቅፋት የነበሩ ምክንያቶችን፣ ስኬቶችን እና ድክመቶችን ሰዎችን በመጠየቅ ወይም መፅሀፍትን በማንበብ ማብራሪያ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

# ምዕራፍ-6

# ቅድመ-ዘመናዊ እና ዘመናዊ የዓለም ታሪክ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ስር በዓለም ላይ የተከሰቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ማለትም በዋናነት የኢንዱስትሪ አብዮትን፣ ሁለቱን የዓለም ጦርነቶች እና የቀዝቃዛው ጦርነትን ያካትታል፡፡ የኢንዱስትሪ አብዮት በሰው ልጅ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣ ክስተት ሲሆን የዓለም ሀገሮችን ያደጉና በማደግ ላይ የሚገኙ በማለት እንዲከፈሉ አድርጓል፡፡ የዚህን አብዮት አጀማመር፣ ሂደትና ውጤቶቹን በዚህ ምዕራፍ ይዳሰሳሉ፡፡ በተጨማሪም የሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ምክንያት፣ ሂደት እና ውጤቶቻቸው ተካተዋል፡፡

*ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡*

*ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦*

- ☞ *ስለ ታላቁ የጅኦግራፊያዊ አሰሳ ዘመን እና ሂደቶቹ ትገልፃላችሁ፡፡*
- ☞ *የህዳሴ እና የሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያሉ መሰረታዊ ጉዳዮችን ትተነትናላችሁ፡፡*
- ☞ *የኢንዱስትሪ አብዮት መገለጫዎችን ታስረዳላችሁ፡፡*
- ☞ *ለኢንዱስትሪው አብዮት መነሻ ምክንያቶችን ማጠቃለያ ዘገባ ታቀርባላችሁ፡፡*
- ☞ *ስለሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ሁነቶችን ትገልፃላችሁ፡፡*
- ☞ *የቀዝቃዛው ጦርነትን ዋና ዋና መገለጫዎች ትዘረዝራላችሁ፡፡*

# 6.1 ታላቁ የጅኦግራፊያዊ አሰሳ ዘመን

## ቁልፍ ቃላት:

- ☞ አሰሳ
- ☞ አዲሱ አለም
- ☞ ቀይ ህንዶች

### ተግባር-1

1. ተማሪዎች አሰሳ ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ምንን ያመለክታል?


በመካከለኛው ዘመን የጅኦግራፊ ዕውቀት በአውሮፓ፣ በሰሜን አፍሪካና በምዕራብ እስያ የተገደበ ነበር:: ከእነዚህ ክልሎች ውጭ ሌሎች ክፍለ ዓለማት ስለመኖራቸው ዕውቅና አልነበረም:: በዘመናዊ ታሪክ በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ታላቁ አሰሳ የተከናወነው በዋናነት በፖርቱጋል ነበር:: ፖርቱጋል በደቡብ ምዕራብ አውሮፓ የምትገኝ አገር ስትሆን በ15ኛው እና በ16ኛው ክፍለ ዘመን አዳዲስ ክፍለ ዓለማትን በማግኘት መሪ ተዋናይ ሀገር ነበረች:: አሰሳን ብሔራዊ አጀንዳ በማድረግ በከፍተኛ ስኬት እንዲከናወን ያደረጉት የፖርቱጋሉ ንጉስ ነገስት ሔነሪ ነበሩ:: በአሰሳው ላይ የነበራቸው ሚና ከፍተኛ ስለነበር "አሳሹ ሔነሪ" የሚል ቅፅል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል:: ወደ አትላንቲክ ውቅያኖስ፣ ህንድ ውቅያኖስ፣ ደቡብና ምዕራባዊ የአፍሪካ የባህር ዳርቻዎች የሚደረገውን አሰሳ በገንዘብና በቁሳቁስ አግዘዋል:: በተጨማሪም አሳሾች፣ የመርከብ ሰራተኞች፣ የካርታ ባለሙያዎችና የስነ-ከዋክብት ተመራማሪዎች አቅማቸውን እንዲያሳድጉ የዕውቀት ማበልፀጊያ ትምህርት ቤት ከፍተዋል::

በ1400ዎቹ ገደማ የፖርቱጋል አሳሾች አዞረስ፣ ማዴራ እና ኬፕ ቨርዲ የተባሉ ደሴቶችን አግኝተዋል:: በ1497 ቫስኮ ደጋማ የተባለ ፖርቱጋላዊ አሳሽ አራት መርከቦችን እየመራ ወደ ህንድ ውቅያኖስ አመራ:: ቫስኮ ደጋማ ጉዞውን ቀጥሎ በ1498 ካልካታ ደረሰ:: በ1500 ፔድሮ ከባራል የተባለ የፖርቱጋል አሳሽ 13 መርከቦችን ይዞ በብራዚል የባህር ዳርቻ ላይ አረፈ:: ብራዚል የፖርቱጋል የባህር ማዶ ግዛት እንድትሆን መሰረቱን ካስቀመጠ በኋላ የምስራቁን አቅጣጫ ይዞ

አፍሪካን በመርከብ ዙሮ የህንድ ውቅያኖስን አቋርጦ ካልካታ ሰፈረ፡፡ በመጨረሻም በ1501 ወደ ፖርቱጋል ተመለሰ፡፡

በ15ኛው እና በ16ኛው ክፍለ ዘመን ከፖርቱጋል በተጨማሪ ስፔንም በአሰሳ ታዋቂ ሀገር ነበረች፡፡ የስፔን ንጉሰ ነገስት ፈርዲናንድ እና ባለቤታቸው ኤዛቤላ አሰሳን የብሔራዊ አጀንዳ አድርገው አሳሾችን በገንዘብና በቁሳቁስ አግዘዋል፡፡ ጣሊያናዊ አሳሽ ክርስቶፎር ኮሎምቦስ የአትላንቲክ ውቅያኖስን በማቋረጥ የካሪቢያን ደሴቶች እና የአዲሱ ክፍለ ዓለም (ሰሜን አሜሪካንና ደቡብ አሜሪካን) እንዲያገኝ ስፔን የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ አድርጋለች፡፡ አትላንቲክ ውቅያኖስን አቋርጦ በማለፍ አዲስ ክፍለ ዓለም አገኘ፡፡ ያገኘውን አዲስ ክፍለ ዓለምም ምዕራብ ህንድ ይባላል ሲል አስታወቀ፡፡ ነገር ግን አዲሱ ክፍለ ዓለም ምዕራብ ህንድ ሳይሆን የአሜሪካን አህጉሮች መሆናቸውን ያረጋገጠው አሜሪጎ ቬስፑቺ ነው፡፡ ስያሜውም ከእርሱ ስም ተወስዶ የአሜሪካ አህጉር ተባለ፡፡

በ1480 በፖርቱጋል የተወለደው ፈርዲናንድ ማጅላን ዓለምን በመረከብ በመዞር የመጀመሪየው መርከበኛ ሆነ፡፡ የምዕራቡን አቅጣጫ ተከትሎ በመሄድ ወደ ሩቅ ምስራቅ መድረስ ይቻላል የሚለውን እሳቤ አንግቦ ተነስቶ ነበር፡፡ ዕሳቤውን እውን ለማድረግ ወደ ሰፔን ሄዶ የስፔንን መንግስት ድጋፍ ጠየቀ፡፡ የስፔን መንግስት ንጉሰ ነገስት የሆኑት ቻርለስ 5ኛም ጥያቄውን በበጎ ስለተረዱት 5 አነስተኛ መረከቦችን ፈቀዱለት፡፡ በኦገሰት 1519 የምዕራቡን አቅጣጫ ይዞ ጉዞውን የጀመረ ሲሆን አትላንቲክ ውቅያኖስን በማቋርጥ የፓስፊክ ውቅያኖስን በኦክቶበር 1520 አገኘ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ውቅያኖስ ላይ በመርከብ የተንሳፈፈ ማጅላን ነበር፡፡ በመቀጠልም በ1520 የፊሊፒንስ ደሴቶችን አገኘ፡፡ ነገር ግን ጉዞውን ከጀመሩት 5 መርከቦች ውስጥ 4ቱ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሲበላሹ ተልዕኮውን አጠናቆ ሴፕቴምበር 9/1522 ወደ ስፔን የተመለሰው አንድ መርከብ ብቻ ነበር፡፡ ምንም እንኳን የማጅላን ህይወት በፊሊፒንስ ቢያልፍም በእሱ የተጀመረው ጉዞ ግቡን ስለመታ ዓለምን በመርከብ የዞረ የመጀመሪያው አሳሽ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡




ምስል 1፡ ፈርዲናንድ ማጀላን ዓለምን በመርከብ ለመዞር የተከተለው መሰመር

በ15ኛው እና በ16ኛው ክፍለ ዘመን የአውሮፓዊያን የአሰሳ ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ ጨመረ:: ለዚህም አነሳሽ ምክንቶች የሚከተሉት ናቸው::

ሀ) ከሩቅ ምስራቅ አገሮች ጋር የንግድ ፍላጎት መጨመር፦ በ1453 ኦቶማን ቱርኮች ኮንስታንቲኖፕልን ስለያዙ የአውሮፓዊያን የየብስ ጉዞና የንግድ እንቅስቃሴ ቆመ:: የየብስ ማለፊያውም በተቃዋሚ ኦቶማን ቱርኮች ስለተያዘ ሌላ አመራጭ መፈለግ ግድ ሆነ:: ከሩቅ ምስራቅ የሚመጡ ቅመማ ቅመሞች በአውሮፓ ገብያ ላይ በጣም ተፈላጊ ስለነበሩ አማራጭ የንግድ መስመር መፈለግ አስገዳጅ ነበር::

ለ) የቴክኖሎጂ እድገት፦ ሰፊ ውቅያኖስን እና ባህርን ለማቋረጥ የሚያገለግሉ የተሻሻሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ ለምሳሌ፡ ካርታ፣ ሉል፣ አቅጣጫ ጠቋሚ ኮምፓስ፣ መግነጢሳዊ አቅጣጫ ጠቋሚ (magnetic needel) እንዲሁም የመርከብና የጀልባ ሞተሮች በውቅያኖስ እና ባህር የሚደርሰውን አደጋ መቀነስ::

ሐ) የአውሮፓውያን የጅኦግራፊ ዕውቀትና የሀብት ፍላጎት መጨመር፦ አውሮፓዊያን አዳዲስ ክፍለ ዓለማትን በአሰሳ የማግኘት ጉጉትን ተከትሎ የሀብት ፍላጎትም በዚያው መጠን ጨመረ:: ምክንያቱም በአሰሳ ከተገኙ ሀገሮች ጋር ቀጥተኛ የሆነ የንግድ ግንኙነት ስለመሰረቱ ኢኮኖሚያቸውን ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው::


## የታላቁ አሰሳ ውጤቶች

ሀ) የማይታወቁ ክፍለ ዓለማት እንዲታወቁ አድርጓል።

ለ) በአውሮፓዊያን መካከል ግጭትን አስከትሏል። አውሮፓዊያን አሳሽ ሀገሮች በአሰሳ በተገኙ አዳዲስ ቦታዎች ላይ የባህር ማዶ ግዛት በመመስረት የምጣኔ ሀብት እና የፖለቲካ ጥቅማቸውን ማስጠበቅ ስለፈለጉ ግጭትን አስከትሏል።

ሐ) ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች አሰሳ ላይ እንዲሳተፉ ከፍተኛ የስነ-ልቦና እና የፖለቲካ መነቃቃትን ፈጥሯል።

መ) ታላቁ የአሰሳ ዘመን በአፍሪካ ላይ የባሪያ ንግድ እንዲስፋፋ ምክንያት ሆኗል። በተጨማሪም በላቲን አሜሪካ የነባር ማህበረሰቦች እሴትና ማንነት አደጋ ላይ ወድቋል። አሳሽ ሀገሮች አዲስ በተገኙ የባህር ማዶ ግዛት ስለመሰረቱ የነባር ማህበረስቦች ቋንቋ፣ ታሪክና የማንነት መገለጫ የሆኑ እሴቶች ወድመዋል በአውሮፓዊያን ባህልም ተወረዋል።




ምስል 2፡ የአውሮፓዊያን አሳሾች መስመርና የባህር ማዶ ግዛቶቻቸው

### ተግባር-2

1. የታላቁ አሰሳን አዎንታዊ እና አሉታዊ ውጤቶች ከለያችሁ በኋላ መልሱን ለመምህራችሁ ግለፁ::

## 6.2 ዘመነ-ህዳሴ፣ የፕሮቴስታንት ዕምነት ንቅናቄ እና የካቶሊካዊያን ምላሽ

### 6.2.1. ዘመነ-ህዳሴ

**ቁልፍ ቃል:**

☞ ህዳሴ

### ተግባር-3

1. ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ እየገነባች ያለውን ግድብ ለምን ህዳሴ ብላ ሰየመችው?
2. ተማሪዎች በአውሮፓ የጨለማው ዘመን መገለጫዎችን ዘርዝሩ::

ጥንታዊ የዓለም ስልጣኔ በአውሮፓ ከ5ኛው-14ኛው ክፍለ ዘመን አሽቆልቁሎ ነበር:: ስልጣኔ እና ማህበረሰባዊ ለውጥ ባለመኖሩ የተነሳ ይህ ጊዜ በአውሮፓ የጨለማው ዘመን ተብሎ ይታወቃል:: በ14ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ገደማ የጥንታዊ ግሪክና የሮማ ስልጣኔዎች ላይ አዲስ የእሴት አሻራዎች ተጨምረው ዳግም ማንሰራራት ጀመሩ:: ይህ እንቅስቃሴ በአንድ ዘርፍ ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በስነ-ጽሑፍ፣ በስነ-ጥበብ፣ በፖለቲካ፣ በሳይንስ፣ በማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ እሳቤዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ አስከትሏል:: የመካከለኛው ዘመን ልሂቃን እሳቤያቸው ከሃይማኖትና መለኮታዊ ነገሮች ጋር የተቆራኘ ነበር:: የዘመነ-ህዳሴ ልሂቃን ግን ከሃይማኖትና መለኮታዊ እሳቤ ይልቅ የሰው ልጆች ተፈጥሮና የገሀዳዊ ዓለም የፈጠራ ውጤቶች የጥናት መስክ እንዲሆኑ አድርገዋል::

የህዳሴ እንቅስቃሴ በ14ኛው ክፍለ ዘመን ቅድሚያ በጣሊያን ብቅ ያለ ሲሆን በሂደት

ወደ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ እንግሊዝ፣ ሆላንድና ሌሎችም ሀገሮች ተሸጋግሯል፡፡ ጣሊያን የጥንታዊ የሮማ ስልጣኔ ማዕከል እና ለግሪክም ቅርብ ስለነበረች የስልጣኔ አሻራዎች የቁጭት ስሜትን ፈጥሯል፡፡

የዘመነ-ህዳሴ እንቅስቃሴ በሰው ልጆች ተፈጥሯዊና ማህበራዊ እሳቤዎች ላይ ትሩፋቶችን አሳድሯል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ልሂቃን በፖለቲካ፣ በስፖርት፣ በሙዚቃ፣ በስነ-ጥበብ፣ በሳይንስ ዘርፉ የነበራቸው የምርምር ተሳትፎ ጨምሯል፡፡
- የሊሂቃን ምርምር ከሃይማኖታዊና መለኮታዊ እሳቤ ይልቅ የሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ተግዳሮት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡
- የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች የስነ-ጽሑፍ ቋንቋ ሆነው እንዲያድጉ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

## ዋና ዋና የዘመነ-ህዳሴ ልሂቃን

ሀ) ዊሊያም ሼክስፒር (1564-1616)፦ እንግሊዛዊው ዊሊያም ሼክስፒር ሐምሌት፣ ሮምዮና ጁሌት፣ ጁሊየስ ቄሳርና ማክቤዝ የተባሉ ተውኔታዊ ድራማዎችን በመስራት ይታወቃሉ፡፡

ለ) ሌዎናርዶ ዳቬንቺ (1452-1519)፦ ዳቬንቺ የብዙ ሙያ ባለቤት ነበር፡፡ ሰዓሊ፣ ቅርፃ ቅርፅ ሰሪ፣ ሙዚቀኛ፣ መሀንዲስና ሳይንቲስት ቢሆንም በጣም የሚታውቀው ግን በሞናሊዛ ስዕልና የመጨረሻው እራት የጥበብ ስራዎቹ ነው፡፡



ምስል 3፡ ሞናሊዛ

ሐ) ሚካኤል አንጀሎ (1475-1564)፦ የአዳም አፈጣጠር የሚለውን የጥበብ ስራ አበርክቷል።

መ) ኒኮላስ ኮፐርኒከስ (1473-1543)፦ ይህ ሳይንቲስት በትውልድ ፖላንዳዊ ሲሆን የሚታወቀውም በስነ-ክዋክብት ምርምር ነው። ፀሐይ የስርዓተ ፀሐይ (solar system) ማዕከል መሆኗን እና መሬትም እንደ ሌሎች ፕላኔቶች ሁሉ በፀሐይ ዙሪያ ስረዓተ-ዙሪት የምትከወን መሆኗን አረጋግጧል።

ሠ) ጋሊሊዮ ጋሊሊ (1564-1642)፦ ይህ ጣሊያናዊ የስነ-ከዋክብትና የፊዚክስ ሊቅ የመሬት ስበትን የተፈጥሮ ቀመር የፈለሰፈና የቴሌስኮፕን አገልግሎት ያሻሻለ ነው።

ረ) አይዛክ ኒውተን (1642-1727)፦ ይህ እንግሊዛዊ ታላቅ የሂሳብና የፊዚክስ ሊቅ ሲሆን የካልኩለስን እና የመሬት ስበትን ቀመር ያሻሻለ ነው።

### ተግባር-4

1. ዘመነ-ህዳሴ ቅድሚያ በጣሊያን ለምን ያንሰራራ ይመስላችኋል።
2. በጋሊሊዮ ጋሊሊ እና በአይዛክ ኒውተን መካከል ስለመሬት ስበት ቀመር መሰረታዊ ልዩነት የፊዚክስ መምህራችሁን ጠይቃችሁ ገለጻ አድርጉ።

## 6.2.2 የፕሮቴስታንት ዕምነት አማኞች ንቅናቄ

### ተግባር-5

1. የሃይማኖት መለያየት ለምን ተፈጠረ?

የፕሮቴስታንት ዕምነት አማኞች ንቅናቄ ከሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ለመለየት የተደረገ እንቅስቃሴ ነው። ለፕሮቴስታንት ዕምነት ንቅናቄ መነሻ የሮማ ካቶሊካዊያን ጳጳሳት እና ቀሳውስት በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የነበራቸው ገደብ የለሽ ተጽዕኖ አስተዋፅኦ አድርጓል። የፕሮቴስታንት ዕምነትን ከሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ለመለየት በእንግሊዝና በቦሂሚያ (ቼክ) እንቅስቃሴ ቀደም ብሎ በ14ኛው ክፍለ ዘመን ሙከራዎች ቢኖሩም በይፋ የተመሰረተው ግን በ1517 በጀርመናዊ ማርቲን ሉተር አማካኝነት ነበር።

ማርቲን ሉተር የካቶሊክ ዕምነት ተከታይ መነኩሴ እና በዊተንበርግ ዩኒቨርሲቲ የቴዎሎጂ ፕሮፌሰር ነበር:: የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ለሃጢያት ማስተሰርያ ብላ ከግለሰቦች የምትሰበስበውን ገንዘብ በመተቸት 95 የመቃወሚያ ሀሳቦችን በዊተንበርግ ቤተክርስቲን መግቢያ በር ላይ በኦክቶበር 31/1517 ለጠፈ:: የሰው ልጆች ከሃጢያት የሚነፁት በበጎ ምግባር እንጂ ገንዘብ በመስጠት አይደለም በማለት ተቃውሞን አሰማ::



ምስል 4፡ ማርቲን ሉተር

የማርቲን ሉተርን ስብከት ለማስቆምና እሱንም ወደ ካቶሊክ ዕምነት ለመመለስ ብዙ ጥረት ቢደረግም አልተሳካም:: ማርቲን ሉተርም ብዙ ተከታይ አፈራ ዕምነቱም ወደ ሌሎች ሀገሮች ተሰራጨ:: በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ሀገሮች የፕሮቴስታንት ዕምነት ተስፋፋ:: ለምሳሌ፡- በፈረንሳይ በዮሐንስ ካልቪን አማካኝነት የካልቪኒስት ፕሮቴስታንት ዕምነት ሲመሰረት ተከታዮችም ሁግኖትስ ይባላሉ:: በእንግሊዝ የአንግሊካን ፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ተቋቋመ:: በስዊዘርላንድም የስዊዝ ተሀድሶ ቤተክርስቲያን ተመሰረተ:: በሌላ መልኩ ደግሞ በብዙ የአውሮፓ ሀገሮች የሃይማኖት ጦርነትን አስከትሏል::

### ተግባር-6

1. ማርቲን ሉተር የፕሮቴስታንት ዕምነትን ለማስፋፋት ምን ዓይነት ዘዴ ተጠቀመ?
2. የፕሮቴስታንት ዕምነት ንቅናቄ የሃይማኖት ብዝሃነትና ምክንያታዊ አስተሳሰብ ላይ ያበረከተውን ሚና ገምግሙ።

## 6.2.3. የካቶሊካዊያን ምላሽ

### ተግባር-7

1. የዕምነት መቻቻል ለሰላም እሴት ያለውን ሚና ተወያዩ።

የፕሮቴስታንት ዕምነት ከፍተኛ ትችትና ተጽዕኖ ስላሳደረ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ውስጣዊ የማሻሻያ እርምጃዎች ወሰደች። እነዚህ ውስጣዊ የማሻሻያ እርምጃዎች የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን ከፕሮቴስታንት ሃይማኖት ንቅናቄ ለመጠበቅ የተወሰዱ ነበሩ።

ከእነዚህም መካከል፦

ሀ) ጠንካራ አመራር መሰየም። የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን ለትችት የዳረጋት የአመራር ብልሽት ስለነበር አቅም ያላቸውን እና ቁርጠኛ የሆኑ ግለሰቦች የመሪነት ቦታዎችን እንዲይዙ ተደረገ።

ለ)ተከታታይ የሃይማኖት ምክክርና ጉባኤ ማዘጋጀት (1545-1563)፦ ተከታታይ የሆነ የሃይማኖት ምክክርና ክርክር ጉባኤዎች ከተካሄዱ በኋላ የዓለማዊ ህይወት ዝንባሌ፣ ለሃጢያት ማስተሰርያ ተብሎ የሚሰበሰበው ገንዘብና ግለሰቦችን በዝምድና ትስስር መሾም እንዲቀር ተደረገ።

ሐ) የእየሱሳዊያን ሕብረት መመስረት፦ በኢግናትየስ ሎዮላ አማካኝነት በ1543 የተመሰረተው የእየሱሳዊያን ሕብረት ዋና ዓላማ በተለያዩ ክፍለ ዓለማት በስውርም ሆነ በግልፅ የካቶሊክ ዕምነትን በስብከት ማስፋፋት ነበር።

### ተግባር-8

1. የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ውስጣዊ ችግሮችን ለመቅረፍ ምን ምን አርምጃዎችን ወሰደች?

## 6.3. የኢንዱስትሪ አብዮት

**ቁልፍ ቃል**

☞ የኢንዱስትሪ አብዮት

### ተግባር-9


1. በአካባቢችሁ የሽመና ወይም የብረታ ብረት ስራ ባለሙያዎች ካሉ ስራቸውን እንዴት እንደሚከውኑ ጠይቃችሁ በጽሑፍ ዘገባ አቅርቡ።

የኢንዱስትሪ አብዮት በ1750 ገደማ ተጀምሮ በማምረት ሂደት ውስጥ የሠው ጉልበትን በማሽኖች መተካት ወይም የማገዝ ለውጥ ነው። ይህም አዝጋሚና ውድ ከነበረው በእጅ ማምረት ፈጣንና ርካሽ ወደሆነው በማሽን የማምረት ሂደት መሸጋገርና እንዲሁም በቤት ውስጥ በተለምዶ ከማምረት በሚገባ በተደራጀ ፋብሪካ ደረጃ ማምረት መጀመሩን የሚያመላክት ነው። የኢንዱስትሪ አብዮት የተጀመረው በእንግሊዝ ሲሆን ቀስ በቀስ ወደ ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮችና አሜሪካ ተዛምቷል። ይህ አብዮት በእንግሊዝ ሊጀመር የቻለባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ማሽኖችን ሰርተውና ገዝተው የመጠቀም አቅም የነበራቸውና ፋብሪካዎችን መገንባት የሚችሉ ባለፀጎች መኖራቸው፣ ምቹ የገበያ ሁኔታ መፈጠር፣ የተፈጥሮ ሀብት (የድንጋይ ከሰልና የብረት ማዕድን) መኖር ናቸው።

በጥንታዊው ዘመን እንዲሁም በአውሮፓ መካከለኛው ዘመን የነፋስ ጉልበትና ውሃ ለሃይል ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል። በኢንዱስትሪ አብዮት የመጀመሪያ ዘመናትም የውሃ ጉልበት ጥቅም ላይ የዋለ ቢሆንም በአዲሱ እና በየትኛውም ቦታ ጥቅም ላይ መዋል በሚችለውና የበለጠ ጉልበት የሚያመነጨው የእንፋሎት ሃይል ተግባራዊ ሆኗል። የእንፋሎት ሞተሮች ውሃን በድንጋይ ከሰል በማፍላት በታመቀ እንፋሎት ሃይል የማመንጨት ቴክኖሎጂ ነበር። በእንግሊዝ የድንጋይ

ከሰል በብዛት የሚገኝና ርካሽ በመሆኑ ለዚሁ ሁኔታ መልካም አጋጣሚን ፈጥሯል:: የመጀመሪያዎቹ የእንፋሎት ሞተሮችም የተፈለሰፉት በሳቭሪ (1698) እና ኒውኮመን (1705-1711) ነበር::

በ1660ዎቹ ከህንድ የሚመጣው ከጥጥ የተሰራ ጨርቅ በህዝቡ ተወዳጅ ሆኖ ስለነበር የእንግሊዝ ነጋዴዎች የጥጥ ጨርቅ ፋብሪካን በሀገራቸው የማምረት ሙከራዎችን አድርገው ነበር:: በእንግሊዝ የጨርቃጨርቅ ምርት ሂደት የጆን ኬይ ፈጠራ(flying shuttle) ስር ነቀል ለውጥ እንዲያመጣ ያደረገ ሲሆን ሸማኔዎች ከሚያመርቱት የበለጠ ፍጥነት ነበረው:: በ1764 ሌላው እንግሊዛዊ ጄምስ ሀርግሬቭስ ማጠንጠኛ (Spinning Jenny) ብሎ የሰየመው ማሽን በአንድ ጊዜ በርካታ ክሮች ልብስ እንዲሆኑ የሚሸምን ማሽን ነበር::



ምስል 5፡ (spinning Jenny) ጥሬ ጥጥ ወደ ክር ተቀይሮ ለልብስ መሥሪያ ሲዘጋጅ

ሌላው የእንፋሎት ሞተር የሃይል ምንጭ በመሆን ያገለገለው በባቡር ትራንስፖርት ላይ ነበር:: የባቡር መጓጓዣ ቴክኖሎጂ ትልቅ እመርታ እንዲያመጣ ሚና የተጫወቱት ጆርጅ ስቲቨንሰንና ልጁ ሮበርት ስቲቨንሰን ነበሩ:: የመጀመሪያው የባቡር ትራንስፖርት የተዘረጋው ከስቶክተን እስከ ዳርሊንግተን ከተሞች በ1825 ሲሆን በመቀጠልም በ1830 ከሊቨርፑል እስከ ማንቸስተር የተሠራው ነበር:: የኢንዱስትሪ አብዮት ትልቅ የቴክኖሎጂ እምርታ ያሳየበት ሌላው መስክ ብረት ማቅለጥ ላይ ሲሆን በብዛትና በርካሽ ዋጋ ሊመረት ችሏል:: የድንጋይ ከሰልን እንደሃይል ምንጭ በመጠቀም በብረት ማቅለጫ ማሽኖች አማካይነት በርካታ

መጠን ያለው ብረት ማምረት ተችሏል።

## ተግባር-10

1. ከኢንዱስትሪ አብዮት በፊት የኢንዱስትሪ ምርቶች እንዴት ይመረቱ ነበር?

የኢንዱስትሪ አብዮት ከጊዜና ከቴክኖሎጅ ዕድገት አኳያ ሁለት ዋና ዋና ደረጃዎችን ያለፈ ነበር። የመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት (1750-1870) የመጀመሪያዎቹ ውስብስብ ማሽኖች የተስፋፉበትና ቀደምት ፋብሪካዎች የተገነቡበት፣ እንፋሎት የሃይል ምንጭ በመሆን ለምርትና ለመጓጓዣ አገልግሎት መስጠት የጀመረበት፣ የድንጋይ ከሰል፣ የብረትና የአረብ ብረት ምርቶች በብዛት መመረት የታየበት እና አዳዲስ የመጓጓዣ አይነቶች በብዛት መመረት የጀመረበት ወቅት ነው።

በሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት (ከ1870 በኃላ) የኤሌክትሪክ፣ የነዳጅና የአቶሚክ ጉልበት በሃይል ምንጭነት ማገልገል ጀምረው ነበር። ሳይንስ ለኢንዱስትሪ ግንባታ ማገልገሉና እንደ ጨርቃጨርቅ፣ ብረታ ብረት፣ ኬሚካል፣ የትራንስፖርት፣ ፕላስቲክ፣ ናይለንና የመሳሰሉት ሠው ሠራሽ ምርቶች በብዛት ስራ ላይ ውለዋል። እንደ አውሮፕላን፣ ሬድዩ፣ ቴሌቪዥን፣ የኤሌክትሮኒክስ መልዕክቶችና የመሳሰሉት አዳዲስ ፈጣን የመጓጓዣ እንዲሁም የመገናኛ መሳሪያዎች መፈልሰፍና ሥራ ላይ መዋል ይገኙበታል። በተጨማሪም በመሬት ዙሪያ የሚሽከረከሩ ሠው ሠራሽ ሳተላይቶች እንዲሁም ወደ ሌሎች ፕላኔቶች የሚላኩትን መንኮራኩሮች ሥራ የሚያጠቃልል ዘመን ነው።

የኢንዱስትሪ አብዮት የዓለማችንን ገጽታ ቀይሮታል። ምንም እንኳ ይህ አብዮት አሉታዊ ውጤቶች ቢኖሩትም ጥቅሞቹ የጎሉ ነበሩ።

## ተግባር-11

1. በኢንዱስትሪ አብዮት ሁለቱ ደረጃዎች የተሰሩ ስራዎችን አወዳድሩ።
2. የኢንዱስትሪ አብዮት ለምን ቀድሞ በእንግሊዝ ጀመረ? ምክንያቶችን ለመምህራችሁ ግለፁ።

# 6.4. ሁለቱ ታላላቅ የዓለም ጦርነቶች

## 6.4.1. የአንደኛው የአለም ጦርነት (1914-1918)

### ተግባር-12

1. ተማሪዎች ስለግጭት ምንነት እና መንስኤ የሆኑ ጉዳዮች ግለፁ? እነዚህ ግጭቶችስ እንዴት ይፈታሉ?

የአንደኛው የዓለም ጦርነት በባህሪው የኢምፒሪያሊስቶች ጦርነት ነው:: በአውሮፓ የካፒታሊዝምን እድገት ተከትሎ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ፉክክሩ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ:: ይህ ፉክክር የአውሮፓ ሀገሮችን በሁለት ወታደራዊ ቡድኖች ሥር እንዲደራጁ እና እንዲዋጉ ምክንያት ሆኗል:: ለአንደኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ መሠረታዊ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው::

ሀ) ኢምፔራሊዝምና የቅኝ ግዛት ግጭቶች፦ የአውሮፓ ኃያላን መንግስታት የአፍሪካንና የእስያ አህጉርን በቅኝ ግዛት ለመቀራመት ከፍተኛ ፉክክር ነበራቸው:: ይህም ግጭት፣ አለመተማመንና ስጋት እንዲነግስ አድርጓል::

ለ) ብሔርተኝነት፦ ብሔርተኝነት ህዝቦች ለሀገራቸው የሚኖራቸውን የአርበኝነት ስሜት እንዲሁም ለሀገራቸው ያላቸው ፍቅርና ታማኝነትን ያጠቃልላል:: በ19ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓ ብሔርተኝነት ዋናው የግጭት መንስኤ ነበር::

### ተግባር-13

1. ብሔርተኝነት እንዴት ለግጭት ምክንያት ሊሆን ይችላል?

ሐ) ቡድንተኝነትና የጦር መሣሪያ እሽቅድምድም፦ በአውሮፓ ሀገሮች መካከል እየጨመረ የመጣው ውጥረት ምክንያት በጦር መሳሪያ እና ወታደራዊ ሀይል አንዱ ሌላውን ለመብለጥ ጠንካራ ፉክክር ውስጥ ገቡ:: በአውሮፓ ሀገሮች ፓርላማዎች ውስጥ ዋናው የውይይት አጀንዳ ወታደራዊ በጀት ሆነ:: ለጋራ ጥቅም ሲባል ቡድንተኝነት ተጀመረ:: አንዱ በሌላው ላይ የነበረው ጥርጣሬ የአውሮፓ መንግስታትን ወታደራዊ ቡድኖችን ለመመስረት አብቅቷቸዋል::

በዚህም መሰረት የሦስትዮሽ ህብረት በኋላ ‹‹ማዕከላዊ ሀይሎች›› (central powers) በጀርመን መሪነት፣ በኦስትሪያ ሀንጋሪ፣ ኦቶማን ቱርክ፣ ጣሊያን (በ1915 ህብረቱን የለቀቀች) እና ቡልጋሪያ (በ1915 የተቀላቀለች) ተመስርቶ ነበር:: ሌላኛው ቡድን ደግሞ በ1907 በእንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ሩሲያ የሶስትዮሽ ወዳጅነት (triple entente) የሚባል የጦር ቡድን መመስረታቸውን አሳወቁ::

### 6.4.1.1. የጦርነቱ አጀማመር

**ተግባር-14**

1. ጦርነት ምንን ያስከትላል? ሰላምንስ እንዴት ማስጠበቅ ይቻላል?

ለአንደኛው ዓለም ጦርነት መፈንዳት ሰበብ የኦስትሪያ ሀንጋሪ መስፍንና አልጋ ወራሽ የነበሩት ፍራንሲስ ፈርዲናንድና ባለቤታቸው ሶፍያ በቦሲኒያ ዋና ከተማ ሳራየቮ በጉብኝት ላይ እንዳሉ በጁን 28/1914 መገደላቸው ነበር:: ግድያውን የፈፀመው የሰርቢያ ተወላጅ የሆነው ጋቢሪሎ ኘርንችፐ በመሆኑ ኦስትርያ ሀንጋሪ በሰርቪያ ላይ ጁለይ 28 ቀን 1914 ጦርነት አወጀች:: ይህም ለጦርነቱ መፈንዳት ሰበብ ሆነ::

ሩሲያ ወዳጅዋን ሰርቢያን ለመርዳት ጦሯን አንቀሳቀሰች:: ጀርመንም የሩሲያን እንቅስቃሴ በመቃወም ኦገስት 2 ቀን 1914 በሩሲያ ላይ ጦርነት አወጀች:: በተመሳሳይ ኦገስት 3 ቀን 1914 ጀርመን በፈረንሳይ ላይ የጦር አዋጅ አስተላለፈች:: ጀርመን ፈረንሳይን ለመውጋት ገለልተኛዋ ቤልጀየምን እንደመሸጋገርያ ድልድይ ተጠቅማለች:: ይህንንም በመመልከት ኦገስት 4 ቀን 1914 እንግሊዝ ጀርመንን ለመዋጋት ከጦርነቱ መግባቷን አስታወቀች:: ቱርክና ቡልጋርያ ማዕከላዊ ኃይሎችን በመደገፍ ወደ ጦርነቱ ገቡ:: የፈረንሳይ፣ የሩሲያንና የእንግሊዝን ቡድን በመደገፍ ደግሞ ወደ ሰላሣ የሚደርሱ ሀገሮች በጦርነቱ ተሰለፉ::

የአንደኛው አለም ጦርነት በሶስት ዋና ዋና ግንባሮች ተካሂዷል:: እነርሱም፦

ሀ) የምዕራብ ጦር ግንባር፦ በዚህ ግንባር ጀርመን ከፈረንሳይ፣ ከእንግሊዝና ከአሜሪካ ጦሮች ጋር ተፋልማለች:: ከዚህ በፊት ለጦርነት ያልዋሉ እንደ አውሮፕላን፣ ታንክ፣ መድፍ፣ የመርዝ ጋዝና የመሳሰሉት የጦር መሳርያዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ውጊያ ላይ የዋሉት በዚህ ግንባር ነበር::

ለ) የምስራቅ ግንባር፦ በዚህ ግንባር ሩሲያ በአንድ ወገን ጀርመንና ኦስትሪያ ሀንጋሪ በሌላ ወገን በመሆን ተዋግተዋል:: በዚህ ግንባር ሩሲያ ከፍተኛ ሽንፈት ደርሶባታል:: ከዚያም በ1917 የሶሻሊስት አብዮት በሩሲያ በመፈንዳቱ ከጦርነቱ ልትወጣ ችላለች::

ሐ) የደቡብ ጦር ግንባር፦ በዚህ ግንባር ሁለቱም ቡድኖች ከፍተኛ ፍልሚያ አካሂደዋል:: በ1917 ጀርመንና ኦስትሪያ ሀንጋሪ አብዛኛውን የባልካን ግዛት መቆጣጠር ችለው ነበር::

ነገር ግን የተባበሩት ኃይሎች በ1918 ባደረጉት ጥቃት ከፊሉን የባልካን ግዛት ነፃ አውጥተው ኦስትሪያ ሀንጋሪ በመሸነፏ ከጦርነቱ ወጣች:: ቀደም ብለው ቱርክና ቡልጋርያ ከጦርነቱ የወጡ ሲሆን በመጨረሻም ጀርመን መሸነፏን በመቀበል በ1918 ተኩስ ለማቆም ተስማማች:: በዚህ መልኩ የአንደኛው የአለም ጦርነት ፍጻሜ ሆነ::

### 6.4.1.2. የፓሪሱ የሰላም ጉባኤ እና የጦርነቱ ውጤቶች

**ተግባር-15**

1. በአካባቢያችሁ ግጭት ሲፈጠር ሽማግሌዎች እንዴት ያስታርቃሉ?

ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ በአሸናፊ ኃይሎችና በተሸናፊዎች መካከል የሰላም ውል ለመፈራረም የፓሪሱ የሰላም ጉባኤ በ1919 ተጠራ:: ይህን ጉባኤ በበላይነት የመሩት ጦርነቱን ያሸነፉት አራቱ ኃያላን አገሮች ነበሩ:: እነሱም የአሜሪካው ፕሬዜዳንት ውድሮው ዊልሰን፣ የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ደቪድ ሎይድ ጆርጅ፣ የፈረንሣዩ ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጅ ክሌመንሱትና የኢጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ቪቶርዮ ኢማኑኤል ኦርላንዶ ነበሩ:: ጉባኤው ለወራት ከተካሄደ በኋላ በአሸናፊ ሀገሮችና በጀርመን መካከል በቨርሳይለስ ከተማ ተፈረመ:: ጀርመን ላይ የማያዳግም የእርምት እርምጃ ተወሰደ:: ለምሳሌ ለአሸናፊ አገሮች ብዙ ገንዘብ እንድትከፍል ተወሰነ:: ከአፍሪካና ከእስያ የነበሯት ቅኝ ግዛቶቿንም ተነጠቀች::

አንደኛው የዓለም ጦርነት በብዙ መስኮች የተለያዩ ውጤቶችን አስከትሏል:: አስር ሚሊዮን የሚሆኑ ወታደሮች ሲያልቁ ወደ ሀያ ሚሊዮን የሚጠጉ ቆስለዋል:: በኢኮኖሚው ዘርፍ በርካታ ሀብት በመውደሙ የኢኮኖሚ ቀውስ በአውሮፓ ተከሰተ:: በሌላ መልኩ ደግሞ በጦርነቱ ምክንያት አሜሪካ ኃያል ሀገር ስትሆን

አዳዲስ ሀገሮችም ተመሰረቱ:: ንጉሳዊ አስተዳደሮች በሩሲያ፣ በጀርመንና በኦስትሪያ ተወገዱ እንዲሁም የአለም መንግስታት ማህበርም (League of Nations) ተመሰረተ::

### ተግባር-16

1. ለአንደኛው ዓለም ጦርነት መፈንዳት ሰበብ ምንድን ነበር?
2. የአንደኛው ዓለም ጦርነት ያስከተለውን ውድመት ገምግሙ::

## 6.4.2. ሁለተኛው የአለም ጦርነት (1939-1945)

### 6.4.2.1. የጦርነቱ መሰረታዊ ምክንያቶች

### ተግባር-17

1. በአካባቢያችሁ ሰዎች በተደጋጋሚ የሚጋጩት ለምንድን ነው? ወደ መፍትሄስ እንዴት ይመጣሉ?

ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት የሚከተሉት መሰረታዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ::

ሀ) የፋሽስት ጠባይ ያላቸው አምባገነን መንግስታት በጣሊያንና ጀርመን ስልጣን መያዝ እና ወታደራዊ መንግሥት በጃፓን ወደ ስልጣን መምጣት::

ለ) ፍጹም ዘረኛ ብሄርተኝነት፦ ከላይ በተጠቀሱት ሶስት መንግስታት ዘንድ ፍጹም ዘረኛ የሆነ ብሄርተኝነት መስረፅ::

ሐ) በጀርመን፣ ጣሊያንና ጃፓን ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት የጦር መሳርያ ማምረት፣ የጦር ኃይላቸውን መገንባት፣ የሕዝባቸውንም አእምሮ ለጦርነት ያዘጋጁ ነበር:: በተጨማሪም ሶስቱ መንግስታት የበርሊን-ሮም-ቶክዮ ሶስትሽ ቡድን መመስረታቸው በሌሎች ሀገሮች ላይ የደህንነት ስጋት ፈጥሯል::

መ) የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግስታት ይከተሉት የነበረው የማግባባት ፖሊሲ (Appeasement Policy) ውድቀትና የመንግስታቱ ማህበር ድክመት ነበሩ::

## 6.4.2.2. የጦርነቱ ሂደት

ጀርመን ፖላንድን ስትወር የጦርነቱ መጀመሪያ ሆነ:: የጀርመን ጦር ፊቱን ወደ ምዕራብ በማዞር ኖርዌይን፣ ዴንማርክንና ሉክሰምበርግን ወረረ:: ኖርዌርይን በመጠቀም የጀርመን ወታደሮች ወደ ፈረንሳይ በማምራት የሰሜንና የምዕራቡን ክፍል ተቆጣጠሩ:: በከፊሉ ደቡብ ፈረንሳይ ክፍል በቪች ከተማ የራሱ የሆነውን መንግስት ሲያቋቁም በስደት ላይ ወደ ውጭ የሸሹት ፈረንሳውያን በጄኔራል ደጎል አስተባባሪነት ነጻ ፈረንሳይ በማለት ትግላቸውን ቀጠሉ::

አሜሪካም የጃፓንን በሩቅ ምስራቅ መስፋፋት በመቃወም በጃፓን ላይ የንግድ ማዕቀብ ጣለች:: ጃፓን ይህን እርምጃ በመቃወም ዲሴምበር 7/1941 በሀዋይ ደሴት የፐርል ሀርበርን የባህር ሀይል በቦንብ ደበደበች:: በዚህ ጊዜ የጃፓን አጋሮች ጀርመንና ጣሊያን አሜሪካ ላይ ጦርነት አወጁ:: አሜሪካም ወደ ጦርነቱ ገባች::



ምስል 6 ፡ አዶልፍ ሒትለር ከናዚ ወታደሮች ጋር

ጁን 22/1941 የጀርመን ጦር ሩሲያን ወረረ:: በተጨማሪም ግሪክንና ዮጎዝላቪያን በከባድ ሁኔታ ማጥቃት ያዘ:: የጀርመን ወታደሮች ሩሲያን በሶስት አቅጣጫ ወረሯት:: በሰሜን የሰታሊንግራድን በመያዝ በመሀል ሞስኮንና በደቡብ ደግሞ ዮክሬይን በእነርሱ እጅ ለማስገባት ወደፊት ገሰገሱ:: በ1943 የሩሲያ ቀይ ጦር ሀይሉን በማስተባበር ለመጀመሪያ ጊዜ በጀርመን ወታደሮች ላይ ስታሊንግራድ በተባለ ስፍራ ድልን ተቀዳጀ:: ከዚህ ጦርነት በኋላ የጀርመን ጦር ሽሽት የጀመረበት እና የሩሲያ ቀይ ጦር ወደ ፊት የገሰገሰበት ነበር:: ወደፊት በመገስገስ የሩሲያ

ቀይ ጦር ጀርመኖችን ከሮማንያ፣ ከቡልጋሪያ፣ ከዮጎዝላቪያ፣ ከሀንጋሪና ከፖላንድ ጠራርጎ አስወጣ። ጀርመንን ለመውረር በምስራቅ አቅጣጫ ጉዞውን ወደፊት ቀጠለ።

በሌላ በኩል አሜሪካ ወደ ጦርነቱ ከገባች በኋላ ከእንግሊዝ ጦር ጋር በመሆን በሰሜን አፍሪካ የነበረውን የጀርመንና የጣሊያን ጦር በግብፅ አል አላሚን የተባለ ስፍራ ላይ ድል አደረጉት። በመቀጠልም የአሜሪካና የእንግሊዝ ጣምራ ጦር ጣሊያንን ወጉ። ጣሊያንም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መሸነፏን ተቀበለች። ጁን 6/1944 ጣምራ ጦሩ ፈረንሳይን ነጻ ለማውጣት ኖርማንዲ የተባለ የፈረንሳይ ግዛት ገባ። ጀርመኖችንም ድል በማድረግ ከፈረንሳይ አስወጣቸው። የእንግሊዝና የአሜሪካ ጣምራ ጦር ጉዞውን ወደ ጀርመን ቀጠለ። ኤፕሪል 25/1945 ጣምራ ጦሩ ጀርመንን ከምስራቅ አቅጣጫ እያጠቃ የመጣው ቀዩ ጦር በኤልቤ ወንዝ ላይ ፊት ለፊት ገጥመው የመጨረሻ ድል አደረጉት።

የጃፓን ጦር በ1942 በተካሄደው ወረራ ፊሊፒንስ፣ ማሌዥያ፣ ኢንዶኔዥያና ኒው ጊኒን ተቆጣጠረ። ሆኖም ግን ይህንን የጃፓንን ግስጋሴ የአሜሪካ ባህር ሃይል ገትቶታል። የአሜሪካ ጦር ጃፓንን በተደጋጋሚ በማሸነፍ ብዙ ደሴቶችን ተቆጣጠረ። ከእነዚህ ደሴቶች በመነሳት የአሜሪካ የአየር ሀይል በጃፓን ላይ ጉዳት አደረሰ። ኦገስት 6 እና 9/1945 ሄሮሽማና ናጋሳኪ በተባሉ የጃፓን ከተሞች ላይ የአሜሪካ አየር ሃይል አቶሚክ ቦምብ ጣለ። ጥቃቱን ለመቋቋም ባለመቻሉ የጃፓን መንግስት መሸነፉን አመነ። በዚሁ የሁለተኛው የአለም ጦርነት እስያ ላይ ተጠናቀቀ።

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል፣ ኮሙኒዝም እንዲስፋፋ አድርጓል፣ አሜሪካና ሩሲያ ኃያል ሀገር ሆነው እንዲወጡ አስችሏቸዋል፣ የቀዝቃዛው ጦርነትን አስከትሏል፣ የሀገራት ድንበሮች ላይ ለውጥ አምጥቷል፣ የጸረ ቅኝ አገዛዝ ትግል እንዲፋፋም ረድቷል እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መመስረት ምክንያት ሆኗል።

## ተግባር-18

1. የሁለተኛው የዓለም ጦርነት መንስኤዎችን አብራሩ።
2. ተማሪዎች ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምን ዓይነት ውጤቶችን አስከተለ?

# 6.5. የቀዝቃዛው ጦርነት (1945-1991)

## ቁልፍ ቃል

☞ የቀዝቃዛው ጦርነት

### ተግባር-19

1. ሰላምን የሚያናጉ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

በካፒታሊዝምና በኮሚኒዚም አቀንቃኝ ሀይሎች የተከሰተ የርዕዮተ-ዓለም ጦርነት ሲሆን አሜሪካና ሩሲያ በፊታውራሪነት መርተውታል:: የቀዝቃዛው ጦርነት ምንም እንኳ አለምአቀፋዊ ፉክክር ቢሆንም በማደግ ላይ ባሉ የአለም ሀገሮች ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጥሯል:: ቀዝቃዛው ጦርነት በአፍሪካ ላይ ተጽዕኖ አስከትሏል:: እርዳታና ድጋፍ በመስጠት መፈንቅለ-መንግስትና አብዮቶች እንዲቀሰቀሱ አድርጓል:: በዚህ ወቅት አፍሪካ ከአሜሪካ፣ ከሩሲያ እንዲሁም ከእንግሊዝ፣ ከፈረንሳይ፣ ከቻይና ከኩባ ጋር ቅርብ የሆነ የፓለቲካ ትስስር ነበራት:: ስለሆነም አፍሪካ ከቅኝ ገዥ ሀይሎች ጋር የነበራት ትስስር እንዲቀጥል አድርጓል:: በአጠቃላይ ቀዝቃዛው ጦርነትና ቅኝ ግዛት ለአፍሪካ ፈጣን የሆነ እድገት እንዳይኖራት አስተዋፅኦ ነበራቸው:: ቅኝ ግዛትና ቀዝቃዛው ጦርነት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን (Neo-colonialism) በአፍሪካ አስፋፍተዋል::

## ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያ ርዕስ ሆኖ የቀረበው አሰሳ ሲሆን በ15ኛው እና በ16ኛው ክፍለ ዘመን ፖርቱጋልና ስፔን ቀዳሚ ሀገሮች ነበሩ። አውሮፓዊያን አሳሽ ሀገሮች በአሰሳ በተገኙ አዳዲስ ቦታዎች ላይ የባህር ማዶ ግዛት በመመስረት የምጣኔ ሀብት እና የፖለቲካ ጥቅማቸውን ማስጠበቅ ስለፈለጉ ግጭትን አስከትሏል። ሁለተኛው ርዕሰ ጉዳይ ዘመነ-ህዳሴ ሲሆን የህዳሴ እንቅስቃሴ የጥንታዊ የሮማና የግሪክ የስልጣኔ ውጤቶችን ዳግም በማጥናትና በማድነቅ የተጀመረ ነበር። ይህም በአንድ ዘርፍ ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በስነ-ጽሑፍ፣ በስነ-ጥበብ፣ በፖለቲካ፣ በሳይንስ፣ በማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ እሳቤዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ አስከትሏል። ይህ እሳቤ ለፕሮቴስታንት ንቅናቄ አነሳሽ ሁኗል።
- የፕሮቴስታንት እምነት አማኞች ንቅናቄ ከሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ለመለየት የተደረገ እንቅስቃሴ ነው። የሮማ ካቶሊካዊያን ጳጳሳት እና ቀሳውስት በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የነበራቸው ተጽዕኖ ለንቅናቄ መነሻ አስተዋፅኦ አድርጓል። በሶስተኛ ደረጃ የታየው የኢንዱስትሪ አብዮት ነው። የኢንዱስትሪ አብዮት በ1750 ገደማ በማምረት ሂደት ውስጥ የሠው ጉልበትን በማሽኖች መተካት ወይም ማገዝ የተጀመረበት ለውጥ ነው። የተለያዩ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችሉ ውስብስብ ማሽኖችን ጥቅም ላይ የዋሉበት ዘመን ሲሆን እነዚህ ፈጠራዎች የበርካታ መቶ ዓመታት ጠንካራ የሥራ ባህልና የብዙ ፈጠራ ድምር ውጤቶች ናቸው።

- በመጨረሻም ሁለቱ የዓለም ጦርነቶችን እና የቀዝቃዛው ጦርንትን መገለጫዎች አይተናል፡፡ አንደኛው የዓለም ጦርነት ኢምፒሪያሊስቶች የኢኮኖሚና የፖለቲካ ፍላጎታቸውን ለማሳካት ያደረጉት ጦርነት ነበር፡፡ በአውሮፓ የካፒታሊዝምን እድገት ተከትሎ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ፉክክሩ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ የአውሮፓ ሀገሮች በሁለት ወታደራዊ ቡድኖች ሥር ተደራጅተው ተዋግተዋል፡፡ የፋሽስት ጠባይ ያላቸው አምባገነን መንግስታት ጣሊያንና በጀርመን ስልጣን መያዝ እና ወታደራዊ መንግሥት በጃፓን ወደ ስልጣን መምጣትም ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት መሰረታዊ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ የሁለተኛው የዓለም ጦርነትም የቀዝቃዛው ጦርነትን አስከትሏል፡፡ የቀዝቃዛው ጦርነት ዓለምን በምዕራባዊና በምስራቃዊ ቡድኖች የከፈለ የርዕዮተ-ዓለም ጦርነት ሲሆን በካፒታሊዝምና በኮሚኒዚም አቀንቃኝ ሀይሎችን አሜሪካና ሩሲያ በፊታውራሪነት መርተውታል፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

*I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ መልሶቻቸውን በትክክል አብራሩ::*

1. የኢንዱስትሪ አብዮት በአፍሪካ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ምን እንደሆነ ግለፁ::
2. የአንደኛውና የሁለተኛው ዓለም ጦርነቶች ውጤቶቻቸውን ዘርዝሩ::
3. የኢንዱስትሪ እድገት ያስከተላቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ውጤቶች ምን ምን ነበሩ?
4. የአውሮፓ ሀገሮች በወታደራዊ ቡድኖች ስር ለመደራጀት ያስፈለጋቸው ለምን ነበር?

*II. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ በ"ሀ" አምድ ስር የተዘረዘሩትን ስራዎች በ"ለ" አምድ ስር ከተጠቀሱት ግለሰቦች ጋር አዛምዱ::*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዓለምን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመዞር የተንቀሳቀሰ | ሀ) ጋሊሊዮ ጋሊሊ |
| 2. የናዚ ጀርመን መሪ የነበረ | ለ) አይዛክ ኒውተን |
| 3. የስነ-ክዋክብትና የፊዚክስ ሊቅ | ሐ) ኒኮላስ ኮፐርኒክስ |
| 4. የመሬት ስበት ህግ ቀማሪ | መ) አዶልፍ ሂትለር |
| 5. የሽመና ማሽን የሰራ | ሠ) ፈርድናንድ ማጅላን |
| | ረ) ቻርለስ ደጎል |
| | ሰ) ጀምስ ሃርግሬቭስ |

*III. ፈታኝ ጥያቄዎች*

1. የአንደኛውና የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀርመን ለምን ጀማሪ ሆነች? ምክንቶቻችሁን ግለጹ::
2. የአንደኛውና የሁለተኛው የዓለም ጦርነቶችን ተመሳሳይነት እና ልዩነት አብራሩ::
3. አፍሪካዊያን በቀድሞ ቅኝ ገዥዎቻቸው ስር ሆነው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መሳተፋቸው ያስገኘላቸው ጥቅም አብራሩ::

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

- አሰሳ፡- የማይታወቁ አዲስ ክፍለ ዓለማትን በማግኘት ለሌላው ዓለም ማስተዋወቅን ያመለክታል።
- አዲሱ አለም፡- በአሰሳ የተገኙ የሰሜን አሜሪካ እና የደቡብ አሜሪካ አህጉሮች
- ቀይ ህንዶች፡- የአሜሪካ አህጉራት በአሰሳ ከመገኘታቸው በፊት የነበሩ ነባር ማህበረሰቦች።
- ህዳሴ፡- የጥንታዊ ግሪክና ሮማ ሥልጣኔዎች ላይ እሴት በመጨመር ዳግም ለማንሰራራት የተደረገ እንቅስቃሴ ነው።
- የኢንዱስትሪ አብዮት፡- የጠንካራ የሥራ ባህል ውጤት ሲሆን “ኢንዱስትሪ” የሚለው ቃል ፍች ሥራን በጥራትና በቀልጣፋነት መስራት ማለት መሆኑ ያመለክታል።
- ቀዝቃዛው ጦርነት፡- ዓለምን ወደ ሁለት ርዕዮተ ዓለም የከፈለ የቃላት እና የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ነው።

# ምዕራፍ-7

# ወቅታዊ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሶስት ዋና ዋና አለም አቀፍ ጉዳዮች ተዳሰዋል፡፡ እነርሱም የአየር ጠባይ ለውጥ፣ የውሀ መጠን መቀነስ እና የደኖች መመናመን ናቸው፡፡ የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ በወስጡ የሚከተሉትን ዋና ዋና ርእሰ ጉዳዮችን ይዟል፡፡ እነርሱም፦ የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤዎች፣ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው ወጤቶች እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚወሰዱ እርምጃዎች ናቸው፡፡

የውሃ መጠን አቅርቦት መቀነስ ሌላው ጽንሰ ሃሳብ ሲሆን የውሀ መጠን አቅርቦት መቀነስ መንሰኤዎች፣ የውሃ መጠን አቅርቦት መቀነስ ያመጣቸው ተጽዕኖዎች እና የንጹህ ውሃ አቅርቦት እጥረትን ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎችን አካቷል፡፡ በሌላ መልኩ የደኖች መመናመን የተዳሰሰ ሲሆን በዚህ ውስጥ የደኖች መመናመን ዋና ዋና ምክንያቶች፣ የደን ውጤቶች እንዲሁም የደኖችን መመናመን ለመቀነስ የሚወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች ተብራርተዋል፡፡

*ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡*

***ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦***

- *የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤዎችን ታነጻጽራላችሁ፡፡*
- *የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸውን ወጤቶች ትተነትናላችሁ፡፡*
- *የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚወሰዱ እርምጃዎችን ትገመግማላችሁ፡፡*
- *የውሀ መጠን አቅርቦት መቀነስ መንሰኤዎች ትተነትናላችሁ፡፡*

- ☞ የንጹህ ውሀ አቅርቦት እጥረት ለመጨመር የሚወሰዱ እርምጃዎችን ትገመግማላችሁ::
- ☞ የደኖች መመናመን ዋና ዋና ምክንያቶችን ትለያላችሁ::
- ☞ የደኖች መመናመን ዋና ዋና ተጽእኖዎችን ትተነትናላችሁ::
- ☞ ለደኖች መመናመን የሚወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ትገመግማላችሁ::

# 7.1. የአየር ንብረት ለውጥ

## 7.1.1 የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ እና ውጤት

### ቁልፍ ቃላት:

- ☞ ለውጥ
- ☞ መከላት
- ☞ መመናመን

### ተግባር-1

1. ተማሪዎች! ነፋስ መኖሩን በምን ታውቃላችሁ? እስኪ የምታውቁትን ተናገሩ::
2. ተማሪዎች! የአየር ንብረት ለውጥ ምን ማለት እንደሆን ታውቀላችሁ? እስኪ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ::

### ሀ) የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤዎች

### ተግባር-2

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ ድርቅ ተከስቶ ያውቃል? ምክንያቱን አብራሩ::

ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚሆኑት በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ሙቀት

አማቂ ጋዞች ከመጠን በላይ መከማቸታቸው ነው:: የሙቀት አማቂ ጋዞችን ክምችት ያባባሰውና ለአየር ንብረት ለውጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገው የሰው ልጅ የድንጋይ ከሰልን፣ የተፈጥሮ ነዳጅና ጋዝን በሰፊው በመጠቀሙ ምክንያት ካርቦን ዳይኦክሳይድ የተሰኘውን ጋዝ ወደ አየር በመልቀቅ ቀድሞ የነበረውን የአካባቢ አየር ተፈጥሮአዊ ሁኔታ እንዲዛባ ምክንያት በመሆኑ ነው:: ይሁን እንጂ የሰውን ልጅ አሁን እየገጠመው ያለው ፈተና በሰው ሰራሽ ምክንያት በከባቢ አየር ውስጥ ባሉት የሙቀት አማቂ ጋዞች ለውጥ ሳቢያ በተከሰተው አየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚደርሱ የተለያዩ አደጋዎች ናቸው:: ይህ ማለት ግን ተፈጥሮም በራሷ ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋጽኦ አታደርግም ማለት አይደለም:: እንደ እሳተ ገሞራና ተፈጥሯዊ የሰደድ እሳትም ለአየር ንብረት ለውጡ አስተዋጽኦ ያላቸው ናቸው::

### ተግባር-3

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ ለአየር ንብርት ለውጥ መንስኤ ናቸው የምትሏቸውን ጉዳዮች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ ለክፍል አቅርቡ::

## ለ) የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው ውጤቶች

### ተግባር-4

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የግብርና ምርት በምን በምን ምክንያት የሚቀንስ ይመስላችኋል?

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው አደጋዎች ድንበር ተሻጋሪ ናቸው:: ለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ የሆኑ ክስተቶች በተከሰቱበት አካባቢ ብቻ ተወስነው የሚቀሩ ሳይሆን በብዙ አገሮች እየተስፋፉ የሚሄዱ ናቸው:: የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው ዋና ዋና ችግሮች እንደሚከተለው ተገልጸዋል::

## ሀ) የግብርና ምርት መቀነስ

የሀገራችን አብዛኛው ህዝብ በግብርና የሚተዳደር መሆኑ ይታወቃል:: የህዝቡ ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ ይገኛል:: የህዝብ ቁጥር መጨመር ተጨማሪ የምግብ አቅርቦትን የሚጠይቅ ነው:: የምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ሲባል በቀጥታም

ይሁን በተዘዋዋሪ አካባቢ ላይ ተፅዕኖ ማድረሱ የማይቀር ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በአካባቢ ላይ ጫና ሲደርስ የግብርናው ዘርፍ ምርታማነት ሊቀንስና ቁጥሩ እያደገ የሚገኘውን ህዝብም መመገብ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## ለ የአፈር መከላት

የኢትዮጵያ መልክዓ ምድር ተራራማ፣ ኮረብታማ እንዲሁም ዝቅተኛ ቦታዎችና ሜዳዎች የሚበዛበት ነው፡፡ ታላላቅ ወንዞችና ጅረቶች መነሻቸው ከደጋማው አካባቢ ነው፡፡ የመሬቱ አቀማመጥ ከወንዞች የፍሰት አቅጣጫ ጋር ተዳምሮ ለአፈር መከላት የተመቸ አድርጎታል፡፡ በዚህም ምክንያት አፈሯ እየታጠበ ወደ ጎረቤት ሃገር መጓጓዙ የተለመደ ሁኗል፡፡ ለአፈር መከላት ዋናው ምክንያት የወራጅ ውሃ እንዲሁም በደረቅ ወቅት እና በሞቃታማው አካባቢ የሚከተለው አውሎ ነፋስ ነው፡፡ ይህም የአየር ንብረት ለውጥን ከማባባሱም በተጨማሪ የድርቅ መከሰትን፣ የበረሃማነት መስፋፋት፣ የተፈጥሮ ሚዛን መቃወስና የመሳሳሉትን አስከትሏል፡፡



ምስል1- የአፈር መከላት እና የበረሃ መስፋፋት

### ተግባር-5

1. በአካባቢያቸሁ ሰዎች የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እየተወሰዱ ያሉትን እርምጃ አብራሩ፡፡
2. ተማሪዎች! ከምስል1 ምን ተረዳችሁ? በምን ምክንያት የተፈጠረ ይመስላችኋል? የተረዳችሁትን ሃሳብ ለክፍላችሁ አጋሩ፡፡

## ሐ) የሰውና የእንስሳት ጤና ችግር

### ተግባር-6

1. ተማሪዎች የሰዎችም ሆነ የእንስሳት በሽታ የሚበዛው በቀዝቃዛ ነው ወይስ በሞቃት እርጥበታማ አካባቢ? ለምን?

የአየር ንብረት ለውጥ የሚፈጥረው የጤና ችግር በሰው ዘር ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም። እንደ ሰው ልጅ ሁሉ የቤትና የዱር እንስሳትም የአየር ንብረት ለውጥ በሚፈጥረው የጤና ችግር ተጠቂዎች ናቸው። አሁን አሁን ደግሞ በቆላማውና በበረሃማው የአገራችን ክፍል ተወስነው የነበሩት በሽታዎች ወደ ደጋው በመሸጋገር ችግር በመፍጠር ላይ ይገኛሉ። ለምሳሌ፦ ወባና የገንዲ በሽታ ተጠቃሽ ናቸው።

የአየር ንብረት ለውጥ እየተባባሰ በሄደ ቁጥር የበሽታዎቹ የመስፋፋት አቀም የበለጠ ይጨምራል እንዲሁም አዳዲሶች የመከሰት እድላቸው እየሰፋ ይሄዳል። እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ይቀንሳሉ እንዲሁም ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬም ሆነ የሃገር ውስጥ ፍጆታ አቅርቦት አናሳ ይሆናል።

## መ) የገፀ- ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ መጠን መቀነስ

### ተግባር-7

1. ተማሪዎች! የአካባቢያችሁ ማህበረሰብ ውሃን እንዴት ይንከባከባሉ? እስኪ የምታውቁትን ተናገሩ።

የአየር ንብረት ለውጥ ከሚያስከትላቸው ዋና ዋና ውጤች መካከል የበረሃ መስፋፋት እና በተደጋጋሚ የድርቅ መከሰት ሲሆኑ የእነዚህ መከሰት ደግሞ በከረሰ መድር እና በገፀ-ምድር የሚገኝ የወሃ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እንዲመጣ ምክንያት ሁነዋል። በአጠቃላይ የአየር ንብረት ለውጥ በሃገር የኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ጉልህ የሆነ ተፅዕኖ ይፈጥራል። ማህበራዊ ችግሮችን በማባባስ አለመረጋጋትን፣ ስደትን፣ ረሃብና ጦርነትን እና የመሳሰሉትን ሁነቶች ሊያባብሳቸው ይችላል።

የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚወሰዱ እርምጃዎች ብዙ ቢሆኑም በዋናነት እንደ መፍትሄ ተብለው የተቀመጡት ደግሞ ለተለያዩ ግልጋሎቶች ብለን የምናቃጥላቸውን ነገሮች መቀነስ፣ ብዙ ዛፎችን መትከል፣ ጥቅጥቅ ደኖቻችንን

መንከባበከብና ካርቦንዳይኦክሳይድን ከከባቢ አየር መምጠጥ የሚችሉ የፈጠራ ውጤቶችን ማበረታታት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

*ተግባር-8*

1. ተማሪዎች የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸውን ወጤቶች መጀመሪያ በግል ከዚያም በጥንድ በመወያየት የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::


## ውስን ጥናት

### የአየር ንብረት ለውጥ እና የኢትዮጵያ ትኩረት

ኢትዮጵያ በተለመደው ሂደት ብትቀጥል በ2002 ዓ.ም የነበረው የ150 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት በ2022 ዓ.ም ወደ 400 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የካርቦንዳይኦክሳይድ መጠን ሊያድግ የሚችል ነበር:: ይህም ማለት ልቀቱ በ150% ይጨምር ነበር ማለት ነው::

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ችግር በዘላቂነት ለመመከት እንዲያስችላት ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ በመንደፍ በ2017 ዓ.ም ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በመገንባት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች:: ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ የኢኮኖሚ ዕድገትንና ልማትን ማምጣት፣ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን መቀነስ፣ ማስቀረት እና ለአየር ንብረት ለውጥ አይበገሬነትን ማጎልበት የሚሉ ሶስት አበይት አላማዎች አሉት:: ለአየር ንብረት ለውጥ አለመበገር ስንል በአየር ንብረት መለወጥ ሳቢያ የሚመጡ ለውጦችን የመቋቋምና የመግታት ብቃት መኖር ማለት ነው:: በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የአየር ጠባይ መዋዠቅ ይከሰታል:: በዚህም አሉታዊ ተፅዕኖዎች ሳቢያ የሰዎች ደህንነትና የኢኮኖሚው አድገት መንተት እንዳያጋጥመው ይህንኑ መቋቋም የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል:: ይህን ጉዳይ የማጣጣም ስራ መስራትን ይጠይቃል:: የአረንጓዴ ኢኮኖሚ እቅዷ በአራት ምሰሶዎች የተደገፈ ነው:: ምሰሶዎቹም:

1. የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት እየቀነሱ የምግብ አቅርቦትን ለማረጋገጥና የገበሬውን ገቢ ለማሳደግ የሰብሎችንና የቤት እንስሳትን ምርታማነት ማሳደግ፡፡
2. ከታዳሽ የኃይል ምንጮች የኤሌክትሪክ ኃይልን በማመንጨት እና በማስፋፋት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሆነ ለጎረቤት አገሮች ማቅረብ፡፡
3. በማጓጓዣ፣ በኢንዱስትሪ፣ በመኖሪያና በመስሪያ ቤት ሕንፃዎች ውስጥ ኃይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በማስፋፋት የኃይል ብክነትን ማስቀረት ናቸው፡፡
4. ካርቦንን ከከባቢ አየር ማግለልን ጨምሮ ሥርዓተ ምሕዳራዊ አገልግሎቶች እንዲበራከቱ ለማድረግ ደኖች እንዲያገግሙና እንዲጠበቁ ማድረግ፡፡



ምስል- 2 ጥብቅ ደን



ምስል-3 እያገገመ ያለ እጸዋት

## ተግባር-9

1. ተማሪዎች! ከላይ የቀረበውን ውስን ጥናት በየግላችሁ በማንበብ ያገኛችሁትን ፍሬ ነገር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ፡፡
2. ተማሪዎች ከምስል2 እና 3 ምን ተረዳችሁ? የተረዳችሁትን አብራሩ፡፡

## 7.2. የውሃ መጠን አቅርቦት መቀነስ

### ተግባር-10

1. ተማሪዎች! በየአካባቢያችሁ የውሃ እጥረት አለ? ካለ በምን ምክንያት የተፈጠረ ይመስላኋል?

ውሃ ህይወት ላለው ነገር ሁሉ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ሀብት ነው:: ዓለማችን 71% የሚሆነው መሬት በውሃ የተሸፈነ ነው:: ይህ ደግሞ አስተማማኝ በሆነ የተፈጥሮ ዑደት አማካኝነት መጠኑ እንደተጠበቀ እንዲቆይ ተፈጥሮ ግድ ትላለች:: እንደ ባለሙያዎች ገለጻ ንጹህ ውሃ ያላቸው ሁሉም የውሃ ማከማቻዎች በፕላኔቷ ላይ በእኩልነት ቢከፋፈሉ ለሁሉም በቂ የመጠጥ ውሃ ይኖር ነበር:: ሆኖም ግን እነዚህ የውሃ ማከማቻዎች ባልተመጣጠነ መልኩ በመሰራጨታቸው የመጠጥ ውሃ እጥረትን የመሰለ አለም አቀፍ ችግር የለም:: ይሁን እንጂ በተለያዩ ምክንያቶች ውሃ በመባከኑ፣ የውሃ ፍጆታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱ እና የጥራት ይዘቱን በማጣቱ ሳቢያ የንፁህ ውሃ አቅርቦት እጥረት በብዛት ያጋጥማል:: የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በአውስትራሊያ እና በእስያ (ምስራቅ፣ መካከለኛው፣ ሰሜን)፣ በሰሜን ምስራቅ ሜክሲኮ፣ ቺሊ፣ አርጀንቲና እንዲሁም በአፍሪካ ውስጥ ችግሮች በስፋት ይታያሉ:: በጠቅላላው በ 80 የዓለም ሀገሮች ውስጥ የውሃ እጥረት ተመዝግቧል::

በአገራችንም በተለይ በአንዳንድ የኢትዮጵያ ከተሞች ችግሩ ጎልቶ ይታያል:: የውሃ መጠን ማነስና የጥራት መጓደል የሰብል ምርትንና ብዝሃ ሕይወትን ይጎዳል:: ሃገራችን ይበልጥ እየጎዳት የሚገኘው የኢኮኖሚ አቅማችን አናሳ በመሆኑና ትላልቅ ወንዞችን ጠልፎ የመጠጥ ውሃ ማቅረብ አለመቻሉ ነው:: የዓባይን ልጅ ውሃ ጠማው" የሚለው አባባልም ከዚህ የመነጨ ይመስላል::

### ተግባር-11

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የውሃ እጥረትን ለመቀነስ በማህበረሰቡ እየተወሰደ ያለውን እርምጃ መረጃዎችን በማሰባሰብ እና ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍሉ አብራሩ::
2. ተማሪዎች ቤተሰቦቻችሁ ውሃ ከየት ያገኛሉ?

## የውሃ እጥረት ውጤቶች

### ተግባር-12

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ በበጋ ጊዜ የሚሞቱ እና የሚሰደዱ እንስሳት አሉ? እንዴት?

በውሃ እጥረት ምክንያት የሚፈጠሩ ዋና ዋና ክስተቶች የሚከተሉት ናቸው::

- የሰብል ምርቶች መቀነስ።
- የቤትና የዱር እንስሳት ሞት እና ስደት መጨመር።
- የእጽዋቶት መመናመን እና የበረሃ መስፋፋት።
- በመጠጥ ውሃ እጥረት የተነሳ የሰዎች ሞት እና ስደት መጨመር ናቸው።



ምስል-4 የእንስሳት ግጦሽ ፍለጋ

## የንጹህ ውሃ እጥረት ችግርን መፍታት

የመጠጥ ውሃ እጥረትን ችግር ለመፍታት የመጀመሪያው መንገድ ውሃ መቆጠብ ሲሆን በምድር ላይ ያለ እያንዳንዱ ሰው ማድረግ ይችላል። ይህንን ለማድረግ የፍጆታዎችን መጠን መቀነስ፣ ፍሳሾችን መከላከል፣ ቧንቧዎቹን በወቅቱ መቀየር እና የውሃ ሀብቶችን በምክንያታዊነት መጠቀም አስፈላጊ ነው። ሁለተኛው መንገድ የንጹህ ውሃ ማጠራቀሚያዎችን ማቋቋም ነው። የውሃ ማጣሪያ እና ማቀነባበሪያ ቴክኖሎጂዎችን እንዲያሻሽሉ ባለሙያዎች ይመክራሉ። የውሃ እጥረትን ችግር ለመቅረፍ እጅግ ተስፋ ሰጭ የሆነውን የጨው ውሃ ወደ ንፁህ ውሃ መለወጥም ይቻላል።

### ተግባር-13


1. በአካባቢያችሁ የንጹህ መጠጥ ውሃ እጥረት ያስከተለውን ተጽእኖ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።
2. በአካባቢያችሁ የውሀ እጥረትን ለመቀነስ በማህበረሰቡ እና በመንግስስት እየተወሰደ ያለውን እርምጃ ግለጹ።

## 7.3. የደኖች መመናመን

### ተግባር-14

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የደኖች ውጤት ለምን ለምን ተግባራት ይውላሉ?
2. የሚከተለውን መዋቅራዊ ቻርት በየግላችሁ በመመልከት የደን መመናመን የሚያስከትለውን ውጤት በክፍት ቦታዎች ከሞላችሁ በኋላ በውጤቱ እና በመንስኤው መካከል ያለውን ግንኙነት አብራሩ።

**መዋቅራዊ ቻርት 1 --› የደን መመናመን ውጤቶች**




ደኖች የሚባሉት ዛፎች በብዛት የሚገኙባቸው የእጽዋት ስብስብ ናቸው፡፡ ቀደም ብለው በነበሩት ጊዜያት ሰፊ የሆኑ የአውሮፓ ክፍሎች፣ አብዛኛዎቹ የሰሜን እስያ፣ የሰሜን አሜሪካ፣ የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ ክፍሎች በደን የተሸፈኑ ነበሩ፡፡ ነገር ግን አሁን በዓለም ላይ እጅግ በጣም ጥቂት የሆኑ የደን ሽፋኖች ይገኛሉ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት፡- በእርሻና በከብት ግጦሽ መስፋፋት፣ በከተማዎች መስፋፋት እንዲሁም የተለያዩ አገልገሎቶች በሚሰጡ ዛፎች ላይ በሚከናዎኑ የቆረጣ ተግባራት ምክንያት ነው፡፡ በአጠቃላይ የደኖች መመናመን የስነ-ምህዳር መቃወስን በማስከተል በአሁኑ ወቅት ብዙ ችግሮች እንዲከሰቱ ምክንያት ሁኗል፡፡ እነርሱም፡- የአየር ንብረት መዛባት፣ የተፋጠነ የአፈር መከላት፣ የሲልት ክምችት መፋጠን፣ ከባድ የጎርፍ ማጥለቅለቅ፣ የማገዶ እንጨት እጥረት፣ የአንድ አንድ እጽዋት ዝርያዎች መጥፋትና ደኖቹ የእጽዋት ዝርያ መራቢ ቦታ ሆነው እንዳይገኙ መሆን ዋና ዋና የዓለም ችግሮች እየሆኑ መጥተዋል፡፡

## የደኖች እንክብካቤ

**ተግባር-15**

1. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ ዛፍ የሚተከለው ለምንድን ነው?

ደኖች ከፍተኛ የመራባትና ራሳቸውን የመተካት ብቃት አላቸው:: የደኖች እንክብካቤ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው::

- ✍ ዳግም ድነና /Reforestation/- ከዚህ ቀደም ደን የነበረበት፣ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የተራቆተ ቦታን መልሶ በደን መሸፈን ማለት ነው።
- ✍ ዛፎችን ጭብጫብ እንዲያወጡ አድርጎ መቁረጥ /Coppicing/ - ይህ የእንክብክቦሽ ተግባር ደግሞ ዘፎችን ለተለያዩ ጥቅሞች ለማዋል ስንቆርጥ ከአልተቆረጠው ግንድ/ጉቶ/ ላይ ጭብጫብ እንዲያወጡ አድርገን የመቁረጥ ተግባር ነው።
- ✍ ደኖችን መከላከል /Forest protection/ - ይህ ተግባር ደኖችን ከመጠን በላይ ከመጠቀምና የስነ-ምህዳርን ሚዛን የሚያዛባ የአጠቃቀም ሁኔታ ካለ የዛፎች ቆረጣን ሙሉ በሙሉ የመከልከል ተግባር ነው።
- ✍ ተገቢ የሆነ የደን ዛፍ አቆራረጦችን መጠቀም።
- ✍ የደን ቃጠሎዎችን መቆጣጠር /Control of forest fires/
- ✍ የደን በሽታዎችን መቆጣጠር /Control of forest diseases/ - በደን ውስጥ የዛፎች በሽታ ሲከሰት መድሃኒቶችን መጠቀምና ለሌላ ጊዜ ደገሞ በሽታ መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎችን ማራባት አስፈላጊ ነው።
- ✍ ተባዮችን መቆጣጠር /Control of pests/ - በደኖች ውስጥ የሚገኙ እንደ ቅንቅን የመሳሰሉ ግንዶችንና ቅርፊቶችነ የሚጎዱ ተህዋስያንን ለመቆጣጠር ከዛፎች ላይ ተቆርጠው የወደቁ ግንዶችን፣ ቅርንጫፎችንና የቅጠላቅጠል ብስባሾችን በማስወገድ ማቃጠል ያስፈልጋል።
- ✍ የመሬት አጠቃቀምን ማቀድ /Applying land use planning/



ምስል-5 ድነና እና ዳግም ድነና/Afforestation and Reafforestation/

## ተግባር-16

1. "ምስል 5"ን ተመልከቱ እና የተረዳችሁትን ግለጹ፡፡
2. ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የደኖች መመናመን ምክንያቶችን አብራሩ፡፡
3. የአካባቢያችሁ ማህበረሰቦች ደኖችን እንዴት እንደሚከባከቡ አብራሩ፡፡

## ማጠቃለያ

- ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶቹ በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ሙቀት አማቂ ጋዞች ከመጠን በላይ መከማቸታቸው ነው። የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው ዋና ዋና ችግሮች የግብርና ምርት መቀነስ፣ የጤና ችግ፣ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሀ እጥረት ናቸው።
- የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚወሰዱ እርምጃዎች ለተለያዩ ግልጋሎቶች ብለን የምናቃጥላቸውን ነገሮች መቀነስ፣ ብዙ ዛፎችን መትከል፣ ጥቅጥቅ ደኖቻችንን መንከባበከብና ካርቦንዳይኦክሳይድን ከከባቢ አየር መምጠጥ የሚችሉ የፈጠራ ውጤቶችን ማበረታታት ይገኙበታል።
- በአሁኑ ጊዜ የውሃ መጠን እጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ መጥቷል። በየአመቱ የንጹህ መጠጥ ውሃ ፍላጎት ጨምሯል። እንደዲሁም የሰብል ምርቶች መቀነስ፣ የቤትና የዱር እንስሳት ሞት እና ስደት መጨመር፣ እጸዋቶች መመናመን፣ የበረሃማነት መስፋፋት፣ የሰዎችን ሞት እና ስደት መጨመር የውሃ እጥረት የሚያስከትላቸው ዋና ዋና ውጤቶች ናቸው።
- በአሁኑ ከጊዜ ደኖች በእርሻና በከብት ግጦሽ መስፋፋት፣ በከተማዎች መስፋፋት እና ለተለያዩ አገልገሎቶች በሚሰጡ ዛፎች ላይ በሚከናዎኑ የቆረጣ ተግባራት ምክንያት እየተመናመኑ ይገኛሉ። ስለዚህ የደኖች እንክብካቤ ተግባራትን በማከናወን ደኖች ከጥፋት መታደግ ከሁሉም የሚጠበቅ ተግባር ነው።

# የክለሳ ጥያቆዎች

ሀ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ መረጡ፡፡

1. በታዳጊ አገሮች ውስጥ ለደኖች መመናነመን አስተዋጽኦ ያለው ደንቢ የትኛው ነው?

   ሀ) የከተማዎች ማደግና መስፋፋት

   ለ) የከብት ግጦሽ ተግባራት በፍጥነት መሰፋፋት

   ሐ) ለእርሻ ቦታ ያለ ፍላጎት መጨመርና መስፋፋት

   መ) ሁሉም

2. ከሚከተሉት የአፈር እንክብካቦሽ መንገዶች ውስጥ ከሌሎቹ ጋር የማይመደበው የትኛው ነው?

   ሀ) ድነና ለ) ዳግም ድነና

   ሐ) እርሻን ማሳደር መ) ከፍታን ተከትሎ ማረስ

3. ከሚከተሉት ውስጥ የደኖች መመናመን ውጤት ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ) የእጽዋቶች ዘርያ መቀነስ ሐ) የከርሰ ምድር ውሃ መጨመር

   ለ) የአፈር መከላት መ) መልስ የለም

ለ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ማብራሪያ ስጡ፡፡

1. በከባቢ አየር ውስጥ ሙቀት አማቂ መጠን እየጨመረ ቢሄድ ምን ይከሰታል?
2. በረሃዎች እየተስፋፉ ነው ሲባል ምን ማለት ነው? መንስኤዎች ምን ምን ናቸው?
3. የውሀ እጥረት የሚከሰትባቸውን ምክንያቶች አብራሩ፡፡

# ማጣቀሻ መጻህፍት

አብክመ ትም/ቢሮ (2008 ዓ.ም). ፊዚካዊ ጅኦግራፊ ዳሰሳ፡ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ማሰልጠኛ ሞጁል. ደብረ ማቆስ፡ ኢትዮጵያ፡፡

_______________ (2008 ዓ.ም). የሰባዊ ጅኦግራፊ ዳሰሳ፡ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ማሰልጠኛ ሞጁል. ደብረ ማቆስ፣ ኢትዮጵያ፡፡

ሙሉግታ ነቅዓ (2012). የአለመግባባት መንስኤዎች እና መፍትሄዎች. ባህርዳር: ጢስ አባ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ባሕሩ ዘውዴ (1999). የኢትዮጵያ ታሪክ 1847 እስከ 1983. አዲስ አበባ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕረስ፡፡

ተክለ ፃድቅ መኩሪያ (1983). አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት. አዲስ አበባ፡ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

________________ (1981). አፄ ቴዎሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት. አዲስ አበባ፡ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

________________ (1982). አፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት. አዲስ አበባ፡ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ት/ሚ (2003). ህብረተሰብ ሳይንስ የተማሪው መጽሐፍ 8ኛ ክፍል. ት/ሚ. አዲስ አበባ. ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ድርጅት፡፡

ANRS (2019). Environment, forest and wildlife protection and development authority document. Bahir Dar, Ethiopia.

Beck, R. B., et. al (2009). World history: Patterns of interaction. USA: McDougal Littrell.

Bradshaw, M. & Weaver, R.., (1993). Physical geography: An introduction to Earth's environments. London፡ Mosby.

Chu, C. M,, (2019). Multiculturalism. Retrieved from http://www.ifla.org/publications/defining-multiculturalism.

EMA (2001). Survey of world geography፡ Distance education project for 2nd cycle primary school teachers, Ministry of Education, Addis Ababa, Ethiopia.

__________ (2001). Introduction to economic geography. distance

education project for cycle primary school teachers, Ministry of Education, Addis Ababa.

__________ (2000). Introduction to landform geography-module 3: major earth shaping processes and resulting landforms. Educational Media Agency, Addis Ababa, Ethiopia.

Monk House, F.J. (1975). Principles of physical geography. London: Hodder Stoughton,

Owen, O. S., (1985). Natural resource conservation: An ecological approach. New York: Macmillan Publishing Company.

Parker, J. and Rathbone, R., (2007. African history: A very short introduction. New York: Oxford University Press Inc.

Skinner, B.Y. (1976). Earth resources. New Jersey: Prentice Hall Inc.